# ከ

**ከ "አ"** ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)።

**ከ—** መዋ. 1.መነሻን ለመግለፅ የሚያገለግል ምእላድ። *ከጎንደር መጣ*። 2.ከተለያዩ ቃላት ጋር እየተጣመረ ጊዜን፥ ቦታን፥ ...። የሚያመለክት ምእላድ። *ከጠረጴዛው ስር/ከወንበሩ አጠገብ/ ከአሁን በፊት/ ከሀንፃው ፊት ለፊት /ከጓደኛው ጋር*። መዓ. 2.ቅድመ ሁኔታን አመልካች ምእላድ። *እቃውን ከሰጠኝ ገንዘቡን እመልሳለሁ*። 3.አንድ ድርጊት ገና እንደተደረገ ወይም እንደተከናወነ ወዲያውኑ ለማለት የሚያገለግል ምእላድ። *ፍየል ከመድረሷ...*። 4.አንድ ድርጊት መከናወኑን ወይም መፈፀሙን ለማመልከት የሚያገለግል ምእላድ። *መንገዱ ከተሰራ ሁለት ዓመት ይሆናል*። 5.አመዛዛኝ ወይም አነፃፃሪ ምእላድ። *ብዙ ከመናገር ብዙ ማዳመጥን ይወዳል*።

**ከሃዲ "ካደ"** ስር ተመ.

**ከለለ[1]** ግ 1.ጋረደ (በአጥር፥ በጨርቅ፥...)። 2.አወረ፥ አሳወረ፥ ማየት ከለከለ (አይንን)። 2.ወሰን፥ ድንበር አበጀ።

**ከለላ** ስ 1.ግርዶሽ። 2.መከታ። 3.አጥር።

**ከላይ** ቅ ድንበር ወይም ወሰን እንዲለይ ወይም እንዲ ያበጅ የተመደበ ወይም የተመረጠ (ሰው)።

**ክልል** ስ 1.ወሰን ወይም ድንበር ተበጅቶለት ከሌላው ቦታ፥ አካባቢ እንዲለይ የተደረገ ቦታ ወይም አካባቢ። 2.ድንበር፥ ወሰን።

**ተካለለ** ግ 1.ድንበር ለየ። 2.ድንበርተኛ፥ ወሰንተኛ ተሆነ።

**አካለለ** ግ 1.አዋሰነ። 2.ብዙ ቦታ ዞረ፥ አዳረሰ።

**ከለለ[2]** ግ እንደ ደወል ወይም መረዋ ያለ ድምፅ አሰማ፤ ጮሀ።

**ኪል (ኪልል) አለ** ግ የቃጭል ወይም የደወል ድምፅ አይነት አሰማ።

**አከላላ** ግ አቅራራ፥ ሸለለ፥ ዘፈነ።

**ከለለ[3]** ግ በጣም ኳ ብሎ ደረቀ፥ ከሸለለ።

**ከለለ[4]** ግ ቆረጠ፥ ሰየፈ (አንገትን)።

**ከለላ "ከለለ[1]"** ስር ተመ.

**ከለሜዳ** ስ ቀይ ሃር ወይም ግምጃ።

**ከለሰ[1]** ግ ተምሮ ወይም አጥንቶ ያለፈውን እንደገና መልሶ አጠና።

**ክለሳ** ስ ተምሮ ያለፈውን እንደገና ደግሞ መማር።

**ተከለሰ** ግ በእውቀቱ ማነስ ምክንያት አልፎት የሄደውን የትምህርት ዘርፍ ወይም ክፍል ደግሞእንዲማር ተደረገ።

**አስከለሰ** ግ ረስቶት የነበረውን ትምህርት እንደ ገና እንዲያጠናው አደረገ፥ ረዳ።

**ከለሰ[2]** ግ 1.ቀላቀለ፥ ደባለቀ፥ ቀየጠ። 2.ቸለሰ፥ በብዛት ጨመረ (ፈሳሽን)።

**መከለሻ [ቅመም]** ስ ቁንዶ በርበሬ፥ ቀረፋ፥ ቅሩንፉድ፥ ጥምዝ፥... በአንድ ላይ ተወቅጦ የሚዘጋጅ የወጥ ቅመም።

**ክልስ** ቅ የተለያየ ዘር ካላቸው ሰዎች የተወለደ (ለምሳሌ ከፈረንጅና ከሃበሻ)።

**ክልስ በርኖስ** ስ በላዩ ላይ ፀጉር እየተነሰነሰና ውሃ ውስጥ በእግር እየታሸ እድሳት እንዲያገኝ የተደረገ አሮጌ በርኖስ።

**ክልስ ጥይት** ስ በአካባቢው የሚገኘውን ባሩድ ዋናው ፋብሪካ ከሰራው የጥይት ባሩድ ጋር በመቀየጥ የሚሰራ ሬጋ ሰራሽ ጥይት።

**ከለበ** ግ ተጣደፈ፥ ቸኮለ፥ ሮጠ።

**ከላባ** ቅ (ስድብ) ቀዥቃዣ፥ ክልፍልፍ፥ ከውካዋ።

**ክልብ** 1.ከላባ። 2.ውሻ።

**ክልብልብ (ከለብላባ)** ቅ (ስድብ) ክልፍልፍ፥ ቀዥ ቃዣ፥ ከውካዋ።

**ተካለበ** ግ 1. ተቻኮለ፥ ተጣደፈ። 2. ተክለፈለፈ፥ ተንቀዠቀዠ።

**ተክለበለበ** ግ ተክለፈለፈ፥ ተንከወከወ፥ ተንቀዠቀዠ።

**አካለበ** ግ 1.አቻኮለ፥ አጣደፈ። 2.አክለፈለፈ፥ አንቀዠቀዠ።

**አክለበለበ** ግ አክለፈለፈ፥ አንቀዠቀዠ፥ አጣደፈ።

**ከለበሰ** ግ 1.በአንድ ትንፋሽ ዥርው አድርጎ ጠጣ። 2.ደፋ፥ ቸለሰ፥ አፈሰሰ።

**ከለብላባ "ከለበ"** ስር **"ክልብልብ"**ን ተመ.

**ከለቻ** ስ የራስ ቁር፥ ጥሩር።

**ከለከለ** ግ 1.ነሳ። 2.አገደ፥ አቆመ፥ ገታ። 3.ጠበቀ፥ ሃይ አለ። 4.አጋፈረ፥ ተቆጣጠረ፥ በስነ ስርአት አስተናገደ።

**ከልካይ** ስ አጋፋሪ፥ በረኛ (የቤተ መንግስት)።

**ክልክል** ቅ የተከለከለ፥ ያልተፈቀደ።

**ክልክል [ሳር]** ስ ከብቶች ገብተው እንዳያበላሹት ወይም እንዳይበሉት ተብሎ ለብቻው ተከልሎ ወይም ታጥሮ የሚጠበቅና

ለድርቆሽ የሚዘጋጅ ሳር።

**ተከለከለ** ግ 1. እንዳይወስድ ወይም እንዳይጠቀም ተደረገ (አንድን ነገር)። 2.ታገደ። 3.እንዳይከናወን ተደረገ።

**ተከላከለ** ግ 1.አንድ ነገር እንዳይደረግ ወይም እንዳይፈፀም፣... ከለከለ። 2.ከሚሰነዘርበት አደጋ ራሱን ለማዳን ተጣጣረ፣ ሞከረ።

**መከላከያ** ስ 1.ምሽግ፣ ከለላ፤ አምባ። 2.የጦር መሳሪያ። 3.የሃገርን ድንበርና ሉአላዊነት የሚያስከብር ሰራዊት። 4.የወሊድ መቆጣጠሪያ ኪኒን።

**መከላከያ ምስክር** ስ ተከሳሽ የሚያቀርበው (የተከሳሽ) ምስክር።

**ተከላካይ** ቅ (ስፖ.) በራሱ ጎል ክልል የተቃራኒው ቡድን ተጫዋቾች የማጥቃት ጨዋታ እንዳያደርጉ የሚጠብቅ ተጫዋች።

**አከላከለ** ግ እንዳይደረግ ወይም እንዳይፈፀም አስደረገ፣ አስተወ።

***ከለወሰ**

**ክልዋሳ** ቅ ጎስቋላ፣ ከሲታ፣ ለዋሳ።

**ተንከላወሰ** ግ 1.ወዲያ ወዲህ አለ፣ ተላወሰ፣ ተንቀሳቀሰ። 2.አዘገመ።

**መንከላወሻ** ስ መላወሻ ወይም መንቀሳቀሻ (ቦታ፣ ገንዘብ)።

**አንከላወሰ** ግ 1.ወዲህ ወዲያ አሰኘ፣ አላወሰ፣ አንቀሳቀሰ። 2.አዘገመ። 3.አንገዋለለ። *በሰነ ስርአት ብላ ምግቡን ኣታንከላውሰው።*

**ከለፈ** ግ ሰረቀ፣ ቀማ፣ ነጥቆ በረረ።

***ከለፈ**

**ክላፋ** ቅ (ስድብ) ከውካዋ፣ ቀዥቃዣ።

**ክልፍልፍ (ክለፍላፋ)** ዝ.ከ.

**ተክለፈለፈ** ግ ተንከወከወ፣ ተንቀዠቀዠ።

**አክለፈለፈ** ግ አንከወከወ፣ አንቀዠቀዠ።

**ከሊፋ** ስ (እስል.) በቁራን ህግ መሰረት የመንግስት ወይም የሃይማኖት እንደራሴ ወይም ወኪል።

**ከላ** ግ አስወገደ፣ ዞር አደረገ፣ አነሳ።

**ክላ** ግ ዞር በል! ወግድ።

**ከላባ** "ከለበ" ስር ተመ.

**ከላይ** "ከለለ[1]" ስር ተመ.

**ከላፋ** "*ከለፈ" ስር ተመ.

**ከል** ስ 1.ከቀንጠፋና ከብረት አር ይዘጋጅ የነበረ ጥቁር ቀለም። 2.ጥቁር ቀለም የተነከረ የሃዘን ልብስ።

**ከልብ** "ከለበ" ስር ተመ.

**ከልካይ** "ከለከለ" ስር ተመ

**ክልዋሳ** "*ከለወሰ" ስር ተመ.

**ከመ—**

**ከመጤፍ አይቆጥረውም** ከምንም አይቆጥረውም፤ ይንቀዋል፣ አያከብረውም፣ አይፈራውም፣...።

**ከመቅፅበት** ወዲያው፤ እጅግ በጣም አጭር በሆነ ጊዜ ውስጥ፣ በፍጥነት።

**ከመእንስሳ** (ስድብ) ከእንሰሳ የማይሻል፤ እንደ እንስሳ ያለ።

**ከመረ** ግ 1.አንዱን በአንዱ ላይ አነባብሮ አስቀመጠ። 2.ቆለለ።

**ክምር** ስ ቁልል።

**ተከመረ** ግ 1.ተቆለለ። (ዘይ.) አኮረፈ።

**ተከመረበት** በድንገት ዘሉ እላዩ ላይ ወጣበት ጉብ አለበት ። *በጫካ ውስጥ ሲሄድ ነብሩ በድንገት ተከመረበት።*

***ከመቸ**

**ክምችት** ስ ስብስብ፣ ጥርቅም።

**ተከማቸ** ግ ተሰበሰበ፣ ተጠራቀመ።

**አከማቸ** ግ ሰበሰበ፣ አጠራቀመ።

**ከመከመ** ግ ከረከመ፣ አስተካከለ፣ ደመደመ (ፀጉርን፣ ሳርን፣...)።

**ከመከም [ጎፈሬ]** ስ በደንብ ተስተካክሉ የተቆረጠና የተበጠረ ጎፈሬ።

**ክምክም [ጎፈሬ]** ዝ.ከ.

**ከሙን** ስ መልኩ እንደ ነጭ አዝሙድ ነጣ ያለ፣ ቅርፁ ቀጫጭንና ትናንሽ ሆኖ ከስንዴ ጋር ተመሳሳይነት ያለው፣ ብዙ ጊዜ ከመከለሻ ቅመም ድብልቆች አንዱ ሆኖ የሚያገለግል የቅመም አይነት።

**ከማን አንሼ** ቅ 1.ያለአቅሙና ያለግእረጉ ሌሎችን ለመምሰል የሚፈልግ ወይም የሚሞክር ሰው። ስ 2.እግር የሚያሳብጥ በሽታ፤ ኮብሽ።

**ከምሱር** ስ ሲተኮስ ታታው የሚወጋው የጥይት ቀለህ ቂጥ፣ እምብርት(የጥይትን ስእል ተመ.)። 2.ለዘለበት ማስገቢያ ተብሉ በተዘጋጀ የቀበቶ፣... ቀዳዳ ዙሪያ የሚገባ ከነሃስ ወይም ከብረት፣... የሚሰራ ክፈፍ።

**ከረመ** ግ 1.የክረምትን ወራት አሳለፈ፣ ክረምት እስኪወጣ ቆየ ወይም ኖረ። 2.ሰነበተ፣ ቆየ።

**ከርሞ** ስ ወደፊት የሚመጣው ወይም የሚቀጥለው አመት።

**ከርሞ ጥጃ** ቅ የማይሻሻል፣ በያመቱ በመሻሻል ፈንታ እያሽቆለቆለ የሚሄድ።

**ክራሞት** ስ ኑሮ፣ አኗኗር።

**ተከራረመ** ግ በመቻቻል አብሮ ቆየ ወይም

ሰነበተ፥ ተኗኗረ።

**ተካረመ** ዝ.ከ.

**አካርሚኝ** ስ 1.ለክረምት ወራት በመኖሪያነት የሚያገለግል ቤት። 2.ዋናው ቤት እስኪሰራ ድረስ ለመኖሪያነት የሚያገለግል አነስተኛ ቤት፤ መቃኞ።

**ከረሜላ** ስ ከልዩ ልዩ ቅመማት፥ ፍራፍሬዎች፥ ስኳር፥... በተለያየ ቅርፅ፥ መጠንና አይነት የሚዘጋጅ ጣፋጭ።

**ከረረ** ግ 1.ደረቀ፥ ገረረ። 2.ጦዘ፥ ደበነ፥ ጠበቀ (ገመድ፥ ፈትል)። 3.ተነፋ፥ አበጠ፥ ተነረተ (ሆድ)። 4.ባሰ፥ አየለ፥ ፀና (ነገር፥ ፀብ፥..)። 5.አለመጠን ጮሀ፥ ተንጩረጩረ(ድምፅ)።

**ከራራ** ቅ 1.ደረቅ። 2.(ስድብ፥ ዘይ.) አጭር፥ ድባኖ።

**ክር** ስ ለስፌት፥ ለሹራብ፥ ለዳንቴል፥... ስራ የሚያገለግል ከጥጥ፥ ከሱፍ፥ ከናይለን፥... የሚዘጋጅ የከረረ ወይም የጦዘ ፈትል።

**ክርር አለ** ግ 1.ሞተ። 2-ወደቀ፥ፍንችር አለ። 3.ከረረ።

**ተካረረ** ግ ተባባሰ፥ አየለ፥ ጠነከረ (ነገር፥ፀብ፥...)።

**ተካረሩ** ግ የምር ተጣሉ።

**አክራሪ** ቅ በሚከተለው እምነትና አስተሳሰብ ውስጥ ፍፁምነት ሊኖር ይገባል ብሎ የሚያምንና የቆየውን እምነትና አስተሳሰብ ከዘመናዊው ሁኔታ ጋር ማስተካከልና ማጣጣም የማይፈልግ አጥባቂ (ሰው)።

**ከረሸመ** "ኮረሸመ"ን ተመ.

**ከረበተ** ግ 1.ጣለ፥ አጋደመ። 2.ገለበጠ፥ አፈሰሰ። 3.ሰነጠቀ፥ ገመሰ (እርሻን)።

**ተንከረባበተ** ግ ተገለባበጠ።

**አንከረባበተ** ግ ገለባበጠ፤ አደራረበ።

**ከረባት** "ክራባት"ን ተመ.

**ከረቦ** "ከበሮ"ን ተመ.

**ከረተሰ** ግ ከረተፈ፥ ሸረከተ፥ ከካ።

**ክርትስ** ቅ ክርትፍ፥ ሽርክት።

***ከረተተ**

**ክርታታ (ከረተት)** ቅ 1.ከቦታ ቦታ የሚዘዋወር፥ ቋሚ ቦታ የሌለው። 2.አውታታ፥ እንግልቱ።

**ክርትት (ክርተት) አለ** ግ ተንከራተተ።

**ተንከራተተ (ተንከረተተ)** ግ 1.ወዲያ ወዲህ በማለት ተንገላታ፥ ተጉላላ፥ ባዘነ። 2.ዞረ፥ ብዙ ቦታ ሄደ ወይም አዳረሰ።

**አንከራተተ (አንከረተተ)** ግ 1.አንገላታ፥ አጉላላ፥ አባዘነ። 2.አዞረ፥ ብዙ ቦታ እንዲሄድ ወይም እንዲያዳርስ አደረገ።

**እንክርት (አንክርት)** በፊደል ተራው ተመ.

**ከረተፈ** ግ 1.በትንሽ በትንሹ ቆረጠ፥ ቀረጠፈ። 2.ገረደፈ፥ ሸረከተ፥ ከካ።

**ክርትፍ** ቅ ግርድፍ፥ ሽርክት።

**ከረቸመ** ግ 1.አጥብቆ ገጠመ፥ ዘጋ፥ ቆለፈ። 2.ቸነከረ። 3.ጥቅጥቅ አድርጎ አጠረ (አጥርን)። 4.ቀፈደደ፥ ጠፈነገ፥ አጥብቆ አሰረ።

**ክርችም አለ** የ "ተከረቸመ"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

**ክርችም ብሎ ዋለ** ምንም ሳይቀምስ ወይም ሳይበላ ዋለ።

**ተከረቸመ** ግ 1.ግጥም ብሎ ተዘጋ፥ ተቆለፈ። 2.አንድ ቤት ወይም ክፍል ውስጥ ለረዥም ጊዜ ዘግቶ ተቀመጠ። 3.ያለ ጋብቻ ውል ከሴት ቤት ውስጥ በባልነት ለመኖር ገባ።

**ተከርቻም** ስ ያለ ጋብቻ ውል ከሴት ቤት ውስጥ በባልነት ለመኖር የመግባት ድርጊት።

**ተከርቸም ገባ** የ"ተከረቸመ"ን 3ኛ ፍቺ ተመ.

**ከረነተ** ግ አጥብቆ አሰረ፥ ጠፈነገ።

**ከረና** ግ በክርን መታ፥ ደለቀ።

**ክርን** ስ የእጅ ረዣዥም አጥንቶች ከሚጋጠሙበት በስተ ጀርባ ያለ የሰውነት ክፍል፤ ኩርሜ(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)።

**ከረከመ** ግ ለማሳጠር፥ ለማሳመር፥... ቆረጠ፥ አስተካከለ።

**ከረከረ** ግ 1.ገዘገዘ፥ መገዘ። 2.ክርክር አበጀ። 3.ከነከነ። *ጉሮሮዬን ይከረከረኛል*። 4.አጥብቆ፥ ሰርስሮ ያዘ (ቀለበት፥ ቀበቶ፥ ክር፥...)።

**ክርክር** ስ ተላላፊ የሆነ የአባለዘር በሽታ።

**ክርክር (ክርክራት)** ስ ልሙጥ በሆኑ ነገሮች ላይ የሚገኝ ብዙውን ጊዜ የቀለበት ቅርፅ ያለው የተገዘገዘ ወይም እንደ ሰንበር ያለ ምልክት።

**ክርክሮሽ** ዝ.ከ.

**ተከረከረ** ግ ክርክር አወጣ ወይም አበጀ።

**አከረከረ** ዝ.ከ.

***ከረከረ**

**ክርክር** ስ 1.በፍርድ ቤት ወይም በሸንጎ ላይ ከሳሽና ተከሳሽ የሚያደርጉት እሰጥ አገባ ወይም ሙግት። 2.በአንድ ጉዳይ ላይ የተለያየ አስተያየትና እምነት፥... ባላቸው ሰዎች መካከል አንዱ ሌላውን ለማሳመን የሚያደርጉት የንግግር ምልልስ ወይም እሰጥ አገባ። 3.በገገርና በሻጭ መካከል የሚደረግ የዋጋ ቀንስ አልቀንስም ንግግር።

**ተከራከረ** ግ 1. በፍርድ ቤት ወይም በሸንጎ

ላይ አንዱ ከሳሽ ሌላው ደግሞ ተከሳሽ ሆኖ ተሟገተ። 2. በአንድ ጉዳይ ላይ ከራሱ አስተያየትና እምነት፥... የተለየ አስተያየትና እምነት፥ ... ካለው ሰው ጋር (የራሱን እምነትና አስተያየት፥... እንዲቀበልለት ወይም እንዲረዳለት ለማድረግ) ሃሳብ ተለዋወጠ፥ ተጨቃጨቀ። 3. ዋጋ ቀንስ በማለት ገገር ከሻጭ ጋር ተጨቃጨቀ።

**አከራከረ** ግ አወዛገበ፥ አጨቃጨቀ።

**አከራካሪ** ቅ አወዛጋቢ፥ አጨቃጫቂ።

**ከረከሰ** ግ 1.አረጀ። 2.ተንሳቀለ። 3.ከርካሳ ሆነ።

**ከርካሳ** ቅ አሮጌ፥ በሚገባና በተሟላ ሁኔታ መስራት የማይችል (ለምሳሌ መኪና)።

***ከረየ**

**ኪራይ (ክራይ)** ስ አንድ ተገልጋይ ለተወሰነ ጊዜ ለተገለገለበትና የራሱ ላልሆነ መገልገያ ነገር (እንደ እንስሳ፥ መኪና፥ ቤት፥ ቁሳቁስ፥... ላሉት) ለባለንብረቱ የሚከፍለው የጉልበት ወይም የአገልግሎት ዋጋ።

**ተከራየ** ግ 1.አንድን መገልገያ(ቤት፥ መኪና፥ ቁሳቁስ፥...) ኪራይ እየከፈለ ለመጠቀም ከባለንብረቱ ወሰደ ወይም ተረከበ። 2.መገልገያ የሆነው ነገር ለባለንብረቱ ኪራይ እየከፈለ ለሚጠቀም ተገልጋይ ተሰጠ።

**ተከራይ (ኪራይተኛ)** ስ ኪራዩን እየከፈለ የራሱ ባልሆነ ነገር የሚጠቀም ሰው።

**አከራየ** ግ ኪራይ እየከፈለ እንዲጠቀምበት መገልገያ ነገሮችን (ቤት፥ መኪና፥ ቁሳቁስ፥...) ለተገልጋዩ ሰጠ።

**አከራይ** ስ አንድን መገልገያ ለተከራይ እየሰጠ ኪራይ የሚቀበል ሰው።

**ከረደደ** ግ ደረቀ፥ ጠነከረ (ለምሳሌ ፀጉር)።

**ከርዳዳ (ከረደድ፥ ከርድድ)** ቅ ደረቅ፥ ጠንካራ፤ የለስላሳ ነገር ተቃራኒ።

**ከረጢት** ስ እንደ ኮሮጆ ወይም እንደ ስልቻ ሆኖ ከጨርቃ ጨርቅ የሚሰፋ የእቃ መያዣ።

**ከረሜ** ስ እህል ውስጥ የሚገኝ ደቃቅ ድንጋይ፥ አሸዋ።

***ከረፈፈ**

**ከርፋፋ (ከረፈፍ)** ቅ 1.(ስድብ) ቅልጥፍና የሌለው፥ ኅታታ፥ ዘርፋፋ። 2.ልጥፍ ወይም ልስቅ የማይል፤ ኅርባባ።

**ከርፍፍ አለ** ግ ተንከረፈፈ።

**ተንከረፈፈ** ግ 1.ቅልጥፍና አጣ፥ ተጎተተ፥ ተንዘረፈፈ። 2.ተንኅረበበ፤ ልጥፍ ወይም ልስቅ ሳይል ቀረ።

**አንከረፈፈ** ግ 1.ቀልጠፍ እንዳይል አደረገ፥ አንዘረፈፈ። 2.ልጥፍ ወይም ልስቅ ወይም ጠጋ እንዳይል አደረገ፤ አንኅረበበ።

**እንክርፍ** ቅ ከርፋፋ።

**ከረፋ** ግ ገማ፥ ጠነባ።

**ከርፋት** ስ ግማት፥ መጥፎ ሽታ።

**ከርፋታም** ቅ (ስድብ) ግማታም፥ ጥንባታም።

**ከራራ** "ከረረ" ስር ተመ.

**ከሬ** ስ 1.በቂጥ መጋጠሚያ ላይ የሚገኝ የአከርካሪ አጥንት። ቅ 2.በጣም የከሳ፥ አጥንቱ የገጠጠ።

**ከርሞ** "ከረመ" ስር ተመ.

**ከርስ** ስ ሆድ።

**ከርሰ ሃመር** ስ 1.የመርከብ ውስጠኛ አካል አማካዩ ቦታ። 2.(ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በመንበር ውስጥ የታቦት ማስቀመጫ ክፍል።

**ከርሰ መቃብር** ስ የመቃብር ውስጣዊ ክፍል።

**ከርሰ ምድር** ስ የመሬት ውስጠኛ ክፍል።

**ከርሰ ፊደል** ስ በያንዳንዱ የፊደል ቅርፅ ውስጥ የሚገኘውና ቀለም ያላረፈበት ክፍት ቦታ።

**ከርሳም** ቅ (ስድብ) 1.ሆዳም። 2.ቀፈታም።

**ከርቤ** ስ 1.ጥሩ ሽታ ያለውና እንደ እጣን የሚጤስ የዛፍ ሙጫ። 2.ከርቤ የተባለው ሙጫ የሚገኝበት ዛፍ።

**ከርታታ** "*ከረተተ" ስር ተመ.

**ከርከሩሜ** ስ ቅልጥሞቹ ረዥም የሆኑ፥ ቁንጮ ያለውና ምንቃሩ ትልቅ የሆነ የአሞራ አይነት።

**ከርከሮ** ስ 1.አሳማ የሚመስል፥ ጥርሱ ወጣ ያለና ቀንድ ያለው የዱር እንስሳ(በእሉንየዱር እንስሳ ስርተመ.)።2.አጭርና ጉልበተኛ የሆነ ሰው።

**ከርካሳ** "ከረከሰ" ስር ተመ.

**ከርክር** "ከረከረ" ስር ተመ.

**ከርዳዳ** "ከረደደ" ስር ተመ.

**ከርፋፋ** "*ከረፈፈ" ስር ተመ.

**ከሰለ** ግ 1.ከነደደ በኋላ ወደ ከሰል ተለወጠ (እንጨት)። 2.አረረ፥ ጠቆረ፥ ከሰል መሰለ። 3.(ዘይ.) ተናደደ፥ በገነ፥ አረረ። 4.በከሰል ወይም በጥቁር ቀለም ሣፈ፥ ሳለ፥ ቀባ። 5.ሰረዘ (ፅሁፍን)።

**ከሰል (ክሰል)** ስ እንጨት ትንሽ አየር እን ዲያገኝ ተደርጎ በዝግታ ከነደደና እንዲጠፋ ከተደረገ በኋላ ጥቁር ሆኖ የሚገኘው የእንጨቱ ክፍል፤ የከሰለ እንጨት።

**ከሰሌ** ስ ለከሰል የሚሆንና እሾክ የሌለው የግራር አይነት።

**ከሰልማ** ቅ የከሰል አይነት፤ ጥቁር።

**ክስል** ቅ የስርዝ ምልክት፥ እርማት የተደረገበት ፅሁፍ::

**ክሰል አክሳይ** ቅ ከሰል አምራች::

**ከሰመ** ግ 1.ሟሸሸ፥ ደረቀ፥ ረገፈ፥ ሻረ (የኩፍኝ፥ የፈንጣጣ፥ የቂጥኝ ቁስል):: 2.ጠፋ::

**ከሰረ** ግ 1.ሸቀጡ ከተገዛበት ዋጋ ዝቅ ብሎ በመሸጡ ሻጩ ዋናውን ሳያገኝ ቀረ፥ ጎደለበት:: 2.የፈለገውን ሳያገኝ ቀረ፥ አጣ:: *እገሌን ላገኘዋለሁ ብዬ ሄጄ ከስሬ መጣሁ*::

**ኪሳራ** ስ 1.አንድ ሸቀጥ ከተገዛበት ዋጋ ዝቅ ብሎ በመሸጡ በዋናው ወይም በወረቱ ላይ የሚደርስ ጉድለት:: 2.ያለመሳካት፥ የፈለጉትን ሳያገኙ መቅረት:: 3.የቁማር ጨዋታ አይነት:: 4.ወጪ:: *በሉ ኪሳራ ተጓጓዙ*::

**ኪሳራ ነው** ትርፍ የለውም::

**ኪሳራ ውስጥ ገባ** ከሰረ::

**ክስረት** ስ የ"ኪሳራ"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.::

**አከሰረ** ግ 1.ዋናውን ሳይመልስ ቀረ፥ አጎደለ (ሸቀጥ):: 2.እንዲጠፋ ወይም እንዲባከን ምክንያት ሆነ::

**አክሳሪ** ቅ 1.ብዙ ወጪ የሚያስወጣ:: 2.ትርፍ የማያስገኝ:: *አክሳሪ ድርጅት*::

**ከሰሰ** ግ 1.የደረሰበትን በደል ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ አካል አመለከተ፥ አቤቱታ አቀረበ:: 2.አጋለጠ፥ ወነጀለ፥ አሳጣ:: 3.በዳይን ወይም ወንጀለኛን ከህግ ፊት አቀረበ::

**ከሳሽ** ስ ወንጀልን ወይም በደልን አስመልክቶ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ አካል በፅሁፍ ወይም በቃል አቤቱታ አቅራቢ::

**ክስ** ስ ወንጀልን ወይም በደልን አስመልክቶ በፅሁፍ ወይም በቃል የሚቀርብ አቤቱታ::

**ተከሰሰ** ግ ክስ ቀረበበት፥ ተወነጀለ::

**ተከሳሽ** ስ ጥፋተኛ ነው ተብሎ ክስ ወይም አቤቱታ የቀረበበት ሰው::

**ተካሰሰ** ግ ከሳሽ ወይም ተከሳሽ በመሆን ህግ ፊት ቀረበ::

**ተካሰሱ** ግ አንዱ ከሳሽ ሌላው ተከሳሽ በመሆን ህግ ፊት ቀረቡ::

**አካሰሰ** ግ ለክስ ምክንያት ሆነ::

**ከሰተ** ግ ገለጠ፡ እንዲታወቅ አደረገ::

**ከሰተበት** ተጋለጠ፥ ታወቀበት::

**ክስተት** ስ 1.ሊዳሰስ፥ ሊሸተት፥ ሊሰማ ወይም ሊታይ የሚችል ማንኛውም ነገር:: 2.መገለጥ፥ መታየት::

**ተከሰተ** ግ ታየ፥ ተገለጠ::

**ከሰከሰ** ግ 1.ሰባበረ፥ አደቀቀ:: 2.ፈነከተ፥ ፈለጠ፥ መታ (በዱላ፥ በድንጋይ):: 3.ብዙ ገንዘብ አፈሰሰ፥ አወጣ፥ አጠፋ:: 4.አጠጋግቶ በብዛት አስቀመጠ፥ ቸመቸመ:: 5.በብዛት አደረገ፥ ፈፀመ (መብላትን፥ መስራትን፥ ... )::

**ክስካሽ** ቅ ስብርባሪ::

**ክስክስ** ቅ ተጠጋግቶ ወይም ተቀራርቦ በብዛት የተቀመጠ፤ ድርድር::

**ተከሰከሰ** ግ 1.ወድቆ ተሰበረ:: 2. በሃይል ወደቀ፥ ፈረጠ::

**ተከሳከሰ** ግ ተፈናከተ፥ ተደባደበ::

**አከሰከሰ** ግ በብዛት አበላ ፥ አጠጣ፥ ...::

**አከሳከሰ** ግ ለመደባደብ ወይም ለመፈናከት ምክንያት ሆነ::

**ከሳ** ግ ቀጠነ፥ የሰውነቱ ውፍረት ቀነሰ፤ ሞገገ::

**ከሲታ** ቅ ኮስማና፥ ሞጋጋ::

**ክሳት** ስ ቅጥነት፤ የውፍረት ተቃራኒ::

**ከሳሽ** "ከሰሰ" ስር ተመ.

**ከሴ** ስ ቅጠሉ ሻካራ ሆኖ ጥሩ ሽታ ያለው የእፅዋት አይነት::

**ከስከሶ** ስ ቅጠሉ ለስላሳ ሆኖ ነጣ ያለ፥ ጥሩ ሽታ ያለውና ችምችም ብሎ የሚበቅል የቁጥቋጦ አይነት::

**ከሸለለ (ኮሸለለ)** ግ ኳ ብሎ ደረቀ::

**ክሽልል (ኮሽላላ)** ቅ ደረቅ::

**ከሸነ** ግ 1.አሳምሮ ሰራ:: 2.አጣፍጦ ሰራ (ወጥን)::

**ክሽን** ቅ የሚያምር፥ ዝይን::

**ተከሸነ** ግ አማረ፥ ተዋበ::

**ከሸከሸ** ግ ኩርሽም ኩርሽም ወይም ከሽ ከሽ እያደረገ አኘከ፥ በላ (ለምሳሌ የደረቀ እንጀራን)::

**ከሽከሼ** ስ ሲበሉት ከሽ ከሽ የሚል ድምፅ የሚሰጥ በፀሃይ ወይም በሰሜ ምጣድ ተንቃቅቶ የደረቀ እንጀራ::

**ከሸፈ** ግ 1.ተሰናከለ፥ ተጨናጎለ፥ ሳይሳካ ቀረ:: 2.አልተኮስ አለ (ጥይት)::

**ከሽ**

**ከሽ አለ** ግ እንደ ሸክላ እቃ፥ ጠርሙስ፥ ... ያለ ነገር ወድቆ ተሰበረ ወይም የተጠቀሱት እቃዎች ወድቀው ሲሰበሩ የሚሰጡት አይነት ድምፅ ሰጠ::

**ከሽ ከሽ አለ** ግ (እንደ ቃሪያ፥ ድርቆሽ፥... ያለ ነገር) ሲያኝኩት ኩርሽም ኩርሽም የሚል ድምፅ ሰጠ::

**ከሽከሼ** "ከሸከሸ" ስር ተመ.

***ከበለለ**

**ክብለል ክብለል አለ** ግ ደብለል ደብለል አለ፥ ተገላበጠ::

**ክብልል አለ** ግ ተንከባለለ።

**ተንከባለለ** ግ 1.መሬት፥ አልጋ፥... ላይ ወዲያ ወዲህ ተገላበጠ። 2.እየተንደባለለ ቁልቁል ወረደ።

**አንከባለለ** ግ 1.አንደባለለ። 2.እየተንደባለለ ቁልቁል እንዲሄድ ወይም እንዲወርድ አደረገ።

**እንክብል** ስ 1.ክብና ድቡልቡል የሆነ ነገር። 2.ኪኒን።

**ከበረ** ግ 1.ባለፀጋ ወይም ሃብታም ሆነ። 2.ክብር፥ አክብሮት፥ ማእረግ አገኘ።

**ከበሬታ** ስ ክብር፥ ማእረግ።

**ከበርቴ** ስ ሃብታም ወይም ባለፀጋ።

**ከቡር** በፊደል ተራው ተመ.

**ክብረት** ስ ክብር።

**ክብር** ስ 1.ማእረግ፥ ወግ። 2.ልእልና፥ ገናናነት፥ ታዋቂነት።

**ክብሩን ጠበቀ** 1.ክብሩ እንዳይደፈር አደረገ። 2.በጨዋነት ተገኘ።

**ክብሯን ጠበቀች** ድንግልናዋን ሳታጣ ባል እስከምታገባ ድረስ ቆየች።

**ክብረ ሰማይ** ስ ሰዎች ለቁስል መድሃኒት ይሆናል ብለው የሚጠቀሙበት የማእድን አይነት።

**ክብረ በአል** ስ በየአመቱ የሚከበር ትልቅ መንፈሳዊ በአል።

**ክብረ ነክ** የአንድን ግለሰብ ወይም አካል ክብር የሚያጎድፍ፥ የሚያንቋሽሽ (ነገር፥ ሁኔታ፥ ...)።

**ክብረ ነገስት** ስ በንቡረእድ ይስሃቅ የተዘጋጀ የነገስታት ታሪክ መፅሃፍ።

**ክብረ ንፅህና** ስ ድንግልና፤ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፅሞ ያለማወቅ ሁኔታ (ለሴት)።

**ክብረ ወሰን** ስ ብዙውን ጊዜ በስፖርታዊ ውድድር ላይ አዲስ የሚገኝና ከዚህ በፊት በሌላ ተወዳዳሪ ያልተደረሰበት ከፍተኛ የውጤት እርከን፤ ሪኮርድ።

**የክብር መዝገብ** ስ ኤግዚቢሽን፥ትርኢት ጎብኚዎች ስለተመለከቱት ነገር ያላቸውን አስተያየት እንዲያሰፍሩበት በኤግዚቢሽኑ ቦታ የሚቀመጥ ወይም በኤምባሲ ወይም በቆንስላ ፅ/ቤቶች ውስጥ ለሃዘን ጊዜ የየአገሩ መሪዎች ወይም ትልልቅ ባለስልጣናት ሃዘናቸውን ገልፀው እንዲፅፉበት የሚዘጋጅ መዝገብ።

**የክብር ተከታይ** ስ አንድ ርእሰ ብሄር ከራሱ አገር ውጪ በሚሄድበት ጊዜ አብሮት የሚሄድ አጃቢ፥ ባለሟል።

**የክብር እንግዳ** ስ እንደ ግብዣ፥ ስብሰባ ባሉ ዝግጅቶች ላይ ከሌሎች ተጋባዥ እንግዶች በተለየ ሁኔታ ጥሪ ተደርጎለት የሚገኝ እንግዳ።

**የክብር ዘብ** ስ አንድን ታላቅ ባለስልጣን ለማጀብ ወይም ለመጠበቅ የተመደበ ወታደራዊ ጓድ።

**ክብርና** ስ ድንግልና፤ ክብረ ንፅህና።

**ተከበረ** ግ 1.ክብር አገኘ ወይም ተሰጠው። 2.ታፈረ፥ ተፈራ። 3.እንዳይነካ ተደረገ፥ ተከለከለ፥ ተጠበቀ (ሃብት፥ ንብረት)። 4.አንድን በአል በሚመለከት ተገቢው ስነስርአት ተካሄደ።

**አከበረ** ግ 1.አላቀ፥ ከፍ አደረገ፥ ወግ ማእረግ ሰጠ። 2.ከበሬታ ሰጠ፥ በትህትና አስተናገደ። 3.በአል አደረገ፤ በበአሉ ምክንያት አረፈ ወይም ስራ ሳይሰራ ዋለ። 4.በበአሉ ስነስርአት ላይ ተሳታፊ ሆነ።

**አስከበረ** ግ 1.በህግ አስጠበቀ፥ አስከለከለ፥ እንዳይነካ አስደረገ (ንብረትን)። 2.እንዳይደፈር አደረገ ወይም አስደረገ (አገርን፥ ወገንን፥ ...)።

**ከበሮ (ከረቦ)** ስ አብዛኛውን ጊዜ የሾላ፥ የኮርች፥... ግንድ ጉማጅ ከአፉ ሰፋ ከቂጡ ጠበብ ያለ ቅርፅ እንዲይዝ ተደርጎ ውስጡ ከተቦረቦረ በሗላ አፍና ቂጡ ላይ ቆዳ ተወጥሮ የሚሰራና በእጅ ሲመቱት ድምፅ የሚሰጥ የሙዚቃ መሳሪያ። (ነጋሪትን፥ አታሞን፥ ድቤን ተመ.)(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

**ከበሮ ቤት** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በቅኔ ማህሌትና በአምደ ወርቅ ግራና ቀኝ የሚገኝ በማህሌት ጊዜ ተማሪዎች የሚቆሙበት ቦታ።

**ከበሰ** ግ 1.ጠመጠመ፥ ደገለለ (ሻሽን)። 2.አሳበጠ፥ አድበለበለ (እግርን)። 3.ክባስ አበጀ።

**ክባስ** ስ 1.ቄሶች ራሳቸው ላይ የሚጠመጥሙት ትልቅ ጥምጥም። 2.በወጋግራ ጫፍ ላይ የሚሰካና ጣሪያ ተሸካሚ የሆነው አግዳሚ ማእዘን የሚያርፍበት ሞላላ ቅርፅ ያለው አጭር እንጨት።



ክባስ 1ኛ ፍቺ

***ከበሰበሰ**

**ክብስብስ** ቅ ዘርፋፋ፥ ጎታታ (በአለባበስ፥ በአካሄድ)።

**ተክበሰበሰ** ግ ሰፊና ረጅም ልብስ ለብሶ እየተግበሰበሰ በዝግታ ተራመደ፥ ተጎተተ።

**አክበሰበሰ** ግ አንዘረፈፈ፥ ጎተተ (ልብስን)።

**ከበበ** ግ 1.ክብ ሰራ። 2.ዙሪያውን ያዘ። *ከተማውን ከበውታል*። 3.አንድን ነገር መሃል በማድረግ ዙሪያውን ሆነ። *ዘፋኞን ከበው ይጨፍራሉ*። 4.ዙሪያውን አደረገ። *በውሃው ጉድጓድ ውስጥ ቆሻሻ እንዳይገባበት ዙሪያውን*

*በድንጋይ ከበበው::* 4.አጀበ፥ ተከተለ፥ አብሮ ሆነ::

**ከበባ** ስ አንድን ቦታ ወይም ጠላትን፥... በዙሪያ የመ ከበብና የመቆጣጠር ድርጊት::

**ከበባ አደረገ** ግ አንድን ነገር ለመያዝ ወይም ለማ ጥቃት ወይም ለመውረር ከበበ::

**ከባቢ አየር** ስ በመሬት ዙሪያ ያለ አየር::

**ከባቢ ጦር** ስ የጠላትን ጦር መሃል አድርጎ ዙሪያውን በመከበብ የሚዋጋ ጦር::

**ከባባ** ስ የመቅረዝ መብራትን ለማጥፋት በመቅረዙ ላይ የሚደፋ መለኪያ የሚመስል እቃ::

**ከበብ** ስ 1.ለአንድ አይነት አላማ ወይም ማህበራዊ ጉዳይ ሰዎች የሚሰባሰቡበት ቡድን ወይም ድርጅት:: 2.መዝናኛ ቦታ (ብዙውን ጊዜ መስሪያ ቤት አካባቢ):: 3.ዙሪያ::

**ክብ** ቅ 1.እንደቀለበት ዙሪያነት ያለው (አካል፥ ቅርፅ):: 2.ድቡልቡል፥ እንክብል::

**አከበበ** ግ ክብ ሰራ::

**አካበበ** ግ አዋሰነ፥ ወሰንተኛ ሆነ፥ አካለለ::

**አካባቢ** ስ 1.ስፍራ፥ ቀበሌ፥ ቦታ:: 2.የአንድ ነገር ዙሪያ፥ ጅክክ፥ አጠገብ፥ አቅራቢያ:: 3. ገደማ(ለጊዜ):: *አስራ ሁለት ሰአት አካባቢ እንገናኝ::*

***ከበከበ[1]**

**ተንከባከበ (ተከባከበ)** ግ 1.በድሎት ወይም በምቾት ያዘ፥ አቀማጠለ:: 2.በጥንቃቄ ያዘ::

**አንከባከበ** ግ ተንከባከበ::

**እንክብካቤ (ክብካቤ)** ስ 1.መልካም አያያዝ:: 2.ምቾት፥ ድሎት::

**እንክብክብ** ቅ በምቾት ወይም በድሎት የተያዘ፥ ቅምጥል::

***ከበከበ[2]**

**አንከበከበ** ግ 1.አድበለበለ፥ እንደ ኳስ አደረገ:: 2.በቀላሉ ብድግ አድርጎ ተሸከመ::

**እንክብክብ** ቅ ድቡልቡል::

**ከበደ** ግ 1.መዘነ፥ በዛ (ሸክም):: 2.አቃተ፥ በረታ፥ አስቸገረ:: *ፈተናና ከበደ / ኑሮ ከበደ::* 3.ተጫጫነ:: *ራሴን ከብዶኛል::* 4.ቀፈፈ:: *ቀኑ ከብዶኛል::* 5.ታፈረ፥ ተፈራ፥ ተከበረ::

**ከበደች** አረገዘች (ላም፥ ፈረስ፥...)::

**ከባድ** ቅ 1.ክብደት ያለው፥ ቀላል ያልሆነ:: 2.ትልቅ:: 3.ብርቱ፥ ጠንካራ:: 4.አስቸጋሪ፥ አዳጋች:: 5.አስፈሪ:: 6.ኀበዝ፥ ሃይለኛ:: *ከባድ ኳስ ተጫዋች ነው::* 7.ከፍተኛ:: *ከባድ ወጪ የሚጠይቅ ስራ::*

**ከባድ መሬት** ስ ጥቁር አፈር፤ መረሬ::

**ከባድ ሚዛን** ቅ ከፍተኛ ክብደት ያለው:: *የከባድ ሚዛን ቦክሰኛ::*

**ከባድ ምግብ** ስ ጨጓራ በቀላሉ ሊፈጨው የማይችለው ምግብ::

**ከባድ ኢንዱስትሪ** ስ ማምረቻ መሳሪያዎችን የሚያመርት ኢንዱስትሪ::

**ክበድ** ቅ እርጉዝ (እንስሳ)::

**ክብደት** ስ 1.የመመዘን፥ የመክበድ ሃይል:: 2.አስቸጋሪነት፥ አዳጋችነት:: 3.ከፍተኛነት፥ አስፈላጊነት:: *የጉዳዩን ክብደት አይተው አስቸኳይ ስብሰባ ጠሩ::* 4.ትኩረት፥ ትልቅ ግምት:: *ለነገሩ ክብደት አልሰጠውም::*

**ክብደት ያነሳል** ሰውነቱን ለማዳበርና ለማጠንከር እንዲሁም ለስፖርታዊ እንቅስቃሴ ተብሎ የተዘጋጀ ድንጋይ ወይም ብረት በእጆቹ ወደላይ በማንሳትና በማስቀመጥ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ያደርጋል::

**ክብደት አንሺ** ስ ሰውነቱን ለማዳበርና ለማ ጠንከር ክብደት ያለውና ለዚሁ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ተብሎ የተዘጋጀ ድንጋይ ወይም ብረት በእጆቹ ወደላይ በማንሳትና በማስቀመጥ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ የሚያደርግ ሰው::

**ተካበደ** ግ ከበደ::

**አከበደ** ግ አጋነነ፥ ትልቅ ቦታ ሰጠ:: *በቀላሉ ሊያልቅ የሚችለውን ጉዳይ አክብደህ አትየው::*

**ከባቢ "ከበበ"** ስር ተመ.

**ከባባ** ዝ.ከ.

**ከባድ "ከበደ"** ስር ተመ.

**ከብት** ስ 1.እንደ ላም፥ ፈረስ፥ በግ፥... ያሉ የቤት እንስሳት በጥቅል የሚጠሩበት ስም:: 2.በሬ ወይም ላም:: 3.(ስድብ፥ ዘይ.) ሞኝ፥ ጅል::

**ከብት ነጂ** ስ 1.የከብት ሌባ ወይም ዘራፊ:: 2.ከብት የሚጠብቅና የሚያንጉዝ የከብት ነጋዴ ተቀጣሪ::

**ከብት አርቢ** ስ መተዳደሪያው ከብት ማርባት ላይ የተመሰረተ (ሰው)::

**የከብት ሃኪም** ስ የእንስሳት ሃኪም::

**የከብት ዝምብ** ስ ትልቅ የሆነ ዝምብ::

***ከተለ**

**ምክትል** ስ ለአንድ ባለስልጣን የቅርብ ተተኪ ወይም የበታች ባለስልጣን ወይም በማእረግ (በደረጃ) ሁለተኛው የሆነ ሰው:: *ምክትል ስራ አስኪያጅ::*

**ከተል አለ** ግ ወዲያውኑ ተከተለ::

**ከተል አደረገ** ግ ቀጠል አደረገ፥ አስከተለ::

**ተከተለ** ግ 1.ለጠቀ፥ ቀጠለ:: 2.ከአንድ ነገር

ኋላ ኋላ ሄደ:: 3.በሌላው ተመራ:: 4.አመነ፥ ተቀበለ (የሌላውን መሪነት፥ ሃሳብ፥...)::

**ተከታይ** ቅ 1.ለጣቂ፥ ቀጣይ:: 2.አጃቢ ወይም አብሮ ሂያጅ:: 3.አማኝ:: *የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ*:: 4.ከታላቁ ቀጥሎ የተወለደ፥ ታናሽ (በእድሜ):: *የእኔ ተከታይ ሴት ናት*::

**ተከታተለ** ግ 1.አንዱ ከሌላው ቀጠለ ወይም አንዱ ሌላውን ተከተለ:: 2.በትጋት ወይም በንቃት ተመለከተ፥ ተቆጣጠረ፥ ተጠባበቀ፥ አጠና:: 3.አሳደደ:: *ተከታትሎ ያዘው*::

**ተከታታይ** ቅ 1.ለማቋረጥ አንዱ ከሌላው የሚቀጥል:: 2.ታላቅና ታናሽ የሆኑ (ለሰው):: 3.ጉዳይ አስፈፃሚ::

**አከታተለ** ግ 1.አንዱን ከሌላው ቀጠለ:: 2.ወዲያውኑ ቀጠለ:: *እሱን ካነጋገረች በሄላ አከታትላ ለኔ ደወለች*:: 3.ደጋገመ:: *አከታትሎ ሶስት ብርጭቆ ውሃ ጠጣ*::

**አስከተለ** ግ 1.ተከታይ አደረገ:: 2.አንድ ነገር ከሌላው ነገር ቀጥሎ እንዲሄድ ወይም እንዲመጣ አደረገ::

**አስከታይ** ቅ የተከታይን 5ኛ ፍቺ ተመ.

**ከተለበ** ግ ሞጨለፈ፥ ነጥቆ ሮጠ::

***ከተለበ**

**ከትላባ** ቅ ከላባ::

**ተከታለበ** ግ ተካለበ::

**አከታለበ** ግ አካለበ::

**ከተለፈ** ግ ሞጨለፈ፥ ነጥቆ ሮጠ::

**ከትላፋ** ቅ (ስድብ) 1.ሞጭላፋ:: 2.ከላፋ፥ ቀዥቃዣ::

**ከተመ[1]** ግ 1.ከተማ ቆረቆረ ወይም መሰረተ:: 2.ተሰበሰበ፥ ተከማቸ፥ ሰፈረ፥ ባንድነት ኖረ (ህዝብ)::

**ከተማ** ስ ከግብርና በስተቀር በሌሎች ሙያዎች የሚተዳደሩ በርካታ ሰዎች በተጠጋጉ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩበት፥ ድርጅቶችና የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚገኙበት ቦታ፥ ሰፈራ፥ አካባቢ::

**ከተማ ቀመስ** ገጠር ሆኖ በአንዳንድ ሁኔታዎች ከከተማ ጋር የሚመሳሰል ቦታ ወይም ገጠሬ ሆኖ አንዳንድ የከተሜ ባህርይ የሚታይበት ሰው::

**የከተማ ልጅ** ስልጡን፥ ሙሌ::

**ከተሜ** ስ የከተማ ሰው::

**ተከታተመ** ግ አንገር ለአንገር ወይም ጎን ለጎን በመሆን ድንኳን ተከለ፥ ሰፈር አደረገ (ዘማች፥ ጦር ሰራዊት):

**ከተመ[2]** ግ የተፈላው ቡና ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ ተጠጥቶ አለቀ::

**አከተመ** ግ 1.የተፈላውን ቡና ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ (አቦል፥ ቶናና በረካውን) ጠጥቶ ጨረሰ:: 2.አበቃ፥ አለቀ፥ ተፈፀመ::

**ከተማ** "**ከተመ[1]**" ስር ተመ.

**ከተሜ** ዝ.ከ.

**ከተረ** ግ 1.ከመሄድ ታገደ፥ ቆመ፥ ረጋ (ለምሳሌ ውሃ):: 2.እንዳይሄድ ገደበ፥ ከለከለቶ አቆመ (ለምሳሌ ውሃን)::

**ከተራ** ስ ለመጠመቂያ እንዲያገለግሉ ወንዞች የሚጠረጉበትና የሚገደቡበት ቀን፣ የጥምቀት ዋዜማ::

**ክትር** ቅ ግድብ፥ እግድ::

**ከተበ[1]** ግ ፃፈ::

**ክታብ** ስ 1.ከበሽታ እንዲያድን ወይም ከክፉ ነገር እንዲጠብቅ ተብሎ በብራና ወይም በወረቀት ላይ ተፅፎና ተጠቅልሎ በአንገት ወይም በክንድ ላይ የሚታሰር መድሃኒት:: 2.በቆዳ ወይም በጨርቅ ተጠቅልሎ አንገት ወይም ክንድ ላይ የሚታሰር የስራስር መድሃኒት::

**ከተበ[2]** ግ ክትባት ሰጠ ወይም አደረገ::

**ክትባት** ስ በሽታን እንዲከላከል በመርፌ ወይም ሰውነትን በመብጣት የሚሰጥ መድሃኒት::

**ተከተበ** ግ ክትባት ወሰደ ወይም ተደረገለት::

**ከተተ** ግ 1.ዶለ፥ ጨመረ፥ አገባ፥ አስገባ:: 2.አስቀመጠ፥ አኖረ:: *ገንዘቡን ባንክ ቤት ከተተ*:: 3.ሰበሰበ (አዝመራን):: 4.ቻለ፥ ያዘ፥ በቃ:: *ይህን ሁሉ ልብስ ሻንጣው አይከተውም*:: 5.ተሰበሰበ፥ አጠረ:: *ረዥም የነበረው ቀሚስ ሲታጠብ ከተተ*:: 6.ዋጠ:: *ድመቷ ትልቋን አይጥ እንዳለች ከተተቻት*:: 7.ተጠቃሎ ተሰበሰበ፥ አንድ ቦታ ተከማቸ:: *ለዋጁ ከተነገረ በሄላ ሰራዊቱ ከተተ*::

**ክታች** ስ አዝመራ ታሰብስቦ የሚያበቃበት ወቅት::

**ክት** ቅ 1.እጥር ምጥን ያለ:: 2.ቁጥብ፥ አመለ ሰብሰብ::

**የክት** ቅ የዘወትር ያልሆነ::

**የክት ልብስ** ስ ለበአል የሚለበስ ልብስ፥ የሰርክ ልብስ ያልሆነ::

**ክትት አለ** ግ ወዲያ ወዲህ ማለት ወይም መዞር ተወ፤ ተሰበሰበ:: *እሱ በጣም ጨዋ ነው በጊዜ ቤቱ ክትት ይላል*::

**ተከተተ** ግ 1.ክትት አለ:: 2.ተፈፀመ፥ አበቃ:: *የእነሱ ነገር አበቃ ተከተተ*::

**ተካተተ** ግ 1. ተጠቃለለ:: 2. ተጠናቀቀ:: 3. ተጨመረ፥ ታከለ::

**መካተቻ** ስ ማለቂያ፥ መደምደሚያ፥ ፍፃሜ::

**አካተተ** ግ 1. አጠቃለለ፥ አጠቃሎ ያዘ:: 2.

አጠናቀቀ፥ ጨረሰ፥ ፈፀመ። 3. ጨመረ፥ አከለ(ቀድሞ በነበረው ላይ)።

**ከተከተ** ግ በአጭር በአጭሩ ወይም በትንሽ በትንሹ ቆረጠ፥ ቀረጠፈ፥ ሸነሸነ። 2.ጨፈጨፈ፥ ቆረጠ። 3.ቆረጠመ፥ ገተገተ (ሀመም ሰውነትን)።

**ክትካች** ቅ ቁርጥራጭ፥ ስብርባሪ (የእንጨት)።

**ተከታከተ** ግ አንዱ ከሌላው ጋር ተማታ፥ ተቀጣቀጠ፥ ተደባደበ (በዱላ)።

**አከታከተ** ግ ለመደባደብ ምክንያት ሆነ።

***ከተከተ**

**ከት ብሎ ሳቀ** በጣም ሳቀ።

**ከትከት አለ** ግ ተንከተከተ።

**ከትከት ብሎ ሳቀ** ዝ.ከ.

**ተንከተከተ** ግ በጣም ሳቀ፥ ተንፈቀፈቀ።

**አንከተከተ** ግ በጣም አሳቀ፥ አንፈቀፈቀ።

**ከተፈ** ግ በትንንሹ መተረ፥ ቆረጠ፥ ሸነሸነ።

**መክተፊያ** ስ እንደ ሽንኩርት፥ ስጋ፥... ያሉ ነገሮችን ለመቆራረጥ ወይም ለመክተፍ የሚያገለግል ዝርግ እንጨት ወይም ሌላ ነገር።

**ክትፎ** ስ ቅቤና ሚጥሚጣ ተጨምሮበት ብዙውን ጊዜ ጥሬውን እንዲበላ ሆኖ የሚዘጋጅ ድቅቅ ብሎ የተከተፈ ብርንዶ ስጋ።

**ክትፎ ለብለብ** ስ በመጠኑ ወይም በጣም ሳይበስል የተጠበሰ ክትፎ።

***ከተፈ**

**ከተፎ** ቅ ፈጣን።

**ከተፍ አለ** ግ ከች አለ፥ በድንገት መጣ ወይም ደረሰ።

**ክትፍትፍ** ቅ 1.ፈጣን። 2.ቀዥቃዣ።

**ተክተፈተፈ** ግ 1.ተቅለበለበ፥ ተንቀዠቀዠ። 2.ተጣደፈ፥ ተቻኮለ።

**አክተፈተፈ** ግ አጣደፈ፥ አቻኮለ።

**ከትላባ "*ከተለበ"** ስር ተመ.

**ከትላፋ "ከተለፈ"** ስር ተመ.

**ከቶ** 1.ጭራሽ፥ ፈፅሞ። 2.አረ፥ እንዲያው ለመሆኑ።

**ከቶውንም** ተው. ግ. ጭራሹንም፥ ይብሱንም፥ ይልቁንም።

**ከቸረ (ኮቸረ)** ግ ደረቀ፥ ከቸቸ።

**ከቸሮ** ቅ ለዛ ቢስ፥ ደረቅ፥ ችኮ።

**ኮቸሮ** ስ 1.የደረቀ እንጀራ። 2.ለስንቅ እንዲሆን ተብሎ ከስንዴ ዱቄት፥... እንደ ብስኩት ሆኖ የሚዘጋጅ ደረቅ ምግብ።

**ከቸቸ** ግ 1.ደረቀ፥ ወዝ አጣ። 2.ለዛ አጣ፥ ችኮ ሆነ።

**ከቻቻ (ክቾ)** ቅ 1. ደረቅ። 2.ለዛቢስ፥ ችኮ።

**ክችች** አለ ግ 1.ድርቅ አለ። 2.ክው አለ (በድንጋጤ)። 3. ሙዝዝ አለ፥ ችኮ ሆነ።

***ከቸቸ**

**ከቸች አለ** ግ ከተፍ አለ፥ ድንገት መጣ ወይም ደረሰ።

**ከች አለ** ዝ.ከ.

**ከቻቻ "ከቸቸ"** ስር ተመ.

**ከነ__ (ከእነ__)** መዋ. __ጋር፥ ___ጭምር፥ __ሳይቀር። *ሴትየዋ ከነልጇ ተሸልማ ነበር /ልጁን ለይቼ ሳላውቀውም ከነመልኩ ጠፍቶኛል።*

***ከነበ**

**ክንብንብ** ስ ነጠላ፥ ጋቢ፥... ሲለበስ ጭንቅላት ላይ የሚያርፈው የልብሱ ክፍል።

**ክንብንብ አለ** ግ ተከናነበ።

**ተከናነበ** ግ እንደ ጋቢ፥ ነጠላ፥... ባሉ ልብሶች (ብዙውን ጊዜ አይኑ አካባቢ ያለው የፊቱ ክፍል ሲቀር) ጭንቅላቱን፥ ማጅራቱን፥ ... ጭምር ሸፈነ።

**አከናነበ** ግ በልብስ ሸፈነ ወይም ሸፋፈነ።

**አከናነበው** አሸከመው (ስድብን)፤ ፈረደበት (ፍርድን)፤ ቆለለበት፥ ጫነበት (እዳን)።

**ከነበለ** ግ 1.ቸለሰ፥ አፈሰሰ። 2.ገለበጠ፥ ደፋ። 3.ጣለ፥ ፈነገለ።

**ክንባላ** ቅ በቂጡ ቅርፅ የተነሳ መሬት ላይ ተደላድሎ መቀመጥ የማይችል፥ ፍንግል የሚል (እቃ)።

**ተከነበለ** ግ 1.ፈሰሰ። 2.ተገለበጠ፥ ተደፋ። 3.ወደቀ።

**ከነተረ** ግ በሃይል መታ፤ ጣለ፥ አፈረጠ።

**ክንተሮ** ስ 1.በአንደኛው ጫፉ ላይ ጉልጥምት ወይም ቋር ያለው አጭር ዱላ። ቅ 2.አጭር ሆኖ ፈርጠምና ጠንከር ያለ (ሰው)።

**ክንትር** ስ አጣድፎ የሚገድል በሽታ።

**ክንትር አለ** ግ 1.ፍንችር አለ። 2.ወዲያው ወይም ከመቅፅበት ሞተ።

**ከነቸረ** ግ 1.ቀነጨረ፥ ደረቀ፥ ደበነ። 2.አጭርና ቀጭን ሆኖ ጠነከረ፥ ከረረ። 3.ቀፍድዶ ወይም ጠርንቆ አሰረ። 4.በሃይል ወርውሮ ጣለ፥ ዘረረ፥ ፈነቸረ።

**ክንችር አለ** ግ 1.ወደቀ፥ ተዘረረ፥ ተፈነቸረ። 2.ወዲያው ወይም ከመቅፅበት ሞተ።

**ተከነቸረ** ግ ተፈነቸረ፥ ወደቀ።

**ከነአካቴው "ከናካቴው"ን** ተመ.

**ከነከታቴው** ዝ.ከ.

**ከነከነ** ግ 1.ከረከረ፥ ሰረሰረ (ጉሮሮን)።

2.ቆረቆረ፥ አሳሰበ (ነገር)። 3.ፀፀተ፥ ቆጨ።

*ከነወነ

**ክንውን** ስ 1.ድርጊት፥ ተግባር። 2.አሰራር፥ አፈፃፀም።

**ክንዋኔ** ዝ.ክ.

**ተከናወነ** ግ 1.ተሰራ። 2.ተጠናቀቀ ወይም ተፈፀመ። 3.ተሳካ፥ ሰመረ።

**አከናወነ** ግ 1.ሰራ። 2.አጠናቀቀ፥ ፈፀመ፥ ጨረሰ። 3.አሳካ፥ አሳመረ።

**ከነዳ** ግ 1.በክንድ ለካ። 2.ከዳኛ ዘንድ እንዲቀርብ የተወሰነበት ሰው ሳይቀርብ በመቅረቱ ተቀጣ፥ ኪሳራ ከፈለ (የቆየ አጠቃቀም)። 3.በአጠፌታ ከፈለ (ካሳን፥ መቀጫን)።

**ክናድ** ስ የልብስ እጅጌ።

**ክንድ** ስ 1.ከእጅ ጣት እስከ ትከሻ ያለው የሰውነት ክፍል። 2.ከኩርማ እስከ እጅ ጣት ያለው የእጅ ክፍል። 3.ርዝመቱ ከኩርማ እስከ እጅ ጣት መጨረሻ የሚደርስ የርዝመት መለኪያ(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)።

**ክንዴ ነው** አጋሬ፥ ደጋፊዬ፥ ረዳቴ ነው።

**ክንዴን ሳልንተራስ** ሳልሞት ወይም በህይወት እያለሁ።

**ክንድ አከለ** አፈረ ወይም ኩምሽሽ አለ።

**ክንድ ያህላል** 1.ትልቅ ነው (ለሙዝ፥ ለበቆሎ)። 2-.ጣም አጭር ነው (ለሰው)።

**ክንድህን አሳይ** ሃይልህን፥ጉልበትህን አሳይ።

**ክንድህን አንሳ** በህብረት፥በአንድነት ተዋጋ፥ ተፋለም፥ ተከላከል።

**ክንድህን አውሰኝ** ምታልኝ፥ ደብድብልኝ።

**አስከነዳ** ግ 1.አስከፈለ (እዳን)። 2.በለጠ፥ ረታ፥ ላቀ። *እገሌ እገሌን በችሎታ ያስከነዳዋል።*

**ከነፈ** ግ 1.በረረ (በክንፍ)። 2.በከፍተኛ ፍጥነት ሮጠ፥ በነነ። 3.ተዋከበ፥ ተቻኮለ፥ ተራወጠ። 4.የሚያደርገውን አጣ፥ አበደ (በፍቅር፥ በደስታ፥...)።

**ክንፍ** ስ በወፍ፥ በዝንብ፥... ጎን ግራና ቀኝ ላይ የሚገኝ በአየር ላይ እየተንሳፈፉ ለመብረር የሚያስችል የአካል ክፍል።



ክንፍ

**ክንፉን ዘረጋ** በከፍተኛ ፍጥነት ሮጠ፥ በነነ።

**ተከንፈነፈ** ግ ተከለፈለፈ፥ ተንቀዠቀዠ።

**አከንፈነፈ** ግ አከለፈለፈ፥ አንቀዠቀዠ።

*ከነፈሰ

**አከነፈሰ** ግ አሸረገደ፥ አጎበጎበ።

**አከንፋሽ** ቅ አሸርጋጅ፥ አጎብጓቢ።

**ከናካቴው (ከነከታቴው፥ ከነአካቴው)** ይባስ ብሎ፥ ከነጭራሹ። *ሲቃው ተበላሽ ስንል ከናካቴው ጠፋ።*

**ከናፍር "ከንፈር"**ን ተመ.

**ከንባላ "ከነበለ"** ስር ተመ.

**ከንተሮ "ከነተረ"** ስር ተመ.

**ከንቱ** ቅ ብላሽ፥ የማይረባ፥ ጥቅም የሌለው፥ ዋጋ ቢስ።

**ከንቲባ** ስ በማዘጋጃ ቤት አስተዳደር ዋናው የከተማ ሹም።

**ከንትር "ከነተረ"** ስር ተመ.

**ከንዋታ** ቅ ዘዋሪ፥ ስራ ፈት።

**ከንፈር.** (ብ.ቁ **ከናፍር**) ስ 1.ከአፍንጫ በታች፥ ከአገጭ በላይ የሚገኝ የላይና የታች ጥርሶች ሽፋን፥ የአፍ ግጣም(ስእሉን ራስ ስር ተመ.)። በተጨማሪ "ለንቦጭን"ና "ምንጭር"ን ተመ. 2.ዳርቻ፥ ዳር፥ ጠርዝ። *ወንዙ ከንፈሩ ድረስ ሞልቷል።*

**ከንፈሩን መጠጠ** አዘነ።

**ከንፈሩን ነከሰ** ዛተ፥ አስፈራራ።

**የከንፈር ቀለም** ስ ከንፈርን ለማስዋብ የተዘጋጀ ማጌጫ ቀለም።

**የከንፈር ወዳጅ** ስ ፍቅረኛ ( ከጋብቻ በፊት በወጣትነት ጊዜ የሚያዝና ግንኙነቱ በመሳሳም ላይ የተወሰነ)።

**ከንፈራም** ቅ ከንፈሩ ትልቅ የሆነ።

**ከካ** ግ 1.ጥራ ጥሬን በወፍጮ በትልቅ በትልቁ ፈነከተ፥ ገረደፈ። 2.(ዘይ.) በብዛት ጠጣ፤ በላ፤ አወራ፤ (አልኮልን፥ ቆሎን፥ ወሬን፥...)። 3.ፈነከተ (በዱላ፥ በድንጋይ ጭንቅላትን)።

**ክክ** ስ ሳይደቅ በትልቅ በትልቁ በወፍጮ የተ ፈነከተ ወይም የተገረደፈ የጥራ ጥሬ እህል።

**ከዚህ "እዚህ"** ስር ተመ.

**ከዚያ "እዚያ"** ስር ተመ.

*ከወረረ

**ከውራራ (ከወረር)** ግ ዘዋሪ፥ ቀውላላ።

**ተንከዋረረ** ግ ዞረ፥ ተንቀዋረረ።

**አንከዋረረ** ግ አዞረ፥ አንቀዋለለ።

*ከወተተ

**ከወተት(ከውታታ)** ቅ አውታታ፡ ከርታታ::
**ተንከዋተተ** ግ ተንከራተተ፡ ባዘነ::
**ተንከዋታች** ቅ ተንከራታች፥ ባዛኝ::
**አንከዋተተ** ግ አንከራተተ፥ አባዘነ::
**ከወነ** ግ 1.አዘጋጀ፥ አሰናዳ:: 2.አስጌጠ፥ አሳመረ:: 3.ፈፀመ፥ ጨረሰ::
***ከወከወ**
**ከውካዋ (ከወከው፥ ከውከው፧)** ቅ ቀዥቃዣ፥ ቀውቃዋ፥ ዘዋሪ::
**ከውከው አለ** ግ ተንከወከወ::
**ከውከው አደረገ** ግ አንከወከወ::
**ተንከወከወ** ግ ተንቀዠቀዠ፥ ተንቀወቀወ፥ ዞረ::
**አንከወከወ** ግ አንቀዠቀዠ፥ አንቀወቀወ::
**ከውር** "**ኩየት**"ን ተመ.
**ከውታታ** "***ከወተተ**" ስር "**ከወተት**"ን ተመ.
**ከውከው፧** "***ከወከወ**" ስር "**ከውካዋ**"ን ተመ.
**ከውካዋ** "***ከወከወ**" ስር ተመ.
**ከዘራ** ሊ በአንድ ጫፉ ቆልመም ያለ የእጅ መጨበጫ ያለው የእንጨት ወይም የብረት፥... ምርኩዝ::


ከዘራ

**ከይሲ** ስ 1.የእባብ ሌላ ስም:: 2.(ዘይ.፥ ስድብ) ክፉ፥ ተንኮለኛ፥ እርጉም::
**ከደነ** ግ 1.ገጠመ፥ ዘጋ (ክፍት የሆነ እቃን):: 2. ሸፈነ፥ አለበሰ (የቤት ጣሪያን በሳር፥ በቆርቆሮ፥...)::
**መክደኛ** ስ የተለያዩ ነገሮችን ለሚይዙ ወይም ለሚከቱ እንደ በርሜል፥ መሶብ፥ ድስት፥... ላሉ የእቃዎች አፍ የሚሆን መዝጊያ፥ መግጠሚያ::
**ክዳን** ስ 1.ግጣም፥ መክደኛ፥ እፊያ:: 2.ለቤት ጣሪያ መክደኛ ወይም መሸፈኛ የሚሆን ሳር ወይም ቆርቆሮ::
**ከዳ** ስ ማሩ ተመጦ ባዶውን የቀረ ሰፈፍ፤ ገጋ::
**ከዳ** ግ 1.ኮበለለ፥ ሸሸ፥ ጠፋ (ለምሳሌ ከሃገር):: 2.በአመፅ፥ በእምቢተኝነት ትቶ ሄደ (ከሰራዊት፥ ከፖለቲካ ድርጅት፥...):: 3.ግንኙነቱን አቋረጠ፥ ተወ:: *ገንዘብ ሲያጣ ጓደኛው ከዳው::* 4.አልታዘዝ አለ:: *እግሩ ከዳው::* 5.ሸሸ፥ ጣለ፥ አንሸራተተ:: ***የቆመበት መሬት ስለከዳው ወደቀ::*** 6.አሌ አለ፥ ሸፈጠ፥ ካደ:: 7.አዘናግቶ ነከሰ (ውሻ)::
**ከዳተኛ** ቅ የገባውን ቃል፥ የተጣለበትን አደራ ወይም እምነት የሚያፈርስ፥ የሚያጎድል::
**ከጀለ** ግ ተመኘ፥ ጓጓ፡ ፈለገ፡ ቋመጠ::
**ክጀላ** ስ ምኞት፡ ጉጉት::
**ከፈለ** ግ 1.ሁለት አደረገ፡ ሰነጠቀ፡ ገመሰ:: 2.ለየ፡ ነጠለ፡ ለየብቻ አደረገ:: 3.ቀነሰ፡ አጎደለ (ከአንድ ነገር ላይ):: 4.ለገዛው ነገር ዋጋውን ለሻጩ ሰጠ:: 5. መልስ ሰጠ፡ መለሰ (ብድርን፡ ውለታን፡...):: 6.ሽንቱን ሸና::
**መክፈያ** ስ እንደ ፖፖ፡ ቅል፡... ያለ የሽንት መሽኛ እቃ::
**ከፊል** ቅ ገሚስ::
**በከፊል** ሙሉ በሙሉ ሳይሆን በገሚስ ወይም በተወሰነ መጠን::
**ከፋይ** "**ገንዘብ**" ስር "**ገንዘብ ከፋይ**"ን ተመ.
**ክፉይ** ቅ ቁራጭ፥ ቁራሽ::
**ክፍል** ቅ 1.ወገን:: 2.ፋንታ፡ ድርሻ፡ እጣ:: ስ 3.ምድብ:: 4.በግድግዳዎች የተከፋፈለ የአንድ ቤት ውስጣዊ አካል:: 5.በትምህርት ቤት ለመማሪያ የሚያገለግል ቤት:: 6.የተወሰነ ትምህርት በተወሰነ ደረጃና ይዘት ተመጥኖ የሚሰጥበት የትምህርት ምድብ:: *1ኛ ክፍል / 2ኛ ክፍል::* 7.በአንድ መስሪያ ቤት የተወሰነ ስራን የሚያካሂድ አካል:: *ሂሳብ ክፍል::* 8.በአንድ ምእራፍ ውስጥ የሚገኝ ንኡስ ምእራፍ::
**ክፍለ ሃገር** ስ በውስጡ ብዙ አውራጃዎችን የሚያቅፍ የአንድ ሃገር የተወሰነ አቢይ የአስተዳደር ክልል::
**ክፍለ አለም** ስ ከሰባቱ ታላላቅ የአለም ክፍሎች (አፍሪካ፥ እስያ፥ አውሮፓ፥...) አንዱ፤ አህጉር::
**ክፍለ ዘመን** ስ የአንድ መቶ አመት ጊዜ::
**ክፍለ ጊዜ** ስ አንድ ነገር በቋሚነትና በተደጋጋሚ የሚፈፀምበት የተወሰነ የጊዜ ርዝመት::
**ክፍለ ጦር** ስ በወታደራዊ የሰራዊት ክፍፍልና ምደባ በስሩ ብዙ ብርጌዶችን አካቶ የያዘ የእግረኛ ሰራዊት ስብስብ ወይም ምድብ::
**የክፍል ስራ** ስ ተማሪዎች በትምህርት ሰአት ክፍል ውስጥ እንዲሰሩት ወይም እንዲመልሱት የሚሰጣቸው ጥያቄ፥ መልመጃ::
**ክፍያ** ስ ለአንድ ለተደረገ፥ ለተገዛ፥... ነገር ወይም ለተሰጠ አገልግሎት የሚከፈል ዋጋ፤ ገንዘብ::
**ከፋፈለ** ግ አንድ ላይ እንዳይሆን አደረገ፥ ለያየ::
**ከፋፍለህ ግዛ** በህዝቦች መካከል የዘር፥ የሃይማኖት፥... ልዩነትን ወይም አለመግባባትን በመፍጠር የሚካሄድ የአገዛዝ ስልት::

**ክፍልፋይ** ስ እንደ½፡ 2/4፡ ¾፡ ⅔፡… ያሉ ቁጥሮች ወይም የምጣኔ መግለጫዎች።

**ተካፈለ** ግ 1.አብሮ ሆነ፡ ተገኘ፡ ተሳተፈ (በሃዘን፡ በደስታ፡ በስብሰባ፡…ላይ)። 2.ተጋራ፡ ድርሻውን ወሰደ። 3. ተከፋፈለ።

**ተካፋይ** ቅ 1.አብሮ የሚሆን፡ የሚገኝ፡ የሚሳተፍ (በደስታ፡ በሃዘን፡… ጊዜ)። 2.ንብረትን የሚካፈል፡ የሚጋራ፡ ባለድርሻ።

**ተካፋይ ቁጥር** ስ አንድ ቁጥር በሌላ ቁጥር ሲካፈል የሚከፈለው ቁጥር። ለምሳሌ አራት ለሁለት ቢካፈል (4÷2) 4 ተካፋይ ቁጥር ነው።

**ተከፋፈለ** ግ 1.ተለያየ፡ ተነጣጠለ፡ ለየብቻ ሆነ። 2.ድርሻ ድርሻውን ወሰደ፡ ተቀራመተ።

**አካፈለ** ግ 1.አጋራ፡ ድርሻ ድርሻውን ሰጠ። 2.ሁለት አደረገ፡ ገመሰ። 3.አዋየ፡ አማከረ (ለሃሳብ)።

**ማካፈል** ስ ከአራቱ የሂሳብ መደቦች አንዱ የሆነና አንድ የተወሰነ ቁጥር ለሌላ የተወሰነ ቁጥር እኩል እንዲዳረስ፡ እንዲሸነሸን የማድረግ የስሌት ዘዴ።

**አካፋይ** ቅ አጋማሽ።

**አካፋይ ቁጥር** ስ አንድ ቁጥር የሚካፈልበት ሌላ ቁጥር። ለምሳሌ አራት ለሁለት ቢካፈል (4÷2) 2 አካፋይ ቁጥር ነው።

**አከፋፈለ** ግ 1.ድርሻ ድርሻውን ሰጠ። 2.ወደ ተለያየ ቦታ ወይም አቅጣጫ እንዲዳረስ ወይም እንዲሰራጭ አደረገ።

**ማከፋፈያ** ስ 1.ማደያ። 2.ማሰራጫ።

**አከፋፋይ** ቅ ወደ ተለያየ ቦታ ወይም አቅጣጫ እንዲዳረስ ወይም እንዲሰራጭ የሚያደርግ (ለምሳሌ ሸቀጥን)።

***ከፈለ**

**መክፈልት** (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ስ የሞተን ሰው ነፍስ ለማስማር ሲሉ የሟች ዘመዶች በቤተክርስቲያን ለካህናት የሚያቀርቡት ምግብና መጠጥ፣ ፀበል ፀዲቅ፣ የቆራቢ እራት።

**አከፈለ** (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ግ ከፀሎተ ሃሙስ ወይም ከስቅለት ማታ ጀምሮ እስከ ትንሳኤ ሌሊት ድረስ ምግብና መጠጥ ሳይቀምስ ቆየ ወይም ፆመ።

**አክፋይ** ስ የሚያክፍል፣ ከፀሎተ ሃሙስ ወይም ከስቅለት ማታ ጀምሮ እስከ ትንሳኤ ሌሊት ምንም ሳይቀምስ የሚፆም ሰው።

**የአክፋይ** ስ ለሚያክፍል ሰው የሚደረግ ስጦታ (አብዛኛውን ጊዜ ምግብና መጠጥ)።

**አክፍሎት** ስ ምግብና መጠጥ የማይቀመስበት ከፀሎተ ሃሙስ እስከ ትንሳኤ ድረስ ያለው ፆምና የፆሙ ጊዜ።

**ከፈረረ** ግ በጣም ደረቀ፡ ቀፈረረ።

**ከፈረር (ከፍራራ)** ቅ በጣም የደረቀ፡ ቀፍራራ።

**ተንከፈረረ** ግ 1.በጣም ደረቀ፡ ተንቀፈረረ። 2.(ዘይ.) ሞተ።

**እንክፍር** ቅ በጣም የደረቀ፡ እንቅፍር።

**ከፈተ** ግ 1.የተዘጋን የበር፡ የመስኮት፡… መዝጊያ ወይም መከለያ ዘወር ወይም ገለል በማድረግ ዝግ የነበረው በር፡ መስኮት፡… ክፍት እንዲሆንና መግባትና መውጣት እንዲቻል አደረገ። 2.ግጣምን ወይም መክደኛን አነሳ፡ አስወገደ። (ለምሳሌ የመሶብን፡ የድስትን፡… ግጣም)።3.መተላለፊያ መንገድ ሰጠ ወይም ለቀቀ። 4.አላቀቀ፡ ፈታ (የበር፡ የሳጥን ቁልፍን)። 5.ጀመረ። *ስብሰባውን በንግግር ከፈተ*። 6.አቋቋመ፡ ሰራ። *ት/ቤት ከፈተ*። 7.ክፍት፡ ብሩህ አደረገ (አእምሮን፡ ልብን)። 8.ገለጠ፡ በራ፡ ወለል አለ፡ ለቀቀ (ጭጋግ፡ ጉም፡…)።

**ቢከፍቱት ተልባ** 1.ከላይ ወይም ከውጪ ሲታይ ደህና የሚመስል፡ ግን ውስጡ መናኛና የማይረባ ሆኖ የሚገኝ። 2.ቁም ነገር የሌለው።

**መክፈቻ** ስ 1.የተቆለፈን መፍቻ ወይም ቁልፍ። 2.እንደ ቆርቆሮ፡ ጠርሙስ፡… ያሉትን እቃዎች ክዳን ወይም ግጣም ለመክፈት የተሰራ መሳሪያ።

**የመክፈቻ ንግግር** ስ በስብሰባ፡ በሴሚናር፡… ላይ የሚደረግ የመግቢያ ወይም የመጀመሪያ ንግግር።

**ከፋታ** ቅ 1.በጥሩ ሁኔታ የማይከደን ወይም ያልተከደነ። 2.አፈ ሰፊ እቃ።

**ክፍት** ቅ 1.ያልተዘጋ፡ ያልተከደነ። 2.ተከፋች የሆነ። 3.ያልተያዘ። *ክፍት ቦታ*።

**ክፍት መኪና** ስ ከበስተሂላው ኮፈን የሌለው መኪና።

**ክፍት ቦታ** ስ ያልተያዘ ስፍራ።

**ክፍት [አፍ]** ቅ (ስድብ) 1.ጫጪ፡ ተሳዳቢ። 2.ባለጌ፡ ንግግሩ ያልታረመ፡ ጋጠወጥ። 3.ፈዛዛ፡ ነሁላላ።

**ክፍት የስራ ቦታ** ስ ሰራተኛ ያልተቀጠረበት የስራ መደብ።


**ክፍተት** ስ 1.ቀዳዳነት፡ ስንጥቃት። 2.የአንድ ነገር ግንኙነት መቋረጥና ክፍት ሆኖ መገኘት።

**ተከፋች** ቅ ተካፋች።

**ተካፋች** ቅ 1.የሚከፈት። 2.ዚፕ ወይም ቁልፍ ያለው (ልብስ)።

**ከፈት** ስ የሚመዘን እቃ የሚቀመጥበት የሚዛን ቆጻ(ስእሉን ሚዛን ስር.)።

**ከፈቸረ** ግ በጣም ደረቀ፥ ከቸረ።
**ክፍቻራ** ቅ ክፍራራ፥ ደረቅ።
**ከፈነ** ግ በከፈን ሸፈነ፥ ጠቀለለ፥ ገነዘ (ሬሳን)።
**ከፈን** ስ የሬሳ መጠቅለያ ልብስ፤ መግነዝ።
**ከፈከፈ** ግ 1.የቤትን ግሪያ በክፍክፋት የአሰራር አይነት በሳር ከደነ። 2.አበጠረ፥ ከመከመ (ጎፈሬን)።
**መክፍከፊያ** ስ 1.ባለክፍክፋት የሳር ክዳን ቤት ሲሰራ የሳሩ ቂጥ እንዲስተካከል የሚተመተምበት ጠፍጣፋ እንጨት። 2.የፀጉር ማበጠሪያ።
**ከፈከፍ** ስ ክፍክፋት።
**ክፍክፋት** ስ ወጣ ገባ እንዳይኖረው ተደርጎ በመክፍከፊያ እየተተመተመ በጥንቃቄ የሚሰራ የሳር ቤት አከዳደን።
**ክፍክፍ** ስ 1.በክፍክፋት የአሰራር አይነት የተ ሰራ የሳር ቤት ክዳን። ቅ 2.በደንብ ተስተካክሎ የተበጠረ (ጎፈሬ)።
**ከፈይ (ከፋይ)** ስ ልጥፍ ያለ ለስላሳ ፀጉር ያለውና ወፈር ያለ የልብስ አይነት።
**ከፈፈ** ግ 1.ክፈፍ አበጀ። 2.ከረከመ፥ አስተካከለ (የአንድን ነገር ጠርዝ፥ ግርጌ)።
**ክፈፍ** ስ ለውበት ወይም ለጥንካሬ ተብሎ በአንድ ነገር ጫፍ ዙሪያ ላይ የሚሰፋ ወይም የሚለበድ እንደ ጨርቅ፥ እንጨት፥ ቆርቆሮ፥.. ያለ ጠርዝ።
**ከፌል** "**ከፈለ**" ስር ተመ.
**ከፋ** ግ 1.መጥፎ ሆነ፥ ጨከነ፤ ክፉ ሆነ። 2.ባሰ፥ ጠና፥ በረታ፥ የበለጠ ተበላሸ (ለመጥፎ ነገር)።
**ቢከፋም ቢለማም** ቢሆንም ባይሆንም።
**አይከፋም** ምንም አይል፥ ይሁን፥ ደህና ነው።
**ከፋው** አዘነ፥ ተበሳጨ፥ ተከዘ።
**ክፉ** ቅ 1.መጥፎ፥ ጨካኝ። 2.ስስታም፥ ንፉግ። 3.ሃይለኛ።
**ለክፉ አይሰጥም** በጣም መጥፎ አይደለም፥ ደህና ነው።
**በክፉ አይን አየ** በጥላቻ አይን አየ።
**ክፉና ደግ ተነጋገሩ** የሚያቀያይም ወይም የሚያጣላ ነገር ተነጋገሩ።
**ክፉ መንፈስ** ስ ሰይጣን፥ ጋኔን።
**ክፉ ቀን** ስ በረሃብ፥ በበሽታ፥ በጦርነት፥... ምክንያት የሰውና የከብት እልቂት የደረሰበት ወይም የሚደርስበት ጊዜ።
**ክፉኛ** ተው.ግ. በጣም፥ በሃይል፥ በፅኑ። *ክፉኛ ታሟል።*
**ክፋት** ስ 1.መጥፎነት፥ ተንኮል። 2.ምቀኝነት።
**ተከፋ** ግ 1.አዘነ፥ ተከዘ። 2.ተበሳጨ፥ ተናደደ። 2. ተቀየመ፥ አኩረፈ።
**አከፋ** ግ 1.ክፉ እንዲሆን ምክንያት ሆነ። 2.አከፋፋ።
**አከፋፋ** ግ አጥላላ፥ አንቋሸሸ።
**አከፋፋ** ዝ.ክ.
**አስከፋ** ግ 1.አስቀየመ፥ አሳዘነ። 2.አስጠላ።
**አስከፊ** ቅ 1.መጥፎ፥ አስቀያሚ። 2.አሳዛኝ። *አስከፊ የሆነ እልቂት ደረሰ።*
**ከፋታ** "**ከፈተ**" ስር ተመ.
**ከፋይ** "**ከፈይ**"ን ተመ.
**ከፍ**
**ከፍታ** ስ 1.ከአካባቢው መሬት ወደ ላይ ላቅ ያለ መሬት፥ ጉብታ። 2.አንድ ነገር ከመሬት ወደ ላይ ሲለካ የሚኖረው ርዝመት። 3.ብልጫ።
**ከፍተኛ** ቅ 1.ከፍታ ያለው። 2.ትልቅ። 3.የበላይ። 4.በከተማ ውስጥ የተወሰኑ ቀበሌዎችን አጠቃሎ እንዲይዝ የተደረገ የተወሰነ የቦታ ክልል ወይም አስተዳደሩ።
**ከፍ አለ** ግ 1.ወደላይ ወጣ አለ። 2.በለጠ፥ ላቀ። 3.አደገ፥በዛ፥ ጨመረ (መጠኑ፥ ቁጥሩ፥...)።
**ከፍ አደረገ** ግ 1.ወደ ላይ ብድግ አደረገ። 2.አበለጠ፥ አላቀ፥ ክብር ሰጠ። 3.አበዛ፥ ጨመረ (በመጠን፥ በቁጥር፥...)።
**ከፍ ከፍ አለ** ግ በለጠ፥ ላቀ፥ ክብር አገኘ።
**ከፍ ከፍ አደረገ** ግ አላቀ፥ ክብር ሰጠ።
**ከፍ ዝቅ አደረገ** አዋረደ (በስድብ፥ በግልምጫ፥...)።
**ክፍራራ** "**ከፈረረ**" ስር "**ከፈረር**"ን ተመ.
**ከፍተኛ** "**ከፍ**" ስር ተመ.
**ከፍታ** ዝ.ክ.
**ክፍቻራ** "**ከፈቸረ**" ስር ተመ.
**ኩ** የ "**ከ**" ፊደል ካእብ ዘር።
**-ኩ -ሁ** ን ተመ.
**ኩሊ** ስ 1.በሸክም ስራ የሚተዳደር ሰው፥ ሸቃይ። 2.የቀን ሰራተኛ።
**ኩሊሊት** ስ በመጠን ከርግብ አነስ የሚል፥ መልኩ አሸዋማ ሆኖ ረጅምና ቀጭን የሆነ ቀይ ቅልጥም ያለው፥ ማታ ወይም ሌሊት ላይ ሰው ወይም አውሬ ሲያይ የሚጮህ ወፍ፤ ሌባ ጠሪም ይባላል።
**ኩላሊት** ስ በሰው ወይም በእንስሳ ሰውነት ውስጥ በወገብ አካባቢ ከጀርባ በኩል ጥንድ ሆኖ የሚገኝ ከደም ውስጥ ቆሻሻ ፈሳሽን ወይም ሽንትን የሚያጣራ የሰውነት ክፍል።



ኩላሊት

**ኩላብ** ስ ሜንጦ::

**ኩል** "**ኳለ**" ስር ተመ.

**ኩልል ኩልል አለ** ግ ወንድ አህያን ጠራ (የወሲብ ፍላጎቱ እንዲነሳሳ)::

**ኩልሽ** "***ኮለሸ**" ስር ተመ.

**ኩልትፍ** "***ኮለተፈ**" ስር"**ኮልታፋ**" ን ተመ.

**ኩልኩል** ዶሮን ለመጥራት የሚባል ቃል::

**ኩልኩልት** ስ 1. በበግና በፍየል አንገት ላይ በበሽታ ምክንያት የሚወጣ እንደ እንቅርት ያለ እብጠት:: 2.ከድሎት የተነሳ ከአገጭ ስር በሰው አንገት ላይ የሚንጠለጠል ውፍረት ወይም ስጋ::

**ኩልኩልቲያም** ቅ (ስድብ) ኩልኩልት ያለበት (ሰው)::

**ኩልፍልፍ** "**ኮለፈ**" ስር ተመ.

**ኩም**

**ኩም አለ** ግ አፈረ፥ ደነገጠ (ያልጠበቀው ስለሆነበት)::

**ኩም አደረገ** ግ አሳፈረ፥ አስደነገጠ::

**ኩምሽሽ**

**ኩምሽሽ አለ** 1.ጭብጥ፥ ኩርምት አለ:: 2. አፈረ፥ ተሸማቀቀ፥ ደነገጠ::

**ኩምቢ (ኩንቢ)** ስ የዝሆን አፍንጫ(የዝሆንን ስእል ተመ.)::

**ኩምት** ስ የከርን ላይ እከክ::

**ኩምችች**

**ኩምችች አለ** ግ 1.እጥር፥ እንስ አለ:: 2.ኩርችች አለ:: 3.አፈረ፥ ተሸማቀቀ::

**ኩምችች አደረገ** ግ 1.አሳጠረ፥ አሳነሰ:: 2.አሳፈረ፥ አሸማቀቀ::

**ኩምክና** "**ኮመከ**" ስር ተመ.

**ኩረጃ** "**ኮረጀ**" ስር ተመ.

**ኩሩ** "**ኮራ**" ስር ተመ.

**ኩሩምባ** "**ኩርምባ**"ን ተመ.

**ኩሩሩ** ቅ በጣም አጭር::

**ኩራተኛ** "**ኮራ**" ስር ተመ.

**ኩራት** ዝ.ከ.

**ኩራዝ** ስ 1. መጠኑ ከቀለም ብልቃጥ ትንሽ ከፍ የሚል፥ ለክርና ለላምባ ወይም ለናፍጣ ማስገቢያ የሚሆን ጠባብ አፍ ያለውና በውስጡ የሚገኘው ክር ጫፉ ሲቀጣጠል ብርሃን የሚሰጥ የመብራት እቃ:: 2.(ዘይ.) አጭር (ሰው)::

**ኩሬ** ስ በጥልቀትም ሆነ በስፋት መጠኑ ከሃይቅ አነስተኛ የሆነ፥ የተጠራቀመና የማይንቀሳቀስ ውሃ::

**ኩርማ** ስ ክርን::

**ኩርማን** ቅ የአንድ ነገር አንድ አራተኛው ክፍል (የእንጀራ፥ የመሬት፥...)::

**ኩርምባ (ኩርንባ)** ስ ጥቅል ጎመን::

**ኩርምባጥ (ቁርምባጥ)** ቅ አጭርና ቀጭን (ሰው)::

**ኩርር...** 1.ተደጋግሞ ሲነገረው ያልሰማን ሰው ጆሮህ አይሰማም? ለማለት ተናጋሪው በቁጣ የሚያሰማው ድምፅ:: 2.አንድ የሚረብሽ ነገር ወይም ድምፅ ጆሮ ውስጥ ሲኖር፥ የሚረብሸውን ነገር ለማስወገድ ጆሮ ውስጥ በመጮህ የሚያሰሙት ድምፅ::

**ኩርሲ** ስ በርጩማ::

**ኩርሽሜ** ስ ሲያኙኩት ከሽ ከሽ የሚል ድምፅ የሚኖረውና ለጥርስ የሚገራ እንደ ቃሪያ፥ ፍርምባ፥ አኒሳ፥.. ያለ ምግብ::

**ኩርባ** ስ መታጠፊያ፥ ማዞሪያ (የመንገድ)::


**ኩርችች**

**ኩርችች አለ** ግ ኩርምት ብሎ ተቀመጠ::

**ኩርንችት** ስ 1.መሬት ላይ ልጥፍ ብሎ የሚበቅል ጠንካራ እሾህ ያለው የእፅዋት አይነት:: 2.ለጫማ ማያያዣ የሚያገለግልና መጠኑ በጣም ትንሽ የሆነ ምስማር::

**ኩርኩር**[1] አህያን ለመጥራት የሚያገለግል ቃል::

**ኩርኩር**[2] ስ 1.ባለ ሶስት ጎማ የሆነና እንደ ሞተር ቢስክሌት ያለ፥ከሂላው ሰው ሊጭን የሚችል መጓጓዣ:: 2በእጅ የሚገፋና እቃ ለማጓጓዣ የሚያገለግል ባለ አንድ ጎማ ጋሪ::



*ኩርኩር 2ኛ ፍቺ*

**ኩርኩር አለ** ግ ድክ ድክ፥ ውንክር ውንክር አለ::

**ኩርኩም** "**ኮረከመ**" ስር ተመ.

**ኩርኳሚ** ዝ.ከ.::

**ኩርዲዳ** ስ አራዊትን የሚያስለጥን ወይም

የሚገራ ሰው።
**ኩርጻ** ቅ ክርጻጻ (ለፀጉር)።
**ኩርፌኛ** "***ኮረፈ**[1]" ስር ተመ.
**ኩርፍያ**[1] ዝ.ክ.
**ኩርፍያ**[2] "**ኮረፈ**[2]" ስር ተመ.
**ኩርፋድ** ቅ አጭርና መልከ ጥፉ (ሰው)።
**ኩርፋፍቻ (ኩርፋፌያ)** ስ እፉኝት።
**ኩርፍ** "***ኮረፈ**[1]" ስር ተመ.
**ኩርፍተኛ** ዝ.ክ.
**ኩርፍታም** ዝ.ክ.
**ኩሳ** ስ ኩሽ።
**ኩሳይ** ቅ የኩሳ ዘር ወይም ወገን።
**ኩሳንኩስ** ስ ግሳንግስ፥ ኮተት፥ ቅራቅምቦ።
**ኩሳይ** "**ኩሳ**" ስር ተመ.
**ኩስ** "**ኮሳ**" ስር ተመ.
**ኩስቱባን** ስ የጣት ቤዛ፤ ልብስ ዘምዛሚዎች መርፌ እንዳይወጋቸው በጣታቸው ላይ የሚደፉት ከብረት የተሰራ የጣት ቆብ።
**ኩስታሪ** "**ኮስተረ**[1]" ስር ተመ.
**ኩስ ኩስ**
**ኩስኩስ አለ** ግ ቱስ ቱስ አለ (የአካሄድ አይነት)።
**ኩስኩስት** ስ 1.ከሸክላ ወይም ከነሃስ፥... በጀበና ቅርፅ የሚሰራ የእጅ ማስታጠቢያ። 2.የቡና ጀበና (ጎጃም)።



**ኩስኩስት** 1ኛ ፍቺ
**ኩሸተኛ** "**ኳሸ**" ስር ተመ.
**ኩሸት** ዝ.ክ.
**ኩሽና** ስ ማድቤት፥ ወጥ ቤት።
**ኩሽኔታ (ኩችኔታ)** ስ በአንድ ማሽን ውስጥ እንቅስቃሴ እንዲኖር የሚረዳና ፍትጊያን የሚቀንስ ክብ ሆኖ በውስጡ ድቡልቡል የብረት ብዮች ያሉበት መሳሪያ።
**ኩበት** ስ የደረቀ የከብት እበት።
**ኩበት ወረራ** ስ የዳግማይ ትንሳኤ ማግስት ሰኞ፥ ከበአሉ በሂላ ስራ የሚጀመርበት የእጅ ሚሚሻ ቀን።
**ኩባንያ** ስ ህጋዊ ሰውነት ያለው ግለሰቦች በህብረት የሚያቋቁሙት የንግድ ድርጅት።
**ኩባያ** ስ ከኒኬል ወይም ከፕላስቲክ ወይም ከሸክላ፥... የሚሰራና እንደ ብርጭቆ ወይም ዋንጫ ለመጠጫ የሚያገለግል እቃ።
**ኩብ** "***ኮበኮበ**" ስር ተመ.
**ኩብኩባ** ዝ.ክ.
**ኩተት** ስ 1.የተጎነጎነ የልጅ ወይም የፈረስ ቁንጮ። 2.የህፃንነት ጊዜ ወይም ዘመን። *ከኩተት እስከ ሽበት አንዷሉ*።
**ኩቲ** ስ 1.ውሻን ለመጥራት የሚያገለግል ቃል። 2.ውሻ።
**ኩቲላ (ቁጢላ)** ስ የውሻ ግልገል፤ ቡችላ።
**ኩታ** ስ ድርና ማጉ ቀጭን ሆኖ በሁለት ነጠላ መጠን ከተሰራ በሂላ እጥፉን ተሰፍቶ እንደ ጋቢ የሚለበስ ሸማ።
**ኩታ ገጠም** ስ ድንበርተኛ፥ ወሰንተኛ።
**ኩታራ** ስ 1.ጉብል፥ ብላቴና። 2.ተራ፥ አልባሌ ሰው።
**ኩት** ዶሮን ሂድ ወይም ወግድ ለማለት የሚባል ቃል።
**ኩት [ውሃ]** ስ በየካቲት ወር የሚወጣ የኮከብ አይነት። በተጨማሪ "**ኮከብ ቆጠራ**"ን ተመ.
**ኩትኮታ** "**ኮተኮተ**" ስር ተመ.
**ኩትኳቶ** ዝ.ክ.
**ኩነኔ** "**ኮነነ**" ስር ተመ.
**ኩንስንስ** "***ኮነሰነሰ**" ስር ተመ.
**ኩንቢ** "**ኩምቢ**" ን ተመ.
**ኩንታል** ስ አንድ መቶ ኪሎ የሚመዝን ማንኛውም እቃ።
**ኩንትሽ** "**ኮነተሸ**" ስር ተመ.
**ኩኩሉ (አኩኩሉ)** 1.የወንድ ዶሮ ጩሀት። 2.የልጆች የድብብቆሽ ጨዋታ ስም።
**ኩኩ መለኮቴ** ስ 1.ዋኔ የምትጠራበት ሌላ ስም። 2.የዋኔ ጩሀት። 3.ልጆች እያዜሙ የሚጫወቱት የጨዋታ አይነት።
**ኩኪ** ስ የጆሮ ግንድ።
**ኩክ** ስ ጆሮ ውስጥ የሚገኝና መጣብቅነት ያለው ቅባት።
**ኩክ ማውጫ** ስ ከጆሮ ውስጥ ኩክ ለማውጣት የሚያገለግል የማንኪያ ቅርፅ ያለውና መጠኑ ትንሽ የሆነ መሳሪያ።
**ኩክኒ** ስ 1.ጭርት። 2.ነጭ እከክ።
**ኩክኒያም** ቅ (ስድብ) ኩክኒ ያለበት።

**ኩየት (ከውር)** ስ ብር ወይም ወርቅ ከቀለጠ በኋላ የተፈለገውን ቅርፅ ይዞ እንዲወጣ ለማድረግ የሚያገለግል የአንጥረኛ መሳሪያ::

**ኩይሳ** "ኮየሰ" ስር ተመ.

**ኩዳዴ** "ሁዳዴ"ን ተመ.

**ኩዳድ** "ሆደደ[1]" ስር "ሁዳድ"ን ተመ.

**ኩዴታ** ስ መፈንቅለ መንግስት::

**ኩፌት** ስ ቆብ፥ ባርኔጣ::

**ኩፍስ** "ኮፈሰ" ስር ተመ.

**ኩፍታ** "*ኮፈፈ" ስር ተመ.

**ኩፍታ** ዝ.ከ.

**ኩፍታ** ስ ሙስሊሞች፥አይሁዶችና ካቶሊኮች የሚያደርጉት ክብና ትንሽ የሆነ ቆብ::

**ኩፍኝ** ስ ሃይለኛ ትኩሳት የሚያስከትልና እንደ እከክ በሰውነት ላይ የሚወጣ የህፃናት በሽታ::

**ኩፍ ጫማ** ስ ባለ ተረከዝ ሽፍን ጫማ::

**ኪ** የ "ከ" ፊደል ሳልስ ዘር::

**ኪሎ ሜትር** ስ አንድ ሺህ ሜትር የሆነ የርዝመት መለኪያ::

**ኪሎ ዋት** ስ የኤሌክትሪክ ሃይል (ጉልበት) መለኪያ::

**ኪሎ ግራም** ስ አንድ ሺህ ግራም የሚመዝን የክብደት መለኪያ::

**ኪራይ** "*ከረየ" ስር ተመ.

**ኪሮሽ (ኪሮሼ)** ስ ዳንቴል ለመስራት የሚያገለግልና ጫፉ ቆልመም ብሎ የተሰራ ቀጭን ሽቦ::

**ኪሳራ** "ከሰረ" ስር ተመ.

**ኪስ** ስ 1.እንደ ሱሪ፥ ቀሚስ፥ ኮት፥... ባሉ ልብሶች ላይ ተሰፍቶ የሚገኝና አነስተኛ እቃዎችን ለመያዣ የሚያገለግል እንደ ከረጢት ያለ የልብሱ ክፍል:: 2.የጠረጴዛ፥ የቁም ሳጥን፥... መሳቢያ::

**ኪሱ ተራቆተ** ኪሱ ባዶ ሆነ፥ ገንዘብ አጣ::

**ኪስ በርባሪ** ቅ ኪስ አውላቂ፥ ሌባ::

**ኪስ ቦታ** ስ በቤቶች መካከል የሚገኝ፥ ቤት ያልተሰራበትና ባለቤት የሌለው ባዶ ቦታ::

**ኪስ አውላቂ** ስ ከሰዎች ኪስ ገንዘብ የሚሰርቅ ሌባ::

**የኪስ መዝገበ ቃላት** ስ በኪስ ለመያዝ በሚያመች ቅርፅ የተዘጋጀ፥ መሰረታዊ ቃላትንና ፍቺዎቻቸውን በአጭሩ የያዘ መዝገበ ቃላት::

**የኪስ ሰአት** ስ በኪስ የሚያዝ ባለሰንሰለት ሰአት::

**የኪስ ገንዘብ** ስ ለጥቃቅን ጉዳዮች ይውል ዘንድ አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎቻቸው እንዲሁም ወላጆች ለልጆቻቸው የሚሰጡት አነስተኛ ገንዘብ::

**ኪታ** ስ ትንሽ ጥብቆ::

**ኪን**

**ኪን (ኪነት) ቃል** ስ ስነቃል::

**ኪን ጥበብ** ስ እንደ ስእል፥ ቅርፃ ቅርፅ፥... ያለ የእጅ ጥበብ ስራ::

**ኪነት** ስ 1.ኪን ጥበብ:: 2.የሙዚቃ፥ የዘፈን፥ የውዝዋዜ ጥበብ::

**ኪኒን** ስ በፍሬ ወይም በእንክብል መልክ የሚዘጋጅ የህመም ማስታገሻ መድሃኒት::

**ኪንታሮት** ስ 1.መጠኑና ቅርፁ እንደብጉር ሆኖ አብዛኛውን ጊዜ በእጅና በእግር ላይ እየወጣ ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆይ ጠንካራ፥ ሻካራና እንደ እትራት ያለ የቆዳ በሽታ:: 2.የእህያ ኪንታሮት::

**ካ** የ "ከ" ፊደል ራብእ ዘር::

**ካህን** "ካነ" ስር ተመ.

**ካሊም** ስ ከወፍራም ክር የተሰራ፥ ዥንጉርጉር የሆነና እንደ አልጋ ልብስ ወይም ምንጣፍ የሚያገለግል ልብስ::

**ካልሲ** ስ ከሱፍ ወይም ከናይለን፥... በእግር ጫማ ልክ የሚሰራ፥ የእግር ማስገቢያ ያለው፥ እስከ ጉልበት ሊደርስ የሚችል የእግር ልብስ ወይም መሸፈኛ፤ የእግር ሹራብ ::

**ካልሲየም** ስ ነጭና ለስላሳ ሆኖ ለህይወት የሚያስፈልጉ የብዙ ነገሮች ውህድ የሆነ፥ በጥርስና በአጥንት ውስጥ የሚገኝ ንጥረ ነገር::

**ካልቾ** ስ በእግር ጫፍ በላይኛው ክፍል የሚደረግ ምት::

**ካሎስ** ስ የሃር ክር አይነት::

**ካሚዮን** ስ የጭነት መኪና::

**ካሜራ** ስ የፎቶግራፍ ማንሻ መሳሪያ::

**ካምቦሎጆ** "ስታዲየም"ን ተመ.

**ካምፕ** ስ 1.ወታደራዊ የጦር ሰፈር:: 2.ሰፈር::

**ካሪ** "ካሬ"ን ተመ.

**ካራ** ስ ቢላዋ::

**ካራቴ** ስ በሩቅ ምስራቃውያን ዘንድ የተለመደና መሳሪያ ባልያዙ ሰዎች መካከል በእጅ፥ በእግር፥ በራስ የሚከናወን ሃይለኛና ጥበባዊ የአመታት ዘዴ::

**ካራት** ስ 1.አንድ ወርቅ የወርቅነቱ ደረጃ ወይም ጥራቱ ምን ያህል እንደሆነ የሚገለፅበት መለኪያ:: 2.የከበሩ ድንጋዮች ክብደት መለኪያ::

**ካሬ (ካሪ)** ስ ፤ መረባ አራት እኩል ጎኖችና ማእዘኖች ያሉት ቅርፅ::

**ካሬ ሜትር** ስ በአራቱም ጎኖቹ በኩል አንድ አንድ ሜትር ርዝመት ያለው ቅርፅ ወይም ወለል፤ መረባ ሜትር።

**ካሬ ኪሎ ሜትር** ስ በአራቱም ጎኖቹ በኩል አንዳንድ ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ቅርፅ ወይም ወለል ፤ መረባ ኪሎ ሜትር።

**ካሬታ** የ "ኩርኩር[2]"ን 2ኛ ፍቺ ተመ.

**ካርቡሬተር** ስ ቤንዚንን ከነፋስ አደባልቆ ለሞተሩ የሚያቀብል የመኪና አካል።

**ካርባይን** ስ የጠበንጃ አይነት (በጥንት ጊዜ የፈረሰኛ ወታደር ትጥቅ)።

**ካርቦሃይድሬት** ስ ካርቦን፣ ሃይድሮጅንና ኦክስጅን በውስጡ ያለበት እንደ ስኳር፣ ስቃርች፣ ሴሉሎስ፣ ... ያለ ንጥረ ነገር።

**ካርቦን** ስ 1.እንደ አልማዝ፣ ግራፋይት፣የድንጋይ ከሰል፣... ባሉ ማእድናት ውስጥ በተጣራ መልኩ፣ እንዲሁም ህይወት ባላቸው ነገሮች ውስጥ በቅይጥነት የሚገኝና ብረትነት የሌለው ንጥረ ነገር። 2.በላዩ ላይ የሚፃፍበት የማንኛውም ነገር ትክክለኛ ቅጂ ከስሩ በሚገኘው ሌላ ወረቀት ላይ እንዲቀረፅ የሚያደርግ፣ በካርቦን ወይም በሌላ ነገር ተቀልሞ የሚዘጋጅ ስስ ወረቀት።


**ካርቦንሞኖክሳይድ** ስ ከተቃጠለ ካርቦንና በነዳጅ ከሚንቀሳቀሱ ሞተሮችና ማሽኖች የሚወጣ መርዝነት ያለው ጭስ።

**ካርቦንዳዮክሳይድ** ስ ሰውና እንስሳ ወደ ውጪ ሲተነፍሱ ወይም አንዳንድ ነገር ሲቃጠል የሚወጣ የተቃጠለ አየር (ጋዝ)።

**ካርቱን** ስ ስለአንድ ሰው ወይም ሁኔታ በሰዎች አስተያየት ላይ ተፅእኖ ለማሳደር ወይም አንድ አይነት መልእክት ለማስተላለፍ በአስቂኝ (ከተፈጥሮ መልኩ ለየት ባለ) ሁኔታ የሚሰራ የስእል አይነት።

**ካርቱን ፊልም** ስ በተንቀሳቃሽ ፊልም የሚቀርብ የካርቱን ስእል።

**ካርታ[1]** ስ 1.የአገሮችን፣ የውቅያኖሶችን፣ የወንዞችን፣ የተራሮችን፣... የቦታ ክልል ወይም አንድን የተወሰነ ቅርፅ የሚያሳይና በወረቀት፣ ... ላይ የተሰራ ስእል፤ የመሬት የተወሰነ ክፍል ወይም ቅርፅ። 2.ለጊዜ ማሳለፊያ፣ ለቁማር፣ ለጨዋታ የሚያገለግል ልዩ ልዩ ስእሎች ወይም ቁጥሮች ያሉበት ካርድ።



ካርታ 2ኛ ፍቺ

**ካርታ[2]** ስ የጥይት ማቀፊያ ወይም መያዣ።

**ካርቶን** ስ 1.ወፍራም ወረቀት ወይም ክርታስ። 2.ከወፍራም ወረቀት ወይም ክርታስ እንደ ሳጥን ሆኖ የሚዘጋጅ የእቃ መያዣ።

**ካርኒ** ስ በተለያዩ ምክንያቶች እቃ ወይም ገንዘብ ገቢ ወይም ወጪ መሆኑን ወይም መሸጡን ለማረጋገጥ የሚዘጋጅ የፅሁፍ ማስረጃ።

**ካርኒ ቆረጠ** ካርኒ ሸጠ ወይም ገዛ።

**ካርኒ ቆራጭ** ስ ገንዘብ እየተቀበለ ካርኒ የሚሸጥ ሰው።

**ካርድ** ስ የተለያዩ ጉዳዮች የሚፃፉበት፣ ብዙውን ጊዜ መጠኑ አነስተኛ የሆነና ወፈር ያለ ወረቀት፣ (ራሽን ካርድ፣ ሪፖርት ካርድ፣ የሃኪም ቤት ካርድ፣ ፖስታ ካርድ፣ የተማሪዎች ውጤት መግለጫ ካርድ፣...)።

**ካሮት** ስ ስሩ የሚበላ፣ ቀለሙ በቀይና በቢጫ መካከል የሆነ የተክል አይነት። የሚበላው ክፍልም ካሮት ይባላል።



ካሮት

**ካሰ** ግ ካሳ ሰጠ፣ ከፈለ ወይም ሌላ ጠቀሜታ ያለው ነገር አደረገ (በዳይ ለተበዳይ)።

**ካሳ** ስ በዳይ ለተበዳይ የሚሰጠው ወይም የሚከፍለው ወይም የሚያደርገው ማንኛውም ነገር።

**ካሳ ቆረጠ** የካሳውን አይነትና መጠን ወሰነ።

**ካሳ በላ** ካሳ ተቀበለ።

**ተካሰ** ግ ካሳ ተቀበለ፣ ወሰደ፣ አገኘ።

**ተካካሰ** ግ 1. ተጣጣ፣ ተቻቻለ፣ የጎደለው በሌላ ተሟላ። 2. ለደረሰበት ችግር፣ በደል፣... ማካካሻ፣ መርሻ፣ መፅናኛ፣... የሚሆን ጥቅም አገኘ።

**አካካሰ** ግ አጣጣ፣ አቻቻለ።

**ካሴት** ስ የቴፕ ወይም የቪዲዮ ክር።

**ካስማ** ስ የድንኳንን አውታር ወጥሮ ለመያዝ የሚያገለግል ራሰ ቀላፋ እንጨት ወይም ብረት፤ ችካል(ስእሉን ድንኳን ስር ተመ.)።

**ካስክ** ስ በኤሌክትሪክ የሚሰራና የረጠበ የራስ ጠጉርን በሙቀትና በነፋስ ሃይል ለማድረቅ የሚያገለግል መሳሪያ::

**ካሸር** ስ የባንክ፥ የግምጃ ቤት፥ የሆቴል ቤት፥... ገንዘብ ተቀባይ ወይም ከፋይ::

**ካሽ** ስ ጥሬ ገንዘብ::

**ካበ** ግ 1.ድንጋይን በድንጋይ ላይ በማነባበር የድንጋይ አጥር ወይም የድንጋይ ግድግዳ ሰራ:: 2.ቆለለ፥ ከመረ:: 3. አሞገሰ፥ አሞካሸ፥ ከፍ ከፍ አደረገ::

**ካብ** ስ ድንጋይን በድንጋይ ላይ በማነባበር የሚሰራ አጥር ወይም ግድግዳ::

**ካቡት** ስ ባለመካፈቻ ረጅም ቀሚስ::

**ካቢኔ** ስ በአንድ መንግስት ርእሰብሄር ተመርጠው የመንግስትን ፖሊሲና አስተዳደር በሃላፊነት የሚመሩ የሚኒስትሮች ቡድን::

**ካባ** ስ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል ድንጋይ የሚገኝበትና የሚፈለጥበት ቦታ::

**ካባ** ስ ቅርፁ ክብ ሆኖ ከፊት በኩል ክፍትነት ያለው ከሱፍ ወይም ከሃር፥ ... የሚሰራና ከልብስ በላይ የሚለበስ መደረቢያ::

**ካባ ላንቃ (ላንቃ ካባ)** ቅ ያንገቱና የትከሻው ዙሪያ የለምድ ቅርፅ ባለው የወርቅ ጥልፍ የተጌጠ የካባ አይነት::

**ካቤላ** ቅ 1.የኮቴው ጥፍር አድጎ ወደላይ የተቆለመመ (አህያ):: 2.(ስድብ፥ ዘይ.) እግሩ ወይም ጫማው ሰፊና ሸፋፋ የሆነ (ሰው)::

**ካብ** "ካበ" ስር ተመ.

**ካቦ**[1] ስ አራት ቁና የሚይዝ መስፈሪያ::

**ካቦ**[2] ስ ትልቅ የሆነ የዋንጫ ወይም የፅዋ አይነት::

**ካቦ** ስ በህንፃ፥ በመንገድ፥ በፋብሪካ፥... ስራ ላይ የሚሰማሩ የጉልበት ሰራተኞችን እንደአለቃ ሆኖ የሚያሰራ ሰው::

**ካቦርት (ካቦርታ፥ ካፖርት)** ስ ከማንኛውም ልብስ በላይ ተደርቦ የሚለበስና ለብርድ መከላከያ የሚያገለግል ረዥም ኮት::

**ካቲ** ስ ከተረከዝ ከፍ ብሎ የሚገኝና ለብቻው ቀጥ ብሎ የሚታይ ወፍራም ጅማት::

**ካቲካላ** ስ በፋብሪካ ሳይሆን በመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚዘጋጅ የአልኮል መጠጥ::

**ካታሎግ** ስ 1.በፊደል ተራ በካርድ ላይ የተመዘገበ የማንኛውም ነገር ዝርዝር:: 2.በአይነት፥ በመጠን ወይም በሚሰጡት ግልጋሎት፥... መሰረት ለምርጫ እንዲያመች ሆኖ የተዘጋጀ የእቃዎች፥ የልብሶች፥ የቦታ፥ የስሞች፥ ... ዝርዝር ያለበት ወረቀት፥ ጥራዝ ወይም መፅሃፍ::

**ካቴና** ስ 1.ሰንሰለት:: 2.በሰንሰለት ቅርፅ ከወርቅ የሚሰራና እጅ ላይ የሚደረግ ጌጥ:: 3.ሁለት ትልልቅ የብረት ቀለበቶችን በሰንሰለት በማገናኘት የተሰራና የእስረኛን እጅ ወይም እግር ለማሰር የሚያገለግል ሰንሰለት::

**ካቴድራል** ስ ደረጃው ወይም ማእረጉ ከፍተኛ የሆነ ታላቅ ቤተ ክርስቲያን፣ ርእሰ አድባራት፣ ገዳም::

**ካትራሜ** ስ ሬንጅ::

**ካቶሊክ** ስ 1.የሮማ ቤተክርስቲያን እምነት:: 2.የካቶሊክ እምነት ተከታይ:

**ካቻምና** "ሃች አምና"ን ተመ.

**ካነ** ግ 1.የድቁና ወይም የቅስና ስልጣን ሰጠ፥ ሾመ፤ ክህነት ሰጠ:: 2.አስተማረ፥ አሰለጠነ::

**ካህን** (ብ.ቁ.ካህናት) ስ በቤተ እግዚአብሄር ለማገልገል የሃይማኖት ትምህርትና ስልጣን ያለው መንፈሳዊ አገልጋይ፥ አስተማሪ::

**ክህነት** ስ ሃይማኖታዊ ስልጣን::

**ክህነት ተቀበለ** የቅስና ወይም የድቁና ስልጣን (ማእረግ) አገኘ::

**ተካነ** ግ 1.ክህነት ተቀበለ:: 2.ሰለጠነ፥ በደምብ አወቀ::

**ካናቴራ(ካኒቴራ)** ስ ከክር ወይም ከናይለን ወይም ከጥጥ፥... የሚሰራ ከወገብ በላይ የሚለበስ የውስጥ ልብስ::

**ካንሰር** ስ የማይድንና አደገኛ የሆነ፥ ብዙውን ጊዜ ሞት የሚያስከትል በሽታ::

**ካንዴላ** ስ እሳት በመርጨት የመኪናው ሞተር እንዲነሳ የሚረዳ የመኪና እቃ::

**ካንጋሩ** ስ ለመዝለል የሚያስችሉ ጠንካራ የሆኑ የሂላ እግሮች ያሉት፥ በአውስትራሊያ ብቻ የሚገኝ የዱር እንስሳ:: ሴቷ ካንጋሩ ልጇን ለመሸከም የሚያስችላት ከረጢት መሰል አካል በስተውጪ በኩል በሆዷ ላይ አላት(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)::

**ካእብ** ስ እንደ ሁ፥ ሉ፥ ሙ፥ ... ያሉ በግእዝና በሳልስ ፊደላት መካከል የሚገኙ ሁለተኛዎቹ የፊደላት ዘሮች መጠሪያ ወይም የድምፅ ምልክቶች::

**ካከመ** ግ ዛለ፥ ደከመ፥ ጣመነ::

**ካከረ** ግ ጠነከረ::

**ካክራ** ቅ ጠንካራ፥ ብርቱ::

**ካኪ** ስ በአይነቱ ከአቡጀዲና ከመርደፋ ሻልና ጠንከር ብሎ በተለያዩ ቀለማት ከጥጥ የሚሰራ የጨርቅ አይነት::

**ካኪ መልክ/ቀለም** የመዳብ ወይም የነሃስ ወይም የአፈር መልክ ያለው ቀለም::

**ካኪሳ** ስ በጣም ያላደገና ያልጠነከረ አደገኛ አዳኝ ዘንዶ።
**ካካ (አካካ)** ስ 1.ኩስ፥ አይነምድር። 2.ቆሻሻ፥ መጥፎ (ለልጆች ወይም ከልጆች የሚነገር)።
***ካካ**
**ካካቴ** ቅ ሳቂታ።
**ተንካካ** ግ 1.ከመውደቅ ወይም ከመጋጨት የተነሳ የሚንኳኳ ድምፅ ሰጠ። 2.እንደ ብርጭቆ፥ ጠርሙስ፥ ሸክላ፥ ... ያለ እቃ ተደራርቦ ሲወድቅ የሚያሰማውን አይነት ድምፅ ሰጠ ወይም አሰማ። 3.ሳቀ፥ ተንከተከተ።
**አንካካ** ግ 1.አሳቀ፥ አንከተከተ። 2.እንደ ብርጭቆ፥ ጠርሙስ፥... ያሉ እቃዎችን አተራመሰ፥ አጋጨ።
**አስካካ (አሽካካ)** ግ 1.እየጮሀ ሳቀ። 2.ጮሀ (ፈረስ)። 3.ሳቅ የሚመስል የጩሀት ድምፅ አሰማ (ጅብ በስሪያ ጊዜ)።
**ካካቲ**[1] ስ የአሪባራ ሌላ ስም።
**ካካቴ**[2] "*ካካ" ስር ተመ.
**ካከራ** "**ካከረ**" ስር ተመ.
**ካውያ** ስ የልብስ መተኮሻ።
**ካዝና** ስ እንደብር፥ ወርቅ፥ ገንዘብ፥... ያሉ ውድ ንብረቶች የሚቀመጡበት የብረት ሳጥን።
**ካይንት** ስ የዝይ ሌላ ስም።
**ካደ** ግ 1.ሃይማኖቱን ተወ፥ ለወጠ። 2.እሌ አለ፥ ሸፈጠ። 3.ውል፥ ቃል ኪዳን አፈረሰ ወይም ጣሰ። 4.ለየ፥ አገለለ፥ ያለውን የስጋ ዝምድና ትስስር ሰረዘ።
**ከሃዲ** ቅ 1.ቃሉን የሚያጥፍ፥ እምነት የማይጣልበት። 2.ሃይማኖቱን የካደና የገዛ ሃይማኖቱ ተቃዋሚ የሆነ።
**ክህደት (ክደት)** ስ 1.የእምነት ተቃራኒ። 2.ሽፍጥ።
**ካደመ** ግ አገለገለ (ቡና በማፍላት)።
**ካዳሚ** ቅ በባህላዊ መንገድ ቡና አፍልቶ ለጠጪዎቹ የሚያድል።
**ካድሬ** ስ በመንግስታዊ ተቋም፥ በፓርቲ፥ በሙያ ማህበራትና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ በተወሰነ የስራ መስክ የተመደበና ለተመደበበትም ስራ የሰለጠነ ሰራተኛ። በጦር ሃይሎች ውስጥ በቋሚ ስራ ላይ የሚገኙ መኮንኖችና የበታች ሹማምንትም ካድሬዎች ተብለው ይጠራሉ።
***ካፈፈ (*ኳፈፈ)**
**ተንካፈፈ (ተንኳፈፈ)** ግ ተንሳፈፈ።
**አንካፈፈ (አንኳፈፈ)** ግ አንሳፈፈ።
**ካፊር** "**ካፍር**"ን ተመ.
**ካፌቴሪያ** ስ ተመጋቢዎች ራሳቸውን የሚያስተናግዱበት ምግብ ቤት ወይም ሆቴል።
***ካፋ**
**ካፊያ** ስ በጣም ቀላል የሆነ ዝናብ (ብዙውን ጊዜ ዝናብ መዝነብ ሲጀምር ያለው አይነት ዝናብ)።
**አካፋ** ግ ካፊያ ጣለ።
**ካፍር (ካፊር)** ስ በበቅሎ ከንፈር ላይ የሚወጣ የበሽታ አይነት።
**ካፒታሊስት** ስ 1.በካፒታሊስት ስርአተ ማህበር መርህ የሚተዳደር አገር። 2.የካፒታል ባለቤት።
**ካፒታሊዝም** ስ የአንድ አገር ንግድ፥ ኢንዱስትሪ፥... በባለሃብቶች የግል ይዞታ ስር ሆኖ የሚንቀሳቀስበት የኢኮኖሚ ስርአት።
**ካፒታል** ስ ትርፍ እንዲያስገኝ በንግድ፥ በምርት፥... ስራ ላይ የዋለ ወረት፥ ገንዘብ።
**ካፒቴን** ስ አለቃ፥ አዛዥ (የመርከብ፥ የአይሮፕላን፥...)።
**ካፖርት** "**ካቦርት**"ን ተመ.
**ኬ** የ"**ከ**" ፊደል ሃምስ ዘር።
**ኬላ** ስ የይለፍ ወይም የፈቃድ ወረቀት የያዙ ሰዎችና በህጋዊነት ሊገቡ ወይም ሊወጡ የሚችሉ እቃዎች የሚተላለፉበት፥ ይህንኑ ተግባር እንዲቆጣጠሩ በተመደቡ ሰዎች የሚጠበቅ የአገር ውስጥ መንገድ ወይም የጠረፍ በር።
**ኬላ ሰበረ** አስፈላጊውን የይለፍ ወይም የፈቃድ ወረቀት ሳይዝ በህገ ወጥ መንገድ ኬላን አልፎ ሄደ።
**ኬላ ተሰበረ** በሰርግ ጊዜ ልጃገረድ ድንግልናዋ ከተገሰሰ በሂላ የሚባል የሰርግ ዘፈን።
**ኬሚስት** ስ በኬሚስትሪ የሰለጠነ ሰው።
**ኬሚስትሪ** ስ ልዩ ልዩ ንጥረ ነገሮች ከምን እንደተሰሩ፥ እርስ በእርሳቸው እንዴት ሊዋሃዱ እንደሚችሉና በተለያዩ ሁኔታዎች ጊዜ ምን አይነት ጠባይ እንደሚያሳዩ የሚያጠና የሳይንስ ዘርፍ።
**ኬሚካል** ስ ለኬሚስትሪ ስራ የሚውል ወይም የኬሚስትሪ ስራ ውጤት የሆነ ንጥረ ነገር።
**ኬማ** ስ የዶማ ወይም የማረሻ እላቂ ብረት።
**ኬሻ** ስ ከቄጠማ ወይም ከዘንባባ ወይም ከእንሰት፥... የሚሰራ ምንጣፍ ወይም ከረጢት።
**ኬብል** ስ በምድር ወይም በባህር ወስጥ የስልክና የቴሌግራም መልእክቶችን እንዲያስተላልፍ የተቀበረ የሽቦዎች ስብስብ።
**ኬንትሮስ** ስ በዲግሪ የሚለካና ከግሪንዊች ወደ ምስራቅ ወይም ምእራብ አቅጣጫ ያለ የቦታ ርቀት።

**ኬክ** ስ ከፉርኖ ዱቄት፥ ከእንቁላል፥ ከቅቤ፥ ከስኳር፥... ተዘጋጅቶ የሚጋገር ጣፋጭ ምግብ።

**ኬክሮስ** ስ በዲግሪ የሚለካና ከምድር ወገብ ወደሰሜን ወይም ወደ ደቡብ አቅጣጫ ያለ የቦታ ርቀት።

**ክ** የ"ከ" ፊደል ሳድስ ዘር።

**-ክ** "- ህ" ን ተመ.

**ክህነት** "ካነ" ስር ተመ.

**ክህደት** "ካደ" ስር ተመ.

**ክለሳ** "ከለሰ" ስር ተመ.

**ክለብ** "ከበበ" ስር የ "ክበብ"ን 1ኛና 2ኛ ፍቺ ተመ.

**ክሊኒክ** ስ ብዙውን ጊዜ ተመላላሽ ታካሚዎችን እየተቀበለ የሚያክም አነስተኛ የህክምና ተቋም።

**ክላ** "ከላ" ስር ተመ.

**ክላርኔት** ስ ሙዚቃዊ የድምፅ ስልቶችን ለማውጣት የሚረዱና በጣት የሚነኩ ቁልፎች ያሉት በትንፋሽ የሚሰራ ዋሽንት መሳይ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

**ክላሰር** ስ ልዩ ልዩ የማስረጃ ሰነዶች የሚያዙበት ወፍራም ወረቀት፤ ዶሴ።

**ክላሲካል ሙዚቃ** ስ 1.ከጥንት ጀምሮ የኖረና ዘመን አመጣሽ ያልሆነ ረቂቅ የሙዚቃ ጥበብ። 2.ድምፃዊ ሳይኖርበት በመሳሪያ ብቻ የተቀነባበረ ሙዚቃ።

**ክላክስ** ስ የመኪና ጥሩንባ።

**ክልል** "ከለለ[1]" ስር ተመ.

**ክልስ** "ከለሰ[2]" ስር ተመ.

**ክልብልብ** "ከለበ" ስር ተመ.

**ክልብሽ**

**ክልብሽ አለው** ግ አቅለሸለሸው።

**ክልትው**

**ክልትው አለ** ግ ከድካም፥ ከመዛል፥... የተነሳ ወደቀ፥ ተዘረረ፤ ተኛ።

**ክልትው አደረገ** ግ ጣለ።

**ክልክል** "ከለከለ" ስር ተመ.

**ክልፍልፍ** "*ከለፈ" ስር ተመ.

**ክምር** "ከመረ" ስር ተመ.

**ክምችት** "*ከመቸ" ስር ተመ.

**ክረምት** ስ ከሰኔ 26 እስከ መስከረም 25 ድረስ ያለው የዝናብ ወራት ወይም ጊዜ።

**ክረምት አግቢ (አግባ)** ስ በክረምት መግቢያ ሰሞን ከመሬት ውስጥ በብዛት የሚፈላ በራሪ ነፍሳት፤ አሸን፥ ምስጥ።

**ክሪክ** ስ የመኪና ጎማ በሚቀየር ጊዜ ወይም ሌላ ጥገና ማድረግ ሲያስፈልግ የመኪናውን አካል ወደ ላይ ለማንሳት የሚጠቅም መሳሪያ።

**ክራር** ስ ባለስድስት አውታር (ክር) ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

**ክራሞት** "ከረመ" ስር ተመ.

**ክራባት (ከረባት)** ስ ቀጠንና ረዘም ተደርጎ ከጨርቅ ወይም ከቆዳ የሚዘጋጅ፥ በአንገት ላይ ከሸሚዝ ኮሌታ ስር የሚታሰርና በደረት ላይ ቁልቁል የሚንጠለጠል ወይም በአጭሩ በቢራቢሮ ቅርፅ ተዘጋጅቶ በስተፊት በኩል በሸሚዝ ኮሌታ ላይ የሚደረግ የሸሚዝ ማስጌጫ።

**ክራንቻ (የውሻ ክራንቻ)** ስ በፊት ጥርስና በመንጋጋ መካከል ከላይና ከታች በኩል ግራና ቀኝ የሚገኙ፥ ቀጠንና ሾል ያሉ አራት ጥርሶች(ስእሉን ጥርስ ስር ተመ.)።

**ክራንቻ ጥርስ** ዝ.ከ.

**ክራይ** "*ከረየ" ስር ተመ.

**ክር** "ከረረ" ስር ተመ.

**ክርስቲያን** የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ።

**ክርስትና** ስ 1.የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት በመቀበል ወይም በማመን ላይ የተመሰረተ ሃይማኖት፤ የክርስትና እምነት። 2.አንድ ሰው የክርስትና ሃይማኖት አባል በሚሆንበት ጊዜ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚፈፀምለት ስርአተ ጥምቀት።

**ክርስትና ተነሳ** የክርስትናን እምነት ተቀበለ፤ በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠመቀ።

**ክርስትና አነሳ** አንድ ሰው በጥምቀት አማካይነት የቤተክርስቲያን አባል በሚሆንበት ጊዜ ስርአቱ ላይ ተገኝቶ ቃልኪዳን በመግባት የተጠማቂው ሰው የክርስትና አባት ሆነ።

**ክርስትና ልጅ** ስ ለክርስትና አባት ወይም እናት በቃል ኪዳን የተሰጠ የሃይማኖት ወይም የጥምቀት ልጅ።

**ክርስትና አባት** ስ ወንድ ልጅ በሚጠመቅበት ጊዜ ሃይማኖትን ሊያስተምረው ቃል ገብቶ ሃላፊነትን የሚወስድ የቃል ኪዳን ወይም የሃይማኖት አባት።

**ክርስትና እናት** ስ ሴት ልጅ በምትጠመቅበት ጊዜ ሃይማኖትን ልታስተምራት ቃል ገብታ ሃላፊነቱን የምትወስድ የቃል ኪዳን ወይም የሃይማኖት እናት።

**የክርስትና ስም** ስ አንድ ህፃን ወይም ትልቅ ሰው ሲጠመቅ ወይም ክርስትና ሲነሳ በቀሳውስት

የሚሰጠው ሃይማኖታዊ ስም።

**ክርስቶስ** ስ የኢየሱስ የተቀብአ (የሹመት) ስም ሲሆን፥ ብዙ ጊዜ ከስሙ ጋር ተጣምሮ ኢየሱስ ክርስቶስ ወይም ለስሙ (ለኢየሱስ) እንደተለዋጭ ስም ሆኖ ያገለግላል።

**ክርታስ** ስ 1.መፃፊያ ወረቀት ወይም ብራና። 2.ለእቃ መያዣ፥ ... እንዲሆን በኪስ፥ ሳጥን፥ ... መልክ ተደርጎ የሚሰራ ወፍራም ወረቀት፥ ካርቶን። 3.በማህፀን ውስጥ ያለ ሽል የሚጠቀለልበት ብራና መሰል ስስ ቆዳ፤ ሰፋድል።

**ክርትስ "ከረተሰ"** ስር ተመ.

**ክርትፍ "ከረተፈ"** ስር ተመ.

**ክርን "ከረና"** ስር ተመ.

**ክርካር** ስ በኪራይ ለተወሰደ ክብት የሚከፈል የጉልበት ዋጋ።

**ክርክራት "ከረከረ"** ስር **"ክርክር"**ን ተመ.

**ክርክር "ከረከረ"** ስር ተመ.

**ክርኽር "*ከረከረ"** ስር ተመ.

**ክርክሮሽ "ከረከረ"** ስር ተመ.

**ክርድድ "ከረደደ"** ስር ተመ.

**ክርፋታም "ከረፋ"** ስር ተመ.

**ክርፋት** ዝ.ከ.

**ክሰል "ከሰለ"** ስረ **"ከሰል"**ን ተመ.

**ክሳት "ከሳ"** ስር ተመ.

**ክሳድ** ስ 1.በግጅራት በኩል ያለ የአንገት ክፍል። 2.አንገትጌ።

**ክስ[1] "ከሰሰ"** ስር ተመ.

**ክስ[2]** ፍየልንና በግን ሂድ ወይም ወግድ ለማለት የሚባል ቃል።

**ክስል "ከሰለ"** ስር ተመ.

**ክስረት "ከሰረ"** ስር ተመ.

**ክስተት[1]** ስ ከዳዊት መዝሙር ተውጣጥቶ የተቀናበረ ያሬዳዊ የዜማ ድርሰት።

**ክስተት[2] "ከሰተ"** ስር ተመ.

**ክስካስ** ስ የጭነት ከብት ወገቡ እንዳይጎዳ ከኮርቻ ወይም ከጭነት ስር የሚደረግለት ድልዳል።

**ክስካሽ "ከሰከሰ"** ስር ተመ.

**ክስክስ** ዝ.ከ.

**ክሽን "ከሸነ"** ስር ተመ.

**ክሽክሽት (ክሽክሽ)** ስ 1.ጤፍ የሚያካክልና ጎመን ላይ የሚገኝ የጎመን ትል። 2.ነጭ የጆሮ እከክ።

**ክበብ "ከበበ"** ስር ተመ.

**ክበድ "ከበደ"** ስር ተመ.

**ክቡራት "ክብርት"**ን ተመ.

**ክቡራን "ክቡር"**ን ተመ.

**ክቡር** (ብ.ቁ.**ክቡራን**፥ አን. **ክብርት**፥ አን. ብ.ቁ.**ክቡራት**) ቅ 1.በከፍተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኝ ባለስልጣን የሚቀርብ የማእረግ መግለጫ ቃል። *ክቡር ሚኒስትር/ክቡር አቶ እገሌ*። 2.የአክብሮት መግለጫ ቃል። *ክቡር ወንድሜ ሆይ*።

**ክቢ**

**ክቢ ሰራው** ጉድ አደረገው።

**ክባስ "ከበሰ"** ስር ተመ.

**ክብ "ከበበ"** ስር ተመ.

**ክብረ ሰማይ** ስ. ሰዎች ለቀስል መድሃኒት ይሆናል ብለው የሚጠቀሙበት የማእድን አይነት።

**ክበረ በአል "ከበረ"** ስር ተመ.

**ክብረ ነክ** ዝ.ከ.

**ክብረ ነገስት** ዝ.ከ.

**ክብረ ንፅህና** ዝ.ከ.

**ክብረ ወሰን** ዝ.ከ.

**ክብረት** ዝ.ከ.

**ክብሪት** ስ 1.ከክብሪት ቤት ላይ ወይም ሻካራ ነገር ላይ ሲጭሩት እሳት የሚሰጥ ማእድን የተጣበቀበት አነስተኛ እንጨት ከነመያዣው። 2.(ዘይ.) ነገር አያያዥ።

**ክብሪት ጫረ** የክብሪትን እንጨት ለዚሁ ተብሎ ከተዘጋጀና ሻካራነት ካለው ነገር ጋር በማፋተግ እሳት አያያዘ።

**የክብሪት ቤት** ስ ከጠንካራ ወረቀት ወይም ፕላስቲክ፥... በሳጥን ቅርፅ (በውስጡ የክብሪት እንጨቶችን እንዲይዝና ውጫዊ ክፍሉ ደግሞ ክብሪትን ለመጫር እንዲያገለግል ሆኖ) የተሰራ መጠኑ አነስተኛ የሆነ የክብሪት መያዣ።

**የክብሪት እንጨት** ስ በአንደኛው ጫፍ ላይ እሳት የሚሰጥ ማእድን የተጣበቀበት ቀጭንና ትንሽ እንጨት።

**ክብር "ከበረ"** ስር ተመ.

**ክብርት "ክቡር"**ን ተመ.

**ክብርና "ከበረ"** ስር **"ክብረ ንፅህና"**ን ተመ.

**ክብስብስ "*ከበሰበሰ"** ስር ተመ.

**ክብካቤ "ከበከበ"** ስር **"እንክብካቤ"**ን ተመ.

**ክብደት "ከበደ"** ስር ተመ.

**ክታብ "ከተበ[1]"** ስር ተመ.

**ክታች "ከተተ"** ስር ተመ.

**ከት** ዝ.ከ.
**ከትር** "**ከተረ**" ስር ተመ.
**ከትባት** "**ከተበ**[2]" ስር ተመ.
**ከትካች** "**ከተከተ**" ስር ተመ.
**ከትክታ** ስ ለአጥር፥ ለዳስ፥... የሚያገለግል፥ በለጋነቱ ደግሞ ተቀጥቅጦ መብራት ሊሆን የሚችልና ጥንካሬ ያለው አነስተኛ የዛፍ አይነት።
**ከትፍትፍ** "***ከተፈ**" ስር ተመ.
**ከትፎ** "**ከተፈ**" ስር ተመ.
**ከችሌ** ስ እንደ ጥቁር ሰሌዳ ለፅሁፍ የሚያገለግል ጠፍጣፋ ድንጋይ።
**ከቾ** "**ከቸቸ**" ስር ተመ.
**ከናድ** "**ከነዳ**" ስር ተመ.
**ከንብንብ** "***ከነበ**" ስር ተመ.
**ከንክና** ስ በበርበሬ ዛላ ውስጥ ፍሬውን የሚሸከመው ክፍል።
**ከንዋኔ** "***ከነወነ**" ስር ተመ.
**ከንውን** ዝ.ከ.
**ከንድ** "**ከነዳ**" ስር ተመ.
**ከንፍ** "**ከነፈ**" ስር ተመ.
**ከክ** "**ከካ**" ስር ተመ.
**ከው አለ**[1] ግ በጣም ደነገጠ።
**ከው አለ**[2] ግ በጣም ደረቀ (በፀሃይ)።
**ከው አለ**[3] ግ ጮሀ፥ ኪው አለ (ደወል፥ ቆርቆሮ)።
**ከዳን** "**ከደነ**" ስር ተመ.
**ከጀላ** "**ከጀለ**" ስር ተመ.
**ከፈፍ** "**ከፈፈ**" ስር ተመ.
**ከፉ** "**ከፋ**" ስር ተመ.
**ከፉኛ** ዝ.ከ.
**ከፉት** ዝ.ከ.
**ከፉይ** "**ከፈለ**" ስር ተመ.
**ከፍል** ዝ.ከ.
**ከፍልፉይ** ዝ.ከ.
**ከፍልፍል** ዝ.ከ.
**ከፍተት** "**ከፈተ**" ስር ተመ.
**ከፍት አፍ** ዝ.ከ.
**ከፍት** ዝ.ከ.
**ከፍክፉት** "**ከፈከፈ**" ስር ተመ.
**ከፍክፍ** ዝ.ከ.
**ከፍያ** "**ከፈለ**" ስር ተመ.
**ከ** ፍ "**ከ**" ፊደል ሳብአ ዘር።

**ኮለለ**[1]
**ኮለል (ኩልል) አለ** ግ 1.ቀስ እያለ ወረደ፥ ፈሰሰ (ፈሳሽ)። 2.እየተንከባለለ፥ እየተሽከረከረ ሄደ (ብዙውን ጊዜ ድቡልቡል ወይም ክብ ነገር)።
**ተንኳለለ** ዝ.ከ.
***ኮለለ**[2]
**ኮለል (ኩልል) አለ** ግ ወለል ወይም ጥርት ብሎ ታየ። *ኮለል ያለ ውሃ /ኮለል ያለች ፀሃይ*።
**ኮለሌ** ስ ከቆዳ ለተሰራ ሚዛን ማንጠልጠያና እንደ ከብደት መጠን መለኪያ ሆኖ የሚያገለግል እንጨት።
**ኮለል** ስ 1.የወንድ አባለዘር ጫፍ። 2.የተጠረበና የተላገ ኽርሙልሙል የበር መቀርቀሪያ እንጨት። 3.የሞፈር ቂጥ። 4.ድብልብል የሚዛን ድንጋይ፥ እንደኪሎ ያለ መለኪያ። 5.ወናፍን ከመደብ (ከወፍራሙ የወናፍ ቧንቧ) ጋር የሚያገናኘው ቀጭኑ የብረት ቧንቧ።
***ኮለተፈ**
**ኮልታፋ (ኩልትፍ)** ቅ አፉን እንዳልፈታ ህፃን የሚናገር፥ ተብታባ።
**ተኮለታተፈ** ግ አፉን እንዳልፈታ ህፃን አድርጎ ተናገረ፥ ተንተባተበ።
**ተኮላተፈ** ዝ.ከ.
**አኮለታተፈ** ግ አፉን እንዳልፈታ ህፃን አድርጎ ተናገረ፥ ተንተባተበ።
**አኮላተፈ** ዝ.ከ.
**ኮለኮለ**[1] ግ በአንድ ቦታ በብዛት ሰበሰበ፥ አከማቸ፥ ደረደረ።
**መኮልኮያ** ስ በቤተ መንግስት በር ላይ የሚገኝ አደባባይ (ሰዎች ግብር ለመብላት ተራ የሚጠብቁበት)።
**ኮልኮሌ** ቅ ቅራቅንቦ፥ ኮተት።
**ተኮለኮለ** ግ ተሰበሰበ፥ ተደረደረ፥ ተከማቸ።
**ኮለኮለ**[2] ግ የ"**ኮረኮረ**"ን 1ኛና 2ኛ ፍቺ ተመልከት።
**ኮለፈ** ግ በጭቃ፥ በደም፥ በወጥ፥... በከለ፥ አበላሸ (ልብስን፥ አካልን)።
**ኩልፍልፍ** ቅ የተበከለ፥ የተበላሸሸ (በጭቃ፥ በደም፥ በወጥ፥...)።
**ኮላ**[1] ግ የቆሸሸ ወይም መልኩ የደበዘዘ ወርቅን፥ ብርን፥ ነሃስን፥ ... በኮመር አፀዳ፥ በረሸ፥ ወለወለ። 2.ብር ወይም ወርቅ ያልሆኑ የጌጥ እቃዎችን፥ ብር ወይም ወርቅ እንዲመስሉ ብር ወይም ወርቅ ቀባ።
**ኮላ**[2] ስ እንደሙቅና ሙጫ ያለ ማጣበቂያ።
***ኮላሽ**

**ኩልሽ** ቅ አባለ ዘሩ የተቀጠቀጠ በሬ፥ በግ፥...።
**ተኮላሸ** ግ 1.ተቀጠቀጠ (የወንድ አባለ ዘር)። 2.ተሰናከለ፥ ተጨናገፈ።
**አኮላሸ** ግ ቀጠቀጠ (የወንዴን አባለ ዘር)። 2.አሰናከለ፥ አጨናገፈ።
**ኮሌታ** ስ አንገትጌ።
**ኮሌጅ** ስ ልዩ ልዩ የሙያ ወይም ከፍተኛ ትምህርት የሚሰጥበት የትምህርት ተቋም።
**ኮልባ** ስ 1.ከጎሽ ወይም ከበሬ፥ ... ቀንድ የሚሰራ ዋንጫ። 2.ከቀንድ የሚሰራ የጎራዴ ወይም የቢላዋ እጀታ። 3.ከጎሽ ቀንድ የሚሰራ ሎቲ ወይም ቀለበት።
**ኮልባቋሬ** ስ የውስጠኛውና የላይኛው ክፍል የተለያየ መልክ ያለው የካባ ጨርቅ።
**ኮልታፋ** "*ኮለተፈ" ስር ተመ.
**ኮልኮሌ** "ኮለኮለ[1]" ስር ተመ.
**ኮሎኒያሊስት** ስ ቅኝ ገገር።
**ኮሎኒያሊዝም** ስ ቅኝ አገዛዝ።
**ኮሎኔል** ቅ ከሌተናል ኮሎኔል በላይ ከብርጋዴር ጀኔራል በታች ያለ የወታደራዊ ማእረግ ስም።
**ኮመረ**
**ኮመረች** ግ እንደ ጠላ፥ ያገር አረቄ፥ ጠጅ፥... ያሉትን መጠጦች እያዘጋጀች ሸጠች።
**ኮማሪ (ኮማሪት)** ቅ እንደጠላ፥ ያገር አረቄ፥ ጠጅ፥ ... ያሉትን መጠጦች የምትሸጥ ሴት።
**ኮመር** ስ 1.ለነሃስ፥ ለብር፥... ጌጣጌጦች ማሳመሪያ ወይም ማደሻ የሚያገለግል በአንድነት የፈላ የጨው፥ የባሩድ፥ የድኝ፥ የእንቆቆ ድብልቅ። 2.እንደ ብር፥ ወርቅ፥... ያሉትን የጌጥ እቃዎች ለማደስ ወይም ለማሳመር የሚያገለግል የኬሚካል አይነት።
***ኮመተረ**
**ኮምታራ** ቅ 1.ጨምዳዳ፥ ጨምታራ።2.ኮስታራ።
**ኮምታሬ** ስ በጣም የከረረ የድር አይነት።
**ኩምትር አለ** ግ 1.ጭምድድ፥ ጭምትር አለ። 2.ቆጥር፥ ኩስትር አለ (ፊት)።
**ኩምትር አደረገ** ግ 1.ጭምድድ፥ ጭምትር አደረገ። 2.ቆጥር፥ ኩስትር አደረገ (ፊትን)።
**ተኮማተረ** ግ 1.ጭምድድ፥ ጭምትር አለ። 2.ቆጥር፥ ኩስትር አለ (ፊት)።
**አኮማተረ** ግ 1.አጨማተረ። 2.ቆጥር፥ ኩስትር አደረገ (ፊትን)።
**ኮመከ** ግ 1.አስቂኝ የሆነ ድርጊት ፈፀመ (ሆነ ብሎ)። 2.አሞኘ፥ ሸወደ፥ አታለለ (ለቀልድ)።
**ኩምክና** ስ አስቂኝ የሆነ ድርጊት።
**ኮሚክ** ቅ ቀልደኛ፥ አስቂኝ።
**ተኮመከ** ግ ተሞኘ፥ ተሸወደ፥ ተታለለ (በቀልድ)።
**ኮመኮመ** ግ 1.በስፌው ተመገበ፥ ጠጣ። 2.ወሬን ለረዥም ሰአት አወራ ወይም አዳመጠ።
**ኮመጠጠ (ሆመጠጠ)** ግ ሲጥ፥ ጠላ፥... ከመቡካት ወይም ብዙ ከመቆየት የተነሳ እንደ ሎሚ ኮስተር ያለ ጣእም አመጣ።
**ኮምጣጤ (ሆምጣጤ)** ስ 1.መጠኑና ቅርፁ እንደ ብርቱካን ያለ ሆኖ የሚኮመጥጥ ፍሬ የሚያፈራ የብርቱካን ዛፍን የሚያክል ተክል። ፍሬውም ኮምጣጤ ይባላል። 2. ከኮምጣጤ ፍሬ እየተዘጋጀ በሰላጣ ውስጥ የሚጨመር ፈሳሽ።
**ኮሚሽነር** ስ የኮሚሽን መስሪያ ቤት የበላይ ሃላፊ።
**ኮሚሽን** ስ 1.የተለያዩ ጉዳዮችን የሚያከናውንና ህጋዊ ስልጣን ያለው አካል። 2.እቃዎችን በማሻሻጥ፥ ጉዳይ በማስፈፀም፥... አገልግሎት ለሰጠ ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚከፈል የአገልግሎት ዋጋ።
**ኮሚቴ** ስ ልዩ ልዩ ጉዳዮችን ለማከናወን ሌሎችን በመወከል ከብዙ ሰዎች መካከል የተመረጠ አካል ወይም ቡድን።
**ኮሚኒስት** ስ የኮሚኒዝም ፍልስፍና ወይም ርእዮተ አለም ተከታይ።
**ኮሚኒዝም** ስ የአንድ አገር ሃብትና የማምረቻ መሳሪያዎች በማህበረሰቡ የጋራ ይዞታ ስር የሚውሉበት ስርአተ ማህበር።
**ኮሚክ** "ኮመከ" ስር ተመ.
**ኮማ** ስ ከህመም ፅናት የተነሳ ራስን የመሳት ሁኔታ፥ ፃእር።
**ኮማሪ(ት)** "ኮመረ" ስር ተመ.
**ኮሜዲ** ስ አስቂኝ ድርጊቶች የሚታዩበት የድራማ አይነት።
**ኮሜዲኖ** ስ በተለያየ መጠንና ቅርፅ የሚዘጋጅ መሳቢያ፥ መደርደሪያ፥... ያለውና ለቤት እቃዎች (ሳህን፥ ብርጭቆ፥ ልብስ፥ ...) ማስቀመጫነት የሚያገለግል ባለመዝጊያ ቋሚ ሳጥን።
**ኮምበር (ኮንበር)** ስ ደንዳና ለምቦጭ።
**ኮምታራ** "*ኮመተረ" ስር ተመ.
**ኮምታሬ** ዝ.ከ.
**ኮምጣጣ** "ኮመጠጠ" ስር ተመ.
**ኮምጣጤ** ዝ.ከ.
**ኮምፒዩተር** ስ ልዩ ልዩ መረጃዎችን ለማጠናቀር እንዲሁም በተሰጠው መረጃ መሰረት ለተለያዩ ችግሮች መፍትሄ ለመፈለግና ሌሎች ማሽኖችን ለመቆጣጠር ወይም ለማሰራት

የሚያስችል በኤሌክትሪክ ሃይል የሚሰራ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ::

**ኮምፓስ**[1] ስ ወደ ሰሜን በሚጠቁም መርፌው (ማግኔት) አማካኝነት እንደ ሰሜን፥ ... ያሉ አቅጣጫዎችን ለማመልከት የሚያገለግል መሳሪያ ፣ መርሃ ሰሜን::

**ኮምፓስ**[2] ስ ክብ መስመር ለመስራት የሚያገለግል፥ በአንድ አፉ ሹል መርፌ በሌላ ጫፉ እርሳስ የሚሰካበት ዘንግ ያለው መሳሪያ::

**ኮረመተ (ኮረተመ)** ግ 1.አጠፈ፥ ጨበጠ (ሰውነትን):: 2. ጨመደደ፥ ጨበጠ::

**ተኮረመተ** ግ ተኮራመተ::

**ተኮራመተ** ግ 1.አጥፍ፥ ጭብጥ አለ (በአቀማመጥ፥ በአተኛኘት):: 2.(ዘይ.) በጣም ተቸገረ::

**ኮረምቱ** ስ የዝሆን አውራ::

**ኮረሪማ** ስ ሽፋኑ ጠንካራ የሆነና ፍሬው ለቅቤ ማንጠሪያ፥ ለወጥ፥... የሚሆን የቅመም አይነት::

**ኮረሸመ (ኮረሽመ)** ግ ከሽ ከሽ የሚል ድምፅ እያሰማ አኘከ (ቃሪያን፥ የእንጀራ ድርቆሽን፥...)::

**ኮረብታ** ስ ከአካባቢው መሬት ከፍ ብሎ የሚገኝ ስፍራ፥ አነስተኛ ተራራ፥ ጉብታ::

**ኮረተ** ግ 1.ክፍተት ባለው ግንብ መካከል ኮረትን ሞላ፥ ሰገሰገ (በግንብ ስራ ጊዜ):: 2.ተሰበሰበ፥ ተከማቸ:: 3. አኮረተ::

**ኮረት** ስ አነስ አነስ ያለ ወይም የተሰባበረ ድንጋይ::

**ኮረተመ** "ኮረመተ"ን ተመ.

**ኮረት** "ኮረተ" ስር ተመ.

**ኮረንቲ** ስ 1.ኤሌክትሪክ:: 2. (ዘይ.) ሃይለኛ:: *ጠላዋ ኮረንቲ ነው::*

**ኮረንቲ ጨበጠ** በጣም ተናደደ::

**ኮረኮመ** ግ 1.እጁን ጨብጦ ወይም ጣቶቹን አጥፎ በኩርኩም መታ፡ ገጨ (ጭንቅላትን):: 2.ከአንድ ነገር ላይ በመጠኑ ቀነሰ፡ አነሳ፡ ቆረሰ፡ ሸረፈ::

**ኩርኩም** ስ በታጠፉ የእጅ ጣቶች ጭንቅላት ላይ የሚደረግ ምት::

**ኩርኳሚ** ስ ያሞሌ ሽራፊ ወይም ስባሪ::

**ኮረኮረ** ግ 1.የብብትን አካባቢ በጣት ወጋ ወጋ አደረገ፡ ኮለኮለ (ለማሳቅ፥ ለማናገር):: 2.ከበቅሎ ወይም ከፈረስ ላይ የተቀመጠ ሰው የእንስሳውን አካል በተረከዙ ነካ ነካ፥ መታ መታ አደረገ፡ ኮለኮለ (ፍጥነቱን እንዲጨምር ለማድረግ):: 3.ጎተጎተ፥ ቀሰቀሰ፥ በነገር ነካካ (ለማናገር፥ ነገር ለማውጣጣት፥ ጠብ ለመጫር፥...):: 4.በጣት፥ በሳር፥ በላባ፥... የጆሮን፥ የአፍንጫን፥... ውስጥ ነካካ፥ አከከ፥ ጎረጎረ:: 5.አማሪትን ወይም የከበሮን ቂጥ እየደጋገመ በስልት መታ::

**ኮረኮራ** ስ በበጋ ወራት የሚፈጠር የዋልካ መሬት ስንጥቃት፥ ንቃቃት::

**ኮረኮር**[1] ስ የበግ ወይም የፍየል በጠጥ::

**ኮረኮር**[2] ስ ሌባ::

**ኮረኮንች** ስ 1.ጭንጫ ወይም ድንጋያማ መሬት:: ቅ 2.በኮረት ወይም በድንጋይ ስብርባሪ የተሰራ (መንገድ)::

**ኮረኳ** ግ ነቀለ፥ መነገለ::

**ኮረዳ** ስ ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ልጃገረድ::

**ኮረጀ** ግ የሌላን ሰው ስራ ወይም ሃሳብ የራሱ ስራ ወይም ሃሳብ እንደሆነ አድርጎ አቀረበ፤ ገለበጠ፤ ቀዳ::

**ኩረጃ** ስ ስርቆት (የእውቀት፥ የስራ)::

**ኮረጃ** ስ በተወሰነ ቁጥር ልክ እየሆነ በአንድነት የታሰረ የፍየል ወይም የበግ፥... የደረቀ ቆዳ::

**ኮረጆ** "ኮሮጆ"ን ተመ.

**ኮረጠ** "ሆረጠ"ን ተመ.

**ኮረፈ** ግ አረፋ አወጣ::

**ኮረፎ** ስ 1.አረፋ:: 2.በድፍድፍ መልክ ተዘጋጅቶ የተቀመጠና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ በውሃ ተበጥብጦ ጥቂት ከቆየ በኋላ የሚጠጣ አረፋነትና ጉሽነት ያለው ወፍራም ጠላ::

**ተኩረፈረፈ** ግ 1.አረፋ አበጀ:: 2.ኩፍ አለ፥ አረፋ አበጀ፥ ፈላ::

***ኮረፈ**[1]

**ኩርፍ** ቅ ጥል፥ ጥለኛ፥ ጠበኛ:: *እከሌና እከሌ ኩርፍ ናቸው::*

**ኩርፈኛ** ዝ.ከ.

**ኩርፍታ** ስ ኩርፊያ::

**ኩርፍተኛ** ቅ አኩራፊ::

**ኩርፍታም** ዝ.ከ.

**ኩርፊያ** ስ በመቀየም፥ በመከፋት፥ በመናደድ የተነሳ ንግግር ወይም ግንኙነት ማቆም::

**ተኮራረፈ** ግ ተቀያየመ፥ ከጠበኛው ጋር ንግግር፥ ግንኙነት አቆመ::

**ተኳረፈ** ዝ.ከ.

**አኮረፈ** ግ በጥል ወይም በሌላ ምክንያት ተቀይሞ ንግግር ወይም ግንኙነት አቆመ::

**አኩራፊ** ቅ በትንሽ በትልቁ የሚቀየም፥ የሚያኮርፍ::

**አኮራረፈ** ግ አቀያየመ፥ እንዳይነጋገሩ አደረገ፥ አጣላ::

**አኳረፈ** ዝ.ከ.

**አስኮረፈ** ግ አስቆጣ፥ አስቀየመ።

***ኮረፈ²**

**ኩርፊያ** ስ በእንቅልፍ ላይ እያለ የሚያንኮራፋ ሰው የሚያሰማው ድምፅ።

**አንኮራፋ** ግ በእንቅልፍ ላይ እያለ ኅርናና የአተነፋፈስ ድምፅ እያሰማ ተነፈሰ።

**አንኳረፈ** ዝ.ከ.

***ኮረፈፈ**

**ተንኮረፈፈ** ግ አኮረፈ።

**አንኮረፈፈ** ግ አስኮረፈ።

**ኮረፌ** "*ኮረፈ" ስር ተመ.

**ኮሪዶር** ስ በቤት ውስጥ (ብዙ ጊዜ በክፍሎች መካከል) የሚገኝና ቀጠን ብሎ ረዘም ያለ ክፍት መተላለፊያ ቦታ።

**ኮራ¹** ግ ታበየ፥ ታጀረ። 2.ተቆነነ፥ ተጀነነ። 3.ተመካ፥ ተማመነ። *የምኮራበት ወንድሜ ነው።*

**ኩሩ** ቅ 1.ጅንን፡ ቁንን። 2.ቀጥብ፥ ጨዋ። 3.ኩራተኛ።

**ኩራት** ስ 1.ትእቢት። 2.የመጀነን፥ የመኮፈስ ስሜት። 3.የንቀት ስሜት። 4.በአንድ ነገር ላይ መመካት ወይም አንድን ነገር አለኝታ ማድረግ።

**ኩራተኛ** ቅ 1.ትእቢተኛ። 2.ጅንን። 3.ሰው የሚንቅ።

**ተኩራራ** ግ 1. ተንቀባረረ። 2.ተማመነ፥ ተመካ። 3. ተበተ።

**አኮራ** ግ 1.አለኝታ ወይም መመኪያ ሆነ። *የሚያኮራ ዘመድ አለው።* 2.የደስታ፥ የአድናቆት፥ የርካታ፥ የክብር ስሜት እንዲፈጠር ምክንያት ሆነ። *አገሩን የሚያኮራ ስራ ሰራ።* 3.ትእቢተኛ አደረገ።

**አኩራራ** ግ የኩራት ስሜት ፈጠረ።

**ኮራ²** ግ ሸጠጠ፥ ተንቋጠጠ፥ ቀጢጥ አለ (የቤት ግሪያ) ፡የደራ ተቃራኒ።

**ኮራ³** ግ በኩርኩም፥ በዱላ፥... ጭንቅላትን መታ።


**ኮርማ** ስ ያልተኮላሸና ልጅነት ያለው በሬ።

**ኮርስ** ስ 1.በተወሰነ ጊዜ የሚጠናቀቅ የተወሰነ የሙያ ወይም የቀለም ትምህርት ስልጠና (የጤና ረዳትነት፥ የፀሃፊነት፥...)። 2.በተወሰነ ጊዜ የሚጠናቀቅየተወሰነ የቀለም ትምህርት (ኮሌጅ፥ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ)።

**ኮርቤሳ** ስ ያልተኮላሸና ልጅነት ያለው ፍየል፣ ወጠጤ።

**ኮርቻ** ስ 1.በበቅሎ፥ በፈረስ፥... ጀርባ ላይ ተደርጎ የሚታሰርና በላዩ ላይ ሰው የሚቀመጥበት ከእንጨት፥ ከቆዳ፥... የሚሰራ እቃ። 2.ብስኪሌት ጋላቢ የሚቀመጥበት የብስኪሌት ክፍል።

**ኮርቻ አራገፈ** ከፈረስ፥ ከበቅሎ፥ ... ጀርባ ላይ ኮርቻ አወረደ።




ኮርቻ 1ኛ ፍቺ

**ኮርቻ ሰፊ** ስ ኮርቻ ሰሪ።

**ኮርቻ ትከል** ስ የሱሪን ወገበር ወይም በቂጥ በኩል የሚውለውን የሱሪ ጨርቅ አቀዳደድና አሰፋፍ ብቻ የሚመለከት ሰያፍ ቅድ።

**የኮርቻ ከብት** ስ ለኮርቻ ጭነት ብቻ የተመደበና ሰው የሚጓጓዝበት በቅሎ ወይም ፈረስ፥።

**ኮርች** ስ ግንዱ ከበሮ፥ ኮርቻ፥... ለመስራት የሚያገለግል እሾሃማ ዛፍ።

**ኮርናፋ** ቅ 1.ነፍናፋ። 2.ኩርፍተኛ።

**ኮርፖሬሽን** ስ በስሩ የተለያዩ ወይም ተመሳሳይ ስራ የሚያከናውኑ ድርጅቶችን የያዘ ትልቅ ድርጅት።

**ኮሮጆ (ኮረጆ)** ስ እንደ ማህደር፥ አኩፋዳ፥ ቦርሳ፥ ከረጢት ያለ የእቃ መያዣ።

**ኮሰመነ** ግ ኮሰሰ፥ ቀጠነ፥ መነመነ፥ ሰለሰለ፥ ጫጨ።

**ኮስማና** ቅ 1.(ስድብ) በጣም ቀጭን፥ ኮሳሳ። 2.ቀጭን፥ ደቃቃ፥ አቅመ ቢስ።

**ኮሰረት** ስ ለቅቤ ማንጠሪያ የሚያገለግልና ከሴ የሚመስል የተክል አይነት።

**ኮሰሰ** ግ 1.ከሳ፥ ኮሰመነ፣ በአካል አነሰ። 2.ደከመ፥ አቅመቢስ ሆነ።

**ኮሳሳ** ቅ 1.ከሲታ፥ ኮስማና። 2.አቅመ ቢስ።

**ኮሰስ ብሎ** ቀሰ፥ ዝግ ብሎ።

**አኮሰሰ** ግ አናናቀ፥ አቃለለ፥ አንቋሸሸ።

**አንኳሰሰ** ዝ.ከ.

**ኮሰተረ¹** ግ 1.ተረከሰ፣ ለይቶ አስወገደ (የተቃጠለ የእንጨት፥ የሲጃራ፥ የጧፍ፥... ጫፍን)። 2.ጠረገ፥ አፀዳ። 3.ቆሰቆሰ፥ ወደ እሳት ገፋ፥ ጨመረ (በምድጃ ውስጥ ያለ እንጨት መንደዱን እንዳያቋርጥ)።

**መኮስተሪያ** ስ 1.መተርኮሻ፣ የሲጋራ አመድ ማጠራቀሚያ። 2.መጥረጊያ።

**ኩስታሪ** ስ 1.የነደደ የጧፍ፥ የሲጃራ ክላይ ወይም አመድ። 2.በርቶ ወይም ነዶ ያላለቀ የጧፍ፥ የሻማ፥ የእንጨት፥... ትራፊ።3.የቆሻሻ

ጥራጊ።

**ኮሰተረ²** ግ 1.ፈጀ፥ ተኮሰ፥ ለበለበ (በርበሬ)። 2.እንደመኮምጠጥ፥ እንደ መሸምጠር አለ (ጠላ፥…)። 3.ቋጠረ፥ አጠቆረ፥ አኮማተረ (ፊትን)። 4.ከወነ፥ ጠነቀቀ፥ ሰበሰበ (የተዝረከረከውን፥ የተንዘረፈፈውን፥… እቃ)።

**ኮስታራ** ቅ 1.ንቁ፥ ጥንቁቅ፥ ቀልጣፋ። 2.ሃይለኛ። 3.ዋዛ ፈዛዛ የማይወድ፥ ቁም ነገረኛ።

**ተኮሳተረ** ግ 1.ተቆጣ፥ ፊቱን አጠቆረ። 2.የሚያቃጥል፥ የሚፋጅ ወይም የሚለበልብ ሆነ (በርበሬ)።

**አኮሳተረ** ግ አስቆጣ፥ ከሰከሰ (ፊትን)።

**ኮሰተረ³** ግ 1.አረመ፥ ኮተኮተ (አትክልትን)። 2.ቆፈረ።

**ኮሰኮሰ** ግ እንደማቅና በርኖስ ወይም እንደ አባጨጓሬ ያለ ነገር ሰውነትን ሲነካ የሚሰማውን አይነት ስሜት ተሰማ፥ ሻከረ፥ ሞረደ (ገላን)።

**ኮስኳሳ** ቅ 1.እንደበርኖስ ፀጉር የሚወጋ ወይም የሚሞርድ፥ ሻካራ። 2.(ዘይ.) አመለ መጥፎ፥ ነጭናጫ፥ ጠባዩ የማይመች።

**ኮስካሴ (አባ ኮስኳሴ)** ስ አባ ጨጓሬ።

**ኮሲ** ስ 1.ቀዬ። 2.የቤት ጥራጊና የከብት ፋግ የሚፈስበት፥ በቤት አካባቢ የሚገኝ የዳበረ ቦታ ወይም መሬት።

**ኮሳ** ግ ኩሱን ጣለ፥ ተፀዳዳ (ዶሮ፥ አሞራ፥ …)።

**ኩስ** ስ የዶሮ፥ የአሞራ፥… አይነ ምድር።

**ኮሳሳ** "ኮሰሰ" ስር ተመ.

**ኮስማና** "ኮሰመነ" ስር ተመ.

**ኮስታራ** "ኮሰተረ²" ስር ተመ.

**ኮስኳሳ** "ኮሰኮሰ" ስር ተመ.

**ኮስኳሴ** ዝ.ከ.

**ኮሶ** 1.በጥሬ ስጋ አማካይነት ከሰው ሆድ ገብቶ በመኖር ህመም የሚያስከትል ጥገኛ የትል አይነት። 2.ኮሶ የተባለውን ትል ከሆድ ውስጥ ለመግደል ወይም ለማስወጣት ተወቅጦና ተበጥብጦ የሚጠጣ መራራ ፍሬ። ፍሬውንም የሚያፈራው ዛፍ ኮሶ ይባላል።

**ኮሶ ታየው /ተጋደደው/ ተጣባው** የኮሶ ትል በሆዱ በመኖሩ ከአይነ ምድሩ ጋር ትሉ ወጥቶ ታየ።

**ኮሶ ኮሶ አለው** መረረው፥ ሰለቸው፥ አንገፈገፈው።

**ኮሶ ፊት** ፊቱ የማይፈታ፥ ፈገግታ የማይታይበት፥ ጨፍጋጋ ፊት።

**የኮሶ ስንብት/መሰናበቻ** ስ የኮሶ መድሃኒት ለጠጣ ሰው የሚሰጥ ወይም የሚዘጋጅ ምግብና መጠጥ ወይም ግብዣ።

**ኮሶኛ** ቅ የኮሶ መድሃኒት የወሰደ ወይም የጠጣ።

**ኮሸለለ** "ኮሸለለ"ን ተመ.

**ኮሸሽላ (ኮሸሌ)** ስ ግንዱም ቅጠሉም በሾክ የተሞላ የቁጥቋጦ አይነት።

**ኮሸኮሸ** ግ ሲያኙት ኮሽ ኮሽ የሚል ድምፅየሚሰጥ እንደ ቃሪያ፥ አገዳ፥ … ያለን ነገር በላ ወይም ኮረሸመ።

**ኮሽኮሼ** ስ ሲያኙት ለጥርስ የሚገራ እንደ ፍርንባ፥ … ያለና ኩርሽሜ የሆነ አጥንት።

**ኮሽኮሽ** ስ 1.ስስና አቅመቢስ የሆነ የአፍንጫ ወይም የሰርን አጥንት። 2.(ስድብ) ተልካሻ።

**ኮሽ**

**ኮሽታ** ስ ኮሽ የሚል አነስተኛ የድምፅ እንቅስቃሴ።

**ኮሽ አለ** ግ የደረቀ ቅጠል፥ ሳር፥ … በነፋስ ወይም በሌላ ሃይል ሲንቀሳቀስ የሚሰጠውን አይነት ድምፅ ሰጠ ወይም አሰማ።

**ኮሽ አይልም** ምንም አይነት ድምፅ የለም ወይም አይሰማም፤ ፀጥ ያለ ነው።

**ኮሽ ኮሽ አለ** ግ ተንኮሻኮሸ።

**ተንኮሻኮሸ** ግ የደረቀ ቅጠል፥ ሳር፥… በነፋስ ወይም በሌላ ሃይል ሲንቀሳቀስ የሚሰጠውን አይነት ድምፅ ሰጠ ወይም አሰማ።

**አንኮሻኮሸ** ግ በመንቀሳቀስ ወይም በሌላ ሁኔታ ኮሽ ኮሽ የሚል ድምፅ እንዲፈጠር አደረገ።

**ኮሻላ** "ኮሸለለ" ስር "ኮሸለል"ን ተመ.

**ኮሽም** ስ እሾህ ካለው የቁጥቋጦ አይነት የሚገኝ ፍሬው እንደ እንኮይ ያለ፥ ሲበስል ቢጫ የሚሆንና ሲበሉት በመጠኑ እንደመኮምጠጥ የሚል ፍሬ። ፍሬውን የሚያፈራው ተክልም ኮሽም ይባላል።

**ኮሽታ** "ኮሽ" ስር ተመ.

**ኮበለለ** ግ የነበረበትን ቦታ ትቶ ወደ ሌላ ቦታ ተደብቆ ወይም ተሸሽጎ ሄደ ወይም ጠፋ።

**አኮበለለ** ግ አስከድቶ ወሰደ።

**አስኮበለለ** ዝ.ከ.

**ኮበሌ** ስ ወጣት፥ ልጅ እግር፥ ጎረምሳ።

***ኮበኮበ**

**ኩብ** ስ 1.በኳስ ቅርፅ የተጠነጠነ ወይም የተጠቀለለ ፈትል፥ ክር፥…። 2. የ"ኩብኩባ"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

**ኩብኩባ** ስ 1.በአንበጣ የእድገት ኡደት ውስጥ ክንፍ አውጥቶ ከመብረሩ በፊት ያለው የግልገሉ አንበጣ መጠሪያ። 2.(ዘይ.) ወጣት።

**አኮበኮበ** ግ 1.ተንደረደረ፥ አቆበቆበ (ወደሰማይ ለመብረር)።2. ተዘጋጀ፥ ቃጣ፥ ተነሳ፥…(አንድን

ነገር ለማድረግ)።

**ማኮብኮቢያ** ስ በተለይ ለአውሮፕላን መነሻና ማረፊያ እንዲሆን በተዘጋጀ ቦታ ላይ አውሮፕላን መሬት እስከሚለቅ እንዲሁም ለማረፍ ሲፈልግ መሬት ነክቶ ወደመቆሚያው እስከሚደርስ በጎማዎቹ አማካይነት የሚንደረደርበት ረዥምና ሰፊ የሆነ መንገድ።

**ኮባ** ስ የእንሰት ተክል። ቅጠሉም ኮባ ይባላል።

**ኮብሽ** ስ ከጫማ እስከ ጉልበት ያለውን የእግር ክፍል የሚያድበለብል ወይም የሚያሳብጥ በሽታ፤ ከማን አንሼ።

**ኮብሻም** ቅ ኮብሽ የያዘው።

**ኮተተ**

**ኮተት አለ** ግ ተንኳተተ።

**ኮተት አደረገ** ግ አንኳተተ።

**ተንኳተተ** ግ 1.ቀስ እያለ ሄደ ወይም ተጓዘ። 2.ዳሀ፥ ተንፏቀቀ።

**አንኳተተ** ግ 1.ቀስ እያለ አጓዘ ወይም ወሰደ። 2.አንፏቀቀ።

**ኮተቴ** ስ ጥቁር የአደንጓሬ አይነት።


**ኮተት** ስ 1.ቅራቅንቦ፥ ግሳንግስ። 2.ብዙና የተለያዩ እቃዎች ባንድነት የሚጠሩበት ስም። 3.እድፍ፥ ጭቅቅት።

**ኮተኮተ** ግ አረምን ለማስወገድና አትክልቱን የለሰለሰ አፈር ለማስታቀፍ በአትክልቱ ዙሪያ ያለውን መሬት ቆፈር ቆፈር አደረገ።

**መኮትኮቻ** ስ ለኩትኳቶ ስራ የሚያገለግል መሳሪያ፥ አነስተኛ ዶማ፥...።

**ኩትኮታ** ስ ኩትኳቶ።

**ኩትኳቶ** ስ የመኮትኮት ተግባር።


መኮትኮቻ

**ኮትኳች** ቅአትክልቶችን በማረምና በመ ኮትኮት የሚንከባከብ (ሰው)።

***ኮተኮተ**

**ኩትኩት አለ** ግ አኮተኮተ።

**አኮተኮተ** ግ 1.ሱክ ሱክ እያለ ቶሎ ቶሎ ተራመደ። 2.አቆበቆበ፥ ለመጀመር ተዘጋጀ። 3.አሳበቀ፥ አዋሸከ፤ ነገር ሰራ።

**አኮትኳች** ቅ አሳባቂ፥ አዋሻኪ፤ ነገር ሰሪ።

**ኮታ** ስ ለተወሰነ ወገን፥ ክፍል፥ ሰው፥... የሚሰጥ የተወሰነ የመጠን ወይም የቁጥር ድርሻ (በተለይ በአንድ የተወሰነ ጊዜና ሁኔታ ሊመረቱ ወይም ሊሸጡ የሚገባቸው እቃዎች ብዛት ወይም ለአንድ የተወሰነ ነገር የሚያስፈልጉ የሰዎች ወይም የሌላ ነገር ቁጥር፥ መጠን)።

**ኮቴ** ስ 1. መሬት የሚረግጠው የእግር ክፍል። 2. ከብት ወይም ሰው የረገጠው ለስላሳ ቦታ ላይ የሚቀረው ምልክት።

**ኮት** ስ በሸሚዝ ወይም በሹራብ ላይ የሚለበስ፥ ባለእጅጌ የሆነና ከፊት ለፊቱ ክፍት ሆኖ ቁልፍ ያለው።

**ኮትቻ** ስ መረሬ፤ ጥቁር አፈር፤ ዋልካ መሬት።

**ኮትኳች** "ኮተኮተ" ስር ተመ.

**ኮቸመ** ግ በጥንቃቄ ልቅምና ጥብቅ አድርጎ ሰራ (ብዙ ጊዜ የእጅ ስራን)።

**ኮቸረ** "ከቸረ"ን ተመ.

**ኮቸሮ** ዝ.ከ.

***ኮነሰነሰ**

**ኩንስንስ** ቅ ዝይን፥ ዘናጭ፥ ሽሙንሙን ሽቅርቅር (በአለባበስ፥ በአካላዊ አኳኋን)።

**ኩንስንስ አለ** ግ ተኩነሰነሰ።

**ተኩነሰነሰ** ግ ተዘየነ፥ ዘነጠ፥ ተሽሞነሞነ፥ ተሽቀረቀረ (በአለባበስ፥ በአካላዊ አኳኋን)።

**አኩነሰነሰ** ግ ዘየነ፥ አሽሞነሞነ፥ አሽቀረቀረ (በአለባበስ፥ በአካላዊ አኳኋን)።

***ኮነተረ**

**ተሽኮነተረ** ግ አጌጠ፥ ተዋበ፥ አማረ።

**ተሽኮንታሪ** ቅ ሽቅርቅር።

**አሽኮነተረ** ግ አስጌጠ፥ አስዋበ፥ አሳመረ።

**ኮነተሸ** ግ በጣም አሳጠሮ ቆረጠ።

**ኩንትሽ** ቅ በጣም አጭር።

**ኩንትሽ አለ** ግ ተኮነተሸ።

**ኩንትሽ አደረገ** ግ ኮነተሸ።

**ተኮነተሸ** ግ በጣም አጠረ።

**ኮነነ** ግ 1.ቀጣ (ነፍስን)። 2.ወነጀለ፥ ጥፋተኛ አድርጎ አቀረበ።

**ኩነኔ** ስ የነፍስ ቅጣት (ከሞት በሂላ በገሃነም ይደርሳል ተብሉ የሚታመንበት)።

**ኩነኔ ገባ** የሚያስኮንን ስራ ሰራ።

**ኮናኝ** ቅ የሚኮንን፥ ፍርድ የሚሰጥ።

**አስኮናኝ** ቅ 1.የሚያስኮንን። 2.አቅመ ቢስ፥ ደካማ፥ ምስኪን (ለኩነኔ ምክንያት የሚሆን)።

***ኮናተረ**

**ኮንትራት** ስ 1.የቁርጥ ስራ ውል ወይም ስምምነት። 2.ለተወሰነ ጊዜ የተወሰነ ግልጋሎት ለመስጠት ወይም ለማግኘት የሚያስችል ውል ወይም ስምምነት።

**ኮንትራት ወሰደ** የስራ ወይም የሌላ ኮንትራት ውል ተዋዋለ፥ ተቀበለ ።

**የኮንትራት ሰራተኛ** ስ ለተወሰነ ጊዜ እንዲያገለግል የተቀጠረ ሰራተኛ።

**ተኮናተረ** ግ 1.የቁርጥ ስራ ለመስራት ወይም ለማሰራት ተዋዋለ ወይም ተስማማ። 2.ለተወሰነ ጊዜ የተወሰነ ግልጋሎት ለመስጠት ወይም ለማግኘት ተዋዋለ ወይም ተስማማ። 3.ገንዘብ እየተከፈለበት አገልግሎት እንዲሰጥ ተደረገ (መኪና፥ ቤት፥...)።

**ተኮናታሪ** ቅ የስራ ተቋራጭ፤ የተወሰነ ስራ በተወሰነ ክፍያ የሚሰራ። 2.በተወሰነ ክፍያ የተወሰነ ግልጋሎት (የቤት፥ የመኪና፥...) ለማግኘት ከባለ ሃብቱ ጋር የተዋዋለ።

**አኮናተረ** ግ የተወሰነ ክፍያ ለማግኘት አንድን ነገር (ለምሳሌ ቤትን) ለተወሰነ ጊዜ ለተገልጋይ (ለተኮናታሪ) ሰጠ።

**አኮናታሪ** ቅ አንድን ስራ ወይም መገልገያ (ለምሳሌ ቤትን) ለተኮናታሪ የሰጠ ወይም የሚሰጥ (ሰው)።

**ኮናኝ "ኮነነ"** ስር ተመ.

**ኮንበር "ኮምበር"**ን ተመ.

**ኮንትራክተር** ስ የስራ ተቋራጭ።

**ኮንትሮል** ስ ተቆጣጣሪ።

**ኮንትሮባንድ** ስ ለመንግስት ቀረጥ ሳይከፈልበት በድብቅ የሚካሄድ ህገ ወጥ ንግድ።

**ኮንዶም** ስ ያልተፈለገ እርግዝናንና ልዩ ልዩ የአባለዘር በሽታዎችን ለመከላከል ሲባል ወሲብ በሚደረግበት ወቅት በወንዱ አባለዘር ላይ የሚጠለቅ ከላስቲክ መሰል ነገር የሚሰራ መከላከያ።

**ኮንግረስ** ስ ጉባኤ።

**ኮንጎ [ጫማ]** ስ የላስቲክ ጫማ።

**ኮከብ** (ብ.ቁ.**ከዋክብት**) ስ 1.በምሽት በሰማይ ላይ ብልጭ ብልጭ እያሉ ከሚታዩና ብርሃን ካላቸው አካላት አንዱ። 2.የአንድን ሰው ባህርይ ይወክላል፥ የወደፊት እድሉንም ይወስናል ተብሎ የሚታመንበት የኮከቡ ስምና ባህርይ። 3.በኮከብ ቅርፅ የተሰራ የወታደራዊ ማእረግ ምልክት። 4.እውቅ፥ ተደናቂ፥ ጎበዝ። *ኮከብ ተዋናይ*።

**ኮከባቸው ገጠመ** ተስማሙ፥ ተጓዳኑ።

**ኮከብ ቆጠረ** ሰዎች በሚወለዱበት ቀንና ሲወለዱ በሚኖሩት ከዋክብት መካከል ያለውን ግንኙነት ወይም የሰዎችን ስምና የእናቶቻቸውን የመጠሪያ ስም ፊደሎች ቁጥር ከልዩ ልዩ ከዋክብት ጋር በማገናዘብ ስለሰዎቹ ባህርይና የወደፊት እድል በቅድሚያ ተናገረ፥ ጠነቆለ፤ መፅሃፍ ገለጠ።

**ኮከብ ቆጠራ** ስ ኮከብን በመቁጠር ስለሰዎችና ስለተለያዩ ሁኔታዎች የሚደረግ ትንበያ(ለትንበያው የሚገለገሉባቸው ከዋክብቶች አቅራብ፥ቀውስ፥ ጀደይ፥ ደለው፥ ሁት፥ ሃመል፥ ተውር፥ጀውዛ፥ሸርጣን፥ አሰድ፥ ስንቡላ የተባሉት ናቸው) ።

**ኮከብ ቆጣሪ** ስ ኮከብ በመቁጠር የሚጠነቁል፤ መፅሃፍ ገላጭ።

**ኮከብ ጫኝ** የኮከብ ምልክት ያለው ወታደራዊ ሹመት አገኘ።

**ኮከበ ነጠላ** ቅ እድለ ቢስ።

**ኮከን (ኮኮኔ)** ስ 1.የአውራ ዶሮ ቁንጮ። 2.ኩኩሉ ማለት የጀመረ ዶሮ።

**ኮክ** ስ ሞላል ያለ ክብ ቅርፅ ያለው፥ የቆዳው ቀለም አረንጓዴ መሰል ቢጫ ሆኖ በሚበላውና በለስላሳው ክፍል ውስጥ የተሸፈነ ጠንካራና ሻካራ ፍሬ በውስጡ የሚገኝ የፍራፍሬ አይነት፡፡ ፍሬውን የሚያፈራው ተክልም ኮክ ይባላል።

**ኮክቴል** ስ መጠጥና ቀላል ምግብ የሚገኝበትና ሰዎች ቆመው የሚጋበዙበት የግብዣ አይነት።

**ኮኮ "እንኮኮ"**ን ተመ.

**ኮኮኔ "ኮከን"**ን ተመ.

**ኮየሰ** ግ 1.ኩይሳ ሰራ። 2.ቆለለ፥ ከመረ (አፈርን)።

**ኩይሳ** ስ አፈር በመቆለል ምስጦች ለራሳቸው የሚሰሩት መኖሪያ ቤት።

**ኮደኮደ** ግ እግር ተወርች አሰረ።

**ኮደደ "ሆደደ[1]"**ን ተመ.

**ኮዳ** ስ ከፕላስቲክ ወይም ከኒኬል፥... የሚሰራና ማንገቻ ያለው የመንገደኞች ውሃ መያዣ።

**ኮድ** ስ 1.ምስጢራዊ የሆነ መልእክትን ለማስተላለፍ ወይም ረዥም መልእክትን አሳጥሮ ለማቅረብ የሚያገለግል ቋንቋ ወይም ምልክት። 2. መለያ፥ ልዩ ምልክት(ለአንድ ነገር፥ እቃ፥... የተሰጠ ወይም የሚሰጥ)።,

**ኮፈሰ** ግ 1.በሚዶ ነቀሰ ወይም አበጠረ (ፀጉርን)። 2.በከንቱ ውዳሴ ካበ፥ አሞገሰ፥ አኩራራ።

**ኩፍስ** ቅ 1.በደንብ ተስተካክሎ የተበጠረ ጎፈሬ። 2.ጥሩ ልብስ በመልበስ የተሽሞነሞነ ወይም የተዋበ። 3.ጅንን።

**ተኮፈሰ** ግ 1.ጥሩ ልብስ በመልበስ ተሽሞነሞነ፥ ተዋበ። 2.ተጀነነ። 3.አኮረፈ።

**ኮፈተረ** ግ በአንድነት ጠቀለለ፥ ጠመዘዘ (ሰበዝን)።

***ኮፈነነ**

**ኮፍናና** ቅ ጅንን።

**ተኮፋነነ** ግ ተኩራራ፥ ታጀረ፥ ተዘባነነ።

**ኮፈን** ስ የመኪናውን ሞተር ከዝናብና ከአቧራ የሚከላከል የሞተር ክዳን።

***ኮፈኮፈ**

**ኮፈኮፍ (ኮፍኳፋ)** ቅ 1.ልክክ የማይል፥ የሚንከረፈፍ (ልብስ)፡፡ 2.(ስድብ) ቁጡ፡፡

**ኩፍኩፍ አለ** ግ ተንከፈከፈ፡፡

**ተንከፈከፈ** ግ 1.ጎረበ፥ ቀረበበ፥ ተነሳ፥ ሊላጥ ቀረበ (የሰውነት ቆዳ፥...)፡፡ 2.አከረፈ፡፡

**አኮፈኮፈ** ግ ጎረበ፥ ቀረበበ፥ ተነሳ፥ ሊላጥ ቀረበ (የሰውነት ቆዳ፥...)፡፡

**ኮፈፈ**

**ኩፍታ**[1] ስ 1.ኩፍ ማለት (ሊጥ)፡፡ 2.ኩርፍታ፡፡

**ኩፍታ**[2] ስ ሊጡ ኩፍ ካለ በኋላ የተጋገረ ቂጣ (ብዙውን ጊዜ የሽምብራ)፡፡

**ኮፈፍተኛ (ኮፈፍታ)** ስ አፍለኛ፤ በጣም ሳይቦካ የተጋገረ እንጀራ ወይም ቂጣ፡፡

**ኩፍ (ኩፍፍ) አለ** ግ 1.ተነሳ፤ ብድግ አለ፤ ቦካ (ሊጥ)፡፡ 2.አከረፈ፡፡

**ኮፈፍ አለ** ግ ልስቅ ወይም ልጥፍ ሳይል ቀረ፤ ወደላይ ጉብ ብሎ ታየ፡፡

**ኮፍናና** "*ኮፈነነ" ስር ተመ.

**ኮፍኳፋ** "*ኮፈኮፈ" ስር "**ኮፈኮፍ**"ን ተመ.

**ኮፒ** ስ ቅጂ፥ ግልባጭ (የስእል፥ የፅሁፍ፥...)፡፡

**ኳ**[1] የ"**ከ**" ፊደል ፍንፅቅ ዘር፡፡

**ኳ**[2]

**ኳ አለ** ግ እንደ እንጨት፥ ድንጋይ፥ ሳህን፥... ያለ ነገር ሲወድቅ ወይም ሲጋጭ የሚሰጠውን አይነት ድምፅ ሰጠ፡፡

**ኳ አደረገ** ግ እንደ እንጨት፥ ድንጋይ፥ ሳህን፥... ያለ ነገር ሲወድቅ ወይም ሲጋጭ የሚሰጠውን አይነት ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ፤ ኳ አደረገ፡፡

**ኳኳታ (ኳኳቴ)** ስ ድግግሞሽ ያለው የሚንኳኳ ድምፅ፡፡

**ኳ ኳ አለ** ግ ተንኳኳ፡፡

**ኳ ኳ አደረገ** ግ አንኳኳ፡፡

**ተንኳኳ** ግ 1.ኳ የሚል ድምፅ በተደጋጋሚ ሰጠ፡፡ 2.ተመታ፥ ተቋረቋረ (በር፥...)፡፡

**አንኳኳ** ግ 1.በተደጋጋሚ ኳ የሚል ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ፡፡ 2.ቆረቆረ፥ መታ (በርን፥...)፡፡

**ኳ**[3]

**ኳ አለ** ግ በጣም ደረቀ፡፡

**ኳ አደረገ** ግ በጣም አደረቀ፡፡

**ኳ**[4]

**ኳ አለ** ግ ወለል ወይም ፍንትው አለ፥ ጠራ፡፡ *ሰማዩ ኳ ብሎ ጠርቷል*፡፡

**ኳለ** ግ 1.የአይንን ቅንድብ በኩል ቀባ፥አስጌጠ፡፡ 2.ቀባ፥ ፃፈ (በቀለም)፡፡

**ኩል** ስ በጹቀት ወይም በእርሳስ መልክ ተዘጋጅቶ ሴቶች የአይናቸውን ቅንድብ በመኳል የሚያስጌጡበት ጥቁር የማእድን አይነት፡፡

**ተኳለ** ግ የአይን ቅንድብ በኩል ተጌጠ፡፡

**የተኳለ የተዳረ** በስርአት ተድሮ ለወግ ለማእረግ የበቃ (ልጅ)፡፡

**ተኳኳለ** ግ ተጊያጊያጠ፥ ተሽሞነሞነ፡፡

***ኳስ**

**ኳስ** ስ ለልዩ ልዩ የጨዋታ አይነቶች እንዲያገለግል በተለያየ መጠን ከጨርቅ ወይም ከቆዳ ወይም ከላስቲክ ወይም ከሌላ ነገር የሚሰራ ድብልብል ቅርፅ ያለውና ውስጡ ባዶ ወይም ድፍን የሆነ መጫወቻ፡፡*የእጅ ኳስ/የጠረጴዛ ኳስ*፡

**ኳስ አበደች** ኳስ ወደሰማይ ጎነች፡፡

**ኳስ ሜዳ** ስ ኳስ ጨዋታ የሚደረግበት ቦታ ወይም ሜዳ(ብዙውን ጊዜ የእግር ኳስ) ፡፡

**ተኳሰ** ግ እንደ ኳስ ሆነ፥ ተድበለበለ፡፡

**አኳሰ** ግ 1.እንደ ኳስ አደረገ፥ አድበለበለ፡፡ 2.ኳስ አነጠረ፡፡

**ኳሸ**[1] ግ 1.ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ በሽንገላ አወደሰ፥ ካበ፥ አሞካሸ፡፡ 2.ዋሸ፥ ጉራ ነዛ፡፡ 3.አጋነነ፤ ትንሿን እውነት በትልቅ ውሸት አጎልምሶና አጋኖ ተናገረ፡፡ 4.ያመሰገነ መስሎ ተሳደበ፥ ተረበ፡፡

**ኩሸት** ስ 1.ጉራ፡፡ 2.ውሸት፡፡ 3.ትንሿን እውነት በትልቅ ውሸት አጎልምሶና አጋኖ ለመናገር የሚያስችል የቅኔ መንገድ፡፡

**ኩሸተኛ** ቅ 1.ያመሰገነ መስሎ የሚሳደብ፥ ተራቢ፡፡ 2.ዋሾ፡፡ 3.ጉረኛ፡፡ 4.ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ በሽንገላ የሚያወድስ፥ የሚክብ፥ የሚያሞካሽ፡፡

**አኳሸ** ግ 1.ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ በሽንገላ አወደሰ፥ ካበ፥ አሞካሸ፡፡ 2.ደለለ፥ አሞኘ፥ እንዲጎመጅ ወይም እንዲጓጓ አደረገ (በውሸት)፡፡

**ኳሸ**[2] ግ ረበሸ፥ አስቸገረ (ህፃን)፡፡

**ኳተ** ግ ቆፈረ፥ ማሰ፥ ፋረ፡፡

**ኳተነ** ግ ማሰነ፥ ደከመ፥ ለፋ (በእግር በመሄድ)፡፡

**ኳንክ** ስ 1.ኮከኔ፡፡ 2.በአውራ ዶሮ አንገት ላይ የሚገኘና ኮከኔ የሚመስል እንጥልጥል፡፡

**ኳንኳ** ስ ታንኳ፡፡

**ኳክ**

**ኳክ አለ** ግ ጮሀ፥ ድምፅ አሰማ (ዶሮ)፡፡

**ኳድሮ** ስ የመኪናን ሞተር ለማስነሳት የሚረዳ የመኪና እቃ፡፡

# ወ

**ወ** ከ“**ከ**” ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሂ)::

**ወህኒ [ቤት]** ስ እስር ቤት÷ ከርቸሌ::

**ወህኒ ወረደ** ታሰረ ወይም እስር ቤት ገባ::

**ወለሳ** ቅ ከዳ ወይም ሰፈፍ÷... የሌለበት ንፁህ (ማር) ::

**ወለሌ** “**ወለል**[1]” ስር ተመ.

**ወለል** ስ 1. በአፈር የተደለደለ ወይም በጣውላ ወይም በስሚንቶ÷...የተሸፈነ የቤት ውስጥ የመሬት ገፅታ:: *ወንበር የለም፤ ወለሉ ላይ ተቀመጥ* :: 2.ውሃ ልኩ የተስተካከለ÷ ተጋደላ ያልሆነ::

**ወለል**[1]

**ወለሌ** ስ የስቃይ ወይም የሃዘን ዋይታ÷ ጩሀት ::

**ወለል ያድርገኝ** እኔ ልዘን ወይም ልንከራተት ለማለትና ሃዘንን ለመግለፅ የሚነገር አባባል ::

**ወለል**[2]

**ወለል አለ** ግ 1. ብርሃን ሆነ፤ ግልፅ አለ:: 2. ጠራ÷ ፀዳ:: 3. በሰፊው ተከፈተ (በር)::

**ወለል አደረገ** ግ 1. ግልፅ አደረገ÷ አጠራ፤ አፀዳ :: 2. በሰፊው ከፈተ (በርን)::

***ወለመ**

**ወለምታ** ስ ከትክክለኛ ቦታው በመዛወሩ ወይም በመዛነፉ÷ እጥፍ በማለቱ÷... የሚሰማ የስር ላይ ወይም የአጥንት መጋጠሚያ ህመም ::

**ወለም አለ** ግ ከትክክለኛ ቦታው በመዛወሩ ወይም በመዛነፉ ህመም ተሰማ (የአጥንት÷ የስር)::

**ወለም ዘለም አለ** ግ ስራ ፈትቶ ወዲያ ወዲህ አለ÷ አውደለደለ÷ አደሸደሸ ::

***ወለመመ**

**ወልማማ** ቅ (ስድብ) ወልጋዳ÷ ጠማማ÷ ሸፋፋ ::

**ተወላመመ** ግ ተዛወረ÷ ተዛነፈ÷ ተጣመመ÷ ተወላገደ ::

**አወላመመ** ግ አዛወረ÷ አዛነፈ÷ አጣመመ÷ አወላገደ ::

***ወለመጠ**

**ወልማጣ** ቅ ( ስድብ) 1. ለማጣ፤ ቀጥተኛ የሆነ አካላዊ አቋም የሌለው:: 2. ጠንክር ብሎ መስራት የማይወድ÷ አልምጥ÷ ዋልጌ:: 3. የተናገረውን ቃል የማያከብር፤ ወላዋይ ::

**ውልምጥምጥ** ቅ ልምጥምጥ፤ አቋሙ ወይም አካላዊ አፈጣጠሩ ቀጥተኛ ያልሆነ ::

**ተወላመጠ** ግ ስራ ፈትቶ ወዲያ ወዲህ አለ÷ ተዘዋወረ ::

**ወለምታ** “***ወለመ**” ስር ተመ.

**ወለሰ** ግ ሳያቋርጥ ቀስ እያለ ለብዙ ሰአት ዘነመ ::

**ወሊስ** ስ ሳያቋርጥ ቀስ እያለ ለብዙ ሰአት የሚጥል ዝናብ ::

**ወለሽ** ስ ውሃ የተኛበት ለም መሬት ::

**ወለቀ** ግ 1. ተነቀለ:: *ጥርሱ ወለቀ*: 2. ወጣ÷ ተነሳ÷ ተገፈፈ:: *ልብሱ ወለቀ*:3. ተዛባ÷ ተዛነፈ÷ ቦታውን ለቀቀ:: *ክንዱ ወለቀ*::

**ወላቃ** ቅ 1. ሙሉ ያልሆነ÷ የወለቀለት:: 2. ጥርሱ የተነቀለ፤ ጥርሰ ወላቃ እየተባለም ይጠራል::

**ውልቃት** ስ የአጥንት መጋጠሚያ ከቦታው መዛባት::

**ውልቅ አለ** ግ 1. ሹልክ ብሎ ወጣ ወይም ሄደ:: 2. ሙልጭ ብሎ ወጣ÷ ለቀቀ ( እድፍ)::

**ወላለቀ** ግ 1. ተንቃቀለ÷ ተለያየ÷ ተበታተነ÷ ተፈታታ:: 2. ደከመ÷ ዛለ÷ ጣመነ:: *ብዙ ከመሄድ የተነሳ ሰውነቱ ወላለቀ*::

**ውልቅልቅ** ቅ የወላለቀ÷ የፈራረሰ÷ የተንቃቀለ::

**ውልቅልቁ ወጣ** 1. ተንቃቀለ÷ ተበታተነ÷ ተፈታታ:: 2. በጣም ደከመ÷ ዛለ::

**አወለቀ** ግ 1. አነሳ÷ አወጣ÷ ገፈፈ (ልብሱን÷ ጫማውን÷...ከላዩ ላይ):: 2. ነቀለ÷ አወጣ:: 3. (ዘይ.) መታ÷ ደበደበ:: *በቦክስ አወለቀው* ::

**አወላለቀ** ግ 1. አወለቀ ( ልብስን÷ ጫማን÷... ):: 2. በታተነ÷ ፈታታ÷ ለያየ :: *የመኪናውን ብሎኖች አወላለቀ* ::

**አውለቀለቀ** ግ አደከመ÷ አዛለ (ሰውነትን)::

***ወለበ**

**ወላባ** ቅ ቀትረ ቀሊል÷ ነጠላ÷ ሾላካ÷ ጥላቢስ::

**ውልብ አለ** ግ ታይቶ ጠፋ÷ ከመቅፅበት ሽው ብሎ አለፈ ::

**ወለብላባ** ቅ ለፍላፊ÷ ምላሰኛ ::

**ውልብልብ** ቅ የሚውለበለብ÷ የሚርገበገብ::

**ውልብልቢት** ስ 1. የከባ÷ የዘንባባ÷ የተምር ዛፍ ቀንበጥ ወይም ጫፍ :: 2. የእሳት ላንቃ:: 3.

ክብደት በሚዛን ላይ ሲወጣ መጠኑን እስከምትጠቁም ድረስ ወዲያ ወዲህ የምትዋዥቅ ምልክት፤ የሚዛን ምላስ ። 4. ብዙውን ጊዜ በንፋስ የሚውለበለብ፣ የሚሽከረከር ማንኛውም ነገር (ለምሳሌ የአውሮፕላን ውልብልቢት)።

**ተውለበለበ** ግ 1. ተወዛወዘ፣ ተንቃነቀ፣ ተርገበገበ ( ለምሳሌ ባንዲራ) ። 2. ለፈለፈ ።

**አውለበለበ** ግ ወዘወዘ፣ ነቀነቀ፣ አርገበገበ።

**ወለባ** ስ በድሮ ጊዜ ፀጉር ላይ የሚሰካና ከብር ወይም ከወርቅ፣... የሚሰራ የጌጥ አይነት።

**ወለብላባ** "*ወለበ" ስር ተመ.

**ወለከፈ** ግ አደናቀፈ፣ ሰነከለ ።

**ወልካፋ** ቅ (ስድብ) ደንቃፋ፣ ሰንካላ፣ ሽፋፋ፣ አካሄድ የማይችል ።

**ውልክፍክፍ** ቅ ድንቅፍቅፍ፣ ስንክልክል፣ ሽፋፋ።

**ተወለካከፈ** ግ ተደነቃቀፈ፣ ተሰነካከለ ።

**ተወላከፈ** ግ 1. ተደናቀፈ፣ ተሰናከለ። 2. ተንሻፈፈ፣ ተጣመመ።

**አወለካከፈ** ግ አደነቃቀፈ፣ አሰናከለ።

**አወላከፈ** ግ 1. አደናቀፈ፣ አሰናከለ። 2. አንሻፈፈ፣ አጣመመ ።

**ወለወለ** ግ 1. ጠረገ፣ አሰሰ፣ አበሰ፣ አፀዳ፣ አጠራ ። 2. ደጋግሞ በጥፊ መታ። *ልጁን በጥፊ ወለወለው።*

**መወልወያ** ስ ማበሻ፣ መጠራረጊያ፣ ማሰሻ፣ ማፅጃ (ጨርቅ ወይም ሌላ ነገር)።

**ውልውል** ቅ የተጠረገ፣ የፀዳ፣ የተወለወለ።

**ተወለወለ** ግ ተጠረገ፣ ታሰሰ፣ ታበሰ፣ ፀዳ።

**አወለወለ** ግ ፊቱ አማረበት ወይም ወዛ ።

**ወለወልዳ** ቅ አሳባቂ፣ ወሽካታ ።

**ወለደ** ግ 1. ልጅ አገኘ፣ ዘር ተካ፣ ረባ። 2. በዛ፣ ተባዛ፣ በረከተ፣... ። 3. አተረፈ፣ አራጣ አስገኘ (ገንዘብ፣...) ። 4. እንደራሱ ልጅ አደረገ (ክርስትና በማንሳት፣ ጡት በማጥባት፣...)። 5. እንደማሽላ፣ ገብስ፣... ያሉ እህሎች ከአደበደቡ በኋላ ፍሬ የሚይዘው ጫፋቸው ወጣ፣ ዘረዘረ። 6. አዳነ፣ አወጣ፣ አተረፈ (ከችግር)።

**ወለደች** ተገላገለች ፣ ልጅ አገኘች (እርጉዝ የነበረች እንስት)።

**ውለዱ ክበዱ** (ምር.) ልጅ አግኙ፣ ክበሩ።

**ውለድ(ውለዳት)** ከየትም ብለህ አምጣ (አምጣት)።

**ወለድ** ስ የገንዘብ ትርፍ፣ አራጣ (በማበደር የሚገኝ ወይም በመበደር የሚከፈል) ።

**ወለድ አግድ** ስ አበዳሪዎች በገንዘብ ትርፍ ወይም አራጣ ፋንታ የተበዳሪን ቤት፣ መሬት፣... በመያዝ የሚጠቀሙበት የብድር ውል አይነት ።

**ወሊድ** ስ በመውለድ ላይ መሆን። *በወሊድ ሞተች ።*

**ወላዲተ አምላክ** ስ ማርያም፣ የክርስቶስ እናት።

**ወላድ** ቅ 1. የወለደች፣ የምትወልድ፣ መካን ያልሆነች። 2. ብዙ የምትወልድ ወይም የወለደች። ስ 3. እናት። *ወላድ በድባብ ትሂድ።*

**ወላጅ** ስ እናት ወይም አባት። *ወላጅ አባቱ ሌላ ነው፤ ይህኛው አሳዳጊ ነው።*

**ውላጅ** ቅ ከቤት አገልጋዮች የተወለደ (ልጅ)።

**ውልድ ቃል** ስ በቋንቋ የቃላት አመሰራረት ህግ መሰረት ቀደም ሲል በነበረ ቃል ላይ ተመስርቶ የሚፈጠር ወይም የተፈጠረ ሌላ ቃል።

**ልደታ** በፊደል ተራው ተመ.

**ልደት** በፊደል ተራው ተመ.

**ልጅ** በፊደል ተራው ተመ.

**ተወለደ** ግ 1. ልጁ ከማህፀን ወጣ። 2. ከተወሰነ ዘር፣ ሰው፣ ቤት፣... ተገኘ። 3. መጣ፣ ተገኘ፣ ታየ። *አዲስ ነገር ተወለደ።*

**እንደገና ተወለደ** ደርሶበት ከነበረው ከፍተኛ ችግር፣ ስቃይ ዳነ ወይም አመለጠ።

**ተወላጅ** ቅ ወገን፣ ዘር፣ ቤተሰብ፣ ዘመድ።

**ትውልድ** ስ 1. በአንድ ዘመን፣ ወቅት ያለ ህዝብ። 2. የተወለዱበት ቦታ ወይም ዘር ።

**ተዋለደ** ግ 1. ተራባ፣ ተባዛ። 2. የአንዱ ወገን የሌላውን ወገን አግብቶ በመውለድ ተዛመደ።

**አዋለደ** ግ 1. ወላድን በወሊድ ጊዜ ረዳ፣ አገዘ። 2. አንዱ ከሌላው እንዲወልድ አደረገ፣ አራባ፣ አባዛ።

**ማዋለጃ ክፍል** ስ ሴቶች ምጥ በያዛቸው ጊዜ በሃኪም እየታገዙ የሚወልዱበት ክፍል ።

**አዋላጅ** ቅ የሚያዋልድ፣ ወላድን በምጥ ጊዜ እንድትወልድ የሚረዳ ( ሃኪም፣ ባለሙያ) ።

**ወለድ**[1] "ወለደ" ስር ተመ

**ወለድ**[2] ስ ከካርታ መጫወቻዎች አንዱ፣ ከአስር ቁጥር ካርታ ቀጥሎ የሚገኝ ወይም የሚከተል ካርታ።

**ወለገመ** ግ ጠመመ፣ ወለገደ።

**ወልጋማ** ቅ ጠማማ፣ ወልጋዳ።

**ውልግምት** ቅ ከፉ፣ ጠማማ፣ ቅንነት የሌለው።

**ተወላገመ** ግ ተጣመመ፣ ተወላገደ።

**አወላገመ** ግ አጣመመ፥ አወላገደ::

**ወለገደ** ግ ጠመመ፥ ጎበጠ::

**ወልጋዳ** ቅ ጠማማ፥ ጎባጣ፥ ጠመዝማዛ የሆነ (እንጨት፥ እግር፥...)::

**ውልግድ** ቅ የጎበጠ፥ ጎባጣ::

**ውልግድግድ** ቅ ጉብጥብጥ ያለ፥ ከብዙ ቦታ ላይ የተጣመመ::

**ተወለጋገደ** ግ ብዙ ቦታ ላይ ተወላገደ፥ በጣም ጥምም፥ ጥምዝዝ አለ::

**ተወላገደ** ግ ጠማማ ሆነ፥ ተጠማዘዘ::

**አወለጋገደ** ግ ብዙ ቦታ ላይ አወላገደ::

**አወላገደ** ግ አጣመመ፥ ጎባጣ፥ ጠምዛዛ አደረገ::

**ወለፈሰ** ግ የማይረባ፥ ልፍስፍስ፥ ቁም ነገር የሌለው ሆነ::

**ወልፋሳ** ቅ (ስድብ) የማይረባ፥ ልፍስፍስ፥ ልክስክስ፥ በቁም ነገር ስራ የማይጠመድ::

**ውልፍስፍስ** ዝ.ከ.

**ወለፈተ** ግ 1. ያልተጠየቀውን ቀባጠረ፥ ዘላበደ፥ በአነጋገሩ ቁም ነገር የሌለው ሆነ:: 2. ስራ ፈቶ ወዲያ ወዲህ አለ፥ በዘኔ ሆነ::

**ወልፋታ** ቅ (ስድብ) 1. ወልፋሳ፥ ቀባጣሪ:: 2. ስራ ፈት፥ ዟሪ ::

**ወለፌንድ** ቅ አመለ ጠማማ፥ ወልጋዳ::

**የወለፌንድ(የወለፌንዳ)** ከሰው የማይስማማ፥ የማይገጥም (ስራ):: *ስራዋ ሁሉ የወለፌንድ ነው::*

**ወሊስ** "ወለሰ" ስር ተመ.

**ወሊድ** "ወለደ" ስር ተመ.

**ወላ**

**ወላ ሸግላ አለ** ግ ወላወለ፥ የማያደርገውን አደርጋለሁ አለ ::

**ወላለቀ** "ወለቀ" ስር ተመ.

**ወላላ** ቅ አባኝ፥ ርህሩህ፥ ደግ፥ ገር ::

**ወላቃ** "ወለቀ" ስር ተመ.

**ወላባ** "ወለበ" ስር ተመ.

**ወላንሳ** ስ 1. ቀይ ከፋይ ወይም አረንጓዴ ባለወርቅ ዘርፍ ሆኖ በዙፋንና በመከዳ ላይ የሚዘረጋ፥ የሚነጠፍ ለስላሳ ምንጣፍ:: ቅ 2. ሰውን የማያስቀይም አመለ ለስላሳ፥ ጥሩ::

**ወላወለ** ግ 1. ተነቃነቀ፥ ተወዛወዘ፥ አልረጋ አለ:: 2. አመነታ፥ ሁለት ሃሳብ ሆነ፥ አልቆርጥ አለ::

**ወላዋይ** ቅ ሁለት ልብ፥ ተጠራጣሪ፥ የሚያመነታ፥ ቆራጥነት የሌለው ::

**አወላወለ** ግ አመነታ፥ ተጠራጠረ ::

**አወላዋይ** ቅ 1. አጠራጣሪ:: 2. የሚያመነታ፥ ወላዋይ ::

*ወላዳ

**ተወላዳ** ግ 1. ደፈረ፥ ተሰናዘረ (የጀግንነት ወይም ሌላ ስራ ለመስራት):: 2. ተዝናና፥ ተቀናጣ::

**አወላዳ** ግ 1. አሰናዘረ፥ ወዲያ ወዲህ ማለት አስቻለ:: 2. አዝናና፥ አቀናጣ ::

**ወላድ** "ወለደ" ስር ተመ.

**ወላጅ** ዝ.ከ.

**ወላፈን** ስ ከሩቅ የሚጋረፍ የእሳት ነበልባል ወይም ሳንቃ ::

**ወላፎ** ቅ ሸፋፋ ::

**ወል**

**በወል** መፋ. በጋራ:: *መሳሪያውን በወል መጠቀም እንችላለን ::*

**የወል** ቅ የጋራ ::

**የወል ስም** ስ ተመሳሳይ ነገሮች ባንድነት ወይም በጋራ የሚጠሩበት የስም አይነት ::

**ወልማማ** "ወለመመ" ስር ተመ.

**ወልማጣ** "*ወለመጠ" ስር ተመ.

**ወልካሳ(ውልክስ)** ቅ አንካሳ፥ ተልካሻ፥ የማይረባ ::

**ወልካፋ** "ወለከፈ" ስር ተመ.

**ወልይ** ስ ስለወደፊት ሁኔታዎች ይተነብያል የሚባል ሰው፤ ጠንቋይ ::

**ወልድ** ስ (ክር.) ቅድመ አለም ከአብ ያለ እናት፥ ድህረ አለም ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለ አባት የተወለደ የአብ የባህርይ ልጅ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ::

**ወልጋማ** "ወለገመ" ስር ተመ.

**ወልጋዳ** "ወለገደ" ስር ተመ.

**ወልጌ** "ዋልጌ" ን ተመ.

**ወልፋሳ** "ወለፈሰ" ስር ተመ.

**ወልፋታ** "ወለፈተ" ስር ተመ.

**ወልፍ** ስ ሱስ (የቡና፥የሲጋራ፥...)::

**ወመቴ** ስ ስራፈት፥ ዱርዬ፥ ወሮበላ::

**ወመኔ** ስ ዱርዬ፥ ወሮበላ ::

**ወማይ** ስ ቀለሙ ጠቆር ያለ አረንጓዴ ሃር የሚመስል ወፍ::

**ወረሃ** ቅ እግሮቹ እንደደጋን የጎበጡ::

**ወረረ** ግ 1. የሌሎችን ሃገር በወታደራዊ ሃይል ያዘ ወይም በቁጥጥር ስር አደረገ :: 2. አንድን አካባቢ በብዛት አለበሰ፥ ሸፈነ (ለምሳሌ አንበጣ፥ ጉንዳን):: 3. በሰውነት ወይም በገላ ላይ

የመዘግንን፥ የመሰቅጠጥ ስሜት ተሰማ:: 4. ዘረፈ፥ በዘበዘ፡ በረበረ::

**ወረር አደረገ** ግ በመጠኑ አሞቀ፥ ሞቅ አደረገ:: *ልብሱ ይለጣና ፀሃይ ወረር ያድርገው ::*

**ወሮበላ** ስ ዘራፊ፡ ዱርዬ፡ ዘርፎ ወይም ቀምቶ የሚበላ::

**ወረራ** ስ 1. ከበባ፥ ዘረፋ:: 2. የሌሎችን አገር ለመያዝ የሚደረግ ጦርነት ወይም ዘመቻ ::

**ወረርሽኝ** ስ ከአንዱ ወደ ሌላው እየተላለፈ በአንድ ጊዜ ብዙ ሰዎችን የሚያጠቃ እንደ ጉንፋን፥ ተስቦ፥... ያለ በሽታ ::

**ወራሪ** ስ አገርን በጦር ሃይል በቁጥጥር ስር ለማድረግ የሚወር ጠላት፡ ዘራፊ ::

**ተወረረ** ግ 1. ተያዘ፡ በቁጥጥር ስር ዋለ (አንድ ሃገር በሌላ ሃገር ጦር):: 2. ተሸፈነ፡ ለበሰ (አንድ ነገር፥አካባቢ):: 3. ተዘረፈ፡ ተበዘበዘ፡ ተበረበረ ::

**የተወረረ ይመስላል** ጭር ብሏል (አካባቢ)::

**ወረር** ስ የፊት አወራረድ፡ ገፅታ፥ መልክ::

**ወረርሽኝ "ወረረ"** ስር ተመ.

**ወረሰ** ግ 1. ከወላጁ፥ ከዘመዱ በኑዛዜ የተሰጠውን ንብረት ወሰደ፡ ተቀበለ፡ የንብረቱ ባለቤት ሆነ:: 2. የሌላውን ሰው ንብረት በቁጥጥር ስር አደረገ፡ ወሰደ (ያለካሳ፥ ያለክፍያ፥ ያለፈቃድ):: 3. ተቀበለ፡ ተማረ:: *ወጣቱ የአባቶቹን እውቀት ወርሷል::* 4. ያዘ፥ አለበሰ፡ አጠለቀ፥ ዋጠ (ለምሳሌ እከክ ሰውነትን፡ አረም መሬትን፡...) ::

**ወራሽ** ስ የሚተላለፍለትን ሃብት፡ ትምህርት፥... በባለቤትነት የሚቀበል፡ ተረካቢ ::

**ውርስ** ቅ የተወረሰ፡ በመውረስ የተገኘ (ንብረት፥ እውቀት፥ ባህል፥...)::

**ውርስ አደረገ** ግ ወረሰ፡ በእጅ አገባ፡ ያዘ (የሌላ ሰውን ንብረት)::

**ውርስ አደረገ** ግ አለበሰ፡ አጠለቀ፡ ያዘ፡ ከብቦ አደረገ (ለምሳሌ እከክ ሰውነትን፡ አረም መሬትን፡...)::

**ተወረሰ** ግ 1. ያለካሳ፥ ያለክፍያ ተወሰደ ወይም ተወሰደበት (ሃብቱ፥ ንብረቱ፥...):: 2. ለተከታይ ተላለፈ፥ ተሸጋገረ:: 3. በብዛት ተያዘ፡ ተከበበ፥ ተወረረ (በእከክ፥ በአረም፡ በቅማል፡...)::

**ተወራረሰ** ግ 1. በአንድ ወረቀት ላይ ያለ መረጃ በሌላ መዝገብ ላይ ሰፈረ፡ ተመዘገበ:: 2. ተመሳሰለ፥ አንድ አይነት ባህርይ ያዘ ::

**ተወራራሽ** ቅ አንዱ በሌላው ቦታ ሊተካ የሚችል፥ ተመሳሳይነት ወይም ተቀራራቢነት ያለው::

**አወረሰ** ግ ሰጠ፥ አስተላለፈ፥ አሸጋገረ (ሃብትን፥ እውቀትን፥...)::

**አወራረሰ** ግ በአንድ ወረቀት ላይ የሰፈረን መረጃ በሌላ መዝገብ ላይ አሰፈረ፥ መዘገበ ::

**ወረቀት** ስ 1. ከእንጨት፥ ከልጥ፥ ከገለባ፥ ከጨርቃ ጨርቅና ከመሳሰሉ ነገሮች በስሱ እየተሰራ ለፅህፈትና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል እቃ፡ የፅህፈት መሳሪያ:: 2. ደብዳቤ፥ ማዘዣ:: *ወንድሜ ወረቀት ፃፈልኝ ::*

**ወረቀት አቀረበ** ጥናታዊ ፅሁፍ አዘጋጅቶ በስብሰባ ላይ አነበበ፡ አሰማ ::

**የወረቀት መብሻ** ስ ወረቀትን ለመብሳት የሚያገለግል የፅህፈት መሳሪያ ::

**የወረቀት ማቀፊያ** ስ ብዙ ወረቀቶችን በአንድ ላይ አድርጎ ለመያዝ፡ ለማስቀመጥ የሚያገለግል የፅህፈት መሳሪያ ::

**የወረቀት ገንዘብ** ስ በወረቀት መልክ ታትሞ የተዘጋጀ ህጋዊ ገንዘብ::

**ወረበ**[1] ግ በዜማ ወረብን አሰማ፥ አለዘበ ::

**ወረብ** ስ ምንባባዊ ይዘቱ አጠር ያለ ሆኖ ካህናት ከፀናፅል፡ ከከበሮ ጋር እያቀናበሩ የሚያለዝቡት፥ የሚወርቡት፡ የሚያሸበሽቡት መንፈሳዊ ዜማ ::

**ወረበ**[2] ግ የካፊያ አይነት ዝናብ ጥሎ በመጠኑ መሬትን አረጠበ ::

**ውርባ** ስ ሌሊት መሬትን አርጥቦ የሚገኝ መጠነኛ የካፊያ አይነት፡ ጤዛ፡ ውርጭ፡ ርጥበት::

**ወረብ "ወረበ[1]"** ስር ተመ.

**ወረተኛ "ወረት[2]"** ስር ተመ.

**ወረታ "ወሮታ"** ን ተመ.

**ወረት**[1] ስ 1. በእጅ ያለ ገንዘብ፥ ንብረት፡ ጥሪት:: 2. እንደመነሻ ሆኖ ለንግድ ስራ የሚያገለግል ዋና ገንዘብ፥ ካፒታል::

**ወረት**[2] ስ ፅናት ወይም መሰረት የሌለው ጊዜያዊ ፍቅር ::

**ወረቱ አለቀ** በአዲስነቱ የነበረው ፍቅር አለቀ፡ ሰለቸ ::

**በወረት** ሳይሰለች፥ በአዲስነቱ ጊዜ:: *በወረት ብዙ ተበላ ::*

**ወረተኛ** ቅ 1. በአንድ የማይፀና፥ ፅኑ ፍቅር የሌለው፡ አንዴ ከአንዱ፥ አንዴ ከሌላው የሚሆን:: 2. ፍቅሩ የማይቆይ ::

**ወረንጦ** ስ እሾህን ለማውጣት የሚያገለግል •የብረት መቆንጠጫ::

**ወረንጦ ቂጥ** ቅ (ስድብ፡ ዘይ.) ቀጭን፡ የቂጣም ተቃራኒ ::

**ወረንጦ አፍ** ቅ (ስድብ) ነገረኛ ::

**ወረወረ** ግ 1. ጣለ፡ አሽቀነጠረ:: 2. ሰደደ፡

ለቀቀ፥... (ቀስትን፥ ጦርን፥...)። 3. ዘጋ፥ ቆለፈ፥ ቀረቀረ (የበር፥ የመስኮት መቀርቀሪያን)። 4. አቀረበ፥ ሰነዘረ (ሃሳብን፥...)። 5. በንቀት፥ በጥላቻ፥...ሰጠ። *ከሬቴ ሂድልኝ ብሎ ትንሽ ገንዘብ ወረወረለት*። 6. ማግን በድር መሃል በመወርወሪያ አስተላለፈ ። 7. በርካሽ ሸጠ። 8. ኸርው አድርጎ ጣጣ።

**መወርወሪያ** ስ 1. መቀርቀሪያ፥ መሸጎሪያ። 2. ማግን በድር መሃል ለማስተላለፍ የሚረዳ የሽመና መሳሪያ።

**ተወረወረ** ግ 1. ዘለለ፥ እንጣጥ ብሎ አለፈ፥ ተሽቀነጠረ (በአንድ ነገር ላይ ለማረፍ ወይም አንድን ነገር ለመያዝ)። 2. በፍጥነት ሄደ፥ ፈትለክ አለ ።

**ተወርዋሪ ኮከብ** ስ በምሽት ከሚታዩ ኮከቦች መሃል በድንገት ቁልቁል እየተወረወረ ሲጠፋ የሚታይ ኮከብ።

**ተወርዋሪ ጦር** ስ በድንገት እየደረሰ አደጋ የሚጥል ጦር።

**ተወራወረ** ግ 1. ወረወረ፥ ጣለ። 2. ስድብና ዘለፋን፥...ተለዋወጠ፥ ተመላለሰ።

**ወረዛ** ግ ራሰ፥ ርጥበት ያዘ ።

**ወረዘት** ስ የእንፋሎት ነጠብጣብ፥ ርጥበት።

**አወረዛ** ግ አረጠበ፥ አራሰ።

**ወረደ** ግ 1. ከፍ ካለ ቦታ ወደ ዝቅተኛ ቦታ ሄደ፥ ተንዘ፥ አቆለቆለ። 2. መሬት ላይ አረፈ (ከዛፍ፥ ከመኪና፥...)። 3. ፈሰሰ። *እንባው ይወርዳል*። 4.ተባረረ፥ ተወገደ (ከማእረግ፥ ከስልጣን፥...) ። 5. አነሰ፥ዝቅ አለ። *ሙቀቱ ወረደ* ። 6. ረከሰ፥ ዋጋ ቀነሰ ። *የቡና ዋጋ ወረደ* ። 7. ደረሰ፥ ወደቀ። *ችግር ወረደበት*። 8. ተንዘረፈፈ፥ ረዘመ (ለምሳሌ ፀጉር) ። 9. ሰፈነ፥ተገኘ። *ሰላም ወረደ*። 10. ተላለፈ። *ከአባት ወደ ልጅ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ* ። 11. መታ፥ ጨፈረ (እስክስታን በአንገት፥ በትከሻ)።

**መውረጃ** ስ መሄጃ ፥ መተላለፊያ፥ መንገድ።

**ወረደበት** 1. ብዙ ተቆጣው፥ ዘለፈው፥ ሰደበው። 2. ብዙ በላ (ምግብ፥...) ።

**ወረዳ** ስ ከአውራጃ በታች ያለ የአስተዳደር ክፍል።

**[የ]ወረዳ ወረደ** ከማእረጉ፥ ከደረጃው ዝቅ ብሎ ያለብጤው ዋለ ።

**ወረዳ ምክር ቤት** ስ በወረዳ ደረጃ የተቋቋመና የተወሰነ ስልጣን ያለው ምክር ቤት።

**ወረዳ አስተዳዳሪ** ስ የወረዳ አስተዳደር ከፍተኛ ባለስልጣን ።

**ወረዳ ገዥ** ስ የወረዳ ከፍተኛ ባለስልጣን ወይም አስተዳዳሪ የቀድሞ መጠሪያ ።

**ወራዳ** ቅ (ስድብ) ነውረኛ፥ ልክስክስ፥ ቅሌታም።

**ወራጅ** ቅ 1. የሚሄድ፥ የሚወርድ፥ የሚፈስ፥ ረግቶ ያልቆመ (ውሃ፥ ወንዝ፥...)። 2. ከተሳፈረበት መኪና ውስጥ የሚወርድ፥ ወደውጭ የሚወጣ። 3. ወደታች ሂያጅ፥ ተጓዥ። 4. የቤት ክዳን ቆርቆሮ የሚመታበትን ማገር የሚሸከም አቀልቋይ እንጨት፥ አውራጅ እየተባለም ይጠራል።

**ወርድ** ስ የጎን ስፋት ።

**ውራጅ** ቅ አሮጌ፥ ያገለገለ (ልብስ፥ ጫማ፥...)።

**ውርደት** ስ ቅሌት፥ አሳፋሪ ነገር ።

**ውርዴ** ቅ የቂጥኝ በሽታ ታሞ የዳነ ።

**ውርድ ንባብ** ስ ጎተት የሚልና በዜማ መልክ የሚነበብ የንባብ ቤት ትምህርት፥ የአነባበብ መንገድ ።

**ውርድ ከራሴ** በሚደርሰው ጉድለት፥ ጥፋት፥...እኔ አልጠየቅም ለማለት የሚነገር አባባል።

**ውርጃ** ስ የሽል፥ የፅንስ መጨንገፍ።

**ውርጅብኝ** ስ ቁጣ፥ መአት፥ድንገት የመጣ አደጋ።

**ውርርድ** ስ እንዲህ ነው፥ አይደለም፥ ይሆናል፥ አይሆንም በሚል በተለያየ ሃሳብና አስተያየት ምክንያት በሰዎች መካከል የሚደረግ ፉክክር (ተረቺ የሚሆነው ወገን የተወሰነውን ነገር ለመክፈል ቃል የሚገባበት ስምምነት)።

**ውርርድ ተከለ** ለውርርድ የሚሆን ገንዘብ አስያዘ፥ አስቀመጠ፥ መደበ።

**ተወረደ** ግ ፈፀመ፥ ጨረሰ፥ተወጣ። *እገሌ እዳውን ተወረደው*።

**ተወራጅ** ቅ አነስተኛ፥ ዝቅተኛ፥ ምክትል (ሹም)።

**ተወራረደ** ግ 1. ተፎካከረ፥ ቢረታ ወይም ቢሸነፍ በውርርዱ ጊዜ የተወሰነውን ነገር ሊከፍል ቃል ገባ፥ ተዋዋለ። 2. ተበላተ፥ ተቆረጠ (ስጋ)። 3. የወጪ ማስረጃው ቀርቦ ከወጪ ቀሪው ተመለሰ።

**ተወራራጅ** ቅ ተፎካካሪ (በውርርድ) ።

**ተዋረደ** ግ 1. ከክብሩ ዝቅ አለ፥ ቀለለ፥ በሚያሳፍር ሁኔታ ተገኘ። 2. ተላለፈ (ካለፈው ወደሚቀጥለው፥...)። *ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ባህል*።

**ተዋረድ** ስ ከከፍተኛ ወደዝቅተኛ የሚሄድ፥ የሚወርድ ደረጃ፥ እርከን።

**በተዋረድ** በደረጃ፥ ከላይ ወደታች።

**አወረደ** ግ 1.አስወገደ፥ አስነሳ (ከስልጣን፥ ከማእረግ)። 2. ከፍ ብሎ ከነበረበት ቦታ ወደታች አመጣ(ለምሳሌ ፍራፍሬን ከዛፍ ላይ)። 3.

ከመኪና ፥ ከባቡር፥... ላይ አራገፈ (ሰውን ወይም እቃን)። 4. አሳነሰ ፥ ቀነሰ ፥ ዝቅ አደረገ። 5. አሰፈነ፥ አነገሰ፥ አሳደረ። *ሰላም ኣወረደ/በረከት ኣወረደ*። 6. በፀናዕልና በክበሮ እየታጀበ በአቋቋም የዜማ ስልት መንገድ አዜመ፥ ዜማውን አንቆረቆረ፥ አሰማ። *ዚቅ ኣወረደ*። 7. አቀነቀነ፥ ዘፈነ፥ ዘፈን አውራጅ ሆነ። 8. አኾሰጎደጎደ (ስድብን፥ ቁጣን፥...)። 9. አቃለለ፥ አራገፈ (ሸክምን፥...)። 10. በብዛት ሰጠ፥ አዘነበ። 11. ምድር ላይ ጣለ። *ኣውሮፕላኑን በጥይት ኣወረደው*። 12. አነሳ፥ ሰረዘ (ዋስትናን፥ ሃላፊነትን)።

**አውራጅ** ስ 1. አቀንቃኝ፥ የዘፈን መሪ፥ ዘፋኝ። 2. እቃን፥ ሸክምን ከጭነት ላይ የሚያወርድ ሰው። 3. አቆልቋይ፥ ሞላላ የመቃ ወይም የሳንቃ ገበታ።4. የቆርቆሮ ቤት የጣሪያ ማገር ተሸካሚ እንጨት፥ ወራጅ ።

**አዋረደ** ግ 1. አቃለለ፥ ከማእረግ፥ ከክብር ዝቅ አደረገ። 2. ሰደበ፥ አሳፈረ፥ እፍረት ላይ ጣለ ።

**አዋራጅ** ቅ ተሳዳቢ፥ ባለጌ፥ ሰውን የሚያዋርድ፥ የሚያሳፍር።

**አውራጃ** ስ በስሩ የተወሰኑ ወረዳዎችን የያዘ የአስተዳደር ክፍል ።

**አወራረደ** ግ 1. የወጪ ማስረጃን በማቅረብና ቀሪውን ተመላሽ በማድረግ ሂሳብን ዘጋ። 2. አፎካከረ፥ እንዲወራረዱ አደረገ። 3. ቆረጠ፥ በለተ፥ ሰየፈ። 4. እየጠጣ፥ ፉት እያለ፥ እያራሰ በላ። *ምሳውን በሻይ እያወራረደ በላ* ።

**ማወራረጃ** ስ ምግብን በደንብ ለመብላት ወይም የተበላውን ለማንሸራሸር የሚረዳ መጠጥ።

**አስወረደ** ግ እንዲወርድ አደረገ።

**አስወረደች** ግ ሽሉ ፥ ፅንሱ ከማህፀኗ እንዲወጣ ፥ እንዲጨነገፍ አደረገች።

**አስወረዳት** ግ (ሽሉ ወይም ፅንሱ) ወጣባት፥ ጨነገፈች።

***ወረገረገ**

**ተውረገረገ** ግ ተረገረገ፥ የኩራት፥ የቄንጥ አረማመድ ተራመደ።

**ተውረግራጊ** ቅ የሚውረገረግ፥ የሚረገረግ።

**ወረገኑ** ስ ቀደም ሲል በነበረው ስርኣት የመንግስትን የእርድ ከብቶች የሚቀልብ ሰው ወይም ከብቶቹ ይቀለቡበት የነበረ ቦታ ።

**ወረጋ** ቅ 1. ጓዝ የለሽ፥ ባዶ እጁን የሚጓዝ፥ የሚሄድ፣ ሌጣ (ተጓዥ)። 2. ያልተጫነ፥ ጭነት የሌለው (የጋማ ከብት) ።

**ወረግቡ** "ወር" ስር ተመ.

**ወረጨ** ግ ውርጭን፥ አመዳይን ጣለ፣ በረደ፥ ቀዘቀዘ ።

**ውርጭ** ስ በበጋ ወራት በአየር ቅዝቃዜ የተነሳ ሌሊቱን መሬት ወይም ሳር ላይ ተጋግሮ የሚገኝ ርጥበት ።

**ውርጭ አነደደው** ውርጭ መታው፥ ጎዳው።

**ውርጭ ከካው** ዝ.ከ.

***ወረጨ**

**ተወራጨ** ግ ተቅበጠበጠ፥ የጭንቅ እንቅስቃሴ ተንቀሳቀሰ፥ ተንፈራገጠ ።

**አወራጨ** ግ አቅበጠበጠ፥ አንፈራገጠ፥ እረፍት ነሳ።

**ወረፈ** ግ ሰደበ፥ ዘለፈ ።

**ወራፊ** ቅ ሰዳቢ፥ ዘላፊ ።

***ወረፈ**

**ወረፋ** ስ ለአንድ ጉዳይ አንድ ቦታ ላይ የተገኙ ሰዎች እንደአመጣጣቸው ቅደም ተከተል የሚጠብቁት ተራ ።

**ወረፋ ነው/አለ** ተራውን ይዞ የሚጠብቅ ብዙ ሰው አለ ።

**ወረፋ ያዘ** ተራ ያዘ፥ እንደአመጣጡ በቅደም ተከተል ተሰለፈ ።

**ወረፍ ወረፍ አደረገ** ግ አለፍ አለፍ እያለ፥ እየዘለለ ሰራ፥ አነበበ፥ አጨደ ።

**ወሬራ** ቅ ገርጋሬ፥ ደንባሬ፥ በርጋጊ (ከብት) ።

**ወሪሳ** ስ ድንገተኛ ወረራ፥ ዘረፋ ።

**ወሪሳ መታ** ድንገተኛ ወረራ፥ ዘረፋ አካሄደ።

**አፈ ወሪሳ** ሳያስቡ ድንገት አፍ እንዳመጣ መናገር ።

**ወራ** ግ ቢጫ መልክ ያዘ፣ ቢጫ መሰለ ።

**አወራ** ግ ቢጫ አስመሰለ።

***ወራ**

**ወሬ** ስ 1. በሰዎች መካከል የሚደረግ ጭውውት፥ ንግግር፣ አንዱ ለሌላው የሚያስተላልፈው የሃሳብ ልውውጥ (ብዙውን ጊዜ ተራ የሆነ)። 2. አዲስ የሚሰማ ነገር፥ ዜና። *ምን ወሬ አለ* ?

**[ለ]ወሬ ነጋሪ አልቀረም** ሁሉም አልቋል፥ ሞቷል ወይም በቦታው የለም ።

**ወሬ ለቀመ** ወሬ ሰበሰበ ።

**ወሬ ለቃሚ** ቅ አሾክሿኪ፥ ከአንዱ ሰምቶ ለሌላ የሚያቀብል ።

**ወሬ ነው** ውሸት ነው፣ ያልተደረገ፥ ያልተፈፀመ፥ ያልተረጋገጠ ነገር ነው ።

**ወሬ አቀበለ** አንሿከከ፥ አሳበቀ፥ ነገር አቀበለ።

**ወሬ አቀባይ** ቅ ወሬን ከአንዱ ወስዶ ለሌላው የሚነግር፣ አሳባቂ ።

**ወሬ አየ** በአካባቢው የሚደረገውን፥ የተፈጠረውን ነገር ተመለከተ ።

**ወሬ ዘረጋ** ወሬ ያዘ፥ ቀጠለ ።

**ወሬ ይቀዳል** ወሬ ይሰበስባል።

**ወሬ ይቀዷል** ወሬ ዘርግቷል፣ ወሬ በማውራት ወይም በማዳመጥ ላይ ነው ።

**ወሬን ዘራ** ወሬን አሰራጨ፥ ለሁሉ አዳረሰ።

**ወሬው ተዛመተ/ዘመተ** ወሬው በሰፊው ተሰራጨ፥ ተሰማ፥ ተዳረሰ።

**ወሬው ደራ** ወሬው ደመቀ፥ ሞቀ፣ እየጨመረ፥ እየሰፋ ሄደ ።

**ወሬው ጠፋ** ስለአንድ ሰው፥ ጉዳይ፥ ነገር፥... የሚሰማ ነገር ታጣ።

**ወሬውን ይሰልቃል** ስራ ፈትቶ ያወራል ።

**ወሬውን ይክሰክሳል/ ይከካል/ ይከመኩማል** ወሬውን በስፋት እያወራ ወይም እያዳመጠ ይገኛል ።

**ወሬ ምሳው** ወሬ ወዳድ፥ ወሬኛ፣ ወሬ ካገኘ ለምሳው እምብዛም ግድ የሌለው ።

**የወሬ አባት** 1. ወሬውን መጀመሪያ ያወራው ወይም ያመጣው (ሰው)። 2. ወሬኛ ።

**የወሬ ቋት** ወሬ የሚወድ፥ የሚሰበስብና መልሶ የሚነዛ፥ በስራ የማይጠመድ ።

**የወሬ ምንጭ** ወሬውን በመጀመሪያ ያመጣ ወይም ያወራ ።

**ወሬኛ** ቅ 1. ወሬ የሚወድ፥ ብዙ የሚያወራ። 2. አሳባቂ፥ ወሬ አመላላሽ።

**ተወራ** ግ ተነገረ፥ ተባለ፥ ተሰራጨ (ወሬው) ።

**አወራ** ግ ነገረ፥ አሰራጨ፥ አስተላለፈ (ወሬን)።

**አዋራ** ግ 1. አናገረ። 2. አወራ ወይም አዳመጠ(ወሬን) ።

**አስወራ** ግ አስነገረ፥ እንዲነመት ወይም እንዲሰራጭ አደረገ (ብዙውን ጊዜ የውሸት ወሬ)።

**ወራሪ** "**ወረረ**" ስር ተመ.

**ወራሽ** "**ወረሰ**"ን ተመ.

**ወራት** "**ወር**"ን ተመ.

**ወራንታ** ስ ከግራምጣ ወይም ከአክርማ፥... የሚሰፋና ከቁና ከፍ የሚል የእህል መስፈሪያ ።

**ወራውራን** ስ በፀሃይ መጥለቂያ ጊዜ የሚታይ ደብዘዝ ያለ የፀሃይ ብርሃን ወይም የእሳት ወጋገን።

**ወራዳ** "**ወረደ**" ስር ተመ.

**ወራጅ** ዝ.ከ.

**ወራፊ** "**ወረፈ**" ስር ተመ.

**ወሬ** "***ወራ**" ስር ተመ.

**ወሬኛ** ዝ.ከ.

**ወር** (ብ.ቁ.**ወራት**) ስ 1. ሰላሳ ቀናትን የሚይዝ የአመቱ አንድ አስራ ሁለተኛ ክፍለ ጊዜ (ለምሳሌ ከመስከረም አንድ እስከ መስከረም ሰላሳ ያለው ጊዜ አንድ ወር ነው)። 2. ሰላሳ ተከታታይ ቀናትን የያዘ የጊዜ መጠን። *መጋቢት 10 ሲመጣ ስራ ከጀመርኩ 1 ወር ይሞላኛል።*

**ከወር እስከ ወር** 1. ሁልቀን፥ ሁልጊዜ። *ከወር እስከ ወር እረፍት የለውም፡* 2. ለወር ያህል ጊዜ። *ደመወዙ ከወር እስከ ወር አያደርሰውም፡*

**ወረግቡ** ቅ ልትወልድ የደረሰች፥ ዘጠነኛ ወሯን የያዘች (ሴት) ።

**ወር ተራ** ስ በየተራ ለወር ያህል የሚካሄድ የስራ ፈረቃ፥ ጊዜ ።

**ወር ተረኛ** ቅ የወሩ ባለተራ (አንድን ተግባር ለማከናወን) ።

**ወር አለፍ** አንድ ወር እያለፉ በየሁለተኛው ወር (የሚደረግ፥...) ።

**የወሩ (የወር) ነው** የአመቱ አይደለም፥ አይነግስም፥ ታቦት አይወጣም። *የጥቅምቱ ሚካኤል የአመቱ መስሎኝ ነበር፥ ለካስ የወሩ ኖሯል ።*

**የወር አበባ** ስ በየወሩ እስከ ሰባት ቀናት ከሴቶች ማህፀን የሚፈስ ደም፥ አደፍም ይባላል።

**የወር ክፍያ** ስ በየወሩ የሚከፈል ገንዘብ (የአገልግሎት፥ የቤ/ቤት፥ ...)።

**ወርሃ_ የ_** ወቅት፥ ጊዜ። *ወርሃ ክረምት፡*

**ወርሃ ፅጌ** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ከመስከረም ሃያ ስድስት እስከ ህዳር ስድስት ቀን ድረስ ያለው የአበባ ጊዜ፥ ማርያም ልጇን ይዛ ከኢየሩሳሌም ወደ ግብፅ የተሰደደችበት ወራት መታሰቢያ ።

**ወርሃዊ** ቅ በየወሩ የሚደረግ፥ የሚወጣ፥ የሚታተም፥...።

**ወርቅ** ስ 1. ልዩ ልዩ ጌጣ ጌጦችን፥ ገንዘቦችን ለመስራት የሚያገለግል የከበረ ማእድን። 2. በስም ተደብቆ፥ ተሸፍኖ የሚነገር የቅኔ ውስጠ ምስጢር። 3. (ዘይ.) ጥሩ፥ ቆንጆ። *ሓመሉ ወርቅ ነው።*

**በወርቅ ነደደ** በወርቅ ተሸቆጠቆጠ፥ አጌጠ ።

**ወርቀ ዘቦ** ስ በወርቅ ፈትል የተጌጠ፥ የተጠለፈ (ካባ፥ ግምጃ፥...) ።

**ወርቃ ወርቅ** ስ ሰሙን ትቶ በወርቅ ብቻ የሚነገር የቅኔ መንገድ፥ ሰም ረገፍ ።

**ወርቅ ቀለም** ስ በወርቅ የተዘጋጀ ወይም ወርቅን የሚመስል ቀለም ።

**ወርቅ ቅብ** ቅ ውስጡ ሌላ ሆኖ ላዩ ወርቅ

ወይም ወርቅ ቀለም የተቀባ፣ የተከላ (እቃ) ።

**ወርቅ ሰሪ** ስ ከወርቅ፥ ከብር፥...የተለያዩ ጌጦችን የሚሰራ ባለሙያ ።

**ወርቅ በሜዳ** ስ መድሃኒትነት አለው የሚባል፥ በመሬት ላይ ልጥፍ ብሎ የሚበቅል፣ ወርቅ የሚመስል ቅጠል ያለው የእፅዋት አይነት።

**ወርቅ ውሃ** ስ የወርቅ ቀለምን ለመበጥበጥ የሚያገለግል ፈሳሽ ።

**ወርቃማ** ቅ 1. ወርቅ የሚመስል፥ የሚያምር። 2. ጥሩ፥ ተፈላጊ፥ ውድ የሆነ። *ወርቃማ ጊዜ* ።

**ወርቅዬ** ስ ፍሬው ትልልቅ፥ ገለባው በቀላሉ የሚለቅ፥ ለቆሎና ለእንጀራ የሚሆን የገብስ አይነት።

**የወርቅ ኢዮቤልዩ** ስ የአንድ ድርጊት ሃምሳኛ አመት ክብረ በአል ።

**የወርቅ ጥርስ** ስ ሰው ሰራሽ የሆነ፥ ብዙውን ጊዜ በወለቀ ጥርስ ፈንታ የሚተከል ከወርቅ የተሰራ ጥርስ ።

**የወርቅ ፍልቃቂ** በጣም የሚያምር፥ ውብ፥ ቆንጆ ።

**ወርች** ስ የከብት የፊት እግር ስጋ ።

**ወርች ከምብል** ቅ ዘቅዛቃነት፥ ቁልቁለትነት ያለው፥ ተዳፋት (መሬት) ።

**ወርካ "ዋርካ"** ን ተመ.

**ወርድ "ወረደ"** ስር ተመ.

**ወሮ በላ "ወረረ"** ስር ተመ.

**ወሮታ(ወረታ)** ስ 1. ለመልካም ስራ የሚሰጥ፣ ለውለታ የሚከፈል ጥሩ ነገር፥ ሽልማት። 2. በጎ ስራ፥ ድርጊት፣ ውለታ ።

**ወሰለተ(ወሳለተ)** ግ ባለገ፥ ማገጠ፣ በስራ የማይገኝ ሆነ፣ ዋለገ ።

**ወስላታ** ቅ በቃሉ የማይገኝ፣ እምነት የማይጣልበት፥ አታላይ ።

**ውስልትና** ስ 1. አለመታመን፣ የማታለል ድርጊት። 2. ማጋጣነት፥ ስራ ፈትነት ።

**አወሰለተ** ግ አማገጠ፥ አባለገ ።

**ወሰራ[ዶሮ]** ስ መላው አካሉ ነጭ ሆኖ ጀርባው ወይም ክንፉ ላይ ቀይ ያለበት ዶሮ ።

**ወሰሰ** ግ ቀጠነ፥ መነመነ፥ ቀለለ (የስንዴ፥ የገብስ ፍሬ) ።

**ወሰስ** ቅ ቀጭንና ቀላል የሆነ (የስንዴ፥ የገብስ ፍሬ) ።

***ወሰበሰበ**

**ውስብስብ** ቅ 1. የተጠላለፈ፥ ውትብትብ (ክር፥ ገመድ፥ መንገድ፥...)። 2. አስቸጋሪ፥ በቀላሉ ሊቃለል የማይችል። 3. በጣም የተመሰቃቀለ፣ ግልፅ ያልሆነ፣ በቀላሉ መረዳት የማይቻል።

**ተወሳሰበ** ግ 1. ተጠላለፈ፥ ተሳሰረ፣ በቀላሉ ሊለያይ ወይም ሊፈታ የማይችል ሆነ (ለምሳሌ ክር፥ ገመድ፥...)። 2. ረቀቀ (ሃሳብ፣ ነገር)። 3. አስቸጋሪ፥ ከባድ፥ በቀላሉ መፍትሄ ሊያገኝ የማይችል ሆነ። *ፈጣን እርምጃ ባለመወሰዱ ችግሩ ሁሉ ተወሳስቧል።*

**አወሳሰበ** ግ 1. አጠላለፈ፥ አቆላለፈ፥ እርስ በርስ አስተሳሰረ (ለምሳሌ ገመድን፥ ክርን)። 2. አስቸጋሪ፥ ከባድ፥ በቀላሉ የማይፈታ አደረገ (ችግርን፥...)።

**ወሰነ** ግ 1. አንድ ነገር እንዲፈፀም ወይም አንድ አይነት እርምጃ እንዲወሰድ ተስማማ፣ አቀደ፥ አዘዘ። 2. ገደበ፥ ከለለ። 3. ደነገገ፥ ስርአትን አበጀ፥ ሰራ። 4. ቆረጠ፣ እንዲህ ይሁን አለ። *ቀን ወሰነ/ ዋጋ ወሰነ/ሃሳቡን ወሰነ* ።

**ወሰን** ስ 1. ድንበር፥ የቦታ፥ የሃገር ክልል። 2. ገደብ፥ መጨረሻ። *አንተን በማግኘቴ ደስታዬ ወሰን የለውም* ።

**ወሰን ገፋ** ከክልሉ፥ ከድንበሩ አለፎ የሌላውን ቦታ ያዘ።

**ከወሰን ያለፈ** እጅግ ብዙ።

**ወሰንተኛ (ወሰነተኛ)** ቅ ድንበርተኛ ።

**ወሳኝ** ቅ 1. የሚወስን፣ ውሳኔ የሚሰጥ። 2. ለውጤት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው፣ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት። *ያንተ መገኘት ወሳኝ ነው*።

**ውሱን(ውስን)** ቅ 1. በጥቂት ነገሮች ብቻ የተገደበ፣እንደፈቀደው በሁሉም ቦታ የማይገኝ፣ ቁጥብ ። 2. ጥቂት፣ ብዙ ያልሆነ።

**ውሳኔ** ስ የተሰጠ ትእዛዝ፣ እንዲፈፀም፣ እንዲደረግ የተባለ ወይም በስብሰባ ወስነው ያሳለፉት ስምምነት።

**ውሳኔ አስተላለፈ** ውሳኔ ሰጠ።

**ውሳኔ ህዝብ** ስ ህዝብ ፍላጎቱን፣ ምርጫውን የሚገልፅበት መንገድ።

**ተወሰነ** ግ 1. ውሳኔ፥ ትእዛዝ ተሰጠ ወይም ተላለፈ፥ ውሳኔ አገኘ። 2. ተደነገገ። 3. ተገደበ፣ ተከለለ። 4. ተቆረጠ ፡እንዲህ ይሁን ተባለ።

**የተወሰነ** መጠነኛ ቁጥር ያለው። *የተወሰነ ህዝብ በስብሰባው ተገኘ/ ለተወሰነ ሰአት ተገኘቼ ነበር።*

**ያልተወሰነ ጊዜ** በዚህ ቀን ይሁን ተብሎ ገደብ ያልተሰጠው ወይም ቀጠሮ ያልተያዘለት ጊዜ።

**ተዋሰነ** ግ 1. ድንበርተኛ፥ ወሰንተኛ ሆነ። 2. ድንበር ተካለለ ፥ አበጀ።

**ተዋሳኝ** ቅ ድንበርተኛ፣ ወሰንተኛ።

**አዋሰነ** ግ 1. በድንበር፣ በወሰን ተገናኘ።

*በስተምእራብ በኩል ሱዳን ኢትዮጵያን ታዋስናለች።* 2. ኣካለለ፥ ድንበር ኣበጀ።

**ኣዋሳኝ** ቅ ወሰንተኛ፥ ድንበርተኛ፥ በወሰን የሚገናኝ።

**ወሰካ** ስ ቃሬዛ።

**ወሰክ** ስ ቆሻሻ፥ እድፍ።

**ወሰወሰ** ግ 1. ጥብቅ ያልሆነ ስፌትን ሰፋ፥ ሸደሸደ። 2. እጅና እግሩን ቶሎ ቶሎ ኣንቀሳቀሰ፥ ኣወራጨ (ለመዋኘት)። 3. እረፍት ነሳ፥ ገፋፋ፥ በል በል ኣለ ።

**ወስዋሳ** ቅ 1. (ስድብ) ኣርፎ የማይቀመጥ፥ እርጋታ የሌለው፥ ቶክቷካ። 2. ሰባቂ፥ ቀጣፊ፥ ሌባ።

**ተወስወሰ** ግ 1. ጥብቅ ያልሆነ ስፌት ተሰፋ። 2. እረፍት ኣጣ፥ ተገፋፋ ።

**ተወሳወሰ** ግ ቀጣፊ፥ ሌባ፥ ወስዋሳ ሆነ ።

**ኣወሳወሰ** ግ 1. ኣዛመረ፥ ኣፈናፈነ፥ ኣንቀሳቀሰ፥ ኣወላዳ። *ዋስ ኣያወሳውስ* ። 2. ኣሳበቀ፥ ኣዋሸከ፥ ነገር ኣመላለሰ ።

**ወሰው** ቃ.ኣ. ድንቅ፥ ግሩም፥ መልካም፥ ጎሽ፥ እሰይ ለማለት የሚነገር ኣባባል። *እጅግ ጠቃሚ ስራ ሰርቶ ነበር፥ ወሰው ያለው የለም እንጂ።*

**ወሰደ** ግ 1. ተቀበለ፥ ተረከበ። 2. ያዘ፥ በእጁ ኣደረገ። 3. ወደ ኣንድ ቦታ ይዞ ሄደ። 4. በላ፥ ጠጣ፥... (ምግብን፥ መጠጥን፥ መድሃኒትን)። 5. ሰረቀ። *ንብረቱን ሌባ ወሰደው፡* 6. ፈጀ፥ ጨረሰ፥ ያዘ። *ጊዜ ወሰደ/ብዙ ቦታ ወሰደ።* 7. ኣመራ፥ ኣደረሰ። *ወደ መ/ቤቱ የሚወስደው መንገድ ተዘግቷል።* 8. ቀነሰ፥ ኣነሳ። *ከሃያ ላይ ኣስር ሲወሰድ ኣስር ይቀራል።* 9. ቆጠረ፥ ገመተ። *ያደረግሁለትን ሁሉ በከፋት ወሰደው፡* 10. ያዘ፥ መዘገበ። *ስልክ ቁጥር ወሰደ/ንጥብ ወሰደ።* 11. ተመለከተ፥ ኣየ፥ መረመረ። *ለምሳሌ ይሀን ብንወስድ።*

**ወሰድ ያደርገዋል** 1. ኣእምሮውን ሳት ያደርጋል፥ ከትክክለኛው የኣእምሮና የሃሳብ መንገድ ይወጣል። 2. ኣልፎ ኣልፎ ነገር ይዘነጋል፥ ይስታል።

**ወሳጅ** ስ ሰይጣን፥ ሰላቢ። *እሁሉን ወሳጅ ወሰደው መሰለኝ ኣልበረከት ኣለ ።*

**ወሳሰደ** ግ በጥቂቱ ደጋግሞ ጠጣ (የኣልኮል መጠጥን) ።

**ተወሰደ** ግ 1. በሌላ ሰው ቁጥጥር፥ እጅ፥ ይዞታ ስር ገባ። 2. ተይዞ ሄደ። *በፖሊስ ተወሰደ።* 3.ተሰረቀ። 4. ተፈጀ፥ ተጠቀመ። *ጊዜ ተወሰደ ከተሰራ በጥሩ ሁኔታ ያልቃል።*

**ተወሰደለት** ተነሳ፥ ተቀነሰ (ከላዩ) ።

**ተወሰደበት** 1. ተቀማ፥ ተወረሰበት። 2. ተሰረቀ ።

**ኣስወሰደ** ግ እንዲወሰድ ኣደረገ።

**ወሲብ** ስ በወንድና በሴት መካከል የሚፈፀም ፍትወተ ስጋዊ ስራ፥ ግብረ ስጋ።

**ወሲባዊ ግንኙነት** የግብረ ስጋ ግንኙነት።

**የወሲብ ፍላጎት** የግብረ ስጋ ፍላጎት ።

**ወሲፉ(ወሲፍ)** ስ ኮረዳ፥ ወጣት፥ ልጅ እግር።

**ወሳ**

**ተወሳ** ግ 1. ተባለ፥ ተነገረ፥ ታተተ። 2. ታወሰ፥ ታሰበ፥ ተነሳ (ነገሩ፥...)።

**ኣወሳ** ግ 1. ኣተተ፥ ተናገረ። 2. ኣስታወሰ፥ ኣነሳ (ነገሩን፥...)።

**ወሳለተ** **"ወሰለተ"** ን ተመ.

**ወሳሰደ** **"ወሰደ"** ስር ተመ.

**ወሳብሬ** ስ የግመል ጊደር ።

**ወሳኝ** **"ወሰነ"** ስር ተመ.

**ወሳጅ** **"ወሰደ"** ስር ተመ.

**ወሳፍቻ(መሳፍቻ)** ስ እንደ ወስፌ ያለ የጫማ፥ የጅራፍ፥ የኮርቻ፥...መስፊያ።

**ወስላታ** **"ወሰለተ"** ስር ተመ.

**ወስከምቢያ(ወስከምባይ)** ስ ከግራምጣ ወይም ከኣክርማ፥...የሚሰፋ የሌማት፥ የመሶብ፥... መክደኛ።

**ወስከምት** ስ 1. የውሻ ማሰሪያ፥ ማነቆ። 2. መቃጥን፥ የኣሳ ማጥመጃ ቆላፋ ብረት። 3. ጅንግላ።

**ወስዋሳ** **"ወሰወሰ"** ስር ተመ.



ወስፈንጥር

**ወስፈንጥር** ስ 1. ጎበጥ ካለ እንጨት የሚሰራ የወፍ፥ የቆቅ፥... መያገሮ፥ ወጥመድ። 2. እንደጠፍር ያለ ሆኖ ጫፍና ጫፉ ባላንትባለው ኣነስተኛ እንጨት ላይ የታሰረና ልጆች ጠጠር ኣጉርሰው እያስፈነጠሩ ወፎችን፥... የሚመቱበት ተለጣጭ ጎማ ወይም ላስቲክ፥ ወንጭፍም ይባላል።

**ወስፋት** ስ 1. ቀጭን፥ ረዥም የሆድ ውስጥ ትል። 2. ኣንድን ነገር በጥሩ ስሜት የማድረግ፥ የመቀበል፥ የመውሰድ፥... ፍላጎት (ብዙውን ጊዜ ከመብላትና ከመጠጣት ጋር ተያይዞ የሚነገር)።

**ወስፋቱ ተቆለፈ /እምቢ ኣለ/ ኣልቀበል ኣለ** የምግብ ፍላጎት ኣጣ፥ ኣልበላለት ኣለ ።

**ወስፋታም** ቅ 1. (ስድብ) ወስፋት ያለበት፡ ወስፋት የያዘው፡፡ 2. ብዙ ምግብ የማይበላ፥ የምግብ ፍላጎት የሌለው፡፡ 3. ቀጫጫ ፡፡

**ወስፌ** ስ እንደ መሶብ፥ ሙዳይ፡... የመሳሰሉትን የስፌት እቃዎች ለመስፋት የሚያገለግል ቀጭንና ሹል ብረት፡፡

**ወስፌ ቂጥ** ቅ 1. (ስድብ፡ ዘይ.) አንድ ቦታ አርፎ የማይቀመጥ፡ ቀዥቃዣ፡፡ 2. የቂጣም ተቃራኒ ፡፡

**ወሸለ** ግ እንደ ነገሩ ሳያጠብቅ አሰረ፡፡

**ወሻላ** ቅ ውትፍትፍ፡ ውሽልሽል፥ ጠባቃ ያልሆነ፡፡

**ውሽልሽል** ቅ ጥብቅነት የሌለው፡ ልል ፡፡

**ተውሸለሸለ** ግ ተውተፈተፈ፡ ጥብቅነት የሌለው ሆነ ፡፡

**አውሸለሸለ** ግ አውተፈተፈ፥ እንደ ነገሩ ሰራ፡ ሳያጠብቅ አሰረ ፡፡

**ወሸለከ** ግ 1. አልያዝ፥ አልጨበጥ አለ፣ ሾለከ፡፡2. ወሰለተ ፡፡

**ወሸላካ** ቅ (ስድብ) ወስላታ፥ ቁም ነገር የሌለው፡ የማይጨበጥ ፡፡

**ወሸላ** ስ 1. ያልተገረዘ የወንድ ብልት፡፡ 2. (ዘይ.) ፈሪ፥ ወኔ የሌለው፡፡

**ወሸመ** ግ ውሽማ ያዘ፡ አደረገ፣ ሚስቱ ካልሆነች ሴት ጋር በወዳጅነት፡ በፍቅር ተሳሰረ፡፡

**ውሽማ** ስ በጋብቻ ያልታሰረ ድብቅ የግብረ ስጋ ግንኙነት ያለው ወዳጅ፥ ፍቅረኛ፡፡

**ተወሸመ** ግ ውሽማ ሆነ፡፡

**ወሸቀ** ግ አንድን ነገር በሌላ ነገር ውስጥ ሸጎጠ፡ ሻጠ፥ አገባ፡ ወተፈ ፡፡

**ወሻቃ** ቅ (ስድብ) 1. የማይረባ ፡ ፈሪ፥ ተልካሻ፡፡ 2. ልክስክስ፡ ወታፋ ፡፡

**ውሽቅ አለ** ግ 1. በአንድ ነገር ውስጥ ድብቅ፥ ሽጉጥ ብሎ ተቀመጠ ፡፡ 2. ወደ ውስጥ ገባ፥ ተሸጎጠ፡፡

**ተወሸቀ** ግ 1. ተሸጎጠ፥ ወደ ውስጥ ገባ ፡፡ 2. ተደበቀ፥ ተሸሸገ፡፡

**ተወሽቆ ዋለ** ወደ ውጪ ሳይወጣ ከቤት ውስጥ ዋለ ፡፡

**ወሸባ**[1] ስ 1. ጥቅልል፥ ሽብልል፥ ቀጭን የማግ አመልማሎ ፡፡ 2. መልከ መልካም፡ ሎጋ ፡፡

**ወሸባ**[2] **(ውሽባ)** ስ ህመምተኛ የሆነ ሰው በተወሰነ ስፍራ ተገልሎና ከሰው ተለይቶ በመቀመጥ የሚደረግለት ባህላዊ የህክምና አይነት፡፡

**ወሸባ (ውሽባ) ገባ** ከሰው ተለይቶና በተወሰነ ቦታ ቤት ዘግቶ በመቀመጥ በባህላዊ መድሃኒት ታከመ (በእፅዋት በመታጠን፡ በመታጠብ፥...)፡፡

**ወሸን** ቅ ደግ፥ ማለፊያ፡፡

**ወሼ** ቅ ውብ፡ ቆንጆ፡፡

***ወሸከ**

**አዋሸከ** ግ አሳበቀ፡ ነገር አቀበለ፡፡

**አዋሻኪ** ቅ አሳባቂ፥ ነገር የሚያቀብል፡፡

**ወሸከሬ** ቅ (ስድብ) የማይረባ፥ ተልካሻ ፡፡

**ወሸከተ** ግ የሆነ ያልሆነውን አወራ፥ እውነቱንና ሃሰቱን እየደባለቀ ተናገረ፥ ለፈለፈ፥ ቀላመደ፡፡

**ወሽካታ** ቅ (ስድብ) የሆነ ያልሆነውን የሚያወራ፥ ውሽታም ፡ ቀባጣሪ፡፡

**ተወሻከተ** ግ የሆነ ያልሆነውን አወራ፥ ዋሸ፥ ቀላመደ፥ ወሸከተ፡፡

**ወሸገረ** ግ ወለገደ፥ ጠመመ፡፡

**ወሽጋራ** ቅ ወንጋራ፡ ወልጋዳ፡፡

**ተወሻገረ** ግ ተወናከረ፥ ተወላገደ፡፡

**አወሻገረ** ግ አወናከረ፥ አወላገደ፡፡

**ወሻቃ "ወሸቀ"** ስር ተመ.

**ወሽ** ስ የላም ጡት (እንደ ከረጢት ያለው የወተት መያዣው)፡፡

**ወሸላካ "ወሸለከ"** ስር ተመ.

**ወሸመጥ** ስ 1. ከብብት እስከ ሙሃይት ያለ ገላ፡፡ 2. የጠበበ ልብስን ለማስፋት በስላች ተቆርጦ የሚገባ ጨርቅ፣ ሰላጤ፡፡

**ወሸመጥ ቆረጠ** ተስፋ አስቆረጠ፡፡

**ወሽማዳ** ቅ (ስድብ) ውልክፍክፍ፥ ወልጋዳ፡፡

**ወሽካታ "ወሸከተ"** ስር ተመ.

**ወሽጋራ "ወሸገረ"** ስር ተመ.

**ወቀረ** ግ 1. የወፍጮ ድንጋይን አተባ፥ አሻከረ፥ እንዲፈጭ አዘጋጀ፡፡ 2. ለቤት ህንፃ የሚሆን ድንጋይን ቀረፀ፥ አዘጋጀ፥ ጠረበ፡፡ 3. ነቀሰ (ጥርስን)፡፡ 4. አስለጠነ፥ ትምህርት የማይገባው ተማሪ እንዲገባው ጥረት አደረገ፡፡

**መዋቅር** ስ 1. ከዋልታ እስከ ታዛ የሚወርድ ዋና ዋና የጣሪያ እንጨት፣ ወራጅ፡፡ 2. አንድ ድርጅት የተመሰረተበት ልዩ ልዩ ክፍሎችና ውስጣዊ ግንኙነታቸው፥ አደረጃጀታቸው፡፡

**መዋቅር ዘረጋ** ልዩ ልዩ ድርጅቶችን በየደረጃው መሰረተ፥ አቋቋመ፥ አደራጀ ፡፡

**ውቃሪ** ቅ 1. ከተወቀረ ወፍጮ የሚወጣ የድንጋይ ድቃቂ፡፡ 2. እህል ከተከካ በሗላ የሚቀር ድቃቂ ፡፡

**ውቅር** ቅ 1. የጣራ ውጥን፥ ጅምር፡፡ 2. የተወቀረ (የድንጋይ ወፍጮ፥...)፡፡

**ውቅራት** ስ ንቅሳት፥ ጥቁራት ፡፡

**ተወቀረ** ግ 1. ተባ፥ ሻከረ(የወፍጮ ድንጋይ)። 2. ተጠረበ፥ ተቀረፀ (ድንጋይ)። 3. ተነቀሰ (ጥርስ)። 4. እንዲሰለጥን፥ ትምህርት እንዲገባው ተደረገ (ተማሪ)።

**ተዋቀረ** ግ 1. ተወጠነ፥ ተጀመረ፥ ተሰራ (ጣሪው)። 2. ተመሰረተ፥ ተደራጀ፥ ተቀናበረ።

**አዋቀረ** ግ 1. ወጠነ፥ ጀመረ፥ ሰራ (ጣሪውን)። 2. መሰረተ፥ አደራጀ፥ አቀናበረ ።

**ወቀሬ** ስ አጋሰስ፤ የኮርቻ ፈረስ ያልሆነ ።

**ወቀሰ** ግ 1. ባለፈ የተደረገን ጥፋት በማንሳት፥ በማስታወስ ገሰፀ፥ ነቀፈ። 2. የተፈፀመበትን በደል፥ የተሰማውን ሃዘን፥ ቅሬታ፥...እያነሳ በደሉን ላደረሰበት ወገን በምሬት ተናገረ፤ በደልከኝ አለ ።

**ወቀሳ** ስ 1. ነቀፋ፥ ተግሳፅ፥ ምክር። 2. በደል የተፈፀመበት ሰው የሚያሰማው የሃዘን፥ የቅሬታ፥ የቁጭት፥ የፀፀት፥ የብሶት ቃል፤ እሮሮ ።

**ተወቀሰ** ግ 1. ተተቸ፥ ተገሰፀ፥ ተመከረ (ባደረሰው ጥፋት፥ በደል)። 2.ወቀሳ ቀረበበት ።

**ተወቃሽ** ቅ 1. ጥፋተኛ፥ በደለኛ ተደርጎ የሚቆጠር። 2. ወቀሳ የሚቀርብበት ወይም የቀረበበት (አጥፊ፥ በደል ፈፃሚ)።

**አስወቀሰ** ግ 1. አስነቀፈ፥ አስተቸ። *ይህ ድርጊት ያስወቅሰናል*። 2. በደለኛ፥ ጥፋተኛ አስደረገ።

**ወቀጠ(ወገጠ)** ግ 1. እህልን ወይም ሌላ ነገርን በሙቀጫ ውስጥ አድርጎ ሸከሸከ፥ አደቀቀ። 2. በሃይል መታ፥ ደበደበ። 3. ቀጠቀጠ፥ አኮላሸ (የከብትን አባለዘር)።

**መውቀጫ** ስ የሙቀጫ ግልገል፥ ዘነዘና ።

**ሙቀጫ(ሙገጫ)** ስ ባንድ ጫፉ በኩል መሃሉ ከተቦረቦረ ግንድ የሚዘጋጅና በዘነዘና አማካኝነት እህልና የመሳሰሉት ነገሮች ውስጡ ተጨምረው የሚወቀጡበት የቤት እቃ።

**ሙቀጫ ቂጥ** (ስድብ) ቂጠ ትልቅ።



ሙቀጫ

**ሙቀጫ እግር** ስ (ስድብ) ከቁርጭምጭሚት እስከ ጉልበት ያበጠ፥ የወፈረ እግር ያለው።

**የሙቀጫ ልጅ** ስ ዘነዘና።

**ውቅጥ** ስ 1. በሙቀጫ የተወቀጠ፥ ያልላመ በርበሬ፤ ውቅጥ በርበሬም ይባላል። ቅ 2. የተኮላሸ (እንስሳ)።

**ተወቀጠ** ግ 1. እህል ወይም ሌላ ነገር ሙቀጫ ውስጥ ተደርጎ ተሸከሸከ፥ ደቀቀ። 2. በሃይል ተመታ፥ ተደበደበ። 3. ተኮላሸ፥ ተቀጠቀጠ (የከብት አባለዘር)።

**ወቃ** ግ 1. አበራየ፤ የእህልን ነዶ አውድማ ላይ ዘርግፎ ፍሬው ከአገዳው ወይም ከብሩ እስኪላቀቅ ድረስ ከብቶች በላዩ ላይ እየዞሩ መላልሰው እንዲረግጡት በማድረግ፥ በከብት እግር ፍሬው ከገለባው ያልተለየውን ወይም መጠኑ አነስተኛ የሆነን የእህል ነዶ በዱላ በመቀጥቀጥና ፍሬውን ከገለባው በመለየት ምርቱን ሰበሰበ። 2. አጋድሞ መታ፥ ደበደበ። 3. በሃይልና በብዛት ጣለ ወይም ዘነበ። *ዝናቡ ወቃው*።

**ውቂያ** ስ እህልን የመውቃት፥ የማበራየት ስራ።

**ተወቃ** ግ 1. ፍሬው ከአገዳው ወይም ከብሩ እስኪላቀቅ ድረስ የእህል ነዶ አውድማ ላይ ተዘርግፎ ከብቶች በላዩ ላይ እየዞሩ መላልሰው እንዲረግጡት ከተደረገ በኋላ ከገለባው እየተለየ ምርቱ ተሰበሰበ። 2. በሃይል ተመታ፥ ተደበደበ።

**ተዋቃ** ግ በዱላ ተደባደበ ።

**ወቄራ** ስ ካራ፥ ቢላዋ ።

**ወቄት** ስ የወርቅ ክብደት መለኪያ (አንድ ወቄት 28 ግራም ነው)።

**ወቅለምት(መቅለምት)** ስ ቢላዋ፥ ካራ ።

**ወቅት** ስ 1. በአየሩ ሁኔታ መለዋወጥ መሰረት ከተመደቡት የአመቱ አራት ክፍለ ጊዜያት አንዱ(የመፀው፥ የበጋ፥ የፀደይ፥ የክረምት ጊዜ)። 2. ጊዜ፥ ሰአት። *በሰርግ ወቅት የሚዘፈን ዘፈን/ በወቅቱ እንድንደርስ መፍጠን አለብን።*

**የወቅቱ ሁኔታ** በአሁን ጊዜ ያለው ሁኔታ ።

**ወቅታዊ** ቅ 1. አሁን ያለው። *ወቅታዊ ሁኔታ*። 2. ጊዜያዊ፥ ዘላቂነት የሌለው። *ወቅታዊ ችግር*።

**ወበራ**[1] ስ ሰዎች በየተራ የሚያካሂዱት የመረዳዳት ስራ፥ ደቦ ።

**ወበራ**[2] ግ 1. ወገሸ፥ በረየ። 2. ቀበጠ፥ ተቀናጣ።

**ወብራ** ቅ ቀበጥ ።

**ተወባራ** ግ ተቀናጣ፥ ቀበጠ ።

**ወበራ**[3] ግ ገረጣ፥ ደረቀ፥ ለመታጨድ ደረሰ (የገብስ፥ የስንዴ፥...ሰብል) ።

**ወበቀ** ግ ጋለ፥ ሞቀ፥ ተኮሰ፥ ላብ ላብ አለ ።

**ወበቅ** ስ ሙቀት (የአየር) ።

**ወባ** ስ በትንኝ አማካኝነት የሚተላለፍ፥ ትኩሳት ያለውና የሚያንቀጠቅጥ የበሽታ አይነት ።

**የወባ ትንኝ** ስ የወባ በሽታን የምታስተላልፍ፥ አብዛኛውን ጊዜ በቆላ አካባቢ የምትገኝ ትንኝ ።

**ወባት** ስ ለተቸገረ የሚቆም ጠበቃ ።

•**ወባት ገባ** ለተጨነቀ፥ ለተቸገረ ጥበቅና ቆመ፥ ረዳ፥ አገዘ።

**ወብራ** "ወበራ[1]" ስር ተመ.

**ወቦሸማኔ(አቦሸማኔ)** ስ ነብር የሚመስል፥

በቢሜ መደብ ጥቁር ጠቃጠቆ ያለበት የዱር አውሬ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

***ወተረ**

**ውትርትር** ቅ 1. ለመራመድ የሚፍጨረጨር፣ የሚግተረተር። 2. አልፎ አልፎ የተተከለ፥ የተታታ (አጥር፥ የቤት ጣራ፥...) ።

**ውትር ውትር አለ** ግ 1. ከአቅም ማነስ፣ ካለመቻል የተነሳ እየተንገዳገደ ለመራመድ፥ ለመሄድ ሞከረ። 2. ተፍጨረጨረ፥ ተግተረተረ።

**ተውተረተረ** ግ 1. ተፍጨረጨረ፣ ተግተረተረ። 2. አልፎ አልፎ ተተከለ፥ ተታታ።

**አውተረተረ** ግ 1. የማድግዳን፥ የአጥርን እንጨት አልፎ አልፎ ተከለ፣ አያያዘ። 2. እንደ ነገሩ ለመስራት ሞከረ፥ ተፍጨረጨረ፣ አውተፈተፈ።

**ወተር** ስ የሽረሪት ድር ።

**አውታር** ስ 1. የጀልባ፥ የድንኳን፣ የቀስት መወጠሪያ ገመድ። 2. የድርጅት፣ የተቋም፣ ... የተለያየ ቅርንጫፍ። *ድርጅቶቹ ብዙ የማከፋፈያ አውታሮችን ዘርግተዋል* ።

***ወተበተበ**

**ውትብትብ** ቅ የተውተበተበ፣ የተሳሰረ፣ የተያያዘ፥ የተጠላለፈ ።

**ተውተበተበ** ግ ተሳሰረ፥ ተያያዘ፣ ተጠላለፈ።

**አውተበተበ** ግ አስተሳሰረ፥ አያያዘ፣ አጠላለፈ።

**ወተት** ስ 1. አጥቢ እንስሳት ልጆቻቸውን በጡት አማካይነት የሚመግቡት ወይም በተፈጥሮ ከሚገኘው ጋር ተመሳሳይ ይዘት እንዲኖረው ተደርጎ በዱቄት መልክ የሚሰራና ተበጥብጦ የሚጠጣ ነጭ ፈሳሽ። 2. ከቁልቋል፣ ከቅንጭብ ወይም ከሌላ እፅዋት የሚወጣ ነጭ ፈሳሽ።

**ወተት ነው** (ዘይ.) 1. የዋህ፥ ገር ነው። 2. ቀላል ነው። *ፈተናው ወተት ነው* ።

**ወተት ይመስላል** በጣም ነጭ ነው ።

**ወተቴ** ስ ገራም የሆነች የፈንጣጣ አይነት የምትጠራበት የቁልምጫ ስም ።

**ወተት አንጀት** ስ የአንጀት አንዱ ክፍል ።

**የወተት ጥርስ** ስ ሌላ በማብቀል የሚተካ ጊዜያዊ የልጅነት ጥርስ ።

**ወተወተ** ግ 1. ያለማቋረጥ ለፈለፈ፥ ብዙ አወራ። 2. ጎተጎተ፥ ደጋግሞ ተናገረ፣ አሳሰበ ።

**ውትወታ** ስ ጉትጎታ ።

**ወተፈ** ግ 1. ጨርቅን ወይም ሌላ ነገርን በመክተት ቀዳዳን፥ ሽንቁርን ደፈነ። 2. ሻጠ፣ አስገባ፥ ቀረቀረ ።

**ወታፋ** ቅ 1. (ስድብ) አቅመ ቢስ፣ ደቃቃ። 2. ከተጠላበት ቤት የማይወጣ፣ የማይጠፋ ።

**ውታፍ** ስ 1. የጠርሙስ አፍ ወይም የሌላ ሽንቁር ነገር መክደኛ። 2. የሌላውን ሰው ስራ ለመሸፈን በምትክነት የገባ ወይም የሚገባ ።

**ውትፍትፍ(ወተፍታፋ)**ቅ የማይረባ፣ ውሽልሽል ስራ።

**ውትፍትፍ አለ** ግ ውሽልሽል አለ፣ ጥበቀት የሌለው ሆነ ።

**ተወተፈ** ግ 1. ተሸጎጠ፣ ተከደነ። 2. ገባ፣ ተቀረቀረ ።

**ተወታተፈ** ግ ጥበቀት በሌለው፣ በማይረባ ሁኔታ ተሰራ ።

**ተውተፈተፈ** ግ የማይረባ፥ መናኛ፣ ጥበቀት የሌለው ስራ ሆነ ።

**አውተፈተፈ** ግ ጥበቀት በሌለውና በማይረባ አኳኋን ሰራ ።

**ወታቦ** ስ 1. እንደ ቁና ባለ ቅርፅ ከጭቃ ተዘጋጅቶና በእበት ተለቅልቆ ለእህል፥ ለጥራጥሬ መያዣ ወይም ማስቀመጫ የሚሆን እቃ። 2. (ስድብ) ክፍት አፍ። 3. (ዘይ.) መልከ ጥፉ፣ ቅርፀቢስ፥ ፉንጋ።

**ወታደር** ስ በፖሊስ ወይም በጦር ሰራዊት ውስጥ ገብቶ የሚያገለግል መለዮ ለባሽ ።

**ወታደራዊ** ቅ በወታደሩ ክፍል ያለ ወይም የሚካሄድ፥ የወታደር። *ወታደራዊ ሰልፍ*፡

**ወታደራዊ መንግስት** ስ ከወታደሩ ክፍል ተውጣጥቶ የአገሪቱን አመራር በሃይል በመያዝ የሚቋቋም መንግስት ።

**ወታደራዊ ሰላምታ** ስ ወታደር እጁን ወደ ግንባሩ አካባቢ በማውጣት የሚያሳየው የአክብሮት መግለጫ፣ ሰላምታ ።

**ወታደራዊ ሰልፍ** ስ የወታደሩ ክፍል በልዩ ልዩ የጦር መሳሪያዎች እየታጀበ የሚያሳየው የሰልፍ ትርኢት ።

**ወታደራዊ ትምህርት** ስ መከላከልን፣ ጠላት ማጥቃትን፣ የውጊያ ስልትን የመሳሰለ ትምህርት።

**ወታደራዊ አስተዳደር** ስ ህዝባዊ ውክልና በሌለው የወታደሩ ክፍል የበላይነት የሚካሄድ የሃገር አስተዳደር ።

**ወታደራዊ አገዛዝ** ስ ከወታደሩ ክፍል የወጡ ጥቂት ሰዎች የመንግስት ስልጣን በሃይል ከነጠቁ በሂላ የሚያካሂዱት የሃይልና የጭቆና አስተዳደር ።

**ወታደራዊ ካምፕ** ስ የወታደሩ ክፍል አባላት የሚሰበሰቡበት፥ ትምህርት የሚያካሂዱበት፣ የሚኖሩበት፥ መሳሪያ የሚያስቀምጡበት ግቢ፣ ካምፕ።

**ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት** ስ በሌላ ሃገር

ጉዳይ ውስጥ በጦር ሃይል ጭምር የሚደረግ ጣልቃ ገብነት ::

**ወታፋ** **"ወተፈ"** ስር ተመ .

**ወትሮ** ተው.ግ 1. ቀድሞ፥ በፊት:: 2. ዘወትር፡ ሁልጊዜ :: *ወትሮ በዚህ ሰአት እዚህ ይገኝ ነበር::*

**ያለወትሮው** ያለልማዱ:: *ያለወትሮው ዛሬ በጧት መጣ* ::

**ወነበደ** ግ 1. ወንበዴ፥ ቀማኛ፥ ዘራፊ ሆነ::2. ስራ ፈት፥ ዘዋሪ፥ ዱርዬ ሆነ:: 3 ደነበረ፥ ሸሸ፥ ሮጠ፥ አመለጠ (ከብት) ::

**ወንበዴ** ስ ቀማኛ፡ ዘራፊ፡ ሽፍታ ::

**ውንብድና** ስ ሽፍተ፡ ቅሚያ፥ ዝርፊያ ::

**ተወነባበደ** ግ ተሳሳተ፥ ተምታታ፡ ተጭበረበረ፡ ተደነጋገረ::

**ተወናበደ** ግ 1. ተደናበረ፥ ተደናገረ:: 2. ተሳሳተ፥ ተምታታ ::

**አወናበደ** ግ 1. አደናበረ፥ አደናገረ:: 2. አሳሳተ፥ አምታታ፡ አጭበረበረ:: 3. የሃሰት ወሬ፡ ፕሮፓጋንዳ ነዛ ::

**አወናባጅ** ቅ አታላይ፥ አጭበርባሪ ::

***ወነከረ**

**ወንካራ** ቅ ሲሄድ የሚንገዳገድ፡ የሚወላገድ፥ ድክድክ የሚል ::

**ውንክርክር** ቅ ውልግድግድ ::

**ተወናከረ** ግ 1. ተወላገደ፡ ተንገዳገደ፡ ተውተረተረ:: 2. አቋቋሙ የተወላገደ ሆነ (ግድግዳው፡ አጥሩ፡...) ::

**አወናከረ** ግ አወናገረ፡ አውተረተረ::

***ወነወነ**

**ውን ውን አለ** ግ ተነቃነቀ፡ ተወዛወዘ ::

**ውን ውን አደረገ** ግ አወዛወዘ፡ አነቃነቀ ::

**ተወናወነ** ግ ተወዛወዘ፡ ተነቃነቀ ::

**አወናወነ** ግ አወዛወዘ፡ አነቃነቀ (ጅራቱን)::

**ወነጀለ** ግ በተፋት፡ በወንጀል ከሰሰ፡ በደለኛ አደረገ (በሃሰት ወይም በእውነት) ::

**ወንጀል** ስ 1. ህገወጥ የሆነ ተግባር (እንደ ሌብነት፥ ግድያ፥...የመሳሰለ):: 2. ጥፋት፡ በደል፥ ስህተት ::

**ወንጀል ሰራ/ፈፀመ** ህገወጥ የሆነ ድርጊት፡ ጥፋት ፈፀመ ::

**የወንጀል ችሎት** ስ የወንጀል ክስ የሚታይበት ችሎት ::

**ወንጀለኛ** ስ የወንጀል ድርጊት፥ ጥፋት የፈፀመ ሰው (ስርቆት፥ እምነት ማጉደል፥ ግድያ፥...)::

**ወንጀለኛ መቅጫ [ህግ]** ስ የወንጀል አይነቶችንና የሚያስከትሉትን ቅጣት የሚዘረዝር ደንብን ወይም ህግን የያዘ መፅሃፍ::

**ወንጃይ** ቅ 1. ከናኝ፥ ስም አጥፊ:: 2. ከሳሽ::

**ተወነጀለ** ግ ህግ በመጣስ፥ ወንጀል በመፈፀም ተከሰሰ፤ በደለኛ፥ ጥፋተኛ ተባለ::

**አስወነጀለ** ግ አስጠየቀ፥ አስከሰሰ:: *ሰዎችን ለማዳን ያደረግሁት አያስወነጅለኝም*::

**ወነገ** ግ ወዘወዘ፥ አንቋለጠ::

**ውንግ ውንግ አለ** ግ ተወዛወዘ፥ ተነቃነቀ::

**ተወነገ** ግ ተወዛወዘ፥ ተነቃነቀ (ከወገቡ፥ ከጅራቱ፥...) ::

***ወነጠ**

**ውንጥ ውንጥ አለ** ግ ውልምጥ ውልምጥ አለ::

**ተወነጠ** ግ ተወነገ፥ ተወዘወዘ::

**ወነጨፈ** ግ ድንጋይን በወንጭፍ ወረወረ::

**ወንጭፍ** ስ 1. ከጠፍር ወይም ከገመድ የሚሰራ የድንጋይ መወርወሪያ::2. የ**"ወስፈንጥር"**ን 2ኛ ፍቺ ተመ.



ወንጭፍ

**ተወነጨፈ** ግ ተወረወረ፤ ፈጥኖ ሄደ፥ አለፈ፥ ተራመደ፥ ተምዘገዘገ ::

**ተወናጨፈ** ግ 1. ተወራጨ፥ ተፈራገጠ:: 2. ተወረወረ፥ ተምዘገዘገ፥ ተፈናጠረ ::

**አወናጨፈ** ግ 1. አወራጨ፥ አፈራገጠ:: 2. ወረወረ፥ አምዘገዘገ፥ አፈናጠረ ::

***ወነፈለ**

**ወንፈል** ስ በገጠር አካባቢ በየተራ የሚደረግ የመረዳዳት ስራ፤ ደቦ (በግብርና፥ በፈትል፥...)::

**ወንፈል አወጣ** ቀደም ሲል በስራ ያገዘውን ወይም የረዳውን ሰው በተራው አገዘ፥ ረዳ፥ ብድሩን መለሰ::

**ወንፈለኛ** ቅ ወንፈል ያለበት፥ የወንፈል ስራ ማህበርተኛ፥ በበኩሉ ባለተራውን በስራ የሚረዳ::

**ተወናፈለ** ግ በየተራ በስራ ተረዳዳ (የግብርና፥የፈትል፥...ስራን በመስራት)::

**አወናፈለ** ግ አገዘ፥ የወንፈል ስራን ሰራ::

**ወና (አና)** ቅ ባዶ፥ ምንም የሌለበት (ቤት፥ በታ)::

**ወና ሆነ** ባዶ ሆነ (ቤት፥ በታ)::

**ወናሄ** ስ ፍሬው ነጭ የሆነ የዛፍ አይነት ::

**ወናሄ ይመስላል** ነጭ ነው:: *ጥርሱ ወናሄ ይመስላል*::

**ወናፍ** ስ 1. ጨበጥ ለቀቅ ሲያደርጉት ወደ ውስጥ

እየሳበ መልሶ በሚያስወጣው የአየር ግፊት የእጅ ባለሙያዎች (ቢላዋ፡ ማረሻ፡...ሰራተኞች) ብረታ ብረቶችን ለማጋል የሚጠቀሙበትን ከሰል የሚያፍሙበት፡ የአየር ማስገቢያና ማስወጫ ጠባብ ቧንቧ የተገጠመበት ስልቻ። 2. (ዘይ.) ወሬኛ ።

**ወኔ** ስ ድፍረት፡ ልበ ሙሉነት፡ አስፈሪ ነገርን፡ መከራን ለመጋፈጥና ለመቋቋም የሚያስችል የቆራጥነት ስሜት።

**ወኔ የለውም** ቆራጥነት፡ ድፍረት የለውም፡ ፈሪ ነው።

**ወኔው ሸና** ፈራ፡ አሞቱ ፈሰሰ ።

**ወኔው ተቀሰቀሰ** የቆራጥነት፡ የጀግንነት ስሜቱ ተነሳሳ ።

**ወኔ ቢስ** ቅ ፈሪ፡ ቆራጥነት፡ ድፍረት የሌለው ።

**ወንበላ** ስ በቆላና በወይና ደጋ የሚበቅል፡ ፍልጡ ለማገዶነት የሚያገለግል ዛፍ ።

**ወንበር** ስ 1. ከእንጨት፡ ከብረት፡...የሚሰራ፡ ለመቀመጫነት የሚያገለግል እቃ። 2. ዳኛ (ለምሳሌ፡- የግራ ወንበር፡ የቀኝ ወንበር)። 3. ከኋላ በመቀመጫ በኩል ያለ የተንፋነፋ ሱሪ ክፍል። 4. ትምህርት። *ወንበር ተዘርግቷል።*

**ወንበር ተከለ** (ቤ.ክህ.) ማስተማር ወይም መማር ያዘ ፡ ጀመረ።

**ወንበር ተዘረጋ** (ቤ.ክህ.) ትምህርት ተጀመረ።

**ወንበር ታጠፈ** (ቤ.ክህ.) የትምህርት ጊዜ አበቃ፡ አቆመ።

**ወንበር ዘረጋ** "**ወንበር ተከለ**" ን ተመ.

**ወንበር ያሞቃል** ያለምንም ስራ ተቀምጦ ይውላል።

**ወንበር ገፉ** ባለተራው ያስተጓጎለውን፡ ያላሟላውን ስራ ተከታዩ ተረኛ አሟላ፡ሰራ።

**ወንበር ገፍ (ገፌ)** ስ በተረኛው ምትክ የሚሰራ፡ የሚከፍል፡ተከታይ ተረኛ ።

**ወንበርተኛ** ስ (ቤ.ክህ.) አንድ አይነት ትምህርት በአንድነት አብሮ የሚማር የትምህርት ጓደኛ።

**ወንበዴ** "**ወነበደ**" ስር ተመ.

**ወንካራ** "***ወነከረ**" ስር ተመ.

**ወንዘረጭ** ስ ጅራቱ ረጅም ወፍ።

**ወንዝ** ስ ተፈጥሮአዊ የሆነ፡በሰፊ በይ እየወረደ ወደ ባህር፡ ወደ ሃይቅ፡... የሚገባ ወይም ከሌላ ወንዝ ጋር የሚቀላቀል ወራጅ ውሃ።

**ወንዝ አድምቅ** ስ በወንዝ ዳር፡አካባቢ የሚበቅል የእፅዋት አይነት።

**የወንዝ ልጅ** የአካባቢ፡ የአገር ልጅ።

**የወንዝ አሞቴ** ስ ረዘም ያለ ቅልጥምና መንቁር ያለው፡ መልኩ ጥቁር ቡናማ የሚመስል፡ በወንዝ አካባቢ የሚገኝ የአሞራ አይነት(ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)።

**ወንድ** ቅ 1. ከሴት የሚለይበት ተፈጥሮአዊ የፆታ ምልክቶች (ለምሳሌ. ፂም ወይም ሌሎች መለያዎች) ያሉት ሰው ወይም ሌላ ሕያው ፍጡር፡ እንስሳ። 2. (ዘይ.) ጎበዝ፡ ጀግና ።

**ወንድ ወጣው** ስ ጎበዝ፡ በረታ ።

**ወንደላጤ** ስ ያላገባ ወንድ ።

**ወንዳ ወንዴ** ስ ማጠፊያ የሌለው የገጠር ቤት ሳንቃ (መዝጊያ) ከላይ ከጉበኑ፡ ከታች ከደፉ ላይ ተሰክቶ በመቆም ያለችግር እንዲከፈትና እንዲዘጋ የሚረዳ፡ በሳንቃው የላይና የታች ጠርዝ ጫፍ ላይ እንደ ቀንድ ሾል ሾል ተደርጎ የሚሰራ የሳንቃው አካል ።

**ወንዳ ወንድ** ቅ 1. ወንድ፡ ጀግና። 2. በሰውነት አቋሟ ወይም በባህርይዋ ወንድ የምትመስል (ሴት)።

**ወንዳ ገረድ** ስ 1. የወንድና የሴት ተፈጥሮአዊ የፆታ ምልክት ያለው፡ ፍናፍንት። 2. (ስድብ) ሴታሴት የሆነ ጠባይ ያለው ወንድ ።

**ወንድ አያት** ስ የእናት ወይም የአባት አባት።

**የወንዶች ገና** ስ የገና በአል የሚከበርበት እለት (ወንዶች የገና ጨዋታ የሚጫወቱበት ስለሆነ የወንዶች ገና ተባለ) ።

**ወንዲላ** ቅ በቅርፅ ወይም በጠባይ የወንድ ባህርይ ያላት፡ ወይም የቤት ባልትና የሌላት (ሴት)።

**ወንዴ** ቅ የወንድ ፆታ ያለው (ለሰው፡ ለእንስሳም ሆነ ለእፅዋት ይነገራል) ።

**ወንድም** ስ 1. አንድ ሰው ከእናቱ ወይም ከአባቱ ወይም ከሁለቱም ከሚወለደው ወንድ ልጅ ጋር ያለው ዝምድና መጠሪያ። *ልጅቱ ከእናትና ከአባቷ የተወለደ አንድ ወንድም ብቻ አላት*። 2.የአክስት ወይም የአጎት ወይም የቅርብ ዘመድ ወንድ ልጅ።3. እንደ እናት ልጅ የሚቆጠር ጥሩ ጓደኛ። 4. በእድሜ ተመጣጣኝ የሆነን ወይም አነስ የሚልን ሰው በአክብሮት ለመጥራት የሚያገለግል ቃል። *ወንድም ስንት ሰአት ነው?*

**ወንጀለኛ** "**ወንጀለ**" ስር ተመ.

**ወንጀል** ዝ.ከ.

**ወንጃይ** ዝ.ከ.

**ወንጌል** ስ በሃዲስ ኪዳን ውስጥ ከተካተቱትና ስለኢየሱስ ክርስቶስ ታሪክ፡ ትምህርትና ተአምራት ከሚተርኩት የመጀመሪያዎቹ አራት መፃህፍት አንዱ ወይም አራቱ።

**ወንጌላዊ**(ብ.ቁ.**ወንጌላውያን**) ስ የወንጌል መምህር፡ ሰባኪ።

**ወንጠፍት** ስ እንደ ወንፊት ሆኖ የሚሰራ ለፈሳሽ ማጥለያነት የሚያገለግል እቃ፣ ማጥሊያ::

**ወንጭፍ** "ወነጨፈ" ስር ተመ.

**ወንፈለኛ** "*ወነፈለ" ስር ተመ.

**ወንፈል** ዝ.ከ.

**ወንፊት** ስ 1. እህልን ወይም ዱቄትን ለመንፋትና ተፈላጊውን ከማይፈለገው ለመለየት የሚያገለግል ከአክርማ፣ ከስንደዶ፣ ከግራምጣ ወይም ከሽቦ ተታቶ የሚሰራ እቃ:: 2. (ዘይ.) ወሬኛ ::

**ወከለ** ግ ለንብረቱ ወይም ለስራው እንደ ራሱ ሆኖ እንዲሰራለት የሚተማመንበትን ሰው መርጦ መደበ፣ ተካ፣ ሃላፊ አደረገ::

**ወኪል** ስ እንደ ዋናው ሆኖ የሚሰራ ተጠሪ፣ ሃላፊ፣ ዋናውን ተክቶ እንዲሰራ የተመረጠ ሰው፣ አካል ::

**ውክልና** ስ ለአንድ ሰው ወይም ድርጅት ወኪል፣ ተጠሪ መሆን ::

**ተወከለ** ግ 1. ተጠራ፣ ወኪል ሆነ:: 2. አንድን ህዝብ ወክሎ በምክር ቤት፣ በስብሰባ፣...ተገኘ ::

**ተወካይ** ቅ አንድን ግለሰብ፣ ድርጅት፣ ሃገር፣ ህዝብ፣ ... የሚወክል ተጠሪ ::

***ወከበ**

**ተዋከበ** ግ ተጣዳፈ፣ ተቻኮለ፣ ግራ ተጋባ ::

**አዋከበ** ግ አጣደፈ፣ አቻኮለ፣ ግራ አጋባ ::

**ወከክ**

**ወከክ አለ** ግ 1. ተሰነጠቀ፣ ተተረተረ:: 2. በድንጋጤ ወይም በደስታ ልቡ ተሰነጠቀ፣ ክው አለ::

**ወኪል** "ወከለ" ስር ተመ.

***ወካ**

**ውካታ(ዋካታ)** ስ መደማመጥ የሌለበት፣ የብዙ ሰው ንግግር፣ ወሬ፣ ጩሀት ::

**ተዋካ** ግ እርስ በርሱ እየተንጫጫ፣ ሳይደማመጥ አወራ፣ ተነጋገረ ::

**አወካ** ግ አወራ፣ ተንጫጫ፣ ሳይደማመጥ ተነጋገረ ::

**አውካካ** ግ እየተሳሳቀ፣ እየተንጫጫ አወራ፣ ተጫወተ ::

**ወዘላ** ስ የአካል፣ የቁመና ውበት::

**ወዘበሬታ** ስ ቧልት፣ የጨዋታ፣ የቀልድ ንግግር::

**ወዘተ** ግ 1. ውሃን ወይም ሌላ ነገርን ለማሞቅ በጣሳ፣ በማንቆርቆሪያ፣ በማሰሮ፣... እሳት ዳር አስቀመጠ፣ ጣደ:: 2. ተሰርቶ ማለቅ የሚገባውን ሳይሰራ አስቀመጠ፣ ወዘፈ::

**ወዘት** ስ የእሳት ዳር ወይም የምድጃ ሙቀት::

**ውዝት** ቅ ከተቀመጠበት የማይነሳ፣ ውዝፍ፣ ሰነፍ::

**ተወዘተ** ግ 1. እንዲሞቅ፣ እንዲሾቅ ወይም እንዲበስል በማሰሮ፣ በጣሳ፣... ተደርጎ በእሳት ዳር ተቀመጠ፣ ተጣደ:: 2. ሳይንቀሳቀስ ስራፈቶ ተቀመጠ፣ ተጎለተ፣ ተወዘፈ::

**ወዘተርፈ**(በአህፅሮት ሲፃፍ ወዘተ.) ተው.ግ. የመሳሰሉት፣ የተቀሩትም ለማለት የሚያገለግል ቃል:: *ላልኮል ነክ የሚባሉ መጠጦች አረቄ፣ ኮኛክ፣ ወዘተ. ናቸው::*

**ወዘና** ስ ውበት፣ ደምግባት፣ ለዛ::

**ወዘናቢስ** ቅ ችኮ፣ ለዛቢስ::

**ወዘወዘ** ግ 1. ነቀነቀ:: 2. አንገላታ ::

**ውዝዋዜ** ስ የእስክስታ፣ የዳንስ እንቅስቃሴ::

**ተወዘወዘ** ግ ተነቃነቀ፣ ወዲህ ወዲያ አለ፣ ሄደ፣ ተንቀሳቀሰ::

**ተወዛወዘ** ግ 1. ተወዘወዘ:: 2. እስክስ አለ፣ ደነሰ::

**ተወዛዋዥ** ቅ 1. ተነቃናቂ፣ ወዲያ ወዲህ እያለ የሚንቀሳቀስ:: ስ 2. እስክስታ ወራጅ፣ ደናሽ::

**አወዛወዘ** ግ አነቃነቀ፣ ወዲያ ወዲህ አንቀሳቀሰ::

**ወዘፈ** ግ 1. ጎለተ፣ አስቀመጠ:: 2. በየጊዜው ሳይፈፅም አስቀመጠ፣ አከማቸ (ስራን)::

**ወዘፍ** ቅ 1. ስራ የማይሰራ፣ ዝም ብሎ መቀመጥ የሚወድ ሰነፍ:: 2. በአጥር መልክ እንዲያገለግል እየተቆረጠ የተጋደመ እሾሃማ እንጨት::

**ውዝፍ** ቅ 1. (ስድብ) ሰነፍ፣ ከተቀመጠበት የማይነሳ:: 2. ሳይከፈል የቀረ፣ የተጠራቀመ:: *ውዝፍ እዳ*: 3. ያልተሰራ ወይም ሳይሰራ የቀረ (ስራ)::

**ተወዘፈ** ግ 1. ተጎለተ፣ ተቀመጠ:: 2.በጊዜው ሳይከፈል ተጠራቀመ (እዳ):: 3.በየጊዜው ሳይሰራ፣ ሳይከናወን ቆየ፣ ተቀመጠ (ስራ)::

**ወዛ** ግ 1. ወዙ ወይም ላቡ ወረደ፣ ፈሰሰ:: 2. ቅባት የተቀባ መሰለ::

**ወዝ** ስ ፊት ላይ ወይም ሌላ ነገር ላይ ቅልጥልጥ ብሎ የሚታይ ላበት፣ ቅባት::

**ወዝ የሌለው** የማይጥም፣ ደስ የማይል (ጨዋታ፣ ንግግር፣...)::

**ወዝ አደር** "ላብ አደር" ን ተመ.

**ወዛም** ቅ መልኩ ያወለወለ፣ የማረበት::

**ተወዛዛ** ግ ቅባት ተቀባ፣ ተባበሰ::

**ኣወዛ** ግ ወዝ ሰጠ፡ በቅባት ኣሳመረ ።

***ወዛገበ**

**ውዝግብ** ስ ንትርክ፡ ኣተካራ፡ ጭቅጭቅ ።

**ተወዛገበ** ግ ተጨቃጨቀ፡ ተጣላ፡ ተነታረከ።

**ኣወዛገበ** ግ ኣጣላ፡ ኣጨቃጨቀ፡ ኣነታረከ።

**ኣወዛጋቢ** ቅ ኣጨቃጫቂ፡ ኣነታራኪ። *ጉዳዩ ኣወዛጋቢ እየሆነ ሄደል።*

**ወዝ** **"ወዛ"** ስር ተመ.

**ወየበ** ግ 1. ቢጫ ሆነ። 2. ወደ ቢጫነት ተለወጠ፡ ተበላሸ (ሰብል)።

**ወይባ** ስ 1. ቢጫ ቅርፊት ያለው የዛፍ አይነት። 2. ቢጫ ቀለም የተነከረ የባህታዊ ልብስ።

**ወይባ ቀለም** ስ ቢጫ ቀለም።

**ወየው(ወዮ)** የሃዘን ስሜት መግለጫ ቃል። *ጓደኛው የሞተ እለት ወየው እያለ ሲያለቅስ ነበር።*

**ወያኔ** ስ 1. ሽፍቶ በረሃ የገባ ኣመፀኛ፡ ጦር ጠማሽ 2. ለግዳይ ሲል ጦርነት የሚገጥም ሰው።

**ወይ[1]** አንድ ሰው የሌላውን ሰው ስም በሚጠራበት ጊዜ ተጠሪው አቤት፡ አለሁ ለማለት ለጠሪው የሚመልሰው ወይም የሚያሰማው ቃል (ጠሪው ልጅ ወይም የእድሜ ጓደኛ ካልሆነ ግን በወይ ፈንታ አቤት ወይም እመት ይባላል፡ በማቆላመጥ ለመናገር "ወዬ" ይባላል)።

**ወይ[2]** የጥያቄ ማቅረቢያ ቃል። *ልጁ መጣ ወይ?* መገረምን፡ አድናቆትን መግለጫ ቃል። *ወይ ጉድ/ ወይ ግሩም።* 2. የ"**ወይም**"ን ፍቺ ተመ.

**ወይ ነዶ** እንዴት ያናድዳል።

**ወይኔ** የጭንቀትና የቁጭት ስሜትን ለመግለፅ የሚነገር ቃል። *ወይኔ ተበላሸሁ/ወይኔ ጉድ መጣብኝ!*

**ወይ ጉድ** መገረምን፡ መደነቅን ለመግለፅ የሚነገር ቃል። *ወይ ጉድ! የሰው ልጅ ጨረቃ ላይ ወጣ?*

**ወይም(ወይንም፡ወይ)** መዋ. አማራጭን ለመጥቀስ የሚያገለግል ቃል፡ ለጥያቄ ሲሆን "ወይስ" ይሆናል። *ቀዩን ወይም ጥቁሩን ባርኔጣ ስጠኝ /ወይ እኔ ወይ አንተ እንሄዳለን/ ትመጣለህ ወይስ ትቀራለህ?*

**ወይራ** ስ 1. ጪሱ ለጋን፡ ለእንስራ፡...ማጠኛ እንጨቱ ለተለያየ ተግባር የሚውል ጠንካራ ዛፍ። 2. (ዘይ.) ብርቱ፡ ጠንካራ (ሰው)።

**የወይራ ዘይት** ስ ከወይራ የሚዘጋጅ ዘይት።

**ወይስ** **"ወይም"** ን ተመ.

**ወይባ** **"ወየበ"** ስር ተመ.

**ወይና ደጋ** ስ በቆላና ደጋ መካከል የሆነ፡ አየሩ ቀዝቃዛና ነፋሻነት ያለው አካባቢ፡ አገር።

**ወይና ግፍት** ስ ለመድሃኒትነት ያገለግላል የሚባል፡ ሽታ ያለው የእፅዋት አይነት።

**ወይኔ** **"ወይ[3]"** ስር ተመ.

**ወይን** ስ ተጠጋግተውና በብዛት እጅብ ብለው ወደታች የሚንዠረገጉ ጣፋጭ ፍሬዎችን የሚያፈራ፡ በቆላና በወይና ደጋ አካባቢ የሚገኝ፡ ግንዱ እንደሃረግ ያለ ስለሆነ ራሱን ችሎ የማይቆም የተክል አይነት፡ ፍሬውም ወይን ይባላል።

**ወይኖ** ቅ ወይንማ፡ የበሰለ የወይን ፍሬ የመሰለ ቀለም ያለው ።

**ወይን ጠጅ** ስ 1. ከወይን ጭማቂ የሚዘጋጅ መጠጥ። ቅ 2. የበሰለ ወይን የሚመስል ቀለም ያለው ።

**የወይን ዘለላ** ስ በአንድነት እጅብ ብለው በቅርንጫፋቸው ላይ የተንዠረገጉ የወይን ፍሬዎች ስብስብ።

**ወይንማ** ቅ የወይን ፍሬ የሚመስል ቀለም ያለው፡ ወደ ሰማያዊነት የሚያደላ የሃምራዊ ቀለም አይነት።

**ወይንም** **"ወይም"** ን ተመ.

**ወይንጠጅ** **"ወይን"** ስር ተመ.

**ወይኖ** ዝ.ከ.

**ወይዘሮ** (ብ.ቁ.. **ወይዛዝርት**) ስ ያገባች ሴት የምትጠራበት የአክብሮት ስም።

**ወይዘሪት** ስ ያላገባች ሴት የምትጠራበት የአክብሮት ስም።

**ወይድ** **"*ወገደ"** ስር **"ወግድ"** ን ተመ.

**ወይጉድ** **"ወይ[3]"** ስር ተመ.

**ወይፈን** ስ ከጥጃ ከፍ፡ ከበሬ አነስ ያለና ያልተቀጠቀጠ ወንድ ከብት ።

**ወዮ** **"ወየው"** ን ተመ.

**ወደ** መዋ. መድረሻን ለመጠቆም የሚያገለግል ቃል። *ወደ አዲስ አበባ ሄደ /ወደ ማታ እመጣለሁ።*

**ወደለ[1]** ግ ወፈረ፡ ጠበደለ ።

**ወደላ** ቅ (የጥላቻ አነ.) ጠብደል፡ ወፍራም ።

**ወደል** ዝ.ከ.

**ኣወደለ** ግ ኣወፈረ፡ ኣጠበደለ ።

**ወደለ[2]** ግ ከኮርቻ ሂላ ጫነ፡ አሰረ።

**ወዴላ** ስ 1.ከኮርቻ በስተሂላ የሚውል፡ ከበቅሎና ከፈረስ ጅራት ስር የሚገባ፡ ከወደመታጠፊያው በኩል በጨርቅ ትልታይ ወይም

በለስላሳ ቆዳ የተሸፈነ፡ የተደገለለ ጠፍር፡ አቡነ ዘለብ። 2. የጋማ ከብቶች ጭነት በሚጫኑበት ጊዜ ከጅራታቸው ስር የሚገባው ጠፍር ፡ ለቢቻ።

**ውዴላ** ስ ከኮርቻ ደሃራይ በስተሂላ የምትታሰር አነስተኛ ጭነት ።

**ወደላ "ወደለ[1]"** ስር ተመ.

**ወደል** ዝ.ከ.

**ወደመ** ግ ጠፋ፡ አለቀ፡ እልም አለ፡ ተበላሸ።

**አወደመ** ግ አጠፋ፡ ጨረሰ፡ አበላሸ።

**ወደረ** ግ 1. እንዳይሄድ ወይም እንዳይራገጥ የከብት እግርን አሰረ፡ ቀየደ። 2. ሳበ፡ ወጠረ፡ ገተረ ።

**ወደሮ** ስ ገመድ።

**ተወደረ** ግ 1. (የከብት እግር) እንዳይሄድ፡ እንዳይራገጥ ታሰረ፡ ተቀየደ። 2. ተሳበ፡ ተወጠረ፡ ተገተረ።

***ወደረ**

**ወደረኛ** ቅ 1.ተተካካይ፡ ተመሳሳይ፡ ተነፃፃሪ፡ ተወዳዳሪ። 2. ተቃራኒ፡ ተፃራሪ ።

**ወደረኛ መስተፃምር** ስ (ሰዋ.) ራሳቸውን ችለው መቆም የሚችሉ አረፍተ ነገሮችን የሚያጣምር፡ የሚያያይዝ፡ የሚያጫፍር ቃል ወይም ምእላድ (ለምሳሌ አበበና ወርቁ ነገ ይመጣሉ /እኔ ረጅም ነኝ፡ እሱ ግን አጭር ነው። በሚሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ "ና" እና "ግን" ወደረኛ መስተፃምር ናቸው)።

**ወደር** ቅ እኩያ ፡ አቻ። *ወደር የለውም።*

**ውድድር** ስ ፉክክር፡ ለአንድ ነገር የሚደረግ ሽሚያ።

**ተወዳደረ** ግ ተፎካከረ።

**አይወዳደርም** የላቀ፡ የበለጠ ነው። *የስእል ችሎታው ከማንም አይወዳደርም።*

**ተወዳዳሪ** ቅ 1. አቻ። 2. ተፎካካሪ ። *ተወዳዳሪ የለውም ።*

**አወዳደረ** ግ 1. አነፃፀረ፡ አስተያየ። 2. አፎካከረ።

**ወደሮ "ወደረ"** ስር ተመ.

***ወደሰ**

**መወድስ** ስ 1. ባለስምንትና ባለዘጠኝ ቤት የሆነ የቅኔ አይነት። 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ .) እሁድ እሁድ ሌሊት በቤተክርስቲያን የሚዜም፡ የሚደረስ የምስጋና ፀሎት።

**ውዳሴ** ስ ብዙውን ጊዜ ለአምላክ የሚቀርብ ምሲጋና፡ ሙገሳ ።

**ውዳሴ ከንቱ** ስ ተገቢ ያልሆነ ምስጋና፡ ሙገሳ።

**ተወደሰ** ግ ተመሰገነ፡ ተሞገሰ ።

**አወደሰ** ግ አመሰገነ፡ አሞገሰ ።

**ወደቀ** ግ 1. በሌላ ሃይል ምክንያት ወይም የራሱን ሚዛን ባለመጠበቅ ከላይ ወደታች በመወርወር እምድር ላይ አረፈ፡ ተጋደመ፡ ተፈጠፈጠ። 2. ደሀየ፡ ከሰረ፡ ተንኮታኮተ (በንግድ፡ በኢኮኖሚ፡...) ። 3. ዋጋው ቀነሰ፡ ረከሰ። 4. አረፈ። *የቤተሰቡ ሃላፊነት እርሱ ላይ ወደቀ*። 5. ወደሚቀጥለው ደረጃ ሳይሸጋገር ቀረ። *ተማሪው በትምህርቱ ወደቀ።* 6. በሰው ወይም በአካባቢው ላይ ደረሰ፡ መጣ፡ ወረደ (አደጋ፡ በሽታ፡ መብረቅ፡...)። 7. ተቀባይነት አጣ። *በድምፅ ብልጫ ሃሳቡ ወደቀ*። 8. ተጣለ፤ አገልግሎት መስጠት አቆመ። 9. አረጀ፡ በእድሜ ገፋ። 10. ተዘናፈለ (ፀጉር) ። 11. ቀጥ፡ ጠንከር፡ ፈርጠም ብሎ የነበረው ላላ፡ ተኛ (ጡት) ።

**ወድቀህ ተነስ የሚለው የለውም** የሚያስብለት፡ የሚቆረቆርለት፡ የሚረዳው ዘመድ፡ ወዳጅ የለውም ።

**ወድቆ ቀረ** የሚያነሳው፡ የሚያስታውሰው አጣ።

**የወደቀበት አይታወቅም** ጠፍቷል፡ የት እንዳለ አይታወቅም ።

**መውደቂያ** ስ መጠጊያ፡ መኖሪያ፡ መጠለያ።

**ወዳቂ** ቅ 1. አገልግሎት የሌለው፡ የሚጣል። 2. ወደሚቀጥለው ደረጃ ሳይሸጋገር የቀረ። 3. ተቀባይነት ያጣ።

**ወዳቃ** ቅ አቅመቢስ ።

**ውዳቂ** ቅ 1. የተጣለ፡ ቆሻሻ። 2. (ስድብ) የማይረባ፡ ተልካሻ። 3. የበከተ፡ ጥንብ ።

**ውድቅ** ቅ ተቀባይነት ያጣ። *ያቀረበው ሃሳብ ውድቅ ሆነበት ።*

**ውድቀት** ስ ክስረት።

**ውድቅት** ስ እኩለ ሌሊት፡ ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ።

**ተዋደቀ** ግ ታገለ፡ ተጋደለ፡ ተሟሟተ(ለሀግ፡ ለነፃነት፡...)።

**አዋደቀ** ግ አራከሰ፡ ዋጋ አሳነሰ፡ አጥላላ፡ አንኳሰሰ።

**ወደብ** ስ ለመርከብ መጫኛና ማራገፊያ የተዘጋጀ የባህር ዳርቻ።

**የወደብ ኪራይ** ስ ለወደብ አገልግሎት የሚከፈል ገንዘብ።

**ወደቴ** ቅ አውደልዳይ፡ ስራፈት፡ ዘዋሪ።

**ወደነ** ግ ሁለት ሁለቱን ሽክም ወይም ጭነት እያቀናጀ አሰረ፡ አቆራኘ፡ ቀረቀበ ።

**ውድን** ቅ ሁለት ሁለት እየሆነ የታሰረ፡

የተቆራኘ ሸክም ወይም ጭነት፤ ቅርቃብ ።

**ተወደነ** ግ ታሰረ፥ ተቀረቀበ ።

**ወደዚህ(ወዲህ)** መዋ. ተናጋሪው ወዳለበት ቦታ፥ አቅጣጫ ።

**ወደዚያ(ወዲያ)** መዋ. 1. ከተናጋሪው ራቅ ብሎ ያለ ቦታ፥ አቅጣጫ:: 2. በሗላ:: *ካሁን ወዲያ እንደዚህ እንዳታደርግ* ።

**ወደደ** ግ 1. አፈቀረ፥ ፈቀደ:: 2. ፈለገ፥ ደስ አለው:: *ችግራቸውን ሊያቃልልላቸው ይወዳል::*

**ሳይወድ በግድ** ተገድዶ፥ በግዴታ:: *ገንዘቡን ሳይወድ በግድ ይከፍላል::*

**ወዶ ሰጠ** ሳይገደድ በፈቃዱ ሰጠ ።

**ወዶ ዘማች** ስ ግዴታ ሳይኖረበት በፈቃዱ የዘመተ ሰው ።

**ወዶ ገባ** ቅ 1. ግዳጅ ሳይኖርበት በፈቃዱ ሌላ ሰው ቤት ገብቶ የሚኖር (ለምሳሌ ውሻ):: ስ 2. በተፈጥሮ ለዛቢያነት ተስማሚ ሆኖ የተገኘ እንጨት (የዶማ፥ የመጥረቢያ፥... እጀታ)::

**ወዳድ** ቅ በጣም የሚወድ:: *ገንዘብ ወዳድ::*

**ወዳጅ** ስ 1. ባልንጀራ፥ ጓደኛ:: 2. ፍቅረኛ፥ ውሽማ:: ቅ 3. አፍቃሪ፥ የሚወድ::

**ውዴታ** ስ ፈቃደኝነት፤ ግዳጅ የሌለበት አድራጎት::

**የውዴታ ግዴታ** ስ በራስ ፈቃደኝነት የሚገቡት ግዴታ::

**ውድ** ስ 1. ፍቅር:: 2. ፈቃድ:: *ያለውድ በግድ::* ቅ 3. ዋጋው ከፍተኛ የሆነ፤ እንደልብ የማይገኝ:: 4. ተወዳጅ፥ ተፈቃሪ::

**በውድም በግድም** በፈቃደኝነትም ሆነ በመገደድ፥ በማንኛውም መንገድ::

**ወደድ አለ** ግ ዋጋው ከፍ አለ፥ ጨመረ፥ ናረ::

**ተወደደ** ግ 1. ተፈቀረ:: 2. ዋጋው ጨመረ፥ ናረ::

**ተወዳጅ** ቅ ተፈቃሪ:: *ለተወዳጁ ወንድሜ::*

**ተዋደደ** ግ 1. ተስማማ፥ ግጥምጥም አለ (መጥረቢያው፥... ከዛቢያው ጋር):: 2. ተፋቀረ::

**አዋደደ** ግ 1. አስማማ፥ አገጣጠመ (ዛቢያውን ከመጥረቢያው ጋር):: 2. ዋጋ ከፍ አደረገ ::

**አስወደደ** ግ ዋጋን ከፍ አደረገ ።

**ወዲህ** "**ወደዚህ**" ን ተመ.

**ወዲያ** "**ወደዚያ**" ን ተመ.

**ወዲያው** ተው.ግ. 1. በፍጥነት፥ ከመቅፅበት:: *ከሄደበት ቦታ ወዲያው ተመለሰ::* መዋ. 2. በዚያው፥ እግረመንገድን:: *ወደ ገበያ ሄጄ ወዲያው ዘመድ እጠይቃለሁ* ።

**ወዳቂ** "**ወደቀ**" ስር ተመ.

**ወዳቃ** ዝ.ከ.

**ወዳድ** "**ወደደ**" ስር ተመ.

**ወዳጃ** ስ አምልኮአዊነት ባለው ሁኔታ አዛውንት ሌሊት ሌሊት ጫት እየቃሙና ድቤ እየመቱ የሚያደርጉት ልመና፤ ፀሎት::

**ወዳጅ** "**ወደደ**" ስር ተመ.

**ወደላ** "**ወደለ**[2]" ስር ተመ.

**ወዴት** ተው.ግ. አቅጣጫን፥ አድራሻን ለመጠየቅ የሚያገለግል ቃል:: *መስሪያ ቤትህ ወዴት ነው ?*

**ወዴት ሄደ** ተው.ግ. የት አለ፥ የት ጠፋ ።

**ወጀብ** ስ ከነፋስ ጋር ተቀላቅሎ አግድም የሚወረወር ዝናብ::

**ወጀድ** ስ በቤት ጓሮና አቅራቢያ የሆነ እርሻ፥ ቦታ (በአጥር፥ በቅጥር የተከበበ)::

**ወጆ** "**ዋጀ**" ስር "**ዋጆ**"ን ተመ.

**ወገል** ስ የቀለበት ቅርፅ ባለው ጫፉ በኩል ማረሻንና እርፍን ከድግር ጋር ባንድነት ጠርንቆ የሚይዝ፥ እንደ ሜንጦ ባለው ሌላው ጫፉ ደግሞ በወገል ጠፍር አማካይነት ከሞፈር ጋር የሚቆራኝ የግብርና እቃ(ስእሉን ሞፈር ስር ተመ.)::

**ወገሜት(ወገሚት)** ስ ተንጦ ቅቤው የወጣለት ወተት፤ አሬራ::

**ወገረ** ግ 1. በድንጋይ መታ፥ ደበደበ:: 2. ያዘ፥ አጠመደ (አሳን)::

**ተወገረ** ግ ተመታ፥ ተደበደበ::

**ወገሬ** ስ ነጭ የሆነ የማሽላ አይነት::

**ወገርት** ስ መድሃኒትነት አለው የሚባል አነስተኛ የሆነ የእፅዋት አይነት፤ ጢሱም ጥሩ ሽታ ስላለው በማእጠንትነት ያገለግላል::

**ወገሸ** ግ በጣም ተቆጣ፤ ሮጠ፥ በረረ፥ ፈረጠጠ፥ ደነበረ (ሰው፥ ከብት)::

**ወገብ** ስ 1. ከቂጥ በላይ ከትከሻ አካባቢ በታች ያለ የአካል ክፍል:: 2. ከዳሌ በላይ ከጎን በታች ያለ የአካል ክፍል:: *በሁለት እጆቹ ወገቡን ይዞ ቆሟል*:: 3. ዙሪያውን በቀበቶ ወይም በመቀነት የሚታሰረው የሰው አካላዊ ክፍል:: 4. ከፍታ ወይም ቁመት ላለው ነገር እንደ አማካይ የሚወሰድ ቦታ:: *ብርጭቆውን ሳትሙላው፤ እስከ ወገቡ ብቻ ቅዳልኝ::*

**ወገቡ ቁምጥ አለ** ሳያስበው፥ በድንገት ደነገጠ፤ ተስፋ ቆረጠ ።

**ወገቡን ሞከረ** ተፀዳዳ፥ እዳሪ ወጣ ።

**ወገቡን ያዘው** አስቸገረው፥ አስጨነቀው (ችግር) ።

**ወገቤን አለ** አነሰ፥ ቅቡጭ አለ፥ ሳይበቃ ቀረ (ገንዘብ፥...) ።

**ወገበ ቀላል** ቅ ሲሄድ፥ ሲራመድ ቀልጣፋ የሆነ፥ ፈጣን ።

**ወገበ ነጭ** ቅ ጠለቅ ያለ እውቀት የሌለው፥ ጥራዝ ነጠቅ ።

**ወገብጌ** ስ ጥበጣብ ወይም ቀበቶየሚያርፍበትና ወገብ ላይ የሚውለው የሱሪ የላይ ጫፍ ።

**ወገነ** ግ ወገን፥ ተባባሪ፥ አጋዥ ሆነ። *ከጠላት ጋር ወግና ወጋኝ።*

**ወገን** ስ 1. ዘመድ፥ ጓደኛ፤ በትውልድ፥ በብሄር፥ በዜግነት አንድ የሆነ። 2. አቅጣጫ፥ አኳያ፥ በኩል፥ ክፍል። *በዚህ ወገን በጎቹ ይበሉ፥ በዚያኛው ወገን ላሞቹን እናሰማራለን* ።

**ወገን ለየ** በዘር፥ በጎሳ፥ በነገድ ከፋፈለ ወይም ተከፋፈለ፤ በየፊናው፥ በየቡድኑ ሆነ። 2.ለዘመድ፥ ለወዳጅ አደላ ።

**ወገን አደረገ** ግ አጋር፥ ዘመድ፥ ጓደኛ አደረገ።

**ባለወገን** ቅ ደጋፊ፥ አጋዥ ያለው።

**የወገን ቅፅል** ስ ዝምድናን፥ ወገንነትን የሚያሳይ ቅፅል (-ዊ)። *ኢትዮጵያዊ*።

**የወገን ጦር** ስ የራስ የሆነ ጦር ።

**ወገኛ** "*ወጋ" ስር ተመ.

***ወገዘ**

**ውጉዝ** ቅ (ሃይ.) የተወገዘ፥ የተከለከለ፥ መጥፎ የተባለ።

**ውግዘት** ስ 1. ግዝት። 2. መነቀፍ፥ መረገም (በመጥፎ ድርጊት፥ ሁኔታ ምክንያት) ።

**ተወገዘ** ግ 1. ከሃይማኖት ማህበር እንዲወጣ፥ እንዲለይ፥ እንዲገለል ተደረገ ፥ተገዘተ። 2. ተጥላላ፥ ተነቀፈ፥ መጥፎ ተባለ ። 3.መጥፎ በመሆኑ በፅኑ ተረገመ፥ ተከለከለ።

**አወገዘ** ግ 1. ከሃይማኖት ማህበር አስወጣ፥ ለየ፥ ረገመ። 2. ተቃወመ፥ ነቀፈ፥ አጥላላ።

**ወገዝ** ስ ከጥጃ በላይ ከወይፈን ወይም ከጊደር በታች የሆነና ጡት የተወ ከብት ።

***ወገደ**

**ወግድ(ወጊድ፥ ወይድ)** ግ ራቅ፥ ዞር በል፤ ከፊቴ ሂድ የሚል ትእዛዛዊ የቁጣ ቃል ።

**ተወገደ** ግ 1. ራቀ፥ እንዳይደርስ ተከለከለ፥ ተለየ። 2. ጠፋ፥ ተቃለለ። *ችግሩ ተወገደ* ።

**አስወገደ** ግ 1. አራቀ፥ አገለለ። 2. አጠፋ፥ እንዳይኖር አደረገ፥ አቃለለ (ችግርን፥...)።

**ወገግ**

**ውጋገን(ውጋጋን)** ስ ከርቀት የሚታይ የፀሃይ፥ የጨረቃ፥ የእሳት ፥... ብርሃን።

**ወገግታ** ስ የንጋት ብርሃን።

**ወገግ አለ** ግ ብርሃን ፈነጠቀ፥ ታየ፤ ጨለማ የነበረው ብርሃን እየሆነ መጣ።

**ወገጠ** "ወቀጠ" ን ተመ.

**ወጊድ** "*ወገደ" ስር ተመ.

**ወጋ** ግ 1. በመርፌ፥ በጦር፥ በሳንጃ ወይም በሌላ ሹል ነገር አንድን አካል ጠቅ አደረገ፥ ሸቀሸቀ። 2. (ዘይ.) ክፉ ነገርን ተናገረ፥ አሸሟጠጠ። *በነገር ወጋኝ*፡ 3. ውጋት አመመ (ጎንን፥ ጀርባን፥...)። 4. በውግ የዝበጣ ጨዋታ ጊዜ የጠጠር አዟሪው (የተጫዋቹ) የመጨረሻ ጠጠር ሶስት ጠጠር በያዘ ጉድጓድ ውስጥ አረፈ፤ ጉድጓዱም የተጨዋቹ ውግ ሆነ። 5. አይን ላይ የህመም ስሜት ፈጠረ፥ አይንን አስጨፈነ (ጨረር፥ ሃይለኛ የብርሃን ነፀብራቅ)። 6. በጦር ሃይል አጠቃ፥ ጉዳት አደረሰ። 7. ለተመ፥ ገጨ፥ በሳ (በሬ፤ በግ፥... በግንባር፥ በቀንድ፥...)።

**ውጊያ** ስ ጦርነት፥ ፍልሚያ።

**ውጋት** ስ 1. ጠቅ የሚያደርግ፥ ቀስፎ የሚይዝ የህመም አይነት። ቅ 2. (ዘይ.) ጨቅጫቃ፥ ነዝናዛ።

**ውግ** ስ በውግ የዝበጣ ጨዋታ ላይ አንድ ተጫዋች ጠጠር በሚያዞርበት ጊዜ እጁ ላይ የምትቀረዋ የመጨረሻዋ ጠጠር የምታርፍበት ሶስት ጠጠር የያዘች ጉድጓድ፥ ያቺም ጉድጓድ የተጫዋቹ ውግ ትሆናለች።

**ተወጋ** ግ 1. በመርፌ፥ በጦር፥ በሳንጃ ወይም በሌላ ሹል ነገር ጠቅ ተደረገ፥ ተሸቀሸቀ። 2. ተጠምዶ ተያዘ (በጥላቻ)።

**ተዋጋ** ግ 1. ጦር፥ ጠመንጃ፥... በመያዝ በጦር ሜዳ ተፋለመ። 2.ታገለ (በሙግት፥በክርክር፥...)። 3. ተላተመ፥ ተፋለመ (ከብት)።

**ተዋጊ** ቅ 1. በውጊያ ላይ ያለ ወይም ለውጊያ የተዘጋጀ ሃይል ወይም ሰው። 2. አመለኛ፥ አስቸጋሪ የሆነና የሚዋጋ ከብት።

**አዋጋ** ግ 1. በጦር ሜዳ ላይ ተዋጊዎቹን በማዘዝና በመምራት አፋለመ ። 2. በጦርነት ለመፋለም ምክንያት ሆነ። 3. (ዘይ.) ክፉ ነገርን፥ ወሬን ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው በማስተላለፍ አጣላ።

**አዋጊ** ስ 1. በጦርነት ላይ የሚያፋልም የወታደሮች መሪ። ቅ 2. ነገር እያሳበቀ የሚያጣላ።

**አስወጋ** ግ እንዲጠመድ አደረገ (በነገር)።

***ወጋ**

**ወግ** ስ 1. ስርአት፥ ደንብ (ከጥንት ሲያያዝ የመጣ)። 2. ወሬ፥ ነገር፥ ጭውውት።

**ለወግ ለማእረግ ደረሰ** ትዳር፥ ሹመት፥...ለመያዝ፥ ለማግኘት በቃ ።

**ወግ ወጉን ይዞታል** የተሟላም ባይሆን ለማስመሰል ሞክሯል (አንድን ነገር በማድረግ) ።

**ወግ ደረሰው** 1. ክብር አገኘ፥ የደንቡ ተሟላለት። 2. ሌሎች የሚያደርጉትን ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ አደረገ። *ለፋሲካ ወግ ደርሶት በግ ኣረደ።*

**በወግ በወጉ** በመልክ በመልኩ ወይም ስነስርአት ባለው መንገድ ።

**ወገ ጠርቅ** ቅ 1. ወሬኛ፥ ተናግሮ የማያባራ። 2. ወገኛ፥ ወሬ ወዳድ።

**ወግ አጥባቂ** ቅ የጥንትን ወግ፥ ባህል እንዳለ እንዲቆይ፥ እንዳይሻሻል፥ እንዳይለወጥ የሚሻ (ሰው፥ ድርጅት፥...) ።

**የወግ እቃ** ስ ባህላዊ የሆነ የሽልማት፥ የጌጣጌጥ፥ የክብር፥...እቃ ።

**ወገኛ** ቅ 1. ወግን፥ የቆየ ደንብን አጥባቂ። 2. (ስድብ) ጉረኛ ከሆነው በላይ ለመምሰል ፈላጊ።

**አወጋ** ግ አወራ፥ ተጫወተ።

**ወጋግራ** ስ የቤት ጣርያን እንደምሰሶ ደግፎ በመያዝ የሚያገለግል ወፍራም እንጨት።

**ወጌሻ** ስ ወለምታን፥ ስብራትን ፥ ውልቃትን በማሸት፥ በመጠገን የሚያክም የልምድ ወይም ስልጠና ያለው ባለሙያ።

**ወግ** "*ወጋ" ስር ተመ.

**ወግድ** "*ወገደ" ስር ተመ.

**ወጠምሻ** ስ እድሜው ያልገፋ፥ ደንዳና፥ ወፍራም፥ ጉልበታም ሰው።

**ወጠረ** ግ 1. ስቦ ያዘ፥ ለጠጠ (የአልጋ ሽቦን፥ ብራናን፥ ቆዳን፥...)። 2. ሆድን ነፋ፥ ቀበተተ። *የበላሁት ምግብ ሆዴን ወጥሮታል*። 3. መጣሁ መጣሁ አለ፥ አስጨነቀ (ሽንት፥ አይነምድር)። 4. አፋጠ ያዘ፥ መረመረ። *በጥያቄ ወጥሮ ያዘው*። 5. ትእቢት ያዘ፥ ኩራት ኩራት አሰኘ። *ምን ይወጥረዋል?* 6. ጠበበ፥ በደንብ አልገባ አለ (ልብስ)። 7. መንገዱ ለጠጣት እንዳያመች በወታደራዊ ስልት ጠበቀ። *ኮንቦይ ሊያልፍ ነውና ከድልድዩ እስከ ከተማው ያለው መንገድ ይወጠር።*

**መወጠሪያ** ስ 1. ከእንጨት የተሰራ የቆዳ፥ የብራና መገተሪያ። 2. በልብስ ስፌት መኪና አማካይነት ጨርቅ ላይ ጥልፍ ለመጥለፍ የሚያስችል ከእንጨት ወይም ከሌላ ነገር የሚሰራና ጨርቁን ወጥሮ የሚይዝ ክብ እቃ።

**ውጥረት** ስ ጭንቀት፥ ጥበት (በስራ ብዛት፥ በጠርነት፥...)።

**ውጥር ውጥር አለ** ግ በኩራት መንፈስ ቀንን ቀንን አለ፥ ቀንጥር ቀንጥር አለ፥ ያላቅሙ ተንጠራራ።

**ተወጠረ** ግ 1. ተስቦ ተያዘ፥ በሃይል ተዘረጋ፥ ተገተረ፥ ተለጠጠ። 2. ተያዘ፥ ተጨነቀ (በችግር፥ በፈተና፥...)። 3. በትእቢት ተሞላ፥ ታበየ። 4. ቁዝር አለ፥ ተነፋ፥ ተቀበተተ (ለምሳሌ ሆድ)።

**ተወጣጠረ** ግ አለቅጥ ኮራ፥ ትእቢት ያዘው።

**ወጠቀ** ግ በብዛት በላ፥ ጠቀጠቀ ።

**ወጠነ** ግ 1. ጀመረ፥ መሰረት ጣለ። 2. አቀደ።

**ውጥን** ቅ ጅምር፣ እቅድ።

**ተወጠነ** ግ ተጀመረ፣ ታቀደ።

**ተውጠነጠነ** ግ ታሰበ፥ ታቀደ፥ (አንድን ድርጊት ለመፈፀም፥ ለመስራት) ።

**አውጠነጠነ** ግ አሰበ፥ አሰላሰለ፥ አወጣ አወረደ፥ አቀደ (ሃሳብን) ።

**ወጠጤ** ስ 1. ለመጥቃት የደረሰ ወንድ በግ፥ ፍየል። ቅ 2. (ስድብ) ያልሰከነ፥ ያልበሰለ፥ ውረጋጥ ።

**ወጣ** ግ 1. ከውስጥ ወደ ውጭ ሄደ። 2 ከታች ወደላይ፥ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ቦታ ተንቀሳቀሰ፥ ተረማመደ። 3. አለ፥ ተናገረ። *ከፉ ቃል ወጣው*። 4. ተለየ፥ ተወገደ። *ከቤት ከወጣ ብዙ ጊዜው ነው*። 5. በቀለ፥ አደገ፥ ረዘመ። 6. ጨረሰ፥ ዘለቀ፥ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ደረሰ። *መፅሃፉን ወጣው*። 7. ይፋ ሆነ፥ ተነገረ፥ ተገለፀ። *ምስጢሩ ወጣ*። 8. ታየ፥ ብቅ አለ። *ፀሃይ ወጣች*። 9. ደረሰ፥ የባለ እድሉ ስም፥ ቁጥር ተመረጠ (ሎተሪ ወይም እጣ)። 10. ወጪ ተደረገ። 11. በስብሰባ፥ በሰልፍ ላይ ተገኘ። *ለሰልፉ ብዙ ሰው ወጣ*። 12. ተነቀለ፥ ተወገደ። *ጥርሱ ወጣለት*። 13. በቀለ፥ ተፈጠረ። *ብጉር ወጣበት።* 14. ለቀቀ። *እድፉ ወጣ*። 15. ለህዝብ ቀረበ። *መፅሃፉ ታትሞ ወጣ*። 16.የ__ ማእረግ፥ ደረጃ ያዘ ወይም አገኘ። *በሩጫ አንደኛ ወጣ*።

**ወጣ አለ** ግ 1. ለትንሽ ጊዜ ከቤት ወይም ከሃገር ውጭ ሄደ። 2. ለየት አለ፥ አፈነገጠ ።

**ወጣለት** 1. ረካ (የፈለገውን ተናግሮ፥ በልቶ፥ አድርጎ፥...)። 2. ዳነ፥ ሻረ። *ሱፍኝ ወጣለት።*

**ወጣው** 1. ሆነ። *ጥሩ ሃኪም ወጣው።* 2. ተናገረ። *ያልወጣኝን ተናገረ ኣትበል።* 3. አጠፋ፥ ከፈለ (ገንዘብን)። *ዛሬ ገና ገንዘብ ወጣው።*

**በ__ ወጣ** _ን መስሉ ተወለደ፥ ባህርዩን ወረሰ፥ አደገ። *በኣባቱ ወጣ።*

**በወጣ ያውጣው (እንዳወጣ ያውጣው)** እንደሆነ ይሁን።

**የወጣለት** ደንበኛ፥ አይነተኛ፥ የታወቀ። *የወጣለት ሰካራም ነው።*

**የወጣለት ስራ** የተሳካ ስራ፥ ጥሩ ሆኖ የተሰራ።

**ወጣ ገባ** ቅ ያልተስተካከለ፥ አባጣ ጎባጣ ::

**ውጣ ውረድ** ስ ድካም፥ ልፋት ::

**መውጫ** ስ 1. ከውስጥ ወደ ውጭ፥ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ቦታ መተላለፊያ ወይም መሹለኪያ (በር፥ መሰላል፥...):: 2. መፍትሄ:: *ለችግሩ መውጫ ጠፋ::* 3. ብቅ የሚባልበት፥ የሚታይበት ጊዜ፥ አቅጣጫ:: *በፀሃይ መውጫ በኩል* ::

**መውጫ መግቢያ አጣ** ተቸገረ፥ ተጨነቀ፥ ሲወጣ ሲገባ ችግር ገጠመው ::

**መውጫ መግቢያውን ያውቃል** የቤቱን፥ የቦታውን፥... ሁኔታ ጠንቅቆ ያውቃል::

**መውጫ ቀዳዳ አጣ** ከችግር፥ ከጭንቅ የሚላቀቅበት ዘዴ አጣ ::

**ወጥ** ቅ 1. ሙሉውን በአንድ አይነት መልክ የተሰራ፥ አንድ አይነት የሆነ:: 2. አዲስ፥ ያልተቀዳ፥ ያልተኮረጀ (ሃሳብ፥ ድርሰት፥...)::

**ወጪ(ወጭ)** ስ ለልዩ ልዩ ጉዳይ የተከፈለ ወይም ለስራ፥ ለኑሮ የሚያስፈልግ ገንዘብ ::

**ወጪ አደረገ** ለተለያየ ጉዳይ፥ ለስራ፥...ገንዘብ ከፈለ::

**ወጪውን ሸፈነ** ለስራ፥ ለኑሮ፥ ለድግስ፥... የሚያስፈልገውን ገንዘብ ሰጠ፥ ከፈለ፥ ቻለ ::

**ወጪና ገቢ** ስ የተከፈለና የተሰበሰበ ገንዘብ ::

**የወጪ** አንድ ሰው ወደ ሌላ ቦታ በሚሄድበት ጊዜ የሚደረግ የመሰነባበቻ ግብዣ ::

**የወጪ ሰነድ** ስ ገንዘብ ለተወሰነ ጉዳይ መከፈሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፥ ደረሰኝ ::

**ውጤት** ስ 1. አንድን ምክንያት ወይም ድረጊት ተከትሎ የመጣ፥ የታየ ሁኔታ ወይም ነገር:: 2. ጥሩ ነገር፥ ፍሬ:: *ድካምህ ከንቱ አይቀርም፥ ውጤት ይኖረዋል::* 3. በፈተና ወይም በውድድር፥... የተደረሰበት፥ የተገኘ ነጥብ:: 4. በመደመር፥ በማባዛት፥... የተደረሰበት የሂሳብ፥ የስሌት መልስ፤ በምርመራ፥ በሙከራ የታወቀ ግኝት:: 5. ፍሬ፥ አላባ፥ ምርት:: 6. ትርፍ፥ ጥቅም:: *ንግዱ ውጤት የለውም::*

**ውጤት አመጣ** በፈተና፥ በውድድር፥ በስራ ነጥብ ወይም ጥቅም አገኘ::

**ውጭ(ውጪ)** ተው.ግ. 1. ደጅ:: 2. ከአንድ ክልል፥ ድንበር፥ አጥር፥... ወዲያ:: 3. በአንድ ደንብ፥ ስርአት፥ ህግ፥ ባህል፥... ውስጥ የሌለ ::

**ውጭ አደረ** ዘወትር በሚያድርበት ቤት ሳይሆን ሌላ ቦታ አደረ ::

**በውጭ ሲያዩት** ጠለቅ ሳይሉ፥ ላይ ላዩን ሲያዩት::

**ውጭ ነፍስ ግቢ ነፍስ** ጭንቅ፥ ጣር ::

**ውጭ [አገር]** ስ ባህር ማዶ፤ በሌላ መንግስት የሚመራ ሃገር ::

**ውጭ ጉዳይ** ስ በሃገሮች መሃከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከት ጉዳይ ::

**የውጭ ንግድ** ስ ከሌላ ሃገር ጋር የሚደረግ ንግድ ::

**የውጭ ምንዛሪ** ስ የሌላ ሃገር ገንዘብ፤ ዶላር፥ ፓውንድ፥...::

**የውጭው አለም** ስ 1. ሌሎች አገሮች:: 2. አካባቢ:: *በስሜት ህዋሳታችን ለማይደሉት ስለውጭው አለም እናውቃለን::*

**ተወጣ** ግ ተግባሩን፥ ግዴታውን፥ ችግሩን አቀለለ፥ ጨረሰ፥ ፈፀመ::

**መወጣጫ** ስ መሸጋገሪያ፥ እርካብ፥ መሰላል::

**ተዋጣ** ግ 1. ገንዘብ ለእርዳታ ወይም ለሌላ ጉዳይ ተሰበሰበ:: 2. አማረ፥ ተሳካ፥ ሰመረ::

**መዋጮ** ስ ከተለያዩ ግለሰቦች፥ ቡድኖች፥... የተውጣጣ፥ የተሰበሰበ ገንዘብ::

**ተውጣጣ** ግ 1. ከተለያየ ወገን፥ አካባቢ ወይም ቡድን፥... ተሰባሰበ (ሰው፥ ሃሳብ፥...):: 2. የተለያየ ዘዴን በመጠቀም ሊደረስበትና ሊታወቅ ቻለ፥ ይፋ ሆነ፥ ታወቀ (ምስጢሩ) ::

**አወጣ** ግ 1. ከውስጥ ወደ ውጭ ወሰደ፥ አጓዘ:: 2. ከፈለ፥ ወጪ አደረገ፥ አጠፋ (ገንዘብን):: 3. ወሰደ፥ ወጪ አደረገ (ገንዘብን ከባንክ):: 4. አበጀ፥ ሰራ፥ ፈጠረ:: *መንገድ አወጣ/አዋጅ አወጣ:* 5. ፈለፈለ፥ አገኘ (ማእድንን፥ ወይም ሌላ የተደበቀ ነገርን፥...):: 6. ተሸጠ፥ አስገኘ:: *መፅሃፉ አስር ብር አወጣ:* 7. አስነገረ፥ ለህዝብ አቀረበ፥ አሰማ:: *አዋጅ አወጣ/ማስታወቂያ አወጣ:* 8. አበቀለ:: *ጥርስ አወጣ/ሽበት አወጣ:* 9.ይፋ፥ ግልፅ አደረገ (ምስጢርን፥...):: 10. አተረፈ፥ አዳነ:: *ከግዜር አወጣኝ:* 11. ደነገገ:: *ህግ አወጣ* :: 12. ነደፈ፥ ቀየሰ:: *ፕላን አወጣ:*

**አወጣ አወረደ** አሰበ፥ አሰላሰለ ::

**አውጭ** ስ እሬሳ እያወጣ የሚበላ አውሬ ::

**ማውጫ** ስ 1. በየመፅሃፉ፥... የመጀመሪያ ገፆች አካባቢ ተፅፎ የሚገኝ፥ በመፅሃፉ ውስጥ ያሉትን ንኡሳን ርእሶች ወይም አርእስተ ነገሮችና መገኛቸውን ገፅ የሚመለከት ዝርዝር:: 2. በሎተሪ አሸናፊ የሆኑትን እጣዎች ዝርዝር የያዘ ሰንጠረዥ::

**አዋጣ** ግ 1. የሚደርስበትን ወይም የሚችለውን ያህል ገንዘብ ወይም ሌላ ነገር ሰጠ (ለችግር፥ ለደስታ፥ ለግብዣ፥...የሚሆን):: 2. ትርፍ አስገኘ:: *ሸቀጡን በሰላሳ ብር ብሸጠው ያዋጣኛል::* 3. አዛለቀ:: *ሁልጊዜ መዝናናት አያዋጣህም::*

**አውጣጣ** ግ 1. ደብቆ የያዘውን ምስጢር ወይም ጉዳይ (የተለያየ ዘዴ በመጠቀም) እንዲናገር ገፋፋ፥ አስለፈለፈ:: 2. ከተለያየ ቦታ አሰባሰበ (ሰዎችን፥ ገንዘብን)::

**አውጫጭኝ** ስ በስውር ከብት ሲሰረቅ፥ ሰው ሞቶ ሲገኝ ወይም የተለያየ ወንጀል ሲፈፀም የአካባቢው ሰው ተሰብስቦ ወንጀለኛውን ለመጠቆም የሚጠቀምበት ዘዴ፤ አፈርሳታ ።

**ወጣት** ስ 1 እድሜው ከአስራ ስምንት እስከ ሰላሳ አመት የሚሆን ሰው። 2 ጠንካራ፥ ብርቱ፥ ያላረጀ። *ላባቱ ገና ወጣት ናቸው።* 3 አዲስ፥ ያልደረጀ፥ ያልዳበረ።

**ወጣጠረ "ወጠረ"** ስር ተመ.

**ወጥ** ስ ሽሮ ወይም ክክ ወይም አትክልት ወይም ስጋ፥... በዘይት ወይም በቅቤ ከተቁላላ ሽንኩርት፥ በርበሬ ወይም እርድ እንዲሁም ከውሃ ጋር አዋህዶ በማብሰል የሚዘጋጅ የእንጀራ ማባያ።

**ወጥ ረገጠ** ባለገ፥ ገደብ አለፈ፥ ስርአት የለሽ ሆነ (ታላቁን፥ መከበር ያለበትን ባለማክበሩ፥...)።

**ወጥ ሰራ** ወጥን አዘጋጀ፥ አበሰለ።

**ወጥ አወጣ** ወጥን በጭልፋ እየጨለፈ ከሰሃን ወይም ከእንጀራ ላይ አደረገ።

**ወጥ ቤት** ስ 1. መደበኛ ስራው ወጥ መስራት የሆነ ሰራተኛ። 2. በድግስ ወይም በግብዣ ጊዜ ወጥ ለማሳለፍ የተመደበ ሰው። 3. ወጥ የሚዘጋጅበት ቤት፤ ኩሽና ።

**የወጥ ቤት እቃ** ስ ድስት፥ ሰሃን፥ ጭልፋ፥...የመሳሰሉት የምግብ ቤት እቃዎች።

**ወጥ "ወጣ"** ስር ተመ.

**ወጥመድ** ስ 1. አውሬን ለመያዝ ወይም ለመግደል የሚያገለግል መሳሪያ። 2. አንድን ሰው ለመጉዳት የተቀናበረ ወይም የተዘጋጀ ተንኮል፥ ሴራ፥...።

**ወጥመዱ ያዘለት** ለመጉዳት ያዘጋጀው ሴራ፥ ተንኮል ተሳካለት።

**ወጥመድ ውስጥ ገባ** የሴራ የተንኮል፥... ሰለባ ሆነ።

**ወጨፎ**[1] ስ ከነፋስ ጋር እየተቀላቀለ አግድም የሚዘንብ ዝናብ፤ ውሽንፍር።

**ወጨፎ**[2] ስ ጥንት የነበረ የጠመንጃ አይነት ።

**ወጪ "ወጣ"** ስር ተመ.

**ወጭ "ወጣ"** ስር **"ወጪ"**ን ተመ.

**ወጭማዳ** ቅ 1. (ስድብ) ሰባራ፥ ሰንካላ። 2. አቅመ ቢስ፥ ተልካሻ ።

**ወጭት** ስ ከሸክላ ወይም ከነሃስ ወይም ከብረት የሚሰራ የወጥ ቤት እቃ ።

**ወጭት ሰባሪ** ውለታ ቢስ።

**ወጭት አብሽ** ስ ከባቄላና ከአብሽ የሚሰራ፥ ከሌላ ወጥ በፊት የሚቀርብ ማባያ።

**ወፈረ** ግ 1 አካል ጠመረ፥ ደነደነ፥ ሰባ፥ ግዙፍ ሆነ። 2. ለደለደ፥ የውሃው መጠን አነስ ያለ ሆነ (ወጥ፥ ቡና፥...)።

**ወፍራም** ቅ 1. ጠብደል፥ ደንዳና፥ ግዙፍ። 2. ቀጭን ያልሆነ (ለምሳሌ ወጥ፥ ቡና፥...)።

**ወፍራም ቆዳ አለው** ችግር፥ መከራ ይችላል ወይም ይቋቋማል።

**ወፍራም ደመወዝ** ትልቅ ደመወዝ።

**ውፍረት(ውፋሬ)** ስ 1. የሰውነት ድንዳኔ። 2. የአንድ አካል የመዳጎስ መጠን፤ ግዝፈት ።

**አወፈረ** ግ ወፍራም አደረገ።

**ወፈፈ** ግ አበደ፤ አእምሮውን ሳተ።

**ወፈፍ አደረገ** ግ አሳበደ፥ አእምሮን አሳተ ።

**ወፈፌ** ቅ እብድ፤ ቀዥቃዣ ።

**ወፈፍተኛ** ቅ 1. በድንገት የሚቆጣ፥ ግልፍተኛ። 2. እብድነት ያለበት፥ አእምሮው የተነካ ።

**ወፍ**(ብ.ቁ. **ወፎች፥ አእዋፍ**) ስ 1. ሁለት እግርና ሁለት ክንፍ ያለው፥ አየር እየቀዘፈ መብረር የሚችል፥ አካሉ በላባ የተሸፈነ እንስሳ (ስእሉን በሚቀጥለው ገፅ ተመ.)። 2. በአንድ ጫፉ ሰረገላ ላይ የሚቆም በሌላው ጫፉ ወራጅ የሚሸከም፥ ጣሪያ ለማዋቀር የሚያገለግል በወፍ ቅርፅ የሚዘጋጅ እንጨት። 3. አውጫጭኝ ወይም አፈርሳታ በሚካሄድበት ጊዜ ወንጀለኛውን ለሚጠቁም ሰው የሚሰጠው የድብቅ ስም።

**ወፌ ቆመች** በእግሩ ለመቆም የሚሞክርን ህፃን ለማበረታታት የሚባል አነጋገር ።

**ወፈ ያሬድ** ስ ድምፀ መልካም የሆነ የወፍ አይነት።

**ወፈ ገነት "ጣዎስ"** ን ተመ.

**ወፈ ገዝት** ቅ ግዝት አስፈላጊነት ሳይኖረው ወይም ባለማወቅ አግባብነት በሌለው ጉዳይ ላይ ሁሉ የግዝት ቃል የሚያስተላልፍ ።

**ወፍ ሲንጫጫ** በጧት፥ በማለዳ ።

**ወፍ አርግፍ** ስ ቡዳ፥ ጠይብ ።


**ወፍ አእላፍ** ቅ እጅግ በጣም ብዙ የሆነ (ሰው ወይም የወፍ መንጋ) ።

**ወፍ እግር** ስ 1. በእጅ መርፌ የሚሰፋ፥ ጫፍና ጫፉ የወፍ እግር የሚመስል ጥልፍልፍ የሆነ የነጠላ ልብሶች አሰፋፍ። 2. (ስድብ) ቀጭን እግር።

**ወፍ ዘረር "ዘረር"** ን ተመ.

**ወፍዘራሽ** ስ 1. ሰው ሳይተክለው በዱር የበቀለ ተክል፤ ወፍ አራሽም ይባላል። ቅ 2. በጥሩ ስነምግባር ያላደገ፥ ባለጌ።

**የወፍ ቆሎ** ስ ስሩ ሲበሉት የሚጣፍጥ የእንግጫ አይነት።




1. ጣዎስ
2. በቀቀን
3. ጨለቆ
4. ንበበል
5. ግንደ ቆርቁር
6. የሌሊት ወፍ
7. ቆቅ
8. ድንቢጥ
9. ጭሩ
10. ጭሪ
11. የረግረግ ወፍ
12. ሰጎን
13. ዋኔ
14. ርግብ

**የወፍ ቋንቋ** ስ ለብዙዎች ግልፅ ያልሆነ፥ ጥቂት ሰዎች ፈጥረው የሚገለገሉበት ምስጢራዊ ቋንቋ ።

**የወፍ በሽታ** ስ አይንን፥ ጥፍርን፥ ሽንትን ቢጫ የሚያስመስል የጉበት በሽታ ።

**የወፍ ጎጆ** ስ ወፎች ከሳር፥ ከገለባ፥ ከላባ፥...የሚሰሩት ማደሪያ፥ እንቁላል መጣያና መኖሪያ ።

**ወፍራም "ወፈረ"** ስር ተመ.

**ወፎች** ስ የደረቀ የእንስት ቅርፊት ።

**ወፍጮ** ስ በሰው ጉልበት ወይም በሞተር ሃይል ሊሰራ የሚችልና እህልን ወይም ሌላ ነገርን ለመፍጨት፥ ለማድቀቅ የሚያገለግል እቃ፥ መሳሪያ፥ ወይም የተወቀረ ድንጋይ።




**ወፍጮ መድፊያ** ስ ከሆሳእና ዋዜማ በፊት ያለው አርብ ቀን፤ እህል የማይፈጭበት ።

**ወፍጮ ቤት** ስ የሞተር ወፍጮ የተተከለበትና አገልግሎት የሚሰጥበት ቤት ።

**የወፍጮ ልጅ** ስ የወፍጮ መጅ ።

**የወፍጮ እህል** ስ ሊፈጭ የተዘጋጀ እህል ።

**ዉ** የ"ወ" ፊደል ካእብ ዘር ።

**ዊ** የ"ወ" ፊደል ሳልስ ዘር ።

**-ዊ (-አዊ)** 1. ከተፀውኦ ስሞች በስተመጨረሻ እየገባ ወገንነትን የሚገልፅ ምእላድ፤ የወገን ቅፅል:: *ኢትዮጵያዊ*:: 2. በ ___ በኩል፥ የ___ የሚል ትርጉም የሚሰጥ ምእላድ:: *ውስጣዊ /ውጫዊ/ሃይማኖታዊ/ ወቅታዊ* ።

**ዋ**[1] የ "ወ" ፊደል ራብእ ዘር ።

**ዋ**[2] የማስጠንቀቂያ፥ የማስፈራሪያ፥ የዛቻ መግለጫ:: *ዋ! ተሳስተህ ታበላሽና ትቀጣለህ* ።

**ዋ**[3] የሃዘን፥ የትካዜ መግለጫ:: *ዋ! ያን የመሰለ ጀግና ተበላሽ* ።

**-ዋ**[1] የሶስተኛ መደብ አንስታይ ያታን የሚያመለክት መስተአምር:: *አንበሳዋ* ።

**-ዋ**[2] የሶስተኛ መደብ አንስታይ ያታ አገናዛቢ ምእላድ:: *በርሳዋ ተከፍቷል*::

**-ዋ**[3] "ሆይ" እንደማለት የሚያገለግል ቃለ አጋኖ:: *አንቾዬዋ/ልጀዋ*::

***ዋሃደ**

**ውህደት** ስ አንድ መሆን፥ መቀላቀል ።

**ተዋሃደ** ግ አንድ ሆነ፥ ተቀላቀለ ።

**ተዋህዶ** ስ መለኮትና ትስብእት ተዋህደው አንድ አካል፥ አንድ ባህርይ፥ አንድ ፈቃድ ሆኑ የሚል ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ።

**አዋሃደ** ግ አንድ አደረገ፥ አቀላቀለ ።

**ዋለ**[1] ግ 1. ሙሉውን ቀን ወይም ከቀኑ አብዛኛውን ክፍል በአንድ ቦታ ቆየ፥ ብዙ ጊዜ አሳለፈ:: 2. ስራ ተሰራበት፥ አገልግሎት ሰጠ:: *ገንዘቡ ስራ ላይ ዋለ* ። 3. በአንድ በተወሰነ ቀን ላይ ሆነ፥ አረፈ:: *እንቁጣጣሽ እሁድ እለት ዋለ*::

**ዋለ አደረ** ሰነበተ፥ ለተወሰኑ ቀናት ቆየ::

**ሳይውል ሳያድር** ዛሬውኑ ።

**በዋል ፈሰስ** በሄደበት የሚቆይ፥ ቶሎ የማይመለስ፤ ግዴለሽ ።

**ውሎ አደረ** ቆየ፥ ሰነበተ ።

**ውሎ ገባ(ውሎ ገብ)** ቅ በጧት ሄደው ሳያድሩ የሚመለሱበት የደርሶ መልስ መንገድ፥ ጉዞ:: *መንገዱ የውሎ ገብ መንገድ ነው* ።

**ውሎ ይግባ** (ምር.) በሰላም፥ በጤና ይኑር፤ በሰላም ውሎ በሰላም ይመለስ ።

**እየዋለ እያደረ** እየቆየ፥ እየሰነበተ ።

**የዋለ** ቅ የቆየ፥ ትኩስ ያልሆነ:: *የዋለ እንጀራ*::

**መዋያ** ስ ቀኑን፥ ጊዜውን ማሳለፊያ ቦታ::

**ውሎ** ስ 1. የሙሉ ወይም የግማሽ ቀን ቆይታ:: 2.ሬሳው በሌለበት ዘመድ ወዳጅ ተሰብስቦና አልቃሽ ቆሞ ቀኑን ሙሉ ለሞተው ሰው የሚደረግ ልቅሶ ።

**ውሎ ተዋለ** ሲለቀስ ዋለ::

**የውሎ አበል** ስ ለስራ ጉዳይ ከመስሪያ ቤቱ ርቆ ለሚሄድ ደመወዝተኛ በቀን ሂሳብ የሚከፈል ገንዘብ::

**አዋለ** ግ 1. አቆየ:: 2. አንድ ስራ እንዲሰራበት፥ እንዲካሄድበት አደረገ (ገንዘብን፥ ጉልበትን):: *ገንዘቡን ንግድ ላይ አዋለ*::

**አዋይ** ስ የቤት ውስጥ ቆሌ::

**የአዋይ** አዋይ ትፈልገዋለች በሚል ልማዳዊ እምነት መሰብ ውስጥ የሚቀመጥ ቁራሽ እንጀራ::

**የአዋይ በላ** ቅ ለአዋይ የሚቀመጠውን ቁራሽ እንኳ የሚበላ ችጋራም፥ ስግብግብ፥ ረሃብ የማይችል::

**ዋለ**[2] ግ 1. በጎ ስራ ሰራ፥ ውለታ አደረገ:: 2. ረዳ፥ አገዘ፥ አዳነ:: *ዛሬ እግዜር ዋለልኝ* ።

**ውል** ስ 1. ስምምነት፤ ለመስራት፥ ለመፈፀም የተገባ ቃል፥ ውለታ:: 2. የቋጠሮ መፍቻ ምልክት::

**ውል ሰረዘ** በውሉ መሰረት ማከናወን ማቆሙን

አሳወቀ፣ ውሉን አፈረሰ።

**ውል አፈረሰ** በተዋዋለውና በተስማማው መሰረት ማከናወኑን ተወ፣ ስምምነቱን ጣሰ ።

**ውል ገባ(አደረገ)** ተዋዋለ፣ ተስማማ ።

**ውሉ ጠፋ** ተምታታ፥ መፍትሄ አፈላለጉ አስቸጋሪ ሆነ።

**ውል ሰሚ** ስ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ወይም ድርጅቶች ሲዋዋሉ በእማኝነት፥ በምስክርነት የሚያዳምጥ ።

**ውል ሰጪ** ስ በውል ስምምነት ድርድር ላይ ስራው እንዲሰራለት፥ ጉዳዩ እንዲፈፀምለት የሚጠይቀው ወይም ቃል የሚያስገባው ወገን (ለምሳሌ በህንፃ ስራ ውል ውስጥ አሰሪው ውል ሰጪ ነው)።

**ውል ተቀባይ** ስ አንድን ተግባር ለማከናወን፥ ለመስራት ከግለሰብ፥ ከድርጅት ጋር ውል የገባ ወገን።

**ውል የለሽ** ቅ 1. በቃሉ የማይገኝ፥ ቀልማዳ። 2. የተወሳሰበ፥ የተሳሰረ፥ የተምታታ ።

**ውል ያለው ነገር** መልክ ያለው፥ መሰረት ያለው ነገር፣ ቁም ነገር ።

**ውለታ** ስ 1. አንዱ ለሌላው የሚያደርገው በጎ ስራ፥ ቁም ነገር። 2. የ"**ውል**"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

**ውለታ መለሰ** ለተደረገለት በጎ ተግባር በፊንታው በጎ ነገር አደረገ፣ ብድር መለሰ ።

**ባለውለታ** በጎ ተግባር ያደረገ፥ ቁም ነገር የሰራ። *እገሌ ባለውለታዬ ነው።*

**ውለታ ቢስ** ቅ የተደረገለትን ውለታ የሚዘነጋ፥ ምስጋና ቢስ ።

**ውለኛ** ቅ ቁምነገረኛ፣ በተናገረበት፥ ባለበት የሚገኝ ።

**ተዋዋለ** ግ ተስማማ፥ ውል ገባ፥ የውል ስምምነት ፈፀመ።

**አዋዋለ** ግ አስማማ (በስራ፥ በገንዘብ) ።

**አዋዋይ** ስ ውል የሚያፈራርም፣ የሚያስማማ አካል ።

**ዋለለ** ግ 1. ዋዠቀ፥ ተንቃነቀ፥ ወዲያና ወዲህ አለ። 2. ባከነ፥ እርጋታ አጣ። 3. መወሰን አቃተው።

**አዋለለ** ግ 1. እንዲዋልል አደረገ፥ አነቃነቀ፥ አዋዠቀ። 2. አባከነ፥ እርጋታ አሳጣ።

**ዋለገ** ግ ወሰለተ፣ ከስራው ላይ ሾልኮ፥ ተሰርቆ ሄደ ።

**ዋልጌ** ቅ በስራው ላይ የማይገኝ፥ ወስላታ፥ አልምጥ ።

**አዋለገ** ግ 1. አወሰለተ፥ በስራው ላይ እንዳይገኝ አደረገ፥ ስራ አስፈታ። 2. አባለገ፥ አወሳለተ።

**ዋሊያ**[1] ስ አፉ፥ እግሮቹና አይኖቹ አካባቢ ፈካ ያለ፥ ከወደ ሆዱ ነጣ ብሎ ሌላው አካሉ ጥቁር ቡናማ የሆነ መልክና የተቀለበሱ ረዣዥም ቀንዶች ያሉት፥ ተራራማና ገደላማ በሆኑ ስፍራዎች የሚኖር፥ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኝ ሳረበል የዱር እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

**ዋሊያ**[2] ስ የማሽላ ሰብል እየበላች የምታስቸግር፥ ከርግብ አነስ የምትል ወፍ ።

**ዋልሴ** ስ ስለቱ እንደማጭድ በስተውስጥ የሆነ ጎባጣ ካራ ።

**ዋልታ** ስ 1. በመካከሉ የምሰሶ ጫፍ መግቢያ ሰፊ ቀዳዳና በዙርያው ብዙ ብስ ያለው፥ በስተላይ በኩል ውቅር ወይም ጭምጭማት የሚደረግበት የባጥ ገበታ፣ ጣራ መወጠኛ። 2. ጋሻ፥ መከታ። 3. መሬት የምትሽከረከርበት የሃሳብ ዘንግ ሰሜናዊ ወይም ደቡባዊ ጫፍ።

**ዋልካ** ስ መረሬ፣ ጥቁር አፈር ።

**ዋልጋ(ወልጌ)** ስ የበግ ግልግል የሚበላ ቀበሮ መሰል አውሬ ።

**ዋልጌ "ዋለገ"** ስር ተመ.

**ዋመሳ** ስ ረዥም ጦር ።

**ዋሜራ** ስ በአንጓና በአንጓ መካከል የሚገኝ የአገዳ አንዱ ክፍል፥ መለልታው ።

**ዋምራ** ስ 1. ለውሃ መቅጃ፥ ለጠላ መያዣ የሚያገለግል ቅል። 2. ሽክና ።

**ዋር** ስ የጣቃ እጥፋት ።

**ዋርሳ** ስ ሚስት የባሏን ወንድም ወይም ወንዱ የወንድሙን ሚስት የሚጠራበት የተዛምዶ ስም ወይም በሁለቱ መሃል ያለ ባህላዊ ዝምድና ።

**ዋርካ(ወርካ)** ስ ከሾላ ፍሬ አነስ የሚልና ከበሰለ በሗላ ብዙውን ጊዜ ደረቅ ሲል የሚበላ ፍሬ ያለው፥ ቅጠሉ ሰፋፊ የሆነና እንጨቱ ነጣ ያለ ፈሳሽ የሚወጣው፥ ጥቅጥቅ ብለው በግንዱ ዙሪያ አግድም የሚንሰራፉ በርካታ ቅርንጫፎች ያሉት በጣም ትልቅ የሆነ ዛፍ።

**ዋርዳ** ስ 1. ጠቆር ያለ መልክ ያለው የወፍ አይነት። ቅ 2. ጠቆር ያለ መልክ ያለው (ለበቅሎ ወይም ለአህያ)።

**ዋርዳ ሳሙና** ስ ከጥቁርነት ፈገግ ያለ ወደ ቅላት የሚወስደው የበቅሎ መልክ ።

**ዋርዴ** የ"**ዋርዳ**"ን 2ኛ ፍች ተመ.

***ዋስ**[1]

**ዋስ** ስ በእዳ፥ በወንጀል ወይም በሌላ ጉዳይ ተጠያቂ በመሆን የሚፈለገን ሰው ለማቅረብ፥ ካላቀረበም በእሱ ፈንታ ወይም ቦታ ለመጠየቅ

የውዴታ ግዴታ የሚገባ ሃላፊ፣ ተያዥ፥ መድን::

**ዋስ ሰጠ** ተያዡን ወይም ዋስ የሚሆነውን ሰው አቀረበ::

**ዋስ በራሴ አለ** እራሱን ለራሱ ዋስ አደረገ::

**ዋስ ጠራ** ዋስ ሰጠ፥ አቀረበ ::

**ዋስ አጋች** ስ የዋስን እቃ የሚይዝ፥ የሚወስድ፥ የሚያግት ሰው ::

**ዋስ የለሽ** ቅ ዋስ የማያገኝ፥ ወሰላታ (ሰው)::

**ዋስትና** ስ 1. ዋስ መሆን፥ ዋስነት:: 2. የሚያስተማምን፥ አስተማማኝ የሚያደርግ ማረጋገጫ:: *ስፖርትን ማዘውተር ለጤንነትና ለቅልጥፍና ዋስትና ነው::*

**ዋስትናውን አወረደ** ዋስነቱን ወይም ዋስ ለመሆን የገባውን ውል ሰረዘ ::

**ዋስትና የሌለው** ዘላቂነቱ፥ አገልግሎቱ የማያስተማምን ::

**ተዋሰ** ግ በእዳ፥ በወንጀል ወይም በሌላ ጉዳይ ተጠያቂ የሆነን ሰው ለማቅረብ፥ ካላቀረበም በእሱ ቦታ ለመጠየቅ የውዴታ ግዴታ ገባ፣ ሃላፊ፥ ተያዥ፥ መድን ሆነ ::

***ዋሰ**[2]

**ውሰት** ስ ለባለቤቱ ተመላሽ የሚሆን እቃን፥...ለተወሰነ ጊዜ የመውሰድ ተግባር ::

**ተዋሰ** ግ በሃላ ለመመለስ ለጊዜው ብቻ በውሰት ወሰደ::

**የተውሶ** ቅ የትውስት፣ የራስ ያልሆነ፥ ለባለቤቱ ተመላሽ የሚሆን ::

**አዋሰ** ግ ለጊዜው ብቻ እንዲገለገልበት በውሰት ሰጠ ::

**ዋስ** "*ዋሰ[1]" ስር ተመ.

**ዋስትና** ዝ.ከ.

**ዋስዳ** ስ 1. ብዙውን ጊዜ የከብት ስጋ ብልቶችን ከላዩ ላይ ሰክቶ በማንጠልጠልና ለሁለት ተሸክሞ ከቦታ ወደ ቦታ ለማጓጓዝ የሚያገለግል እንደ አጠና ያለ እንጨት:: 2. ከሃረግና ከመሳሰለው የሚሰራና ስጋን ማስቀመጫ የሚሆን ትልቅ ማቶት::

**ዋሸ** ግ 1. አበለ፥ ቀጠፈ፣ ሃሰት ተናገረ:: 2. ተስፋ ሰጠ:: *ልብስ እገዛልሃለሁ ብሎ ዋሸቶልኛል::*

**ዋሾ** ቅ ውሸታም፥ አባይ፥ ቀጣፊ፥ ሃሰተኛ::

**ውሸት** ስ ሃሰት፥ እብለት፥ ቅጥፈት::

**ውሸቱ በቁመቱ ልክ ነው** በጣም ዋሾ ነው::

**ውሸቱ ቆሞ ይሄዳል** በጣም ይዋሻል::

**የውሸት** የቀልድ :

**የውሸት ጎሬ** ቅ ውሸታም ::

**ውሸተኛ** ቅ ሃሰተኛ፥ ቀጣፊ፥ አባይ ::

**ውሸታም** ዝ.ከ.

**ዋሻ** ስ 1. ተራራ፥ ገደል፥ ቋጥኝ፥...ባለበት አካባቢ በተፈጥሮ ወይም በሰዎች ወይም በአውሬዎች የተቆፈረ መኖሪያ፥ ጎሬ፥ ጉድጓድ:: 2. መሸሸጊያ፥ መደበቂያ፥ መሰብሰቢያ:: *የሌባ ዋሻ ነው::*

**ዋሸንት** ስ ውስጡ ክፍት ከሆነ ቀርከሃ ወይም ሸንበቆ፥...የሚሰራ አራትና ከዚያም በላይ ብሶች ያሉት ባህላዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ::(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)::

**ዋሸንት ይነፋል** በዋሸንት ሙዚቃ ይጫወታል::

**ዋሾ** "ዋሸ" ስር ተመ.

***ዋበ**

**ውብ** ቅ ቆንጆ፥ ያማረ፥ የተዋበ፥ ሸጋ፥ ለዛ ያለው::

**ውበት** ስ 1. የመልክ፥ የድምፅ፥ የቅርፅ፥ የአቋቋም፥...ቁንጅና፥ ማማር፥ የመሳብ ሃይል፥ ለዛ:: 2. የስነ ጥበብ ውጤት ማማር፥ ቁንጅና የመሳብ ሃይል::

**ተዋበ** ግ አማረ፥ ቆንጆ፥ ሸጋ ሆነ::

**አስዋበ** ግ አቆነጀ፥ አሳመረ፥ አስጌጠ::

**ዋቢ** ስ ሃላፊ፥ ተጠያቂ፥ ዋስ ::

**ዋቢ መፃህፍት** ስ በምርምር ፅሁፍ ጊዜ አገልገሎት ላይ የዋሉ፥ የተነበቡ የማመሳከሪያ መፃህፍት ::

**ዋተተ** ግ ተንከራተተ፥ ባተለ፥ ወዲያ ወዲህ አለ፥ ደከመ፥ ለፋ፥ ታከተ ::

**አዋተተ** ግ አንከራተተ፥ አባተለ፥ አደከመ፥ አለፋ ::

**ዋነኛ** "ዋና" ስር ተመ.

**ዋና** "ዋኘ" ስር ተመ.

**ዋና** ቅ 1. አለቃ፥ ሃላፊ፥ ባለቤት፥ ቀዳሚ፥ ከሁሉም በላይ የሆነ፥ የበለጠ:: 2. በጉልህ የሚታይ፥ የሚታወቅ፥ አስፈላጊ የሆነ:: *ዋና ዋና ጉዳዮች ታይተዋል::* ስ 3. መነሻ፥ መነገጃ፥ መንቀሳቀሻ ገንዘብ (ትርፉን ሳይጨምር)::

**ዋና ነው** የዋዛ አይደለም ::

**ዋናውን መለሰ** ለንግድ የተገዛው እቃ፥ ድርጅት፥...የተገዛበትን ዋጋ መለሰ፥ አስገኘ ::

**ዋና ሃሳብ** ስ ፍሬ ነገር፥ ዋና መልእክት:: *የፅሁፉ ዋና ሃሳብ ምንድን ነው?*

**ዋና መስሪያ ቤት** ስ ከስሩ ሌሎች ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች ያሉት የበላይ መስሪያ ቤት ::

**ዋና መንገድ** ስ ከሌሎቹ ይልቅ በርካታ ተመላላሾች የሚገለገሉበት ትልቅ መንገድ ::

**ዋና ስራ አስኪያጅ** ስ የአንድ ድርጅት የስራ አመራር ከፍተኛ ባለስልጣን፤ መሪ ::

**ዋና በር** ስ ከሌሎች አነስተኛና በየአቅጣጫው ከሚገኙ በሮች የተለየና ትልቅ የሆነ የፊት ለፊት በር ::

**ዋና ከተማ** ስ 1. ዋና ዋና መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች፥ ድርጅቶች፥ ተቋሞች፥... የሚገኙበት የአስተዳደሩ ማእከል:: 2. የአንድ አገር ርእሰ ብሄር የሚኖርበት የአገሪቱ ዋና መዲና::

**ዋና ክፍል** ስ ከመምሪያ በታች ሆኖ በስሩ የሚገኙትን የተለያዩ ክፍሎች ስራ የመምራት፥ የመቆጣጠር፥ የማስተባበር ስልጣን ያለው ክፍል::

**ዋና ፀሃፊ** ስ የአንድ ድርጅት የስራ አስፈፃሚ የበላይ ባለስልጣን::

**ዋነኛ** ቅ አይነተኛ፥ አስፈላጊ፥ ከሁሉም የበለጠ::

**ዋናተኛ** "ዋኘ" ስር ተመ.

**ዋኔ** ስ ርግብ የምትመስልና ከርግብ አነስ የምትል ወፍ(ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)::

**ዋንኬ [በግ]** ስ ቆላ በሆነ አካባቢ የሚገኝ የበግ አይነት::

**ዋንዛ** ስ ፍሬው የሚበላ፥ እንጨቱ ጠንካራ፥ ቅጠሉ ሰፋፊ የሆነ ትልቅ ዛፍ::

**ዋንጫ** ስ 1. ከቀንድ፥ ከእንጨት፥ ከወርቅ፥ ከብር፥... የሚሰራ መጠጫ:: 2. ከወርቅ፥ ከብር፥... የሚሰራና በስፖርት ወይም በሌላ ውድድር ላሸነፈ ወይም የበለጠ ውጤት ላገኘ የሚሰጥ ሽልማት::



*ዋንጫ 1ኛ ፍቺ*    *ዋንጫ 2ኛ ፍቺ*

**ዋንጫ ወሰደ** አሸናፊ በመሆን ወይም በሌላ ምክንያት ዋንጫ ተቀበለ ::

**ዋንጫ ልቅለቃ** ስ በአንገት የሚወርዱት የእስክስታ አይነት ::

**ዋንጫ አንጣጭ** ስ ዋንጫ የሚሰራ ሰው ::

**ዋኖስ** ስ ርግብ የምትመስል ወፍ፤ ዋኔ ::

**ዋኘ** ግ በእጅ፥ በእግር፥ በክንፍ፥...እየቀዘፈ በባህር፥ በሃይቅ፥... ላይ ሄደ፤ ተንሳፈፈ::

**መዋኛ** ስ ለዋና አመች የሆነ ባህር፥ ሃይቅ፥... ወይም ለዋና ተብሎ የተዘጋጀ ሰፊ የውሃ ገንዳ ያለው ስፍራ::

**ዋና** ስ በእጅ፥ በእግር፥... እየተቀዘፈ በባህር፥ በወንዝ፥ በሃይቅ፥...ላይ የሚደረግ ጉዞ፥ እንቅስቃሴ፤ ውሃ ዋናም ይባላል::

**የዋና ልብስ** ስ በዋና ጊዜ የሚለበስ ልብስ::

**ዋናተኛ** ቅ ዋና አዋቂ::

**አስዋኘ** ግ መዋኘት አስቻለ:: *ወንዙ ጥልቀት ስለሌለው አያስዋኝም::*

**ዋካታ** "*ወካ" ስር ተመ.

**ዋዋ** ግ ጣመ፥ ጣፈጠ::

**ዋዋቴ** ስ ስሩ ሲያኝኩት በመጀመሪያ የሚመር፥ እየቆየ የሚጣፍጥ የእፅዋት አይነት::

**አዋዋ** ግ 1. ጥሩ ጣእም ሰጠ፥ አጣፈጠ:: 2. ዋዋ::

**ዋዛ** ስ ቀልድ፥ ፌዝ፥ ዘበት፥ ቧልት፥ ጨዋታ:: *ዋዛ አታብዛ ::*

**እንደዋዛ** ትኩረት ሳይሰጠው፥ እንደቀልድ፥ ሳይታሰብበት::

**የዋዛ አይደለም** በቀላሉ የሚታይ፥ የሚናቅ አይደለም::*እገሌ ምኝ ይመስላል እንጂ የዋዛ አይደለም ::*

**ዋዛ ፈዛዛ** ስ ቀልድ፥ ፌዝ:: *በዋዛ ፈዛዛ ጊዜን ማባከን አይገባም ::*

**ዋዘኛ** ቅ ቀልደኛ፥ ፌዘኛ፥ ተጫዋች ::

**ዋዘኛ መስሎ** ሳይጠረጠር፥ ቁም ነገር ያለው ሳይመስል::

**ተዋዛ** ግ ተቃለደ፥ ተቃበጠ::

**አዋዛ** ግ 1. አታለለ፡ አማለለ፥ አዘናጋ፥ አጫወተ:: 2. ቀስ ብሎ እያላመደ፥ በዘዴ ተጠቀመ (አንድን ነገር ለማድረግ)፤ አለሳለሰ፥ አባበለ:: *መቀርቀሪያውን አዋዝተህ አስገባው::*

**ዋዜማ** ስ 1. ከዋና በአል ወይም ከአንድ ከሚጠቀስ ቀን አስቀድሞ የሚውል ቀን:: 2. አንድ መንፈሳዊ ክብረ በአል ከሚከበርበት እለት አንድ ቀን ቀደም ብሎ በእሉን በሚመለከት በቤተክርስቲያን የሚዘመር ከሃያ ሁለቱ የድጓ አርእስተ ዜማዎች አንዱ :: 3. ባለ አምስት ቤት ቅኔ ::

**ዋዠቀ** ግ 1. ተንቃነቀ፥ ተወዛወዘ፥ ዋለለ:: 2. አንድ አቋም አጣ፥ ወላወለ:: 3. አንዴ ከፍ አንዴ ዝቅ አለ (ዋጋ፥...) ::

**ዋዣቂ** ቅ ወላዋይ ::

**ዋዥማ** ስ ከብቶች ሲበሉት ሆዳቸውን የሚነፋ፥ ከሳር ጋር የሚበቅል አነስተኛ የእፅዋት አይነት ::

**ዋዥንቢጥ(ዋዥንቢት)** ስ ክንፎቿ ላይ ቀይ ያለባት፥ ጠቆር ያለች ነፍሳት ::

***ዋየ**

**ውይይት** ስ. 1. የሃሳብ ልውውጥ፥ ምክክር፥ ጭውውት። 2. ከሾፌሩ በስተሂላ አምስት አምስት ተሳፋሪዎችን የሚየአስቀምጡ ሁለት የግራና የቀኝ አግዳሚ መቀመጫዎች ያሉት የከተማ ታክሲ መጠሪያ።

**ተወያየ** ግ 1. ሃሳብ ለሃሳብ ተለዋወጠ፤ አስተያየት ሰጠ፥ ተቀበለ። 2. ተነጋገረ፥ ተጨዋወተ፥ ተመካከረ።

**አዋየ** ግ 1. አስተዛዘነ፥ አጫወተ (በችግር፥ በመከራ ጊዜ)። 2. አማከረ ።

**አወያየ** ግ ሃሳብ ለሃሳብ አለዋወጠ፥ አነጋገረ ።

**አወያይ** ስ የስብሰባ፥ የውይይት መሪ፤ ሊቀመንበር።

**ዋይ**

**ዋይታ** ስ ጩሀት፥ እሪታ።

**ዋይ አለ** ግ ጮሀ፥ አለቀሰ ።

**ዋይ የለሽ** ግድ የለሽ፥ ሃሳብ የለሽ ለማለት የሚነገር።

**ዋይከማ** ስ የእንጨት ልጓም፤ ልጓጥ።

**ዋዲያት(ዋድያት)** ስ ብዙውን ጊዜ የሊጥ ማቡኪያ በመሆን የሚያገለግል ጎድጓዳ የሸክላ ወይም ተለቅ ያለ የእንጨት እቃ።

**ዋጀ** ግ 1. ገዛ። 2. ካሳ፤ ጉማ፥... ከፈለ (ከሞት፥ ከባርነት፥... ለማዳን)። 3 አዳነ ።

**ዋጀ(ወጀ)** ስ በሰው እጅ ለተገደለ ሰው የገዳይ ወገን ወይም ገዳዩ ለሟች ቤተሰብ የሚከፍለው የነፍስ ዋጋ፥ ካሳ፤ ጉማ (ገንዘብ፥ ከብት፥...) ።

**ዋጅለት** ስ ያልታረሰና አረም መጣያ ሆኖ የቆየ ለም መሬት ።

**ዋገምት(ዋግምት)** ስ የታመመ ሰው ገላ ከተበጣ በሂላ በበሽታ የተበከለ ደሙን መጦ ለማውጣት የሚያገለግል ከቀንድ የሚሰራ ባህላዊ የህክምና መሳሪያ።

**ዋጊኖስ** ስ በደጋ የሚበቅል መድሃኒትነት አለው የሚባል የእፀዋት አይነት።

**ዋጋ** ስ 1. አንድ ነገር የሚገዛበት ወይም የሚሸጥበት፤ አንድ ስራ ለተሰራበት ወይም ለተሰጠ አገልግሎት የሚከፈል የገንዘብ መጠን፥ ልክ፥ ተመን። 2. ረብ፥ ጥቅም፥ ፋይዳ። ***ዋጋ የለውም*** 3. ተገቢ፥ ተመጣጣኝ ቅጣት።
***ዋጋውን አገኘ/ ዋጋዬን ሰጠኝ፡***

**ዋጋ ሰቀለ** ዋጋ አስወደደ።

**ዋጋ ሰበረ** መግዣ ዋጋውን አራከሰ፥ ዋጋ ቀነሰ።

**ዋጋ ቆለለ** ዋጋውን በጣም አበዛ፥ ከልክ አሳለፈ ።

**ዋጋ ቆረጠ** ዋጋውን ወሰነ፤ ርግጡን፥ መሸጫውን፥ መግዣውን ተናገረ።

**ዋጋ አሳረረ** መግዣ ዋጋውን ከፍ አድርጎ፥ ከሌላው አብልጦ ሰጠ (ተጫራቹ)።

**ዋጋ አዋረደ** መግዣ ዋጋውን አሳንሶ፥ ዝቅ አድርጎ ሰጠ (ገዥው)።

**ዋጋ አፋረሰ** በተነጋገረበት ዋጋ ሳይስማማ ቀረ፤ እንዳይሸጥ፥ እንዳይገዛ አደረገ።

**ያለ ዋጋ** በከንቱ፥ ያለጥቅም። ***እዚያ ድረስ የደከምኩት ያለ ዋጋ ነው።***

**ዋጋ ቢስ ቅ** የማይረባ፥ ጥቅም የሌለው ።

**ዋጋ የለሽ** ዝ.ከ.

**ዋጋ ያለው** ከፍ ያለ ጠቀሜታ፥ ቁምነገር ያለው ።

**የዋጋ ቅናሽ** ከወትሮው፥ ከመደበኛው፥ ከነበረው ዋጋ ዝቅ ያለ የዋጋ መጠን ።

**የዋጋ ንረት** የ"**ዋጋ ግሽበት**" ን ተመ.

**የዋጋ ውጣ ውረድ** የዋጋ ከፍና ዝቅ ማለት፥ መዋዠቅ ።

**የዋጋ ግሽበት** የገንዘብ የመግዛት ሃይል መቀነስ፤ አጠቃላይ የሸቀጦች ዋጋ ማሻቀብ፤ የዋጋ ንረትም ይባላል።

**ዋግ** ስ ማሳ ላይ ያለ እህልን ወይባ የሚያስመስልና ፍሬ እንዳያፈራ የሚያደርግ የእህል በሽታ።

**ዋግ መታው** ዋግ እህሉን እንዳያፈራ አደረገው፥ አበላሸው።

**ዋግምት** "**ዋገምት**"ን ተመ.

**ዋግንቦ(ዋግምቦ)** ስ 1 ከእንጨትና ከሸንበቆ፥... የሚሰራ የድር አራባ መወጠሪያና ማድሪያ። 2. የወጥመድ አይነት።

**ዋጠ** ግ 1.ወደ ሆድ አስገባ ፥ ሰለቀጠ። 2. አጠለቀ፥ አሰረገ፥ አሰመጠ (ጭቃ፥ ውሃ፥...ሰውን ወይም ሌላ ነገርን)። 3. በብዛት በላ። 4. አፍኖ ያዘ፥ ቻለ፥ ታገሰ። ***ንዴቱን ዋጠ***: 5. ቻለ፥ አጠቃሎ ያዘ። ***ጎዳራቹ ያን ሁሉ ሰው ዋጠው***: 6. ሸፈነ፥ ወረሰ። ***ሰብሉን አረም ዋጠው***

**ምን ዋጠው** 1. ምን በጀው። 2. የት ሄደ፥ የት ጠፋ።

**አልዋጥ አለው** ነገሩን መቀበል፥ ማመን አቃተው።

**ተዋጠ** ግ 1. ጠለቀ፥ ሰረገ፥ ሰጠመ (በጭቃ፥ በውሃ፥...)። 2. ተወረረ፥ ተሸፈነ፥ ተጥለቀለቀ (ለምሳሌ ሰብል በአረም)። 3. ተጎረደ፤ ድምፁ ሳይሰማ፥ ሳይነበብ ቀረ (ፊደል፥ ቀለም፥...)። 4. ከብዙ ነገር ጋር በመደባለቁ ወይም አብሮ በመሆኑ መኖሩ የማይታወቅ ሆነ፥ ተሸፈነ።

**አዋጠ** ግ አበላ፥ አጎረሰ ።

**ዋጣ** ስ (የግ. አጠ.) አዝማሪ፥ ማሲንቆ ተጫዋች።

**ዋሮጮ** ስ በቆላ አካባቢ የሚበቅል ነጭ ግራር::

**ዌ** የ"ወ" ፊደል ሃምስ ዘር::

**ው** የ"ወ" ፊደል ሳድስ ዘር::

**-ው**[1] የተወሰነ ነገር አመልካች ምእላድ፤ መስተአምር:: *ሰውዬው/ገበያው::*

**-ው**[2] 1. በግስ መጨረሻ እየገባ "እሱን" የሚለውን ተሳቢ የሚያመለክት ምእላድ:: *ጠራው/ገደለው::* 2. በግስ መጨረሻ እየገባ "ለእሱ" የሚለውን ትርጉም የሚያመጣ ምእላድ:: *ሰጠው/ነገረው::*

**ውሃ** ስ በዝናብ መልክ የሚወርድ፥ በምንጭነት የሚፈልቅና በሃይቅ፥ በኩሬ፥ በባህር፥ በወንዝ የሚገኝ ለመጠጥና ለሌሎችም አገልግሎቶች የሚውል ፈሳሽ፤ የሁለት እጅ ሃይድሮጅንና የአንድ እጅ ኦክስጅን ውሁድ::

**በውሃ ይለቅ** አዲስ ልብስ ለለበሰ ወይም ለገዛ ሰው የሚነገር ምርቃት::

**ውሃ ሆነ** 1. ቀጠነ፤ ጣእሙ፥ ሃይሉ ቀነሰ:: 2. ደነገጠ፥ ክው አለ :: 3. ጠረሰ፥ ላሳኝክ አለ (ጥርስ):: 4. ቀለጠ፥ ሟሟ::

**ውሃ ቀጠነ አለ** ምክንያት ሊሆን የማይገባን ነገር እንደምክንያት አድርጎ ጠብ ፈለገ ::

**ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ** የተለየ ውጤት የማይኖረው፥ ድርጊቱ ቢደጋገምም ውጤቱ ያው አንድ አይነት ነገር ብቻ በመሆኑ ልፋት እንጂ ለውጥ የሌለው::

**ውሃ ቋጠረ** 1. በተለያየ ምክንያት (በህመም፥ በቃጠሎ፥...) ውሃ መሰል ፈሳሽ ያዘ፥ አዘለ (እጅ፥ እግር፥...):: 2. ውሃ ያዘ፥ አቆረ፥ አጠራቀመ (መሬቱ፥ መንገዱ፥...)::

**ውሃ በላው** 1. በውሃ ሙላት አደጋ ሞተ:: 2. ድራሹ ጠፋ፥ የት እንደሄደ ሳይታወቅ ቀረ፥ እልም አለ:: 3. መና፥ ከንቱ ሆኖ ቀረ::

**ውሃ ቢወቅጡት እምቦጭ** ለውጥ ለማስገኘት ጥረት ቢደረግም ተመልሶ ያንኑ ሆኖ መገኘት፥ አለመሻሻል፥ ለውጥ አለማሳየት ::

**ውሃ አላየውም** ፈፅሞ አልታጠበም፤ ውሃ አልነካውም::

**ውሃ ወረደ** ከወንዝ፥ ከምንጭ፥...ውሃ ለመቅዳት ሄደ::

**ውሃ ወሰደው** 1. በውሃ ሙላት አደጋ ሞተ:: 2. በመጠጥ ሰከረ::

**ውሃ ውሃ አለ** 1. ቀጠነ፥ ሳይጣፍጥ ቀረ፥ ጣእም አጣ (ለምሳሌ ጠላ፥ ጠጅ፥...):: 2. ደከመ፥ አለከለከ (በመሮጥ፥ ዳገት በመውጣት፥...)::

**ውሃ ውሃ አሰኘ** አደከመ::

**ውሃ ያነሳል** ብዙ ውሃ ይፈልጋል (ለምሳሌ የሚቦካ ዱቄት)::

**ውሃ ጠጣ** ጠፋ፥ ቀለጠ፥ ታጣ (ገንዘቡ፥ ንብረቱ፥...)::

**የውሃ መንገድ አደረገው** ብዙ ጊዜ ተመላለሰበት::

**የውሃ ሽታ ሆነ** ጠፋ፤ ብዙ ጊዜ ሳይታይ ቆየ::

**ውሃ ልክ** ስ 1. የቤት ግድግዳ፥ ወለል፥...ትክክለኛና ቀጥ ያለ ገፅታ ይዞ መገኘትና አለመገኘት፤ አቀማመጡ በውሃ ወለል ልክ መሆንና አለመሆን:: *ውሃ ልኩ ኣልተስተካከለም::* 2. ግድግዳ፥ ወለል፥...አባጣ ጎባጣ መሆን አለመሆኑ የሚለካበት፥ የሚዋልል ውሃ ውስጡ ያለበት ባለመስተዋት መሳሪያ:: 3 በቤት ግድግዳ ስር ከውጪ በኩል ግድግዳውን አቅፎና ከመሬት ከፍ ብሎ ዙሪያውን የሚገነባ መደብ መሰል ግንብ::

**ውሃ ሙላት** ስ በዝናብ ምክንያት የሚመጣ ጎርፍ፥ ሃይለኛ ውሃ::

**ውሃ ሰማያዊ** ቅ ፈካ የሚል ሰማያዊ::

**ውሃ ሽንት** ስ ሽንት ብቻ (አይነ ምድርን የማይጨምር መሆኑን ለማመልከት)::

**ውሃ ቀለም** ስ በውሃ የሚበጠበጥ ቀለም ::

**ውሃ አጣጭ** ስ ባል ወይም ሚስት፤ የትዳር ጓደኛ ::

**ውሃ ዋና** "ዋኘ" ስር "ዋና"ን ተመ.

**ውሃ ገብ** ውሃ ያለበትና ለመስኖ እርሻ የሚያመች መሬት ::

**ውሃ ጥርስ** ስ የፀዳ ወይም እድፍ፥ ልማም የማይዝ ጥርስ ::

**[የ] ውሃ ቆጣሪ** ስ ከቧንቧ የተጠቀሙበትን የውሃ መጠን የሚቆጥር፥ የሚመዘግብ መሳሪያ ::

**የውሃ እናት** ስ 1. በረጋ ውሃ ላይ የምትዋኝ፥ የምትዞር ጠቆር ያለችና ከጥንዚዛ አነስ የምትል የነፍሳት አይነት:: 2. (ዘይ.) ብዙ ውሃ የሚጠጣ ሰው ::

**የውሃ ወፍጮ** ስ በውሃ ሃይል የሚሰራ ወፍጮ::

**የውሃ ጉድጓድ** ስ ውሃ የሚቀዳበት ወይም የሚወጣበት ጉድጓድ ::

**የውሃ ጋን** ስ ለአንድ ለተወሰነ አካባቢ መገልገያ የሚሆን ውሃ ማጠራቀሚያ፥ ማከማቻ::

**የውሃ ግድብ** ስ ለተለያየ አገልግሎት ሊውል የሚችል ወራጅ ውሃን አግዶ ለመያዝና በከፍተኛ መጠን ለማከማቸት የሚችል በግንብ የሚሰራ የውሃ መከተሪያ ::

**የውሃ ጎማ** ስ አትክልትን ውሃ ለማጠጣት፥ ውሃን ከአንድ ቦታ ስቦ ወደ ሌላ ቦታ ለመውሰድ፥...የሚያገለግል እንደ ቱቦ ሆኖ

በረጅሙ የተሰራና የሚጠቀለል ጎማ ።

**የውሃ ጥም** ስ የውሃ፥ የመጠጥ ፍላጎት ።

**ውሀደት** "ዋሀደ" ስር ተመ.

**ውለታ** "ዋለ[2]" ስር ተመ.

**ውለን**[1] ስ የጆሮ ያለመስማት ችግር፤ የጆሮ መዘጋት፥ መደንቆር ።

**ውለናም** ቅ (ስድብ) 1. ጆሮው የማይሰማ። 2. ደንቆሮ፥ ደደብ ።

**ውለን**[2] ስ ያልሞላ የእህል ስፍር፤ ድርበብ።

**ውለኛ** "ዋለ[2]" ስር ተመ.

**ውሊጥ ውሊጥ አለ** ግ አንድ ጊዜ ወደ ግራ አንድ ጊዜ ወደ ቀኝ እያለ አስቸገረ፤ አንድ መስመር አልይዝ አለ።

**ውላጅ** "ወለደ" ስር ተመ.

**ውል** "ዋለ[2]" ስር ተመ.

**ውል**

**ውልታ** ስ አምሮት፥ ትዝታ።

**ውል አለ** ግ እንደ ሱስ ትዝ አለ፥ አማረ፥ ተናፈቀ።

**ውል ውል አለ** ዝ.ከ.

**ውልምጥምጥ** "*ወለመጠ" ስር ተመ.

**ውልቃት** "ወለቀ" ስር ተመ.

**ውልቅልቅ** ዝ.ከ.

**ውልብልቢት** "*ወለበ" ስር ተመ.

**ውልብልብ** ዝ.ከ.

**ውልብኝ** ስ በእሳት ተጠብሶ የሚበላ የማሽላ እሸት ።

**ውልክስ** "ወልካሳ" ን ተመ.

**ውልክፋ** ስ መለል መለል ያለ ቁመና ያለው፥ ልጡ ለማሰሪያነት የሚያገለግል የጨፈቃ ዛፍ አይነት ።

**ውልክፍክፍ** "ወለከፈ" ስር ተመ.

**ውልውል** "ወለወለ" ስር ተመ.

**ውልግምት** "ወለገመ" ስር ተመ.

**ውልግድ** "ወለገደ" ስር ተመ.

**ውልግድግድ** ዝ.ከ.

**ውልፍስፍስ** "ወለፈሰ" ስር ተመ.

**ውሉ** "ዋለ[1]" ስር ተመ.

**ውሉ አበል** ዝ.ከ.

**ውሪ** ስ (የን.አነ.) ትንሽ ልጅ ።

**ውሪያ** ስ መልኩ ቢጫነት ያለው የወፍ አይነት።

**ውራ** ስ ስሩን ውስጥ ለውስጥ እየሰደደ የሚንሰራፋ የሳር አይነት።

**ውራ** ቅ በውድድር፥ በእሽቅድድም መጨረሻ የወጣ ፡

**ውራጅ** "ወረደ" ስር ተመ.

**ውር**[1]

**ውር አለ** ግ ጠራ (ድመትን)።

**ውሮ** ለድመት መጥሪያነት የሚያገለግል ቃል፡

**ውር**[2]

**ውር ውር አለ** ግ በብዛት ሳይሆን አልፎ አልፎ ሲንቀሳቀስ፥ ሲመላለስ ታየ።

**ውርርድ** "ወረደ" ስር ተመ.

**ውርስ** "ወረሰ" ስር ተመ.

**ውርባ** "ወረበ[2]" ስር ተመ.

**ውርንጭላ** ስ የአህያ ግልገል፤ ውርንጫ እየተባለም ይጠራል ።

**ውርደት** "ወረደ" ስር ተመ.

**ውርዴ** ዝ.ከ.

**ውርድ** ዝ.ከ.

**ውርጃ** ዝ.ከ.

**ውርጅብኝ** ዝ.ከ.

**ውርጋጥ** ስ (የን.አነ) ለአቅመ አዳም ያልደረሰ፥ ገና እድገቱን ያልጨረሰ፤ በአመለካከት፥ በአስተሳሰብ፥... ያልጎለመሰ ልጅ ።

**ውርግርግ** "*ወረገረገ" ስር ተመ.

**ውርጭ** "'ወረጨ[1]" ስር ተመ.

**ውሮ** "ውር[1]" ስር ተመ.

**ውሰት** "*ዋሰ[2]" ስር ተመ.

**ውሱን** "ወሰነ" ስር ተመ.

**ውሳኔ** ዝ.ከ.

**ውስ** ተጃን ለማባረር፥ የሚያገለግል ቃል።

**ውስ አለ** ግ ተጃን ከለከለ፥ አባረረ፥ አገደ፤ ተው፥ ወይድ አለ።

**ውስልትና** "ወሰለተ" ስር ተመ.

**ውስብስብ** "*ወሰበሰበ" ስር ተመ.

**ውስን** "ወሰነ" ስር ተመ.

**ውስኪ** ስ እንደ አጃና ገብስ ከመሳሰለው የእህል ብቅል የሚሰራ፥ ከፍተኛ አልኮልነት ያለው መጠጥ።

**ውስያን** ስ የእቃ፥ የስጋ መስቀያ፤ ማንጠልጠያ።

**ውስጥ** መዋ. 1. የውጭ ተቃራኒ፥ በስተውጭ ያልሆነ። 2. ከሞላ ጎደል ዙሪያው ዝግ ሆኖ መሃሉ ክፍትነት፥ ባዶነት ያለው። *ጓድጓድ ውስጥ /ዝግ ውስጥ/ ብርጭቆ ውስጥ።* 3. ለውጭ ወይም ለሌላ ሰው በግልፅ የማይታይ ነገር፥

ሁኔታ:: *ውስጤን የማውቀው እኔ ነኝ*:: 4. በግልፅ፥ በይፋ ሳይሆን በምስጢር:: *ትእዛዙን በውስጥ ሸረውታል*::

**በ__ ውስጥ** 1. በ__ ጊዜ:: *በወር ውስጥ ሰርቶ ጨረሰው*:: 2. በተወሰነ ቦታ፥ ክልል፥ አካባቢ:: *በኢትዮጵያ ውስጥ የማይገኝ እቃ ገዝቶልኝ መጣ*: 3 መሃከል:: *በእኔና በእሱ ውስጥ ላትገባ*:

**ውስጡን ለቄስ** 1. ገልጠው ሲያዩት፥ ጉዳዩን ሲረዱት የማይረባ:: 2. ጉዳዩ ምስጢር ነው፥ ለሁሉ አይነገርም ለማለት የሚነገር::

**ውስጠ ምስጢር** ስ ድብቅ የሆነ፥ ያልታወቀ ምስጢር::

**ውስጠ ወይራ** ስ በቀላሉ ሊረዱት የማይቻል ምስጢር አዘል አነጋገር ::

**ውስጥ ለውስጥ** ሳይታይ፥ ሳይታወቅ በምስጢር ::

**ውስጥ ልብስ** ስ ሴቶች ከቀሚስ ስር የሚለብሱት ብዙውን ጊዜ ስስ የሆነ ገላ ነክ ልብስ ::

**ውስጥ ሱሪ** ስ ሙታንቲ፤ ገላ ነክ የሆነ አነስተኛ ሱሪ ::

**ውስጥ አዋቂ** ቅ 1. ቤተኛ፥ መውጫ መግቢያውንና ሁኔታውን የሚያውቅ፤ ሊጎዳ የሚችል (አብዛኛውን ጊዜ ለሌባ የሚነገር):: 2. ምስጢሩን በቅርብ የሚያውቅ::

**ውስጥ እጅ** ስ የእጅ ውስጠኛ ክፍል፤ መሃል እጅ (ስእሉን እጅ ስር ተመ.)::

**ውስጥ እግር** ስ መሬት የሚረግጠው ውስጠኛው የእግር ክፍል::

**ውስጥ ውስጡን** ይፋ ሳይሆን፥ በድብቅ::

**የውስጥ በሽታ** በውጫዊ አካል ላይ የማይታይ በሽታ (ለምሳሌ የልብ፥ የአንጀት በሽታ)::

**የውስጥ ጉዳይ** ሌሎች እንዲገቡበት የማያስፈልግ የራስ ጉዳይ፤ በባለቤቱ ብቻ ሊፈታ የሚገባው የግል ችግር (ብዙውን ጊዜ ለሃገር) ::

**ውስጠኛ** ቅ ከውስጥ ያለ፥ በውስጥ በኩል የሆነ::

**ውስጣዊ** ቅ 1. የግል፥ የራስ የሆነ:: *ውስጣዊ ችግራችንን እራሳችን እንፈታዋለን*: 2. በግል፥ እርስ በእርስ፥ በምስጢር:: *ውስጣዊ ስምምነት አድርገዋል*:: 3. የውስጥ::

**ውሽተኛ "ዋሸ"** ስር ተመ.

**ውሽታም** ዝ.ከ.

**ውሸት** ዝ.ከ.

**ውሻ** ስ 1. ከሰው ጋር አብሮ የሚኖር፥ የጌታውን ቤትና ንብረት የሚጠብቅ ለማዳ አውሬ፤ ሰው ወዳጅ፥ ቤት ጠባቂ፥ ያልለመደው ሰው ወይም አውሬ ሲመጣ የሚጮህ፥ የሚናከስ:: 2. (ስድብ) ልክስክስ፥ ተለማማጭ(ስእሉን የቤት እንስሳ ስር ተመ.)::

**የውሻ ቁስል ያድርግልህ** ቁስሉ ቶሎ ይዳንልህ ለማለት የሚነገር ምርቃት ::

**ውሻ በጨው የማይቀምሰው** (ዘይ.) አስቀያሚ፥ የማይረባ፥ የማይፈለግ ::

**ውሻ ሆድ** (ዘይ.) የማይጨክን፥ የማይቆርጥ፥ ቂም የማይዝ::

**የውሻ ምላስ** ስ 1. መልኩ ጥቁር አረንጓዴ ሆኖ መለል መለል ብሎ የሚበቅልና በግራ በቀኝ እሾህ ያለው ጠፍጣፋ የእፅዋት አይነት:: 2. ጠፍጣፋ ሆኖ በጣም የሳሳ (ብዙውን ጊዜ ለእንጀራ)::

**የውሻ ስንደዶ** ስ ስንደዶ የሚመስል የሳር አይነት::

**የውሻ በሽታ** ስ በንክሻ የሚተላለፍ፥ የሚያሳብድና ካልታከሙት እስከሞት ሊያደርስ የሚችል የደመ ሞቃት እንስሳት የነርቭ ስርአት በሽታ ::

**የውሻ ዝምብ** ስ ተርብ ::

**ውሻል** ስ 1. በጎደለ መሙሊያ ወይም የነገር ጭማሪ:: 2. ሽብልቅ:: 3. (ስድብ) እራሱን ያልቻለ፥ ለማሟያነት የሚገባ:: 4. የላላ እስርን ለማጥበቅ የሚገባ አነስተኛ ውታፍ::

**ውሽልሽል "ወሸለ"** ስር ተመ.

**ውሽማ "ወሸመ"** ስር ተመ.

**ውሽሽ** ስ ስሩ ድንች የሚመስል የተክል አይነት::

**ውሾባ "ወሸባ²"** ን ተመ.

**ውሽንፍር** ስ ንፋስ የተቀላቀለበት አግድም የሚዘንብ ዝናብ፤ ወጨፎ::

**ውቂያ "ወቃ"** ስር ተመ.

**ውቃሪ "ወቀረ"** ስር ተመ.

**ውቃቢ** ስ 1. ከእያንዳንዱ ሰው ጋር አብሮ ይኖራል የሚባል ጠባቂ መልአክ፤ ውቃቢ አምላክም ይባላል:: 2. ዛር፥ ርኩስ መንፈስ::

**ውቃቢ ራቀው** 1. ጥላቢስ ሆነ፥ ተጎሳቆለ:: 2. በረከት አጣ ::

**ውቃቢ ቀረበው** 1. ጥሩ ነገር ገጠመው፥ ተሳካለት:: 2. የተረጋጋ ጨዋ ሰው ሆነ፥ ግርማ ሞገስ አገኘ ::

**ውቃቢ አስራቀው** 1. አስደነገጠው (በጩሀት፥ በስድብ፥...):: 2. በረከት አሳጣው::

**ውቃቢው ተገፈፈ** በጣም ደነገጠ::

**ውቃቢው አልወደደውም** ደስ አላለውም፥ አስጠልቶታል (ያየው፥ የተመለከተውና

የቀረበለት፥... ነገር)።

**ባለውቃቢ** ስ ውቃቢ ያለበት፥ ጠንቋይ፥ ባለዛር።

**ውቃቢ ቢስ** ጥላቢስ፥ ነጠላ፥ ቀትረ ቀላል፥ ግርማ ሞገስ የሌለው ።

**ውቃቢ የለሽ** ዝ.ከ.

**ውቃጭ** "ወቀጠ" ስር ተመ.

**ውቅራት** "ወቀረ" ስር ተመ.

**ውቅር** ዝ.ከ.

**ውቅያኖስ** ስ 1. የመሬትን ሶስት አራተኛ የሚሸፍን፥ ጥልቅና በጣም ሰፊ የሆነ ባህር (እንደ አትላንቲክና ህንድ ውያቅኖስ የመሳሰለው)። 2. (ዘይ.) ጥልቅ፥ ሰፊ።

**ውቅጥ** "ወቀጠ" ስር ተመ.

**ውበት** "*ዋበ" ስር ተመ.

**ውብ** ዝ.ከ.

**ውታፍ** "ወተፈ" ስር ተመ.

**ውትርትር** "*ወተረ" ስር ተመ.

**ውትብትብ** "*ወተበተበ" ስር ተመ.

**ውትወታ** "ወተወተ" ስር ተመ.

**ውትፍትፍ** "ወተፈ" ስር ተመ.

**ውን**

**ውን ውን አለ** ግ 1. ተንቃነቀ፥ ተወዛወዘ (ጭራ)። 2. ወዲያ ወዲህ አለ፥ ተዘዋወረ የደከመ ሰው)።

**ውንብድና** "ወነበደ" ስር ተመ.

**ውንክርክር** "*ወነከረ" ስር ተመ.

**ውካታ** "*ወካ" ስር ተመ.

**ውክልና** "ወከለ" ስር ተመ.

**ውዝት** "ወዘተ" ስር ተመ.

**ውዝዋዜ** "ወዘወዘ" ስር ተመ.

**ውዝግብ** "*ወዘገበ" ስር ተመ.

**ውዝፍ** "ወዘፈ" ስር ተመ.

**ውዥዋ** ስ ውስጠ ክፍትና ረዥም የሆነ፥ በጋያ የሚጨስ ትንባሆ መጠጫ (ሽንበቆ፥ ቧንቧ፥...)።

**ውይይት** "*ዋየ" ስር ተመ.

**ውዳሴ** "ወደሰ" ስር ተመ.

**ውዳቂ** "ወደቀ" ስር ተመ.

**ውዴላ** "ወደለ[2]" ስር ተመ.

**ውዴታ** "ወደደ" ስር ተመ.

**ውድ** ዝ.ከ.

**ውድማ** ስ ጫካ፥ ደን የወረሰው፥ ሰው የማይኖርበት መሬት።

**ውድማ** "አውድማ" ን ተመ.

**ውድቀት** "ወደቀ" ስር ተመ.

**ውድቅ** ዝ.ከ.

**ውድቅት** ዝ.ከ.

**ውድን** "ወደነ" ስር ተመ.

**ውድንቢ** ስ መልኩ ወርቅማ ሆኖ በጀርባው ላይ ነጫጭ ሽንትሮች ያሉበት፥ ጠመዝማዛ ቀንድ ያለው፥ ጫካ ባለበት ቆላማ ስፍራዎች መንጋ ሆኖ የሚታይና ስጋው ለምግብነት የሚያገለግል የዱር እንስሳ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

**ውድድር** "*ወደረ" ስር ተመ.

**ውጉዝ** "*ወገዘ" ስር ተመ.

**ውጊያ** "ወጋ" ስር ተመ.

**ውጋት** ዝ.ከ.

**ውጋገን** "ወገግ" ስር ተመ.

**ውጋጋን** "ወገን" ስር "ውጋገን" ን ተመ.

**ውግ** "ወጋ" ስር ተመ.

**ውግዘት** "*ወገዘ" ስር ተመ.

**ውጤት** "ወጣ" ስር ተመ.

**ውጥረት** "ወጠረ" ስር ተመ.

**ውጥኔ** ስ ወደ ብርቱካንነት መልክ የሚቀርብ የቀይና የቢጫ ቅልቅል የሆነ የቀለም አይነት ።

**ውጥን** "ወጠነ" ስር ተመ.

**ውጥንቅጥ** ቅ የተቀላቀለ፥ የተቀያየጠ፥ የተደባለቀ።

**ውጥንቅጡ ወጣ** ተመሰቃቀለ፥ ተደበላለቀ።

**ውጪ** "ወጣ" ስር "ውጭ" ን ተመ.

**ውጭ** "ወጣ" ስር ተመ.

**ውፋሬ** "ወፈረ" ስር "ውፍረት" ን ተመ.

**ውፍረት** "ወፈረ" ስር ተመ.

**ዎ** የ"ወ" ፊደል ሳብእ ዘር ።

**—ዎ (—ዎት)** (የአክብሮት አጠቃቀም) የሁለተኛ መደብ፥ ነጠላ ቀጥር አገናዛቢ ምእላድ። መፅሃፍዎ።

**—ዎች** "—ኦች" ን ተመ.